@OLDBOOKSPDF

# ደራሲው



ከበዓሉ ግርማ

@OLDBOOKSPDF

# ደ ራ ሲ ው

ከበዓሉ ግርማ

@OLDBOOKSPDF

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
ALL RIGHTS RESERVED

መጀመሪያ እትም 1972 ዓ.ም
ሁለተኛ እትም 1977 ዓ.ም
ሦስተኛ እትም 1980 ዓ.ም
አራተኛ እትም 1999 ዓ.ም
አምስተኛ እትም 2005 ዓ.ም
ስድስተኛ እትም 2008 ዓ.ም
ሰባተኛ እትም 2011 ዓ.ም

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ

## ምእራፍ ፩

@OLDBOOKSPDF

እኩለ ሌሊት አልፎአል፡፡ ደራሲው ሲራክ ዝም ብሎ አፍጦአል፡፡ እንደ ጅረት የሚፈስ አሳብ — አሳታፊ ቃላት — ነበልባላዊ አረፍተ ነገሮች — ምንም፡፡

ከፊቱ ያለው ባዶ ነጭ ወረቀት አፉን ከፍቶ የሚያዛጋበት፣ የወረቀቱ መስመሮች ከአይኖቹ ስር እየደነሱ የሚሰቁበት መሰለው፡፡ — ተሰጥዎ የሚባለው ነገር ለካስ ስቃይ ኖሮአል፣ አለ፡፡

ግንባሩን፣ ማጅራቱን፣ ማጅር ግንዱን አሸ፡፡ የተፈጠረ ተአምር አልነበረም፡፡ ኪነታዊ እውነት ከነሙሉ ውበትዋ አልተከሰተችለትም፡፡ ቃላት እንደ ፈርጥ እየተንቦገቦጉ ወረቀቱ ላይ አልደነሱም፡፡ የገደል ማሚቶ ብቻ ሆነበት፡፡

—ኤጭ! ድርሰውንስ የፈጣሪን ሚና ማን ተጫወት አለኝ!? ወይስ ሰው የፈጣሪን ሚና ለመጫወት ሲሞክር የሚቀጥት መላእክት የፈጠራ ችቦዬን ነጠቁኝ!? እንኩዋን ደስ አላቸው፡፡ ክንፎቻቸውን ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ዘርግተው እምቢልታቸውን እየነፉ ከአድማስ አድማስ በመርገጥ ይደንሱ፡፡ ከፈለጉም ከጠረፍ ጠረፍ እየተሩዋሩዋጡ ከሳጥናኤል ሰራዊት ጋር ጦርነት ገጥመው በደም ዝናብ አለምን ያጥለቅልቁዋት — ከሰይፎቻቸው መፋጨት የሚወጣው ብልጭታ ፀሐይን የኩራዝ ብርሃን ያስመስላት — የሳጥናኤልን እንገት የሳተው የሚካኤል ሰይፍ ጨረቃን እንደ ቡሂ ዳቦ ለሁለት ገምሶ ይጣላት — የፈረሶቻቸው ኮቴ ከዋክብትን ረግጦ እንደ ጤዛ ያርግፋቸው ከዋክብት ረግጦ እንደ ጤዛ ያርግፋቸው — ክንፎቻቸው እየተጋጩ ተሰምቶ የማይታወቅ ነጎድጉዋድ ያውርዱ፡፡ ምዕላት ይምጣ! . . .

ደረቅ ንፋስ በሀይል ይነፍሳል፣ ያቃስታል፣ ያፋዋጫል፡፡ የመንደሩ የቆርቆሮ አጥሮች፣ የተሰበሩ መዝጊያዎች፣ በሮችና የተነቀሉ የቤት ቆርቆሮዎች እያተራመሰ እንግዳ የሆነ የምዕላት ቀን ቁዋንቁዋ ያናግራቸዋል፡፡

ያ ልማደኛ የጎረቤት ውሻ ያለ ማቁዋረጥ ያላዝናል፡፡ ሁልጊዜ ያላዝናል፡፡ አይሰሙህም፣ እንደ ውሻ አይሰሙህም፡፡ ጅብ ሊጠዝጥ ሲሰሙህ እሱ ያላዝናል፡፡

@OLDBOOKSPDF



ከጎረቤት እንዲት ኪዮስክ ውስጥ የሚኖሩ አሮጊት ያረጀው እጥንታቸው እስኪንቋቋቁዋ ድረስ ይስላሉ፡፡ ዘወትር ይስላሉ፡፡ ደረቅ ሳል ይስላሉ — ትንፋሻቸው ቁርጥ እስኪል ድረስ፡፡

ሰፈሩ ከአሮጊትዋ ጋር አብሮ ይስላል፤ ይጨነቃል፤ ከውሻው ጋር አብሮ ያላዝናል፤ ከንፋሱ ጋር ያፏጫል፤ ከሰማዩ ጋር ያጉረመርማል፤ ከደራሲው ጋር ያነጥሳል፤ ከደራሲው ባለቤት ጋር ያንኮራፋል፤ ከደራሲው ልጅ ጋር ይቃዣል፡፡

ሚስቱ፤ ፅጌ ሀይለ ማርያም፤ ከእንቅልፍዋ ነቅታ መጥታ ብቅ አለችበት፡፡ አያት፡፡ አየችው፡፡ ተያዩ፡፡ ምንም አላለችውም፡፡ እሱም ምንም አላላትም፡፡ ዝንፍልፍል እያለ ከሚወርደው ጥቁር ሉጫ ጠጉርዋ ላይ ሻሽ አይረጋም፡፡ ጠይም አሳ መሳይ ብትሆንም ጠቆር ብላ ታየችው፡፡ ቦግ ቦግ የሚሉት አይኖችዋ ደብልጥ ቦግ ብለው አፈጠጡበት፡፡ እንደ ባህላዊ የቤተ ክርስቲያን ስእሎች አይን ብቻ ሆና ታየችው፡፡ በመገረም ራስዋን ነቅንቃ ዝም ብላ ወደ መኝታዋ ተመልሳ ሄደች፡፡ ሰላም የሰፈነበት እንቅልፍ የሚተኙ የታደሉ ናቸው፡፡ መልካም እንቅልፍ ያድርግሽ አለ — በልቡ፡፡

ተመልሶ ከወረቀቱ ጋር መፋጠጥ ገባ፡፡ ነጩ ወረቀት ነጭ ነበር፡፡ መስመሮቹ ሰይጣናዊ ሳቅ የሳቁበት መሰለው፡፡ እሳቡን መሰብሰብ ስላቃተው ተናደደ፡፡ ወረቀቱን በንዴት ቡጭቅጭቅ አድርጎ ጣለ፡፡

ብቸኛ ጅብ ይጮሃል፡፡ የመንደር ዶሮዎች በየቆጦቻቸው ይንጫጫሉ፡፡ ውሻው ያላዝናል፡፡ ሌሎች የመንደር ውሾች እየተቀባበሉ ይጮሃሉ፡፡ አሮጊትዋ ደረቅ ሳላቸውን ይስላሉ፡፡ ደረቅ መብረቅ ሰማዩን ይሰነጥቃል፡፡ የኮሬንቲ መብራት ብልጭ ድርግም ይላል፡፡

የሰፈሩ ሰካራም አቶ ብርሌ ደጉ፤ «ሰው በላው ጎንደሬ!» እያለ ይጮሃል፡፡ «ሸህ ገዳይ የጎንደሬዪትዋ ልጅ፡፡ እኔ ፋሲል ግንብ ላይ ቆሜ፤ ምንትዋብ ሰገነት ላይ ወጥቼ ቁልቁል ብሸና፤ ማን ይጠይቀኛል፡፡ ሰው በላው ጎንደሬ! መቅደላ ላይ ቆሜ ሸህ ብጠጣ! ያባይን ልጅ ውሃ ጠማው፡፡ መተማ ወርዶ ቅንጥስ ብጥስ፡፡ ዘራፍ!» ይቆይ ይቆይና ደግሞ፤ «በአብዮቱ አምላክ፤ በደርጉ!» ይላል፤ ጎረቤቱን ሁሉ . . .

ሃጂ ሙስጠፋ ቤት ወዳጃው ደርቶአል፡-

@OLDBOOKSPDF



ያባትህ ከራማ ይታረቅህ፡፡
አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡
የእናትህ ከራማ ይታረቅህ፤
ሼህዪ ደጉ ያስታውስህ፡፡
አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡
ምቀኛ ሸረኛውን ይያዝልህ፡፡
አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡
የቢስ ንግድ ላንተ ይሁንልህ፡፡
አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡
በፒያሳ ሱቅ ከፈትበት፡፡
አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡
በቸርቺል ጎዳና መኪና ንዳበት፡፡
አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡
ባራት ኪሎ ፎቅ ስራበት፡፡
አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡
ጀባ ፤ ጀባ ፤ ጀባ . . .

ደራሲው እቦል ቡና ሸተተው፡፡ እጣኑ ቡልቅ ቡልቅ ሲል ታየው፡፡ የቄጠማው ጉዝጉዋዝ፤ የሜቱ ከምር በእይኑ መጣ፡፡

እቦል ጀባ፤ በረካ ጀባ፡፡ ከራማው የሃጂ ሙስጠፋን ቤት ታርቆታል፡፡ ምርቃቱ እብቅቶ እርግማን ይወርድ ጀመር፡፡ ሲራክ በደበሎ ጆሮውን እቆመ፡፡

ሸረኛውን ያዝልን፡፡
አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡
ምቀኛውን አጥፋልን፡፡
አሜን፤ አሜን አሜን፡፡
በላውን ተብሪድ አድርግልን፡፡
አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡

ይህችስ እርግማን ለኔ ሳትሆን አትቀርም፤ አለ ሲራክ፡፡ ኪኑት ጀባ፤ ድርሰት ጀባ፤ የድርሰት ካራማውን አቅርብልን፤ ችቦውን እንድድልን፡፡ እሳየን ውበትን እቦ . . . ብሎ ወደ ድርሰቱ ተመለሰ፡፡ ባዶው ነጭ ወረቀት ላይ ምን ቢያፈጥ ባዶው ነጭ ወረቀት እሱው ላይ መልሶ ከማፍጠጥ ሌላ የሆነ ነገር የለም፡፡ ከፍልሚያው መድረክ ራቅ ለማለት እሰበ ተነሳ፡፡ ከተፋፋመ ጦር ሜዳ እንዳንዴ ገለል ማለት ተእምር ሳይሰራ ይቀራል? አለ፡፡

@OLDBOOKSPDF



እንደ እርኩም አጉንብሶ ከጠረጴዛው እየራቀ ሄደ፡፡ የጠፋ እቃ እንደሚፈልግ ሰው ሁልጊዜ መሬት መሬት እያየ ነው የሚሄደው፡፡ ቀና ቢል በድንገት የራሱን መልክ ግድግዳው ላይ ካለው መስታወት ውስጥ አየ፡፡ ጥላውን ነው እንጂ የራሱን መልክ የሚመለከት አልመሰለውም፡፡
– የነበረ ሰው ጥላ፡፡ ጠጋ አለ ወደ መስታወቱ፡፡

ትንንሽ አይኖቹ ቀልተዋል፡፡ የንስር አይን የሚመስሉ ትናንሽ አይኖች ናቸው ያሉት፡፡ አቁር! ፈጣጣ ግንባሩ በትርጉም ቢስ መስመሮች ታርሰዋል፡፡ ግንባሩ ሰው ላይ ያፈጣል፡፡ የተፈጥሮ ጫካ የመሰለው ጠጉሩ ተንጨፍርሮ መሳ የጠፋው ቃልቻ አስመስሎታል፡፡ አይኖቹ ስር ያሉት ቆዳዎች ተጨማድደዋል፡፡ የጉንጮቹ አጥንቶች እንደ እለት ቆመዋል፡፡ ቀይ ፊቱ በማዲያት ተዥጎርጉሮአል፡፡ አፍንጫው ብቻ ነው ተገትሮ የቀረው፤ የህይወትን መአዛ ለማሽተት የሚንጠራራ ይመስል፡፡ ቀጥ ብሎ ወርዶ ከስር ሰፋ የሚለው አፍንጫው እንደ ነፍጠኛ ጎራዴ ሰው ያሸሙቀጥጣል፡፡ ቀጫጭን የብር ዘንግ የመሰለ ሽበት ከጥቁር ጠጉሩ መሃል ብቅ ብቅ ማለት ጀምሮአል፡፡ የወጣትነት ዘመኑ ወደ ሁዋላ እየቀረ ሲሄድ ታየው፡፡

የጊዜ ቀስት የሚያመለክተው ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ነው፡፡ ሰዎች ከቶም ወጣት እየሆኑ አይሄዱም፤ አለ፡፡

ድንገት ወጣትነት እንደ ጠዋት ጀምበር የሚሞቅ ፈገግታ እያሳየው፤ እንደ ከዋክብት በሚያብለጨልጨ አይኖቹ እየጠቀሰውና እንደ ፀዳል የሚያበራ ከብሩህ ተስፋ ሌላ ምንም የማይነበብበት፤ ትኩስ ደም የሚተራመስበት ሳቂታ ውብ ፊት እያሳየው፤ ግለት ባለው ጠንካራ እጁ ጨብጦት በመሰናበት፤ ትከሻውን አሳብጦ፤ ደረቱን ነፍቶ፤ ወገቡን እየሰበቀ፤ እንጥር እንጥር እያለ፤ እንደ ቦና ጥጃ እየቡዋረቀ፤ ሜዳው እስኪጠበው ድረስ እየፈነደቀ እየራቀ፤ እየጨለለ፤ እንደ ጥላ እየከበለለ ሲለየውና፤ እርጅና መላጣውን፤ ጥጥ የመሰለ ሽበቱን፤ ባዶ ድዱን፤ ብርሃናቸው ደብዝዞ ጭል ጭል የሚሉ የተጨናበሱ ጭጭሙጭጫ አይኖቹን፤ እድሜ ብዙ ትዝብት የፃፈበትን በደንብ እንዳልለፋ ቆዳ የተጨማደደ፤ ኩምትር፤ ጭምድድ ያለ ፊቱን እያሳየው፤ ወገቡ ጎብጦ፤ ሰውነቱ ዝሎ፤ ተመርኩዞ በዱላ፤ ሰውነቱንና እሳቡን ማስተባበር አቅቶት እየተንቀጠቀጠ፤ ከንፈሩን መክደን ተስኖት እየተዝረከረከ፤ አገጩን እንጠልጥሎ፤ የሚረግጠውን መሬት አሳምን ብሎ፤ መሬት እየከዳውና እርምጃውን እየቆጠረ መጥቶ አጥንታም እጁን ይዘረጋለታል - በቀዝቃዛ እጁ ሊጨብጠው፡፡

– ወግድልኝ! እምቢዮ!

@OLDBOOKSPDF



እርጅና ባዶ ድዱን እያሳየ የሚንቀጠቀጥ አጥንታም እጁን ዘርግቶለት ይቆማል፡፡ ወጣትነት ከወንዝ ማዶ እየቡዋረቀ ይስቃል፡፡ ሳቁ ያስተጋባል፡፡

— እምቢዮ! እጄን አልሰጥም! በቃ!

የራሱ ድምፅ አስገረመውና ከቁም እንቅልፍ ነቃ — ደራሲው፡፡ በመጀመሪያ ያደረበት ስሜት አስደነገጠው፡፡ ተንቀጠቀጠ፡፡ ወደ እርጅና እድሜ የመግባት ስቃይ አዘል ስሜት መጥቶ አደረበት፡፡ እንባ አላፈሰሰም፡፡ ይልቅ በሳቅ ፈነዳ፡፡ የኮረኮሩትን ያህል ተንከትክቶ ሳቀ፡፡ ሳቀ—እንባ እስኪወርደው ድረስ፡፡ ሳቅና እንባ፡፡ ደስታና ስቃይ፡፡ ኪነታዊ ጭንቀት፡፡ ለምንድን ነው ይህን ሁሉ ስቃይ በገዛ እጁ ራሱ ላይ የሚያደርሰው? ለምን? ሀያውነት! የሩቅ ገደል ማሚቶ ናት! አለ፡፡ እንባው እያሳቀው ሳቀ፡፡

ያ የመንደር ውሻ ሲያሳዝን ሰማና፦ ሙዋርተኛ! ያሙዋርትብኛል ልበል! ማን ይፈራል ሞት! ኢጋቶሪ እንደሻውን መሰልኩት? አለ፡፡ በሳቁና በእንባው ውስጥ ኢጋቶሪ እንደሻው! መፅሀፉ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህርይ! ብቅ ብለው ታዩት፡፡

በስድሳ ስድስት አመታቸው፦ እኔ ያባ ፍታው ልጅ! ምን ሲደረግ፡፡ ይህ ሌባ፡፡ ጨለማን ተገን አድርጎ የሚመጣ ፈሪ ውላጅ፡፡ ሞት አያሸንፈኝም! እያሉ ሞትን ለመሸሽ በምድረ አለም ይንከራተታሉ፡፡ እና! ደራሲውም አብሮአቸው ይንከራተታል — ጉብዝናቸው ጥንካሬአቸውና ድፍረታቸው እያስደነቀው! ያልሞት ባይ ተጋዳይነት ትግላቸው እያሳዘነው! የሚሸሹት ሞት በጉያቸው ተሸጉጦ ባየ ቁጥር እያሳቀው . . .

ሞትን ለመሸሽ ስንት ወንዝ አቋርጠው ተጉዘው አንድ መንደር በደረሱ ቁጥር! መጀመሪያ ያገኙትን ሰው፦ የሞተ ሰው አለ? ብለው ይጠይቃሉ — ከሰላምታ በፊት፡፡

— በሽታ ገብቶአል?

— አልሰማሁም፡፡

— የታመመስ?

— አንድ አሮጊት ብቻ ታመዋል ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡

@OLDBOOKSPDF



– የታባቱ ይህ መናጢ ሊባ፡፡ ከዚህም ለስርቆት መጥቶአል በለኝ፡፡ ማን ቆሞ ሊጠብቀው፡፡ ምኑን ይፈልግ! ብለው በቅሎአቸውን በመኮርኮር በሃይል እያስገሩ በመጡበት ፍጥነት ቶሎ ውልቅ – ስንቃቸው የጫነው መጋጃ ከሁዋላቸው ጎፍ ጎፍ እያለ መንደሩን ጥለው ጭልጥ! ሞትን ወደ ሁዋላ ትተው – እሱ እየቀደማቸው፡፡

መኖር ለምን እንደሚያንቀዋቅዋቸው ኢጋፋሪ አይናገሩም፡፡ ደራሲውም ምክንያታቸውን ለይቶ ለማወቅ አልቻለም፡፡ አብሮአቸው ከአድማስ አድማስ ባሳብ መንከራተት ብቻ . . .

ጉዋደኞቻቸው የሉም፡፡ ሁሉም ሞተዋል፡፡ ኢጋፋሪ እንደሆን ቀብር ደርሰው አያውቁም፡፡ ሞት! መቃብር፣ የፈረሰ ሰውነት፣ ትል፣ የሊእል ትል፣ ያገጠጠ አጥንት፣ መቃብር፣ የተካበ ድንጋይና አፈር ካለበት ምን ሊያደርጉ ይደርሳሉ! ጥላ ቢስ! የሞት ጠረን ሽታ አይፈልጉም፡፡ ከሩቁ ነው ፊታቸውን አዙረው የሚሸሹት፡፡ የተወለዱበት ያደጉበት መንደር ተለውጦአል፡፡ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ደሳሳ ጎጆዎችን፣ የተንጣለሉ አስፋልት መንገዶች አቡዋራማ የእግር መንገዶችን፣ ያሸበረቁ ቡና ቤቶች ጠጅና ጠላ ቤቶችን ተክተዋል፡፡ ተራራ የነበረው ሜዳ፣ ሜዳ የነበረው ሸለቆ፣ ጫካ የነበረው እርሻ፣ እርሻ የነበረው ጫካ፣ መንደር የነበረው ቅልጥ ያለ ከተማ፣ የደራ ከተማ የነበረው ጭር ያለ መንደር ሆኖአል፡፡ ወንዞችም አቅጣጫቸውን ከጊዜ ብዛት ሳይለውጡ አልቀሩም፡፡ ዘለአለማዊ ለውጥ፡፡ መወለድ፣ ማደግ፣ ማርጀት፣ መክሰም መሞት፡፡ ከመሆን ወደ አለመሆን! የህይወት ህግ፡፡ ኢጋፋሪ ግን አሻፈረኝ ብለዋል፡፡

– እኔ፡፡ አሁን ገና ገባኝ፡፡ ምስጢሩ ይህ ኖሮአል ለካ? ኢጋፋሪ! ለመኖር መብት አለኝ፣ እኔ ሞቼ፣ ይህችን ፀሀይ ማን ይሞቅልኝ? ይህን ንፁህ አየር ማን ይተንፍስልኛል፡፡ የተፈጥሮን ውበት፣ የጠዋት ሥራን፣ የምሽት ጀምበርን፣ የከዋክብት ትቅኝን፣ የጨረቃ ድምቀትዋን፣ የህፃን ፈገግታን፣ የጎረምሳን ንቃት፣ ድንፋታና ኩራት፣ የሽማግሌን እርጋታ፣ ብስለትና እውቀት፣ እምን – የባህር ሞገድ መነሳትና መውደቅ፣ የደመናዎችን መዥጎርጎር፣ መፈራረቅ፣ የበጋ ምንጭ ኩልል ብሎ ሲወርድ፣ የፀደይ አበባ ሲፈነዳ፣ የበልግ እርሻ ሕይወት ሲያረግዝ፣ የክረምት ወንዝ ሲሞላ፣ ንቦች ሲያምሙ፣ ቢራቢሮዎች ውርውር ሲሉ፣ አእዋፍ ሲዘምሩ፣ የያሬድን ቅዳሴ መዝሙር፣ ያለቃ ገብረሃናን ቀልድ፣ የኮረዳዎችን ዳሌና አንጠጉጡ፣ የሰውን ልጅ የስልጣኔ ሂደት፣ ተስፋውንና ሀዘኑን፣ እኔ ሞቼ ማን ያድንቅልኝ ነው የሚሉት? ንፁህ የማር ጠጅ በብርሌ የዶሮ አይን የመሰለ የገብስ ጠላ በሽክና፣ እኔ ሞቼ ማን ይጠጣልኝ፣ በቅመም

@OLDBOOKSPDF



አርር ድብን ያለ ዶሮ ውጥ፣ በንጭ ጤፍ እንጀራ፣ ብርዶ ምላስ ሰምበር ባዋዜ፣ እኔ ሞቼ ማን ሊበላልኝ ነው የሚሉት? ይህችን ውብ አገር፣ ይህችን ኢትዮጵያ፣ ይህችን ድንግል መሬት እምን፣ ከቀይ ባህርና ከመሬት መቀነት በትምክህት ወደ ሰማይ መጥቃ ተራሮችዋ በግርማ ሞገሳዊ ኩራት ከደመናዎች ጋር የሚታከኩበት፣ እግሮቹ በተራሮቹ መንጠራራትና ኩራት ተናዶ በታላቅ ቁጣ በሃያል ክርን ቁልቁል የደቆሳትና እንደ ግመል ጀርባ ውግ ገብ ሆና የቀረች፣ ህይወት ፈዋሽ የሆነው ቀዝቃዛ፣ እየሩዋ እየነፈሰ ጤፉን፣ ማሽላውንና ገብሱን ለሽ፣ ቀና፣ እጥፍ፣ ዘርጋ እያደረገ የተፈጥሮ ዳንኪራ የሚያስረግጥበት፣ በምስጢራዊ ድንግል ሽንተረሮችዋና ሸለቆዎችዋ ጉያ ውስጥ፣ እያስመሰሙ፣ እየተገማሸሩ የሚንሸራሸሩትን ብርማ ምንጮችና ወንዞች፣ ስልታዊ ሙዚቃ እየተከተሉ በደስታ የሚፈነድቁት ዱር አራዊት፣ እልልታ የሚያቀልጡት አእዋፍ — ሱራፌልና ኪሩቤል ዋሽንት እየተጫወቱ የሚሩዋሩዋጡባቸውን ሜዳዎች፣ መላእክት ፀሀይ የሚሞቁባቸውን ተራሮች — ይህችን ውብ ድንግል ታይታ የማትጠገብ መሬት ለማን ትቼ የት ልሂድ! ነው የሚሉት? ህይወት ትጣፍጣለች፣ ሳልጠግባት ማንነው ጠግበሃል፣ በቃህ ሊለኝ መብት ያለው? መኖር አለብኝ፣፣ እና እያንዳድዋ ሴኮንድና ደቂቃ ህይወቴ ናት፣፣ የሙጥኝ እላለሁ፣፣ እምቢዮ! በቃ አልሞትም ነው የሚሉት?......

— አይደለም እንዴ አጋፋሪ?

— ቂ ቂ ቂ ቂ - ወላቃ፣ ሻጋታ ጥርሳቸውን እያሳዩ፣፣

— ምን ያስቅዎታል?

— አንተ፣፣ ህይወት፣- ቂ ቂ ቂ ቂ፣፣

— አይ አጋፋሪ፣፣ ይቀልዳሉ መሰለኝ፣፣ እጅ መኖርም አለመኖርም እንዲ በሌላው ውስጥ ያለ ነገር ነው፣፣ ህይወት በሁለት ዘለአለማዊ ጨለማዎች መካከል ያለች ቅፅበታዊ ብልጭታ ናት፣፣ ህይወትና ሞት ያንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፣፣ ቁም ነገሩ ግን ይህ አይደለም፣፣ ዋናው ነገር ለውጥ የተፈጥሮ ህግ መሆኑን ከማወቅ ላይ ነው፣፣ የማይለወጥ ነገር የለም፣፣ መወለድ፣ ማደግ፣ መኖር፣ መክሰም፣ መሞት — ያለ፣ የነበረ ወደ ፊትም የሚኖር ሂደት ነው፣፣ መሆን፣ አለመሆን አይነጣጠሉም፣፣ ይህን የተፈጥሮ ህግ ለመለወጥ ምንም ሃይል የለንም፣፣ የህይወት ወይም የመኖር ፍፃሜ ሞት ከሆነ፣ የማሰብ ችሎታ፣ ተስፋ የማድረግ፣ የመፍጠርና የማፍቀር ተሰጥዎ ላላቸው የሰው ልጆች ሁኔታው ጭካኔ የተሞላበት ከንቱ መፍጨርጨር ሆኖ የሚታይ ይመስላል ነው የሚሉት፣ አይደለም?

@OLDBOOKSPDF



— ቲ ቲ ቲ ቲ — ሽበታም ራሳቸውን እየጎነተሉ።

— ምንድን ነው እኮ የሚያስቅዎት?

— እንተ፣ ህይወት፣ ሳቅም ያስቀኛል — ቲ ቲ ቲ ቲ — ትላልቅ ጆሮዎቻቸው እስኪነቃነቁ ድረስ።

— እሺ፣ ህይወት በሁለት ዘለአለማዊ ጨለማዎች መካከል ከመቅፅበት ብልጭ ብላ መልሳ ድርግም የምትል ብልጭታ ናት። በዚህችም ብልጭታ ውስጥ ደስታና መከራ፣ ሀሴትና ስቃይ አለ። መኖር ደስታ ነው። ሞት ስቃይ ነው። መውደድ ደስታ ነው። መለየት ስቃይ ነው። ስለሆነም ምንም እንኳዋን ለውጥ የተፈጥሮ ህግ ቢሆንም፣ መወለድ፣ ማደግ፣ ማርጀት፣ መክሰምና መሞት ቢኖርም፣ የመኖር ትርጉም ደስታን መጨመርና ባንፃሩ ደግሞ መከራና ስቃይን መቀነስ ነው። ደስታን መሻት፣ ስቃይን መቀነስ የተፈጥሮ ህግ ነው። እንዲህ ነው የሚሉት? ሆኖም ደስታና ስቃይም ቢሆን ተነጣጥለው ሊታዩ አይችሉም። መኖር ካለ መሞት ይኖራል። ራሱን ያዳነ ይሞታል ይል የለ መፅሐፉም። ለመኖር መታገል ግዴታ ነው። ይገባኛል። መኖርን መምረጥ ሞትን መፍራት ላይሆንም ይችላል። ግን እርስዎ ዝም ብለው ሞትን የሚፈሩ መሰለኝ።

ቲ ቲ ቲ ቲ ቲ ።

— ነገሬ አልጣመዎትም መሰለኝ። እርግጥ ቁም ነገሩ መኖር ብቻ አይደለም። መኖርማ ጎመንም እንስሳትም ይኖራሉ። የመኖር ትርጉም በደመ ነፍስ ብቻ መንቀሳቀስ ማለት አይደለም ነው የሚሉኝ። የማዳመጥ፣ የማየት፣ የመዳሰስ፣ የማሽተትና ጣእም ለይቶ የማወቅ ተሰጥኦዎችንን በሃይል አንቅተን ህይወት እዳመጣጥዋ በመቅሰም ሙሉ ህይወት መኖር ማለት ነው ህይወት። ከህይወት ስልትና ሂደት ጋር መሽከርከር ማለት ነው ህይወት። እና ዘለአለም ከህይወት ሂደት ጋር እየተሽከረከሩ ለመኖር ይፈልጋሉ አይደለም? ግን ማወቅ ያለብዎት ሌላ ነገር አለ። ተፈጥሮ ለእንደኔና ለእንደርስዎ ያሉ ግለሰቦች ደንታ የላትም። ተፈጥሮ የምታተኩረው በዘር ላይ ነው። ስለዚህ ተፈጥሮ የግለሰቦችን መወለድና መሞት፣ የነገሮችን እድገትና መክሰም አታውቅም። ትውልድ ያልፋል፣ ትውልድ ይተካል። ፀሐይ ትወጣለች፣ ትጠልቃለች። ህይወት ያልፋል፣ ትውልድ ይተካል። ፀሀይ ትወጣለች፣ ትጠልቃለች። ህይወት ይቀጥላል። ዘለቄታ ያለው ዘር ነው። ግለሰብ አይደለም። ስለዚህ ሞትን እመልጣለሁ ማለት ዘበት ነው።

@OLDBOOKSPDF



— ቲ ቲ ቲ ቲ ቲ ቲ። እስቲ ልሳቀው። ሁሉም ነገር ያልፋል ነው የምትለኝ። በዚህ አለም ዘለቄታ ያለው ነገር ምንም የለም ነው የምትለኝ። ሰማይ፣ ምድር፣ ፀሀይ፣ ከዋክብት፣ ጨረቃ፣ በፊት አልነበሩም? አሁን የሉም? ወደ ፊትም አይኖሩም? ምንነው ሰው ብቻ! ወቸ ጉድ!!

— እነሱ አያልፉም ያለ ማን ነው!

— ሲያልፉ አላየንም። ቲ ቲ ቲ ቲ ።

— እና ፀሀይ፣ ከዋክብት፣ ጨረቃ መሆን ይፈልጋሉ? መፋጠጥ ከሞት ጋር፣ እ?

— ወደ መቃብሬ ልታወርደኝ አትቸኩል። የኔ ወደ መቃብር መውረድ እንተን የትም አያደርስህም። ዘራፍ ብያለሁ። ሞት እያሸንፈኝም፣ የታባቱንስና። እፋለመዋለሁ።

— በአለም ውስጥ አንድ አይነት ስርአት ያለ ይመስላል። የከዋክብት ንቅናቄ፣ የምድር መዞር፣ የወቅቶች መፈራረቅና የሰው ልጅ ህይወት ኡደት። ግን፣ የሰው ህይወት ራሱ መላ ቅጡ የጠፋ ነው። ሁሉም የራሱ አቋም፣ እመለካከትና ስሜት አለው። የራሱን መብትና ፍላጎት ብቻ ለማስከበር ይፈልጋል። አብዛኛውን ጊዜ የሌላውን መብትና ፍላጎት፣ እንዳንዴም የራሱንም ጭምር ባለማወቅና ባለማጤን። ግን፣ የምንኖራት ህይወት መጨረሻ ምን እንደሆነች ሁላችን እናውቅም። ማእበል ከሚያንገላታት መርከብ ላይ አብረን የምንጉዋዝ ፍጡራን ነን። የጉዞአችን ፍፃሜ ላይ ስንደርስ ግን እያንዳንዳችን ብቻችንን እንቀራለን — ብቸኛ በረራ ወደ ዘለአለማዊነት። እና ብቻዬን እልሄድም ነው የሚሉት አይደለም?

— ቲ … ቲ … ቲ ….

ደራሲው ትንግርት ነው ብሎ ወደ ጠረጴዛው እያነጠሰ ተመለሰ። ግጥጥ፣ ፍጥጥ፣ እንደ አ.ጋፋሪ እንደሻው። ድርቅ፣ ግትር፣ ጠብ የሚል ነገር የለም። እሳቡን በቃላት ወረቀት ላይ ለማስፈር አልቻለም። ሰብለ መጥታ ከፊቱ ድቅን። እቤት ፈገግታዋ። ልብ ያሞቃል።

— ምን ክርቢ ላጢስ? ለየትኛው አምላክ ወይም ዛር፣ በየትኛው ተራራ ወይም ምኩራብ ላይ ምን መስዋእት ልሰዋ? ማንን ምን ብዬ ልማፀን? ለየትኛው አምላክ ወይም ሰይጣን ልስገድ? የማንን ስም

@OLDBOOKSPDF



በምን ቃላት ልጥራ? የመፍጠር ጥዋፍ በርቶ ዕርሃ እርያም እንዲታየኝ? አለ፡፡

ምንም አዲስ አሳብ አልተከሰተለትም፡፡ እጋፋሪ እንደኛውን ምን እንደምጊደርጋቸው አልተገለፀለትም፡፡

– እኔው ፈጥሬአቸው የማደርጋቸው ነገር እንዴት ይጠፉኛል? ፈጣሪያቸው መሆኔን ዘንጉት ወይስ ካንተ የበለጠ ህይወት አለኝ ማለታቸው ነው! አለ፡፡ የሚደርጋቸው ነገር አልታይ አለው፡፡

ይልቅ፣ ሰብለ ፀሀያማ ፈገግታዋን እያሳየችው እጆዋን በማውለብለብ ከሩቅ ስትጠራው – ወደ ህይወት ምንጭ ና ስትለው ታየችው፡፡ አንዳንዴ ብቅ ብላ ትታየዋለች – ሰብለ ወርቅ፡፡ የሰብለ ስእል በድንገት ከወረቀቱ ውስጥ ብቅ፣ ከቃላቱ መሀል ብቅ፣ ከአረፍተ ነገሮቹ መሀል ቁልጭ እያለ ይታየዋል፡፡ ግን አይቆይም፡፡ ምስልዋ እንደ ሰባቢ አሽኩርምሞት ውልብ፣ ጥፍት ይልበታል፡፡

– ተዪኝ አባክሽን፡፡

ወከክ የሚያደርግ ፈገግታ፡፡

– ተዪኝ ብዬሻለሁ፡፡

ፈገግታዋ በይበልጥ በግ፡፡

– በሰላም ባልሽን አትፈዪ ለምን አትተኚም? ምን ታደርጊያለሽ ካሳቢ ጉዋዳ ውስጥ?

የታችኛው ከንፈርዋን ጣል! እንቁ መሳይ ጥርሶችዋን ብልጭ! ስለ መፅሀፉ ምን ተሰምቶአት ይሆን?. . . ደሞስ ለምን ሰጠሁዋት? የሚፅፈውን ሁሉ ለምን እንደሚያስነብባት አይገባውም፡፡

ደራሲው ባሳቡ ከሰብለ ወርቅ ጋር ለመጫወት ጊዜ አላገኘም፡፡

ዕጌ ከእንቅልፍዋ ነቅታ እንደ ገና ብቅ፡፡ ደራሲው እንድ እፍኙት መንፈስ መሰላው ድንገጥ፡፡ ሻሽዋ ተፈትቶአል፡፡ ጠጉርዋ ተበታትኖአል፡፡ አንድ ጡትዋ ከሴሊት ልብስዋ ውስጥ አፈትልኮ ወጥቶ ይታያል፡፡ ደረትዋ ትኩስ እንደተላጠ ሽንኩርት ያንፀባርቃል፡፡

"ለራስህ እንቅልፍ አጥተህ እኛንም እረፍት ባትነሳን ምናለበት?" አለች፡፡ ·

@OLDBOOKSPDF



«ምንጠፋሁ?» አላት፥ በጎረና ድምፅ።

«ደሞስ፥ ንፋሱ እንዲህ አገሩን ሲደበላልቅ ልጄን ሂደህ አይዞህ ብትለው ነውር ነው?»

«ምን ይሆናል ብለሽ ነው የተቸገርሺው? ንፋስ ይዞት አይሄድ። ወይስ ጣራያው ተደርምሶ ይወድቅበታ ብለሽ ነው!»

የምላስ ወለምታ በቅቤ አይታሽም አሉ። ስለ ቤቱ ጣራያ መደርመስ በማንሳቱ ተፀፅቶ ሸምቅቅ አለ።

ስለ መኖሪያ ቤት ካነሳች መቆሚያ የላትም። — ጣራያው ያንጠባጥባል፤ ግድግዳው ውሀ አዝሎ ኩፍ በማለት በዘነበ ቁጥር ያመረቅዛል። መስኮቶቹና መዝጊያዎቹ አመለኞች ናቸው፤ እሺ ብለው አይዘጉም። ሽንት ቤት ተራ መጠበቁ ከዳቦ ቤት ወረፋ ይብሳል። የቤቱ ወለል ቢውሉበት አይፀዳው፤ ዘለአለም አመዳም መስሎ እጅ ስባራ ያደርጋል። የመንደሩ ፍሳሽ ሁሉ መጥቶ የሚተኛው ከደጃፋችን ላይ ነው። ጉልበቱም ሰውነቱም በዚህ ቤት ላይ አለቀ። ልጄም በየጊዜው በጉንፋን ይሰቃያል። ተስቦ ወይም ወረርሽኝ አንድ ቀን ሳይገድለው አይቀርም። እርፍ — ገልገል። ይህንኑ ነው የምትጠብቀው። የኛ ደራሲ!

«ቤቱ መስራቱ ይቅር። መቼም እኔና ልጄ ለዚህ አልታደልንም። ራሳችን በወግ የሚወጣበት ቤት ይኖረናል ብለን አናስብም። ቀበሮ ጉድጉዋድ፥ ወፍም ጎጆ አላቸው። እኛ ግን አንገታችንን የምናስገባበት ቀዳዳ የለንም። ሌላ ቤት ኪራይ ለመፈለግ እንኳዋን ጊዜ የለህም። ዘወትር ከምትፅፈው ብእር ጠብ ያለልን ነገር ቢኖር መከራና ስቃይ ብቻ ነው። 'አትጩሁብኝ! ልጄን አስወጧልኝ!' ተሰቃይቶ፥ ተጨንቆና ተጠቦ ኑሮ። እንደ ልባችን የምንተነፍስበት ቦታ እንኳዋ የለንም። ዝግት። ድፍን። መቃብር። የመቃብር ኑሮ።

«ማለቴ እኮ» አለ ደራሲው፥ የባለቤቱን አሳብ ለማሳከር። ስለ ቤት አላነሳችም።

— ስለ ህመምዋ ታነሳ ይሆን? ምንዋን ይሆን ዛሬ ደግሞ ያመማት? ያልያዛት በሽታ የለም። ቤቱ—ግድግዳው፥ ጣራያው፥ ወለሉ፥ አልጋው ከእሱዋ ጋር ዘወትር ያቃስታል። ወይስ የትኛው ሀኪም ቤት ልሂድ ልትለኝ ይሆን? ግን ይሆን አዲስ ሀኪም

@OLDBOOKSPDF

መጥቶእል ወይም ተአምር የሚሰራ አዲስ ጠበል ተገኝቶአል ያላት? ደራሲው እንገቱን ደፍቶ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ቆመ፡፡

የያዘችውን ቁራጭ ወረቀት ሰጠችው፡፡

ወረቀቱን ከእጅዋ ተቀብሎ ሳያነብ፣ «የምን ወረቀት ነው?» አላት፡፡

«ሃጂ ሙስጠፋ ናቸው የላኩት» አለችው፡፡

የሃጂ ሙስጠፋን ደብዳቤ ባያነብም ምን እንደሚፈልጉ ያውቃል፡፡ በወጣ በገባ ቁጥር ደጅ እየጠበቁ አላስወጣ፣ አላስገባ እያሉ የሚያስቸግሩት እንሶ አሁን ደግሞ በደብዳቤ ጀመሩኝ እያለ ወረቀቱን ገለጠ፡-

«አቶ ሲራክ— በአላህ ብለህ ቤቱን ልቀቅልኝ፡፡ እንደምታውቀው ቤቱን ስለ መረጥኩ አበል አላገኝበትም፡፡ ከቤቱም ከአበሉም ሳልሆን እንዴት በስተርጅና ባዶ እጄን እመድ አፋሽ ሆኜ ልቅር? በአላህ ብለህ ፍረደኝ — ሃጂ ሙስጠፋ . . .»

ሲራክ ደብዳቤውን ቡጭቅጭቅ አድርጎ ጣለና፡- «ይህን መፅሀፍ ሳልጨርስ ንቅንቅ አልልም!» አለ፡፡

የፈራው አልቀረለትም፡፡

«ምናለ ይህን ቤት ለቀን ብንሄድ? ከቤቱ ወይም ከሰፈሩ ጋር አልቆረብክ» አለች፣ ፀጉርዋ ላይ የማይረጋውን ሻሽዋን እያስተካከለች፡፡

«ቆርቤአለሁ!»

«እኔንም ልጀንም ልታሰወጋን ነው፣ ለሌላ አይደለም፡፡ አንድ ነገር ቢደርስብን ምን ትጠቀማለህ?»

«ምንድን ነው የሚደርስባችሁ?»

«ሜት እየበሉ ሲረግሙ የሚያድሩት ማንን መሰለህ? እኛን ነው፡፡ የውሀ ጠብታ እያደረ ድንጋይ ይበሳል አሉ፡፡ እርግማንም እንደዚሁ ነው፡፡»

@OLDBOOKSPDF



«ሃጂ ሙስጠፋን የሚለመን እግዜር እኔን የማይሰማ ከሆን ምናለ፡፡ እኔም ወዳጀ ተቀምጬ ሜት እየበላሁ እደንቁረዋለሁ . . . እና፣ ፍርዱ ያኔ ይታያል» አላትና፣ ወደ ድርሰቱ ሊመለስ ሲል፡-

ስለ ቤቱ ትታ፣ «እሊጋው አስጠልቶሃል መሰለኝ?» አለች፡፡

የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነው ይባሉ፣ አለና በልቡ፡፡ «የሰላም እንቅልፍ የሚተኙ እድለኞች ናቸው» አላት፣ እንገቱን ደፍቶ ከሜማው ውስጥ ሾኮ የወጣውን ያውራ ጣቱን ቁልማማ ጥፍር እየተመለከተ፡፡

እንደ ፈራው፣ «እሱን ነው እኮ የምልህ» ብላ ጀመረች፣ «ይህ ቤት ሰላም እንደማይሰጥህ እኔስ መቼ አጣሁትና፡፡ ሞኝ መሰልኩህ? ሞኝ አይደለሁም፡፡ ተገንዝቤዋለሁ፡፡ ቆይቶአል ከተገነዘብኩት፡፡ እኔም ሆንኩ ልጀ ሰላም አንሰጥህም፡፡ ከኛ ጋር ሰላም የለህም፡፡ ባይገባህ ነው እንጂ እንዳንተው እኛም ሰላም የለንም፡፡ ካንተ ንቀት ሌላ የሃጂም እርግማን ሰላም ነስቶኛል፡፡ ሙቱ ነው የምትለን፡፡ የዚህ ቤት ሰላም ጉዳይ ነገር አለሙ አብቅቶአል፡፡ የተከፋፈለ ቤት አይቆምም፣ አሉ፡፡ የተከፋፈለ ልብ ማደሪያ የለውም . . .»

«የኔ እመቤት ባሳሰብኩት መንገድ ነው የመጣሽው፡፡ እኔ እኮ ለማለት የፈለኩት . . .»

«ተው ባክህ፡፡ ለማለት የፈለከውን ብለሃል፡፡ አፍ ሲያመልጥ፣ ጠጉር ሲመለጥ አይታወቅም ይባሉ፡፡ ሲታሰብ የነበረውን ነው እንጂ የተናገርከው . . .»

ደራሲው ጠጉሩን ነጨ፡፡ ጠጉር መንጨት ዋጋ ያለው ይመስል፡-

«አልገባሽም፡፡ ፈፅሞ አልገባሽም፡፡ ሊገባሽም አይችልም. . .»

«ደንቆሮ ነኝ! ደንቆሮ ነሽ በለኝ፡፡ ይሄው ነው የቀረህ፡፡ ያንተን አባባል ቀርቶ የዝንብ ጠንጋራ አውቃለሁ . . .»

«ደንቆሮ ነሽ ማለቴም አይደለም . . .»

«ታዲያስ?»

@OLDBOOKSPDF

«ቆዪ እንጂ፡፡ አድምጪኝ፡፡ እንደማመጥ . . .»

«የምን መደማመጥ ነው? ሰላም ያጣ ሰው ይቆርጣል፡፡ እንደማመጥ ብሎ ነገር! መደማመጥ ቀርቶአል፡፡ አክትሞአል፡፡ ድሮ ቀረ ልጄ . . .»

«እፉ!»

«እፉ ራስህ!»

«የሰላም እንቅልፍ አግኝቶ የማያድር ሰው እድለኛ ነው ስል ምን ለማለት እንደ ፈለኩ አልገባሽም፡፡ ባጭሩ፥ አሳብ አለብኝ ማለቴ ነው . . .፡፡»

«እኮ ያንተ አሳብ ሁልጊዜ ውጭ ነው፡፡ እኔ እቃ ነኝ፡፡ ስለኔ ታስባለህ አላልኩም፡፡ ያንተ አሳብ ወደ ውጭ ከኮበለለ ጊዜ የለውም፡፡ አንተ ምን ታደርግ፡፡ እኔ በገዛ እጄ ነው ራሴን እቃ ያደረኩት . . .»

«አባክሽ በፈጠረሽ! እንደ መንደር ጠበቃ ነገር አትጠምዝዢ፡፡ አሳብ አለብኝ ስል ስለ መፅሀፌ አስባለሁ ማለቴ ነው፡፡ የጀመርኩትን ከፍፃሜ ማድረስ አለብኝ! ይህን ለማድረግ ደግሞ ሙሉ ጉልበቴንና አእምሮዬን መጠቀም አለብኝ . . .»

«እህህ . . . እሆሆሆ . . . እህህህ . . . መፅሀፍ፡፡ ዶሮን ሲያታልሉዋት በመጫኛ ጣሉዋት አሉ፡፡ መፅሀፍ ነው ዘወትር የሚያስመሽህ — እ? መፅሀፍ ነው መሸተኛ ያደረገህ — እ? መፅሀፍ ነው ቤት በገባህ ቁጥር እንደ ህልም እየታየህ የሚደብትህ? ቤት ያፈራው እህል እንዲያቅርህ የሚያደርግህ? እንቅልፍ ነስቶ አልጋህን የሚያስጠላህ፥ ቤት በገባህ ቁጥር የሚያነጫንጭህ፥ የሚያስኮርፍህ፥ እኛን ማየት የሚያስጠላህ፥ መፅሀፍ ነው! አይደለም! እህህህ . . . ሰው የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል አኮ፡፡ እህህህ! ልሳቀው እንጂ፡፡ በልጅ አመሃኝቶ ይበሉዋል እንጉቶ ይባላል፡፡ ለጠባይህ መለወጥ ሌላ ምክንያት ብትፈልግ ይሻል ነበር፡፡ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ አሉ፡፡ መፅሀፍ ብሎ ነገር፡፡ አይዞህ አትጨነቅ፡፡ ቤቴ አስጠልቶኛ ነው፡፡ ልቤ ወደ ውጭ ኮብልሎ ነው፥ ማርታ ትዝ እያለችኝ ነው ብትል ምንኛ ባማረብህ . . .፡፡»

«ምን እንደምትዪ አይገባኝም . . .»

@OLDBOOKSPDF



«እንዴት ብሎ ይገባሃል! ልብህ ያለው ማርታ ጋ፡፡ ታዲያ አይምሰልህ፡፡ እንዲህ እንደ ቀለድክብኝ አትቀርም፡፡ እኔም ተራዬን አቀልድብሃለሁ፡፡ ላንተ የዘነበው እድል ለኔም ያካፋል፡፡ እቃ ሆኜ አልቀርም፡፡

«ስታገባኝ የገባህልኝን ቃል ታስታውሰዋለህ? ምን ልብ አለህና፡፡ ነበር እንዲህ ቅርብ፡፡ የተረፈኝ ሀዘን ብቻ ነው፡፡ ውርደት ብቻ ነው፡፡ ቤትን ማክበር፥ ባልን መውደድ ያዋርዳል? ቤተሰቤን፥ ልጄን በማለት ቀና ደፋ ማለት ያስንቃል? አይምሰልህ፡፡ ባንተ ቤት ነው ርካሽ እቃሊ ጨው የሆንኩት፡፡ ግን አትሳሳት፡፡ እኔም ለባብሼና አጊጬ ብወጣ ሽህ አስከትላለሁ! ደሞ ላዲሳባ ወንድ . . .!፡፡»

እሳታዊ የሰይጣን ምላስ፡፡ ወላፈኑ ከሩቅ የሚጋረፍ የሚንቀለቀል የገሃነም እሳት፡፡ የእሳት ላንቃ፡፡ ሲኦል የወረደች ነፍስ፡፡ እረፍት የማይሰጥ የሲኦል ትል፡፡ ነደደ፡፡ ተቃጠለ፥ በጣ እለ — ደራሲው፡፡

«እና፥ ታዲያ ምን ያዘሽ! መንገዱ ሰፊ ነው፡፡ ሂጂ፥ ደንታ የለኝም፡፡ ልጃገረድ ሆንሽ ያገባሁሽ መሰለሽ? የተገናኘነው ሰራተኛ ሰፈር ነው — ከፊለግሽ!»

ፅጌ ወገብዋን ይዛ ሻሽዋን እየነቀነቀች፥ «ጥሩ፥ ይህንኑ ነበር ካንተ የጠበኩት፡፡ ውለታዬ ይህ ሆነ? ሰራተኛ ሰፈር ብታገኘኝ ታዲያ እግርህ ላይ ወድቄ አላገባኸኝ፡፡ ለምንህ ነው ያገባኸኝ፡፡ እንደ ማርታ የሚኒስትር ልጅ አለመሆኔን፥ እንደሰዋ ያልተማርኩ፥ መናጢ ደሃ መሆኔን እያወክ ነው ያገባኸኝ፡፡

«ታስታውስ እንደሆን እኔም ነግሬህ ነበር፡፡ አይሆንም ብዬህ ነበር፡፡ ግን አንተ ምናልክ፡፡ «ግድ የለሽም፡፡ ቤተኛ አዳሪ የሆንሺው ወደሽ አይደለም፡፡ ችግር አስገድዶሽ ነው፡፡ ያለፈው አለፈ፡፡ ሞተ፡፡ ተረሳ፡፡ የሰው ማንነት የሚለካው ባለፈው ኑሮው ሳይሆን አሁን ባለው አቋሙ ነው፡፡ እኔ ከወደድኩሽ ፅጌ እንዲህ ነበረች ቢሉ ደንታ የለኝም» እያልክ ነው ያግባባኸኝ፡፡ እሺ ያልኩህ ለት ምላሴን በቆረጠው ኖሮ . . .!፡፡»

ፅጌ ባንድ ፊት እሳታዊ ምላስዋን እያንቀለቀለች በሲላ በኩል እንባዋን እያዘራች ስትራመህበት፥ ደራሲው፥ የሚቆምበት፥ የሚቀመጥበትና የሚገባበት ቀዳዳ ጠፍቶት ቢጨነቅ ቆየና፥ ግንፍል

@OLDBOOKSPDF

ሲልበት እያፈጠጠ ሲስቅበት የነበረውን ንጭ ወረቀት ቡጭቅጭቅ አደረገ።

ድርሰት፡፡ ውበት፡፡ ኪነት፡፡ ድርሰትና ህይወት፡፡ ኢጭ ብሎ እጁ ውስጥ የቀረውን እፍኝ ብጫቂ ወረቀት ወደ ላይ በተነ፡፡

## ምእራፍ ፪

ሰብለ ወርቅ ታፈሰ በሩ ሲንኳኳኳ አልሰማችም፡፡ ሶፋው ላይ እንደ ተጋደመች እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወስዶአት ነበር፡፡ ደስ የሚል ፈገግታ ከብ ፊትዋ ላይ ይታያል፡፡

ሲታነበው የነበረው ባረንጉዋዴ ከላሰር የተሸፈነ የዕሁፍ ረቂቅ ከደረትዋ ላይ ተዘርግቶ ቀርቶአል፡፡ የሳሎኑ መብራት ዝም ብሎ ይጠፋል፡፡

ንዴት የታከለበት ኩዋኩዋታ፡፡ ሰብለ ወርቅ ከእቅልፍዋ ብንን፡፡ ያለችበትን በመርሳትዋ ድንግር፡፡ ምዕአት ደርሶ የሲኦል በር የተደረመሰ ይመስል ድንግጥ፡፡

የባሰ ንዴት የተቀላቀለበት ሃይለኛ ኩዋኩዋታ፡፡

ሰብለ እየተንጫነጨች ከተጋደመችበት ቀና ስትል፥ ደረትዋ ላይ ተዘርግቶ ቀርቶ የነበረው የዕሁፍ ረቂቅ ተንሸራትቶ ከቀዩ ምንጣፍ ላይ ወደቀ፡፡ አላነሳችውም፡፡ አእምሮዋን ሰብስብ ለማድረግ ጊዜ አላገኘችም፡፡ አይኖችዋን አሻሸችና እያዛጋች ሄዳ በሩን ከፈተች፡፡

‹‹የሞትሽ መሰለኝ ነበር›› አላት፥ ባልዋ በቁጣ፥ በግዙፍ ቁመናው ላይዋ ላይ እያንገርበበ፡፡

በፈጣጣ አይኖቹ ሰብለ ተኝታበት የነበረውን ሶፋ ቃኘ፡፡ ከሴቱ እታ ሌላ ምንም አልነበረም፡፡

ሰብለ ዝም - ድካሙን ፈርታ፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹ወይስ ለክፋት ብለሽ ነው?››

ሰብለ ጥፊውን ፈርታ እጅ እጁን እያየች ዝም፡፡ ዘመን አለሙ፥ የትም አምሽቶ በገባ ቁጥር አስቀድሞ ይቆጣል፤ ሲለውም ይማታል፡፡ እብዮቱ ከፈነዳ ወዲህ ያመጣው ጠባይ ነው፡፡

‹‹የት እንዳመሸሁ ለምን አትጠይቂኝም?›› አላት፡፡

የት እንዳመሸ ትንፋሹ ይናገራል፡፡ የውስኪው ሽታ ከሩቅ ይገፋተራል፡፡ አይኑ የዝንጀሮ ቂጥ መስሎአል፡፡ ጥቁር ፊቱ እንደ ኑግ ተቅለጥልጦ ያብለጨልጫል፡፡ ሳቅ ቃጣት፡፡ ግን አልሳቀችም፡፡ የትስ ብታመሽ እኔ ምን ቸገረኝ ለማለት ፈልጋ ነበር፡፡ ግን አሳብዋን ለወጠችና፥ ‹‹አንተው ንገረኝ›› አለችው፥ የታችኛውን ከንፈርዋን ጣል አድርጋ፡፡

ሲከፋትም፥ ደስ ሲላትም የታችኛውን ከንፈርዋን ጣል ታደርጋለች፡፡

‹‹አንቺ ለምን አትጠይቂኝም? ወይስ ደንታ የለኝም ማለትሽ ነው? አይደለም? አይደለም? እ? ብሎ ተጠጋት፡፡

ሰብለ እጅ እጁን በንቁ ትናንሽ አይኖችዋ እየጠበቀች፥ ሳቂታ ፊትዋን እንደ ማሸሽ አለች፡፡

ወፍራም ከንፈሩን ነክሶ አይኖቹን ሲጎለጉልባት ፈርታ፥ ‹‹ራት ይቅረብልህ?›› አለችው፡፡

‹‹የት ያማስልሽውን ወጥ? ለመሆኑ ወጥ ቤቱ ምን እንደሚመስል ታውቂዋለሽ? አታውቂም፡፡ አንቺ የምታውቂው ጨርቅ፥ የጥፍር፥ የከንፈርና የፀጉር ቀለም ማማረጥና ተኩዋኩለሽ ቢሮ መግባትና መውጣት ነው፡፡ ሌላ ምን ታውቂያለሽ? ልጆቹ ምን በሉ? ምን ጠጡ? የት ወደቁ? - ምን ሲደረግ ትገቢ ብሎሽ፡፡ ውሻ! አንቺ ሰርተሽ የምታመጪው ደሞዝ ከብጣሽ ጨርቅ አያልፍም፡፡ ገረዶች በየወሩ ቆንጥረው የሚወስዱት ቢታሰብ ካንቺ ብጣሽም ደሞዝ ይበልጣል፡፡

‹‹ደሞ ፋይዳ ያለው ይመስል ስራዬ ማለት፡፡ ስራ ስራ የምትዪው ለምን እንደ ሆነ አላጣሁም፡፡፡›› ምራቁን ጢቅ አደረገና፥ ‹‹ለመሽራሞጥ ነው፡፡ ለሌላ አይደለም፡፡ በገዛ መኪናዬ ሾፌር ሆኜ

@OLDBOOKSPDF

እያመላለስኩ ማቃጠሬ ነው የሚቆጨኝ። አንድ ቀን ደህን ትንዢረኛ ፊትሽን ሳላጣምመው ብቀር እኔ ወንድ አይደለሁም!» አላት።

ዘመን ከራሱ ድምፅ ሌላ ምንም አልሰማም። ድምፁ ግድግዳ ላይ እየነጠረ ተመልሶ ከጆሮው ውስጥ አስተጋባ። በንዴት እንደፈረሰ እናፉ። ከአብዮቱ ወዲህ የዘመን ስድብ የዘወትር ምስዋ ስለሆን ሰብለ ነገሩን ባንድ ጆሮዋ በግማሽ ልብ እየሰማች በሌላው ጆሮ ዝም ብላ ታፈስዋለች። ቁጣውን የሚያባብሰው ደግሞ ዝምታዋ።

«ንቀት ነው። ንቀት ነው ኮ እንዲህ የሚዘጋሽ። ለምንድር ነው መልስ የማትሰጪኝ?»

«ምን ብዬ?» አለች፥ በተሰላቸ ድምፅ።

«ጅል!»

«ጠብ ያለሽ በዳቦ። ምን በደልኩህ? እኩለ ሌሊት ድረስ ተጎልቼ ስለ ጠበኩህ ነው ይህ ሁሉ ውርጅብኝ የሚደርስብኝ? ጡር ነው። በውነት ግፍ ነው። ጡር ብትፈራ ምናለበት!» አለችውና፣ የታችኛውን ከንፈርዋን ጣል አደረገች።

አፍዋ ሰፋ ብሎ ጥርሶችዋ በጥንቃቄ የተደረደሩ ትናንሽ እንቁዎች ይመስላሉ። ከግንባርዋ ላይ ከንበል ደፋ ብሎ የሚታየው እጭር ፀጉርዋ ክብ ፊትዋን የባሰውን ክብ ያደርገውና ሙሉ ጨረቃ ያስመስለዋል።

«የምን ጡር?» ብሎ በወፍራም ድምፅ አንባረቀባት።

የታችኛውን ከንፈርዋ የባሰውን ጣል አደረገች።

«እሺ። የጡሩን ነገር እንተወውና ራት ይቅረብልህ» አለችው፥ ስልችት ብሎአት። አዛጋች። አይኖችዋ እንባ አቀረሩ።

«ምናለሽና!» ብሎ አመናጨቃት

«ከክ ወጥ። ጎመንም አለ» አለችው፥ ውስጥ ውስጡን እየሳቀች።

@OLDBOOKSPDF



ፊቱን ከሶ እስመሰሉ አፈጠጠባት፡፡ የሚወደው ክትፎ የለም፡፡ ክትፎ ሲኖር ነው ፊቱን ትንሽ ፈታ አድርጎ የሚጎርሰው፡፡ ጥሬ ስጋ የለም፡፡ ቢኖርም ያቅበጠብጠዋል፡፡ ቤቱ የሚሰራ ምግብ አይጥመውም፡፡ የሰው ቤት ያልፈላ ሽሮ ይመርጣል – ሰብለን ለማብሸቅ በፊት የሰውን ቤት የማይረባ ምግብ እያደነቀ ሲበላ ትበሽቅ ነበር፡፡ አሁን ግን፣ ምን ብሰራ ሳይጥመው በማለት የባልትናውን ነገር እርግፍ አድርጋ ትታዋለች፡፡

‹‹ክክና ጎመን!›› አላት፡፡

‹‹ይኸው ነው ያለው፡፡ ለሱም ተመስገን ማለት ያስፈልጋል፡፡ ስንቱ ነው ሆዱን እያከከ የሚያድረው፡፡ የገበያውን ሁኔታ የሚገነዘበው ያየው ብቻ ነው፡፡ ሁሉም ነገር ሰማይ ወጥቶአል›› አለች፡፡

‹‹ማስተዳደሩን ባታውቂበት ነው እንጂ የኔ ደሞዝ ለሆዳችን እንኳ አይደለም፡፡ ዝርክርክ!›› አላት፡፡

ተናደደችና፣ ‹‹የኔም ተጨምሮበት አልበቃም፡፡ በገፍ የተለመደ ኑሮ አክትሞአል፡፡ ችግሩ በኛ ቤት ብቻ የመጣ መሰለህ እንዴ ሆን ተሳስተሃል፡፡ ባገር ነው የመጣው፡፡ ቀበቶህን ጠበቅ፣ እኔን ለቀቅ›› አለች፣ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፡፡

ቀጠለችና አንገትዋን እንደ እስክስታ ወራጅ አንከት አድርጋ፣ ‹‹አህያውን ፈርቶ ዳውላውን እሉ፡፡ ያባትክን ርስት ሰብለ ነጠቀችህ አሉ እንዴ? እኔን ነጋ ጠባ በመጨቅጨቅ የተወረሰው መሬትና ቤት አይመለስልህም፡፡ ሰብለ ለሀብት ደንታ እላት ብለህ አታስብ!›› አለችው፡፡

– እንግዲህ የልቤን ተናግሬ ከወጣልኝ የፈለገውን ያድርግ፣ ቢፈልግም ይግደለኝ ብላ ዝም አለች፡፡

ዘሎ ያንቀኛል ብላ ትጠብቀው ነበር፡፡ ዘመኑ ግን ከቆመበት ቦታ አልተንቀሳቀሰም፡፡ ሳያስበው ድንገት ራሱን የተመታ ሰው ይመስል ተደናግሮ ፈዞ ቆሞ ቀርቶ ነበር፡፡

ረጋ ባለ ድምፅ፣ ‹‹አብረን ያፈራነው ሀብት ቢሆን ኖሮ እንዲህ አትዪም ነበር›› አላት፡፡

ሰብለ፣ ድህነቱን ለማስታወስ ብሎ የተናገረው ነገር ነው ብላ በማሰብ፣ ‹‹አንተም አላፈራኸውም፡፡ በውርስ የተገኘ ሀብት ነው፡፡

@OLDBOOKSPDF



አብረን ያፈራነው ሀብት ቢሆንም፥ ቢሄድ ግድ የለኝም፡፡ ዋናው ቁም - ነገር ፍቅርና ሰላም ነው፡፡ ሀብት አይደለም፡፡ ፍቅር፣ ሰላምና ጤንነት ካለን፥ ሰርተን ለመኖር ከቻልን፥ ሀብት ምንድን ነው?» አለች፡፡

«አይ የኛ ፈላስፋ!» ብሎ አንጉዋጠጣት፡፡

ከስተር ብላ፥ «መፈላሰፍ ሳይሆን የጊዜው ጥያቄ ነው» አለችው፡፡

«ይህ እውቀትሽ የተገኘው ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምድ ነው? ወይስ ከምታነቢያቸው ርካሽ መፅሀፎች?» አላት፡፡

«ከምንም ይሁን ከምን እውነት ነው፡፡ ሰርቶ ለመኖር መጣጣር የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው» አለች፥ ፍርጥም ብላ፡፡

ራሱን በትዝብት ነቀነቀና፥ «አይ የኛ ሰራተኛ! አይ የኛ አዋቂ! እንዲህም አርጎ የለ» አለ፡፡ «አንቺ ብሎ ሰራተኛ፡፡ አንቺ ብሎ አሳቢ፡፡ ርካሽ መፅሀፍ ማንባቢጥሽን ትተሽ ቤትሽን በጠረግሽ፡፡ እንደ ሴቱ ጉዋዳሽን በዞርሽበት፡፡ ደሞ በገበያ ማላከክ፡፡ ጉልት፥ የት ምን እንደ ሆነ ታውቂአለሽ ለመሆኑ? ምን ሲደረግ፡፡

«ብየወሩ ለቤት ወጭ የምሰጥሽ ገንዘብ ትንሽ አይደለም፡፡ በዚህ ላይ የቤት ኪራይ የለብን፡፡ ያሉን ሁለት ህፃናት ልጆች ናቸው፡፡ ውጤቱ ምንድን ነው? ከከና ጎመን ያውም የጎረና፡፡ በትንሽ ደሞዝ፥ ያውም በኪራይ ቤት፥ ከኛ አስር ጊዜ የተሻለ ኑሮ የሚኖሩ ሞልተዋል፡፡ ለምን ይመስልሻል? ትዳሬ የሚሉ ሴቶች ስላሉበት ነው፡፡ ሰርተን ለመኖር ከቻልን ሀብት ምንድን ነው? ብሎ ነገር፡፡ እስካሁን ያኖረሽ በገፍ የሚመጣው ሀብት ነበር፡፡ አንቺ ቢሮ ገብተሽ መውጣትሽን፥ ማኪያቶ ስታንቃርሪ መዋልሽን፥ ቢሮ ከመጣው ጎረምሳ ጋር ስትገለፍጭና ስትዳሪ ጊዜ ማሳለፍሽን ነው እንጂ የትዳር ነገር ምን ሲደረግ ትውስ ይልሻል! ሽርሙጣ!» አላትና፥ ምራቁን ጢቅ አድርጎ ተጠጋት፡፡

በጥፊ እንዳይላት ፊትዋን አሸሸች፡፡ አልመታትም፡፡ ትኩር ብላ ተመለከተችው፡፡ ከነጭ ሸሚዙ ኮሌታ ላይ የከንፈር ቀለም ቦግ ብሎ ይታያል፡፡

«እኔ ሽርሙጣ አይደለሁም» አለችው፥ አፍዋን ሞልታ፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹ታዲያ ምንድን ነሽ?›› አላት፥ የውስኪ ትንፋሹ እስኪገፈትራት ድረስ፡፡

‹‹የሸሚዝህን ኮሌታ እየው፡፡››

ለማየት ሞከረ፡፡ አልቻለም፡፡ ክራቫቱን ፈታ፡፡ ኮቱን አወለቀ፡፡ ሸሚዙንም አወለቀ፡፡ የውስጥ ልብስ መልበስ አይወድም፡፡

የሸሚዙን ኮሌታ እየና፥ ‹‹ታዲያስ?›› አላት፡፡

‹‹የፋብሪካው ምልክት ይሆናል›› አለችው እያሾፈች፡፡

‹‹ጅል!››

‹‹ሌላ ጊዜ ስትገናኝ ሳትስምህ በፊት የከንፈር ቀለምሽን ጥረጊ በላት፡፡ ደሞ ከንፈርህ እያለ ለምን ሸሚዝህ ላይ ጊዜዋን ታጠፋለች? እጠባው እንዲተርፈኝ ነው?›› አለችውና፥ የታችኛውን ከንፈርዋን ጣል አደረገች፡፡

ፊትዋ ላይ ምንም አይነት ስሜት አይነበብም፡፡ በቅናት ጦፋ ጥፍሮችዋን በማሾል አልቡዋጨረችውም፡፡ ጥርሶችዋን እግጣ አልነከሰችውም፡፡ ሻሽዋን እየነቀነቀች፥ ወገብዋን እየሰበቀች፥ ሽንጥዋን በሁለት እጆችዋ ይዛ ምላስዋን አላሾለችበትም፡፡ ጫማዋን አውልቃ አልወረወረችበትም፡፡ ዝም ብላ ነበር በንቀት አይን የምትመለከተው፡፡ አመለካከትዋ እንደ ጦር ወጋው፡፡ ውስጡ፥ ብስጭት፥ ንድድ፥ ሽምቅቅ፥ ኩምትር ሲል ተሰማው፡፡ አፍሮ አይደለም፡፡ ለምን አትቀናብኝም በማለት ነበር፡፡ ሳታስበው በድንገት ቃሪያ ጥፊ አላሳት፡፡ ከግድግዳው ጋር ተላትማ ተመለሰች፡፡ ለመከላከል ያህል እንኳዋን እጆችዋን አላነሳችም፡፡ ዝም ብላ ትክ ብላ አየችው፡፡ በዚያች ቅፅበታዊ ትከታ ውስጥ ከዚህ ሰው ጋር ያሳለፈችውን ከንቱ፥ ባዶ፥ መና አመታት ባስታወሰች ጊዜ ውስጥዋ ተናጠ፥ ተናወጠ፡፡ እሱን ለማስደሰት፥ እሱን አክብራ ለመክበር፥ ፍቅር ሰጥታው፥ ፍቅር ለመቀበል ምን ያህል ጥረት እንዳደረገች ትዝ ሲላት፥ ያርባ ቀን እድልዋን ረገመች፡፡ ላደረኩት ጥረት ሁሉ አፀፋው ምን ነበር? ንቀት፥ እርግማን – ስድብ፥ ጥርጣሬ፥ እንደ ቤት ገረድ መታየት፥ ወቀሳ፥ ደኅው ብቻ ነው ብላ አሰበች፡፡ ወፍራም ከንፈርዋን ነከሰች – በቁጭት – በንዴት፡፡

@OLDBOOKSPDF



ወንዶች ቀርተው ሴቶችም ቢሆኑ ቅናታቸውን በመዋጥ እንደ ብርቅ የሚያደንቁላት የተፈጥሮ ውበትዋ እንደ ጠወለገ አበባ ረግፎ የበሰለ የበረሃ ሎሚ መስለው ጉች ጉች ብለው የሚታዩት ጡቶችዋ ሙሽሽ ብለው ወድቀው፣ ንቁ አእምሮዋን የትዳር ዝገት አበልዞት፣ ሲጋ ሲግላጋ ሰውነትዋን የኑሮ ነቀዝ በልቶት፣ ተመጦ፣ ታኝኮ፣ የተጣለ የአገዳ ምጣጭ ሆና፣ የህይወት ምስጥ የቦረቦረው ባዶ ቀፎ መስላ፣ በመኖር ባለመኖር መካከል በቀጭን ክር ተንጠልጥላ ስትንገላታ፣ ህይወት እያሳቀ፣ ሳቁን የገደል ማሚቶ እየተቀበለች ካድማስ አድማስ ስታላጋ፣ ከገደል ገደል ስትወረውርና ስታማታ – ህይወት እየሳቀ፣ በጊዜ ክንፍ እየከነፈ አልፎአት፣ ወደ ሁዋላ ጥሎአት ‹‹ቻዎ!›› እያላት ሲሄድ ታያት።

ወፍራም ከንፈሮዋን እንደ ገና ነከሰች። በሀይል ነከሰች። ለመቁረጥ አልቻለችም። አሳብዋን አትቆርጥም። ሁልጊዜ ታስባለች። ልብዋ መንገደኛ ነው። ቆራጮችን ታደንቃለች። እስዋ ግን ከማሰብ አልፋ አሳብዋን አትቆርጥም። የታችኛውን ከንፈሮዋን ጣል አደረገች።

እድላችንን የሚወስነው ከመወለዳችን በፊት ሽክርክሪታችን ላይ የተጻፈው ያርባ ቀን እድላችን ሳይሆን፣ እኛው ራሳችን ነን. . . ፈሪ ከመሞቱ በፊት አስር ጊዜ ይሞታል፣ የጀግና ዕዋ ግን አንድ ናት . . . መቁረጥ ወይም አለመቁረጥ፣ ይህ ነው ጥያቄው . . . ይህ ነው ጥያቄው . . . እያለች ታስብ ነበር።

ዘመን እንደ ፈረስ እናፍና ብርድ ስለ ተሰማው ሽሚዙን አጠለቀ። የብብቱ ፀጉር አንፍሮአል።

ሚስቱን ተመለከተ። አይኖችዋን ሳትሰብር ዝም ብላ ተመለከተችው። የሚያደርገው ነገር ጠፋው። ‹‹ሽርሙጣ!›› አላትና፣ ሽሚዙን እየቆለፈ ዞር ሲል፣ ከምንጣፉ ላይ ተዘርግቶ የቀረ አረንጓዴ ክላሰር አየ። የሰብለም አይን ክላሰሩ ላይ አረፈ። ለማስጣል ጊዜ አላገኘችም።

ዘመን ክላሰሩን አንስቶ ካየው በሁዋላ ከፈት አደረገው። ‹‹ሊጋፋሪ እንደሻው ዘብሄረ ሸዋ›› የሚል በትላልቅ ቁም ፅሁፍ የተፃፈ አርእስት ከወረቀቱ ላይ ብቅ ብሎ አፈጠጠበት። ስለ አርእስቱ አላሰበም፣ አልተጨነቀም። ዋጋም አልሰጠውም። አይኑ የሚፈልገው ሌላ ነገር ነበር። ዝቅ አለ። የደራሲውን ስም ነበር የሚፈልገው። የበላለ ልብ ከበሮ መደለቅ ጀመረ። ከአርእስቱ ስር ዝቅ ብሎ በትናንሽ ፊደላት የተፃፈው፣ ‹‹ከሲራክ አርአያ›› ይላል።

@OLDBOOKSPDF



በሰይጣናዊ አይን ክፉኛ እያያት፥ «ማንነው ሲራክ?» አላት፡፡

ወፍራም፥ ነጎድጓዳማ ድምፁ ጆሮዋ ውስጥ አንባረቀ፡፡ ጥርሱን እንቃጨጨ፡፡ የደም ስሮቹ እያበጡ ሄዱ፡፡

«የመፅሀፉ ደራሲ ነው» አለችው፥ ስልቱን በሳት ድምፅ፡፡

«እሱን አላጣሁትም፡፡ ማይም መሰልኩሽ? ማን ነው እሱ ነው ያልኩሽ!»

«ለኔ ምኔም አይደለም፡፡ ጥያቄህ ይህ ከሆነ . . .»

«ምንሽም ካልሆነ የመፅሀፉ ረቂቅ እዚህ ቤት ለምን መጣ?»

«እንብቤ ምን እንደ ተሰማኝ እንዲነግረው ነው፡፡ ሌላ ጉዳይ በመካከላችን ኖሮ አይደለም፡፡ ብዙ ደራሲዎች ብቸኝነት ይሰማቸዋል፡፡ የሚፅፉትን ሌሎች ሰዎች እንዲያዩላቸው ይፈልጋሉ፡፡»

«እና አንቺን መረጠሽ?»

«የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ልብ ወለድ መፅሀፍ ማንበብ እንደምወድ ስለሚያውቅ ነው፡፡»

«የኛ አንባቢ፡፡ የኛ አዋቂ፡፡ የኛ የስነ ፅሁፍ ሰው፡፡ የኛ የኪነት ወዳጅ - እ? ኪነት ማይ ፉት! ኪነት እናትሽን! አንቺ ብሎ የኪነት አዋቂ፡፡ ሲታደንቂለት ከርመሻላ! እሱም ሲያስነብብሽ፡፡ ኪነት፥ ጥበብ ስትሰሩ! ስለ ስሜታችሁ ስታወሩ፡፡ ብቸኝነት እዳይሰማው ስታሜውቺው ከርመሻላ፤ የኛ ኪነት አፍቃሪ! ሽርሙጣ! ደንቆሮ!» እያለ፥ ጥርሱን እግጦ ሲንደረደር መጣባት፡፡

ሳይታወቃት አጠገብዋ ካለው ቡፌ ላይ መጋዝ የመሰለ ረጅም የዳቦ መቁረጫ ቢላዎ አነሳች፡፡ ጥርሱን እንዳገጠጠ አይኖቹን አፍጥጦ ቆመ፡፡ አልተጠጋትም — አይኖችዋ ውስጥ ከሩቅ የሚዋጋ ቀንድ ያለው፥ አረንጉዋዴ አይኖቹ እሳት የሚወረውሩ፥ መንታ ምላሱ የሞት መርዝ የሚተፉ፥ ጠረንገሎ፥ ፀጉራም ሰይጣን በድንገት ያየ ይመስል ቀጥ! ከቆመበት አልተንቃነቀም፡፡

@OLDBOOKSPDF



የደረቁትን ወፍራም ከንፈሮችዋን በሹል ምላሰዋ ላስ አረጠበችና ሰይጣን ከነተንኮሉ፤ ዛር ከነጉዋዙ መጥተው ያረፈባቸውን አይኖችዋን እያፈጠጠችበት፡ «አንተ እንደምታስበው ሸርሙጣ አይደለሁም። የልብ ኩራት ያለኝ ሴት ነኝ። እንዳንተም ግምት ደንቆሮ አይደለሁም። ጭንቅላት አለኝ። አንተ እንደምትለው አስቀያሚም አይደለሁም። ላንተ፤ እኔ ሸርሙጣ፤ ደንቆሮ፤ አስቀያሚ፤ የመንገድ ሴት ነኝ። ግን አይደለሁም! አይደለሁም! በቃ!

«ሴት ነኝ። ለዚያውም ተራ ሴት አይደለሁም። አይዞሽ፤ በርቺ የሚለኝ፤ ጥሩ ስራዬን የሚያደንቅልኝ፤ መጥፎም ከሰራሁ ከስህተቴ እንድማር የሚያደርገኝ፤ ከቤት እቃዎች ውስጥ አንዱ አለመሆኔን የሚገነዘብልኝ ባል እፈልጋለሁ። አንተ ግን ጠዋት ማታ፤ ነጋ ጠባ ሞራሌን ልትገድል ነው የምትፈልገው። ገረድ ልታደርገኝ ነው የምትፈልገው። ቢሻህ፤ አንተ ባሰኘህ ጊዜ፤ የምታገኘኝ እቃ አድርገህ ልትቆጥረኝ ነው የምትፈልገው፤ በቃኝ፤ እንገፈገፈኝ። በቃኝ!» አለች፤ ሲቃ ይዞአት እንባ እየተናነቃት።

«ሲራክ ያድንቅሽ። አይዞሽ፤ በርቺ ይበልሽ» አላት፤ ክላሰሩን አይኑዋ ስር አስጠግቶ።

«እኔ ከሲራክ ጋር ምንም ነገር የለኝም። ይልቅ መፅሀፉን ስጠኝ!» አለችው።

«መፅሀፉን ነው የምትፈልጊው? ይሄውልሽ» አላትና፤ ክላሰሩን ለመቅደድ ይታገል ጀመር። ጥራዙ ወፍራም ስለሆነ ባንድ ጊዜ ሸርክቶት ከፊትዋ ላይ ሊጥለው አልቻለም። በጥቂት በጥቂቱ እያደረገ፤ ወረቀቶቹን እየሸረከተ፤ እየቦጫጨቀ፤ 'ሲራክ ያውልሽ። የምታደንቂው ኪነት፤ ጥበብ፤ ኪነታዊ፤ ጥበባዊ ፍቅር። ሲራክ ማን እንደ ሆነ አጣሁትና ነው? አውቀዋለሁ። እንዳንቺው ሸርሙጣ ነው። የሚፅፈው ስለ ትንዝር፤ ስለ ወሲብ፤ ስለ ብልግና እንደ ሆነ ሰምቻለሁ። የማርታ ባል የነበረው አይደለም? ሌላ ማርታ ይፈልጋል። ማርትዬ ይልሻል አይደለም? እና ፅሁፉን ታደንቂያለሽ፤ ኪነቱን፤ ጥበቡን፤ እና እሱም የኪነት ሰውነትሽን ያደንቃል» እያላት፤ እሱዋም፤ «እረ በፈጠረህ . . . ምን ነው ሞቼ ባረፍኩት. .! ምናለ የሰው ፅሁፍ ባትቀድ. . . ደራሲውን እንደ መግደል ያህል ነው ኮ . . . ህይወቱን ነው ኮ የምታጠፋው . . . እረ እባክህን» እያለችው፤ እሱም ጥርሱን ነክሶ፤ ስሮቹን አሳብጦ፤ አይኖቹን ጎልጉሎ ከጥራዙ ጋር እየታገለ፤ አንጀት ጉበቱን እያወጣ፤ ሸርክቶ፤ ሸራክክቶ፤ ቦጭቆ፤ ቦጫጭቆ፤ ፊትዋ ላይ በተነላት . . .

@OLDBOOKSPDF



ሰአትዋን ተመለከተች፡፡ እኩለ ሌሊት አልፎአል፡፡ እዚያ ቤት ለማደር አልፈለገችም፡፡ ብረሪ ብረሪ አላት - የትም! ወዲትም፡፡ እግርዋ ወዳደረሳት ስፍራ፡፡ ገሃነም ይሁን ገነት፣ ገደል ይሁን ጉድጉዋድ፣ ግድ አልነበራትም፡፡

እንጀት ጉበቱ ወጥቶ፣ ተቦጭቆ፣ ተቦጫጭቆ የተበተነውን ወረቀት በመገረም እየተመለከተች፣ ሌላ ቅጂ ይኖረው ይሆን እምላኬ?

— ይንጋ ብቻ፡፡ እህል ውሀዬ አልቆአል፡፡ በቃ!፣ እንዳለች፣ ትንሽዋ ልጅዋ፣ ቲቲ፣ «ማሚ — ማሚ፣» እያለች ባዶ እግርዋን ድክድክ ስትል መጥታ፣ «ፈላሁ ማሚ፣ ፈላሁ፡፡ ውሀ ተማኝ» ስትላት፣ ቢላዎውን ጥላ ብድግ አድርጋ እቀፈቻት፡፡ ቲቲ እስከ እንገትዋ ድረስ በሽንት ርሳለች፡፡

«ፈላሁ፣ ማሚ!»

«እደይዞሽ ቲቲዬ» ብላ ሳመቻት፡፡ አቅፋ እንገትዋ ስር ሸጎጠቻት፡፡ ቲቲ ራስ ላይ ፊትዋን ደፍታ ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር፡፡

«ህይወት ወጥመድ ናት» አለች በልቡዋ፣ እንባዋን እየረጨች፡፡

ምእራፍ ፫

— ቆርቆሮ ያለው!

— ጣሳ ያለው!

ሰላላ ድምፅ . . .

— ጠርሙስ ያለው!

@OLDBOOKSPDF


ጎርነን ያለ ድምፅ . . .

– ደላው ያለው በገመድ!

እንደ መረዋ የሚደውል ድምፅ . . .

– ፍራሽ አላዳሽ!

– ፍራሽ አላዳሽ!

የሙክት በግ ድምፅ . . .

– ከሰል ፈላጊ!

የሚያንቋቁል ድምፅ

– እላ - ትኩስ አለ!

ሽካራ ድምፅ . . .

– ልዋጭ፥ ልዋጭ፥ አለ ልዋጭ!

የፍየል ወጠጤ ድምፅ . . .

– ፈርሶ ሰውነቴ በቁሜ ተበልቶ፥

ያስለፈልፈኛል ሆዴ ብቻ ቀርቶ፡፡

ቆማጣው ለማኝ፡፡

– ዓይኔን ግንባር ያ'ርገው ብሎ ይምላል ሰው፥

የጨለማን ኑሮ እንደኔ ባይቀምሰው፡፡

አይኔን ግንባር ያርገው ብላችሁ አትማሉ፥

ይቸግር የለም ወይ መሬ ማባበሉ፡፡

አካሌን አጥቼ ብርሃኔን አጥቼ፥

@OLDBOOKSPDF



እለፈልፋለሁ ጨለማ ገብቼ፡፡

እለሞቼ ስላማላጂትዋ ማርያም . . .

እውሩ ለማኝ . . .፡፡

ሲራክ ተገላበጠ፡፡ ሰው አካሉ ፈርሶ፥ ብርሃኑን አጥቶ… ግን ህይወትን የሙጢኝ ብሎ ለመኖር ከመንገድ ዳር ወድቆ ሲወተውት… የህይወት እንቆቅልሽ… ይገርማል፡፡ ለነዚህ ምስኪን የአለም ጎስቋዋሎች ቀርቶ ለሌሎችስ ቢሆን ህይወት ምን የሚያጉዋጉዋ ነገር አላት፤ ዞሮ ዞሮ አፈር መሆን ላይ ቀር… ህይወት በሚሉት ሸክም ለምን እንሰቃያለን? ወይስ ህይወት እስቃ የምታስለቅስ ቀልድ ናት? ቂ… ቂ ... ቂ… እያሉ ሲስቁ ሰማ– አጋፋሪ እንደሻው፡፡

እለሞቼ ስላማላጂትዋ ማርያም . . .

ከእውሩ ለማኝ፥ ወር ከገባ ሃያ አንድ ቀን መሆኑን ተረዳ፡፡ ምን የቀን መቁጠሪያ ያስፈልጋል ብሎ ከተጋደመበት ቀና አለ፡፡

እኔ ለሀገሬ

እሞታለሁ ዛሬ . . .

የሰፈሩ ህፃናት ይዘፍናሉ፡፡ ዘፈኑ ሲሰለቻቸው ደግሞ፡-

ኑሮ ሸብር በቀይ ሽብር ይመታል!

ይመታል!

አረንጉዋዴው ዘመቻ የቀዩ ትርኢት አካል ነው!
ነው!

የሰርቶ አደሩ ፓርቲ በሀቀኛ ኮሚኒስቶች አንድነት በትግላችን ይመሰረታል!

በትግላችን ይመሰረታል!

ከሁሉም በላይ አብዮቱ!

 @OLDBOOKSPDF

አብዮት!

ኢትዮጵያን የዳቦ ቅርጫት እናደርጋታለን!

እናደርጋታለን!

እናሸንፋለን፥

እንጠራጠርም ሳይንሳዊ ሀቅ ነው፥ ወደፊት!

እያሉ መፈክር ያሰማሉ፡፡ ይንጫጫሉ፥ የቆርቆሮ ታምቡር እየደለቁ...

ወድር . . . ውጋ . . . ንቀል!

የነገው ትውልድ – አለ ክልቡ፡፡

– ቱ ቱ ቱ ቱ! የእድረ ጥሩምባ፡፡

– እመት ብርቄ አርፈዋልና ቀብር እንድትወጡ፡፡ የቀረ እድርተኛ ሁለት ብር መቀጫ ተብሎአል - ቱ ቱ ቱ ቱ ቱ...

‹‹ውይ በሞትኩት! ምንነው ትናንት ሰይጣን ቤት አጠገብ አግኝቼአቸው›› አለች ፅጌ፡፡

- ሀሎ! ሀሎ! ሀሎ! የቀበሌ ድምፅ ማጉያ፡፡

- ዛሬ ልክ በሁለት ሰዓት ስብሰባ ስላለ የቀበሌው ነዋሪ የሆናችሁ ሁሉ እንድትገኙ አብዮታዊ ጥሪ ቀርቦላችሁአል፡፡ በቀሪ የተመዘገበ ከቀበሌው የህብረት ሱቅ ማንኛውንም ነገር ሊገዛ እንደማይችል በጥብቅ እናስታውቃለን - ሀሎ! ሀሎ! ሀሎ!

‹‹ኢጭ!›› አለች ፅጌ፡፡

– ይህች የምድር ጎስቋቋሎች ደሴት፥ ይህች ዝገታም፥ ቯጋታ አብዋራ የቃመች ሰፈር፡፡ ይህች ገነት፡፡ ይህች ተረት ሰፈር፡፡ ነጋላት፥ አለ፡፡

@OLDBOOKSPDF



ሳንጻፍታ ሰፈሬዋን በእግረ ህሊናው እየዞረ ጎበኘ፡፡ ጎርዶሜን ወደ ቀኝ ትቶ ቴዎድሮስ አደባባይን ዞሮ፣ በሰይጣን ቤት አልፎ፣ በድሮው ቁራ መንገድ አድርጎ ወደ ታላቁ ቤተ መንግስት በሚያመራበት ጊዜ፣ ተረት ሰፈር፣ ከላይ ሰረገላ ባቢ ሰፈርን ተንተርላ፣ ከታች ሲሴ ገብረ ማርያም ትምህርት ቤትንና የራስ ናደውን ቤት ከግርጌዋ አድርጋ እያዛጋች ስትንቃና ጠላና ጠጅ ቤቶች በራቸውን ሲከፍቱ – አተላው ሲደፋ – ልጆች ትኩስ የተቆላ ቆሎ ይዘው ለመሸጥ ሲሮጡ – ቆሎ የፈሰሰባቸው ልጆች ሲያለቅሱ – በየደጃፉ ጉልቶች ጉልት፣ ጉልት ሲሉ - ከህፃናት ቀጥሎ በሰፈሩ የሚበዛው የቤተኛ አዳሪዎች ቤት በር ተዘግቶ ሲያንቀላፉ ታየው፡፡ የእፈር ድሜ ጠጅ ቤት እንቡላ ሸተተው፡፡ ፀሀይዋ ትሰቅ ይሆን? ወይስ ሰማዩ አኩርፎአል? ሲራክ ኩትጋደመበት እንደ ምንም ብሎ ተነሳ፡፡ ሰውነቱ ዝሎአል፡፡ አጥንቶቹ ሁሉ ደቀዋል፡፡

አጋፋሪ እንደሻው ከአደባባይ መልስ እንደ ወትሮአቸው በሰፈሩ የታመመ አለ? የሞተ አለ? . . .መርዶም አልተሰማ? ብለው ጠይቀው፣ መልእክ ሞት በሰፈሩ ያልዞረ መሆኑን ከተረዱ በሁዋላ፣ ቤት ገብተው፣ መከዳቸውን ተደግፈው፣ ጠጅ በብርሌ እያንደቀደቁ፡-

እነማቱሳላ እነ አብርሃም፣

ጠጡ ሁቲሃላ እድሜ'ሚያረዝም፣

ምስጢሩን ለማንም አልተናገሩም፣

ጠጥተው ዝም ዝም፣ እንዲያው ዝም ዝም ...

ብለው፣ ቲ ቲ ቲ ቲ እያሉ ሲስቁና ረጅም ሸበቶ ሪዛቸውን በረጃጅም ጣቶቻቸው እየጎነታተሉ፡-

– ሂዋን አዳምን አሳሰታ እፀ በለስን እንዲቀምስ ባደረገችው ጊዜ አይኑን ከፈተ፡፡ አየ፡፡ ሀፍረቱ ሲጋውንም ሸፈነ፡፡ እውቀት ተከሰተለት፡፡ አወቀ፡፡ እግዜር ተቆጣ፡፡ ተቆጥቶም ዝም አላለ፡፡ ቶሎ ተከሰተለት፡፡ አወቀ፡፡ እግዜር ተቆጣ፡፡ ተቆጥቶም ዝም አላለ፡፡ ቶሎ ብሎ አባረረው፡፡ አዳም እፀ በለስን እንደ በላ ከህይወት ዛፍም እንዳይበላ ፈርቶት ቶሎ ብሎ አባረረው – ቀናተኛው አምላክ . . .

ቲ ቲ ቲ ቲ . . .

 @OLDBOOKSPDF

ሲሉ ድንገት ታዩት፡፡ ብልጭ አሉበት፡፡ ደራሲና ገፀ ባህርይ ተገጣጥመው ተገናኙ—ልብ ለልብ፡፡ ሲራክ እሳታዊ የሆነ፣ የሚገፋፋ የመፃፍ ፍላጎት ከውስጥ ገንፍሎ መጣበት፡፡ የገነት በር ወከክ ብሎ ተከፈተ፡፡ ያሬድ ይቀድሳል፡፡ ሲታን መላእክት ማህሌት ቆመዋል፡፡ መላእክት ያሸበሽባሉ፡፡ ነጋሪት ይጎሰማል፡፡ ከበሮ ይደለቃል፡፡ እምቢልታ ይነፋል፡፡ ዋሽንት ይንቆረቆራል፡፡ መሲንቆ ይታኛል፤ ይመታል፡፡ በገና ይደረደራል፡፡ እልፍ አእላፍ ጡዋፍ ይነዳል፤ ይንቀለቀላል፤ ይንቦገቦጋል፡፡ አለቃ ገብረሃና ከዳር ቆመው ቅኔ ይዘርፋሉ፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ባንድ እግራቸው ቆመው ይመለከታሉ፡፡ ገብረ ክርስቶስ ክሩት ቁጭ ብሎ ይለምናል፡፡ መልአክ ሞት ሽህ በጥርሱ፣ ሽህ በእጁ ይዞ፣ ነጋሪት እያስጎሰመ በጴጥሮስ አደባባይ ያልፋል፡፡ ሰላም በምድር፤ ይለዋል ጴጥሮስ የወርቅ ቁልፍ ይዞ፡፡ አጋፋሪ የሉም – ከሙቶቹ መሃል፡፡ ኪሩቤል የነበልባል ሰይፍ ይዞ ወደ ህይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ይጠብቃል፡፡

ሲራክ እሳቡ ይመጥቃል፡፡ አሁን አሁን ይለዋል፡፡ ቃላት ሲፈንድቁ፣ አረፍተ ነገሮች ተጠረቃቅመው፣ ጅረት፣ ወንዝ፣ ባህር ሲሆኑ ይታየዋል፡፡ ስሜት ይይዘዋል፡፡ ቁጭ ብሎ ለመፃፍ ይፈልጋል፡፡ ግን የሚፅፍበት ቦታ ያጣል፡፡

ቤቱ ውስጥ ፀጥታ የለውም፡፡ ዮሀንስ፣ ትንሹ ልጁ፣ ሲነሳ እገር ምድር ይጠበዋል፡፡ ይጮሃል፣ ይቦርቃል፡፡ እቃ ያነሳል፣ ያወርዳል፣ ይሰብራል፣ ይስቃል፡፡

ፅጌና ገረድዋ፣ ወሎዬዪትዋ ውባንቺ ፀጥታ አይሰጡትም፡፡ ቤቱን ሲጠርጉ፣ ሲያራግቡ፣ ምናምኑን ሲከትቱ፣ ሲያማስሉ፣ ከጎረቤት ጋር ቡና ሲያከትሙ – ሰላም፣ ሰላም የለም፡፡ ፅጌ ዝም ብላ ስራዋን ብትሰራ ግድ የለውም፡፡ ግን ዝም አትለውም፡፡ ለምን ስራ አትሄድም ብላ ትጨቀጭቀዋለች፡፡ ጭቅጭቅ፣ ውትውት ታደርገዋለች፡፡

ቢሮ ሄዶ እንዳይፅፍ ፋይሉ ተከምሮ ይጠብቀዋል፡፡ ለዚያውም ለብቻው ቢሮ የለውም፡፡ የስልኩ ጥሪ–የቡናው – የሻሂውና የማኪያቶው ግብግብ–ያሉባልታው – የሀሜቱ – የወሬው መአት – ሰላም፣ ሰላም የለም፡፡ ስራ፣ ስራ፡፡ ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ – ሱሪ ባንገት አውልቅ ምርት – ምርት – አረንጓዴ ዘመቻ – ውይይት ክበብ – የውይይት ክበብ ውግዘት – ርግማን – መኮነን – መኮነን – መጠቆም – ማጋለጥ – ኢህአፓውን – ትሮትስካይቱን – ቀኝ መንገደኛውን – ጠባብ ብሄረተኛውን – ለዘብተኛውን – ኢድህን – የለየለት አድሃሪውን – ሰብሰባ፣ ሰብሰባ – መዋጮ፣ መዋጮ፣ መዋጮ – ለእናት አገር ጥሪ –

@OLDBOOKSPDF



ለመልሶ ማቋቋቋዎም – ለዘማች ቤተሰቦች – ላረንጉዋዴው ዘመቻ ለመሰረተ ትምህርት ዘመቻ – ቁዋት አይዋሳም – እትሙ ትንሽ – ችግሩ ብዙ – የሰፊው ህዝብ መራራ ትግል፡፡ ቁጭ ብሎ በፀጥታ የሚፅፍበት ቦታ የለውም – ደራሲው፡፡ እንቁላልዋን የምትጥልበት ምቹ ቦታ አጥታ እየዞረች እንደምታስካካ ቄብ ዶሮ ሆኖ ነበር – ሲራክ . . .

ማታ፥ ወረቀቱን ከምር፣ ብእሩን አሹሎ በሚጠብቅበት ሰአት አልመጣ ብሎ ያስቸገረው አሳብ አሁን ገንፍጹ ካልወጣሁ ብሎ ሲታገለው አስገረመው – ባልጠበቀው ሰአት፣ ባልሰጠው ቀጠሮ፡፡ እንደ ህይወት ነው – ኪነት ህይወት ነው፡፡ ህይወት ኪነት ነው፡፡ እሀ? አለ – ተሰጥዎ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ መሰረቱ የውዴታ ግዴታ ሆኖ ዘለአለም ርካታን በማታውቅ ነፍስ ሰቃይ፥ ባላሰቡትና ባልጠበቁት ሰአት መንጥቆ የሚወጣ የውበት ልእልና ነው . . .

‹‹ተንስተህ ስራ አትሄድም እንዴ?›› አለችው ፅጌ፥ እየተንጫነጨች፡፡

ዮሐንስ ከእንቅልፉ ነቃ፡፡

በስራ ቀልድ አታውቅም፡፡ ከሲራክ ስራ ሌላ እስዋም ሆነች ልጅዋ በዚህ አለም ለህይወታቸው እንዳችም ዋስትና እንደ ሌላቸው ታውቃለች፡፡ እሱም ያውቃል፡፡ ግን፥ ምን ያደርጋል! ልቡ በኪነት ፍቅር ተሰልቦአል፡፡ የኪነት ውቃቢ አርፎበታል፡፡ የኪነት ዛር ሲነሳበት ስራ መሄድ ያስጠላዋል፡፡ ዛሩ ሲነሳበት ብረር ብረር ይለዋል፡፡ ግን ምን ይዞ ጉዞ! የሚለውን ጭንቀት እያስታወሰ፥ የልጁን ህይወት እያሰበ ሳይወድ በግድ ስራ ይሄዳል፡፡

‹‹እሺ ቦስ›› አላትና፥ ሻይ ስታቀርብለት፥ ‹‹ስለ ማታው ወፍራም ይቅርታ፡፡ ስታኮርፊ ደስ አይለኝም፡፡ ያኮረፈ ሰው ፊት ከማየት እንደ ክርስቶስ ስቅለው ጎኔን ቢወጉኝና መራራ ቢያጠጡኝ እመርጣለሁ፡፡ እሺ ፅጊዬ፥ ይቅርታ አደረግሺልኝ?›› ብሎ፥ ከልቡ ተለማመጣት፡፡

‹‹ምንም አይደል፡፡ ይልቅ ተነስና ስራ ሂድ፡፡ ረፍዶአል›› አለችው፥ የብር ጉልላት በሚመስሉት ነጭ ጥርሶችዋ የነገሬ እያየችው፡፡

‹‹እቤት በዚህ አለም ቦስ መብዛቱ! ብሎ ሲነሳት ተነሳና፥ ‹‹ሙሲን›› አግዜር ይይለት አቦ፡፡ እስርቱን ቃላት ይዞ ከተራራ

 @OLDBOOKSPDF

ባይወርድ ኖሮ፤ ይህን አታድርግ፣ ያን አታድርግ የሚል አይበዛም ነበር። ወይ ጣጣ!» እያለ፣ በመንገዳገድ ሱሪውን አጥልቆ ሲያበቃ ቀበቶውን እያጠበቀ፣ «ሰዎች አገዛዝን እስካላጠፉ ድረስ ራሳቸውን በደንብ ሊገዙ አይችሉም» አላት።

«እንኩዋን ከስራ ወጥተህ እየሰራህም አልደላንም እቴ። እርፍደህ ስራ መግባትና ከስራ መቅረት ሁዋላ እያዋጣም። እኔ ነግሬሃለሁ። የዚህ ሰፈር ተንኮለኞችና ምቀኞች መተታቸውን ሳይተበትቡብህ አልቀሩም። የተቋዋጠረ ነገር፣ የሞተ አይጥ፣ ምናምንቴው ዘወትር ከደጃችን አይጠፋም። ልጄም ጤና አላገኘም። እኔም ጤና የለኝም። ያመኛል ሁለመናዬን። ከዚህ ሰፈር ጋር፣ ከዚህ ቤት ጋር አልቀረብክ። ምናለ ቤት ብትፈልግ» አለችው፣ ምርር ብላ የሃጂ ሙስጠፋን እርግማን እያስታወሰች።

ጀመረች እንግዲህ አለ በልቡ። ቤት የመለወጥና የበሽታ ነገር ሲነሳ ያመዋል። ያቅለሸልሸዋል። ውስጡ ይበግናል።

«ቤት የት ይገኛል ብለሽ ነው? ይህንንም በማግኘታችን እድለኞች ነን። ስንቱ መሰለሽ ከነቤተሰቡ በየሆቴል ቤቱ የሚንከራተተው? ቤት የለም። ወይስ ሌላ ሰፈር ሄደን ደባልነት እንግባ ነው የምትዪኝ? ኪራይ ቤቱን ሁሉ ምን እንደ በላው እግዜር ይወቀው» ካላት በሁዋላ፣ ፊቷ በነገሩ እንዳትበሳጭበት በማሰብ፣ «አብርሃም በዚህ አለም አንድ መቶ ሰባ አምስት ዘመን የኖረው በድንኩዋን ነበር» ቢላት፣ ቀበል አደረገችና፣ «ታዲያስ?» አለችው።

«ታዲያማ» ብሎ ሳቀና፣ 'ለምን ቤት አትሰራም?' ቢሉት፣ ምን አለ መሰለሽ? 'ለዚህች አጭር እድሜ ለምን ብዬ!' አለ ይባላል» አላት።

«እኔ ቤት ስራ መቼ አልኩህ። የኪራይ ቤት ፈልግ ነው ያልኩህ። ልጄ በእርግማን ሳይቀሰፍ በደህና ነፍሱን ይዤ መውጣት አለብኝ» አለችው፣ ፍርጥም ብላ።

ቀልዱ በግንባርዋ ድፍት ስትል ታየችውና፣ «ጎጆ መስራት ጉድጓድ መቆፈር፣ የእንስሳት ተፈጥሮ ባህርይ ነው። የኔ ቤት የሰው ልጅ ልብ ነው» አላት እየሳቀ።

«ካልተኛህ ግባበት» አለችው፣ በንቀት እንጋገር።

@OLDBOOKSPDF



ቀልዱ አልጣማትም፡፡ መሳቅ ቀርቶ ፈገግም አላለች፡፡ እሱም የባጡን የቆጡን የሚቀባጥረው ከእንጀቱ አልነበረም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ተረት ሰፈርን ለቆ መሄድ አይፈልግም፡፡ ሰፈሩ ከደሙ ጋር ተዋህዶአል፡፡ የሰፈሩ ሽታ ካፍንጫው አይወጣም፡፡ የሰፈሩ ስእል ከአይኑ አይለይም፡፡ የሰፈሩ ድምፅ በጆሮዎቹ ያስተጋባል፡፡ ተረት ሰፈር የህይወቱ አካል፣ የመፅሀፉ አካል ሆኖአል፡፡ መፅሀፉን የፀነሰበትን ቤት፣ መፅሀፉን ከፍፃሜ ሳያደርስ ለቆ ለመሄድ አይፈልግም፡፡ ትምባ ፈቃድክ፡፡ ምዕላት ቢመጣ፡፡ በቃ፡፡

‹‹ሰንቱ ያገኝ የለም እንዴ?›› ለኛ ብቻ ነው ቤት የሚጠፋው? ልጄን እዚች ጉሮኖ ውስጥ አፍኜና ለእርግማን ዳርጌው እስከ መቼ እዘልቀዋለሁ?›› አለች፣ ዮሀንስን እያለባበሰችው፡፡

‹‹ለምን ውጭ ወጥቶ አይጫወትም?›› አላት፡፡

‹‹ቡዳውስ? ደንቃራውስ? ቆማጣው፣ ቆሻሻው፣ ግማቱ፣ ቅርናቱ፣ ይመሻት ነው የምትለው? እኔን ያስቀድመኝ፡፡ ጠላቴ ድብን ይበል›› ብላ ደረትዋ ደለቀችና፣ ‹‹አንተ ስለ መፅሀፍህ ብቻ ነው የምታስበው፡፡ ራስህን ብቻ ነው የምትወደው፡፡ እኔ ደ'ሞ ህይወቴ ልጄ ነው›› አለችው፣ ንዴትዋ እየገነፈለ፡፡

ቶሎ ከቤት ለመውጣት ቶሎ ቶሎ ልብሱን እየለበሰ፣ ‹‹ምን ይሆናል ብለሽ ነው?›› አላት፡፡

‹‹ደንቃራውን እያየህ፣ እርግማንን እየሰማህ፣ እንዴት ምን ይሆናል ትላለህ?›› አለች፡፡

ሲራክ ልጁን እያየ፣ ‹‹ደ'ሞ ምንድን ነው አንገቱ ላይ ያሰርሺው?›› አላት፡፡

‹‹የአይን መድሀኒት ነው›› አለች፡፡

በንዴት ተነስቶ ከልጁ አንገት ላይ የታሰረውን ክታብ በጥሶ ጣለና፣ ‹‹ይህን ነገር ተዪ ብዬሽ ነበር፡፡ እንዲህ አይነቱን እጉል እምነት በልጅ አእምሮ ተርዖ ማሳደግ ጥሩ አይደለም›› አላት፡፡

በክታቡ መጣል ደንግጣ እየተርበተበተች፣ ‹‹ከዚህ ሰፈር እንድንወጣ ቤት አትፈልግም ፕሮአል ታዲያ›› አለችው፡፡

@OLDBOOKSPDF



ልብሱን ለብሶ ከጨረሰ በሁዋላ የበረዶ ሻሂውን ባንድ ትንፋሽ ጨለጠና፥ «ስሚ የኔ እመቤት» ብሎ፥ ያደረ ፊቱን በርጥብ ፎጣ አባብሶ ሲያበቃ፥ ጠጉሩን በማበጠሪያ መኳኳል እያደረገ፥ «ያ ውጭ ያለው ግማት — ቅርናት — የቆሸሸ ኮረብታ — ያይንምድር ክምር — ያ ሁሉ፥ ያ ውጭ ቁጭ ብሎ የሚለምነው አንካሳና አፍንጫ የሌለው፥ ባንቃውና ሰርኑ የሚታየው ቆማጣ — እሱም — ያ አይነ ስውር ለማኝ — እሱም — ያ እንካሳው ለማኝ — ያ ለምፃም ሳሊበላ — እነሱ ሁሉ — እየሽ የኔ እመቤት — ድንቁርናው — ጉስቁልናው — ቡቱቶው — ምን ልበልሽ — ማይምነቱ — የቆርቆሮው ዝገት — የማድማጸው ሽንቁር — ምርጊቱ ፈርሶ እንደ ጣእረ ሞት ያገጠጠው ግድግዳ — እሳት የማይጨስበት ምድጃ — እህል ያልዞረበት አፍ — ኮረኮንቹ ጭምር — ዝገቱ — ሻጋታው ሁሉ እነዚያ ሁሉ የኛ ተቀፅላዎች ናቸው፡፡ እኛም የነሱ ተቀፅላዎች ነን፡፡ የአለማችን አካሎች ናቸው፡፡ እኛም የነሱ አካል ነን፡፡ እኔም፥ አንቺም ልጆም፥ ሁላችንም . . .

«እና፥ ከዚህ ተለይተን የት እንሂድ?» ወይስ እንደ አንዳንድ በራሳቸው የህልም አለም ውስጥ እንደሚኖሩ ሰዎች፥ አይተሽ የለም — በጉስቁልና ባህር ውስጥ ደሴት ፈጥረው፥ ቆማጣዎችን እንዳያዩ፥ የለማኞችን ልቅሶ እንዳይሰሙ፥ የጭቁኖችን ዋይታ እንዳያዳምጡ ከግንብ ቤታቸው ዙሪያ ትልቅ ግንብ ሰርተው፥ በብረት መዝጊያ በራቸውን ዘግተው፥ አይናቸው ከቶ እንዳያይ ግቢያቸውን በፅጌረዳ አበባ አስጊጠው የሚኖሩ ሰዎች — እንደነሱ እንሁን ነው የምትዪኝ? አንሆንም፡፡ መሰላቸው እንጂ የጉስቁሎች አይን ግንብ ቀርቶ ተራሮችን ቀዶ ያያል፡፡ የኔ አለም የልጄ አለም ተረት ሰፈር ነው፡፡ ሌላ አለም የለንም፡፡ ህይወታችን ነው፡፡ እውነታችን ይኸው ነው፡፡ ኑሮአችን ይኸው ነው፡፡ ልጃችንም ደሴት ከሆነ ቤት ደሴት ወደሆነ ትምህርት ቤት ሳመላለስ አልገኝም፡፡ አለማችን ይኸው ነው፡፡ እና፥ እወድሻለሁ፡፡ ስለ ሃጂ አርማማን ደንታ የለኝም!» አላትና፥ ሚዶውን ወርውሮ ሲወጣ . . .

«አይገባኝም፥ አይገባኝም፥ አንተ የምትለው ሁሉ አይገባኝም፡፡ እብደት ነው ሌላ አይደለም» እያለች ስትጮህ፥ ጩኸትዋ ደጃፍ ድረስ ተከተለው፡፡

ወደ ድሮ ቁራ ከሚያወጣው ኮረኮንች መንገድ ውስጥ ገብቶ እየተደናቀፈ ሲሄድ ባሳቡ፥ «በዚህ አለም መኖር ለምን ያጉዋጉዋል?» አለ፡፡

ቂ ቂ ቂ ቂ . . .

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፬

ሲራክ እናዶአት ከቤት ከወጣ ጀምሮ ዕጌ እንዴም አላረፈችም፡፡ እንደ ቆሰለ አውሬ እየተንጎራደደች፣ ሰስ ከንፈርዋን እየነከሰች፣ አስር አስር ጊዜ ረጃጅም ጣቶችዋን ቋዋ ቋዋ እያደረገች የተወለደችበትን ቀንና ያርባ ቀን እድልዋን ስትረግም ከቆየች በሁዋላ ድንገት አንድ አሳብ መጣባት፡፡

– ጣውንት የሆነኝ እሱ ነው . . . ድራሽ አባቱን ባጠፋውስ? ብላ ፍሊጋ ገባች፡፡ መሳቢያውን ከፈተች፡፡ ባዶው መሳቢያ ባዶ ነበር፡፡ ወደ ቁም ሳጥኑ ሮጠች፡፡ ከልብስ ሌላ ምንም የለም፡፡ ቁም ሳጥኑ ባዶ እስኪሆን ድረስ ልብሱን አንድ ባንድ አወረደች፡፡ ምንም፡፡ እንደ እብድ እያደረጋት፣ የታባቱ አደርጎት ይሆን የሂደው? እያለች፣ ትራሱን፣ ፍራሹን፣ አገላበጠች፡፡ የሲራክ ድርሰት ረቂቅ የትም የለም፡፡ ምን ዋጠው? አልጋው ስር አድርጎት ይሆን? በማለት ጎንበስ አለች፡፡ የደነገጠ ትልቅ አይጥ ሹልክ ሲል አስደነገጣትና «ዋይ» ብላ ቀና ስትል ያልጋው ጠርዝ እናትዋን አለው፡፡

ሻሽዋ እንደ ልማዱ ተፈቶአል፡፡

«የድቁና ሚካኤል ይግድህ አቦ!» ብላ፣ እናትዋን እያሸች ተነሳች፡፡

የት ይሆን ደብቆት የሂደው ብላ አሰበች፡፡ ጥላቻ አደረባት፡፡ ጣውንት . . . ምቀኛ . . . ደንቃራ . . . ምናልባትም ትዳራቸውን ለማፍረስ መሃላቸው የገባ ሰይጣን . . . የት ይሆን የደበቀው? ባሳብዋ ቤቱን ካንድም ሁለት ጊዜ ዞረች፡፡ ሰርቻውና ሽንቁሩ ሁሉ አንድም አልቀራትም . . .

«ዛር የዛራም ልጅ – ረጋ በል እስቲ!» አለች፣ ልጅዋ እየሮጠ አሳብዋን እየከፈለ ስላስቸገራት፡፡

ያኔ፣ ካብዮቱ በፊት እና ከፈነዳም ወዲህ ሰራተኛ ሰፈር በሴተኛ አዳሪነት ስትኖር ቤትዋ እየመጣ፣ ሱቁን በጊዜ እየዘጋ ቶአት

@OLDBOOKSPDF



አብሮአት ፏጺት እየበላ፡ አብሮአት እየጠጣ፡ በፏጺቱ ምርቃና፡ በመጠጡ ሞቅታ መሬት ለቀው ተስተደመና ላይ አብረው ሲሮጡ፤ ከጉም ላይ ተቃቅፈው ሲተኙ፥ የገነት በር ተከፍቶ ሙዚቃው በጆሮዎቻቸው ሲንቆረቆር ወለል ብሎ ታያት፡፡

‹‹ውባንቺ . . . ጆሮሽ አይሰማም እንዴ›› ብላ ተጣራችና፥ ‹‹... እስቲ ለልጁ ቁርስ አምጪለት፡፡ ፊቱንም እጠቢው›› በማለት ገረድዋን ካዘዘች በሁዋላ ልጁን ሰጥታት ጀምራው ወደ ነበረው ያሳብ ጎዳና ተመለሰች፡፡

አይ ጊዜ አለች፡፡ ሲለወጥ ምሬቱ፡፡ አብዮቱ በፈነዳ በጥቂት ወራት ውስጥ . . . በታህሳስ ወር በጥምቀት ሰሞን . . . ያለ ወትሮው ለጥቂት ሳምንታት ጠፍቶ ከከረመ በሁዋላ አንድ ምሽት ላይ . . . ሀሙስ . . . የቀን ቅዱስ . . . ሲራክ መጥቶ የጣለባት ዱብ እዳ ትዝ አላት፡፡ ሁሉንም ነገር አንድ ባንድ አስታወሰች፡፡ ፊቱ ጠቁሮአል፡፡ ከስቶአል፡፡ ከሰውነት ወጥቶአል፡፡ ፊቱ ላይ አሳብ ያንገዋብባል፡፡ ገና ሲታየው ደስታ ፈንቅሎአት፥ ደንበኞች ያዘዙትን መጠጥ ሳያጋቡ ቸኩላ ሉቁን ዘግታ . . .

— ምንነው ጠፋህ ልጄ? ስትለው . . .

— አልጠፋሁም፡፡ እንደኛውን ከተት ብዬ መጣሁ፥ ሲላት...

— ደ'ሞ ምን ሆነሃል? ብላ ስትጠይቀው . . .

— ምን ሆኛለሁ? ብሎ መልሶ ሲጠይቃት . . .

— ያዘንክ ትመስላለህ ስትለው . . .

— ምኔ ላይ? ብሎ ሲያስጨንቃት፥ አይኖቹን፥ ጉንጮቹን፥ ከንፈሮቹን በናፍቆት እንሳብጣ ስማ ስታበቃ፤ ፏጺት አቅርባ፦ እስቲ ሀራራችንን እንወጣው እቦ! ስትለው . . .

ፏጺቱን ትቶ ከስተር በማለት . . .

— አንድ ነገር ብለምንሽ እሺ ትዪኛለሽ? ሲላት . . .

— አንተ ጠይቀኸኝ ምን እምቢ ብዬህ አውቃለሁ? ብላ ስትመልስለት፤ ድንገት፦ እንጋባ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ሚስቴ እንድትሆኝ

@OLDBOOKSPDF



እፈልጋለሁ፡፡ በዚች ርጥብ፣ ዘለላ ሜት እምልልሻለሁ፡፡ ከልቤ ነው፣ ብሎ ሳም ሲያደርጋት . . .

ቀልዱን ይሆን? ወይስ የምሩን? በማለት የከረከርዋት ያህል ከት ብላ ስቃ . . .

– የሚኒስትር ልጅ ባል ሴተኛ አዳሪ ምን ቆርጦት ያገባል የኔ ሺጋ? አብሬህ መቅበጡ መቼ አነሰኝና? ጋብቻው ቀርቶ እዚህ መምጣትህ ይገርመኛል – ያቺን የማርያም ስእል የምትመስለውን ሚስትህን እዚያ ገነት ከሚመስለው ቤት ውስጥ ብቻዋን ትተህ፡፡ ያዲስ አበባ ወንዶች ትገርሙኛላችሁ፡፡ አንዳንዴ የኔና ያንተን ነገር ሳስበው ምን አይቶብኝ ይሆን? እላለሁ፡፡ ዞር እልና ደግሞ ሚስቱስ ምን ቢጎላት ነው? ብዬ እጨነቃለሁ፡ ስትለው . . .

እንደ ገና ከሱቱር ብሎ፥ ሚስቱም ልጅም የሉም፣ ብሎ፣ ነገሩን ፍርጥ አድርጎ ሲነግራት . . .

መቼም ጊዜው ያብዮት ጊዜ ነውና፣ ሚስቱም እንደ አባትዋ በወታደሮች ክቤት ከነልጅዋ የታፈሱ መስሎአት ከመደንገጥም ሌላ በማዘን፣ 'ህፃኑ ደግሞ ምናደረጋቸው?' ብላ፣ ሲራክ ልጁን ምን ያህል እንደሚወደውና እንደሚንገበገብለት ስለምታውቅ፣ አዝና እደናገጥ እንባ ማቅረር ሲጀምሩ፣ ሳቅ ብሎ፥ የታሰሩ መስሎሽ ነው? አይደለም፡፡ ያዛው ኮበለለች – ወደ እንግሊዝ አገር፣ ሲላት . . .

ተገርማ፣ ጆሮዋን ማመን አቅቶአት፣ «ሳትነግርህ? ሳታማክርህ? እንዲያው ዝም ብላ? ሳታስጠንቅቅህ እንኩዋን?» ብላ ስትጠይቀው . . .

– ሳትነግረኝ፣ ሳታማክረኝ፣ እንዲያው ዝም ብላ፣ ሳታስጠንቅቀኝ – አዎን፡፡ ታውቀኛለቻ፡፡ ስሜቴ ይገባታል፡፡ እኔ ከዚህ ለመውጣት አግሬን እንደማላነሳ ታውቃለች፡፡ የጢሰኛ ልጅ ከኢትዮጵያ ወጥቶ የት ይሄዳል? ከባላገር ብወጣም ባላገርነት ከልቤ ውስጥ አልወጣም፡፡ ታዲያ ሳትነግረኝ የሄደችው ጨካኝ ሆና አይደለም፡፡ ምርጫ ሳይኖራት ቀርቶ ነው፣ ሲላት . . .

አሁንም ነገሩ አልገባ ብሎአት፥ ሚስት ባልዋን ባዶ ቤት ውስጥ ጥላ እንዴት ትኮበልላለች? ምናኔ መግባት ያባት ነው፡፡ ችግር ሲመጣ ግን ከባል ጋር ሞት ይመረጣል እንጂ እንዴት ባልን ጥሎ

@OLDBOOKSPDF



ይከበለላል? እይ ዘመን? እድሜ ከሰጠን እኮ ይህ አብሮት የማያላየን ጉድ የለም፣ እያለች፣ ክርክር ልትጀምረው ስትል . . .

መደብ ከልጉዋም ይሰባል አሉ፡፡ እሰዋም ወደ መረጠችው አለም . . . በሄደችበት አድባርዋ ትቀበላት፡፡ እኔም ወደ መደቤ፡፡ ያለፈው አለፈ፡፡ እንግዲህ ካለፈው ህይወቴ የቀረኝ ትዝታ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ህይወት ወደ ፊት ነው እንጂ ወደ ሁዋላ አይኖርም፡፡ እና፣ ካንቺ ጋር ለመኖር መርጬ መጥቻለሁ፡፡ አፈን በምን? ብሎ ሲያቅፋት፣ አቅፎ ሲሰማት . . .

ካለችበት ግሃነማዊ ኑሮ ወጥታ ከሱ ጋር በክብር ለመኖር ልብዋ እየፈለገ፣ ግን ልብዋ መልሶ እየተጠራጠረ፣ በቀሰተ ዳመና ላይ አብረው በሚንሸራሸሩበት ሰአት ልብዋ ከሩቅ ይመኘው የነበረው ነገር ድንገት እውን ሆኖ ሲገኝ፣ እውን ነው? ወይ ህልም? እያለች፣ ነገሩ እውን ሆኖ ሲታያት ደግሞ፣ ከልቡ ነው? ወይስ ውሸቱን በማለት ነፍስዋ እየተሙዋገተች፡- አፍከን በጻቦ፣ ብላው በወፍራም ከንፈርዋ ስትገርሰው፣ ልብዋ የገባው ምኞት አንድ ነገር ብቻ ነበር – ወንድ ልጅ ልትሰጠው . . . እና . . .

– የልጅህስ ነገር እንዴት ከልብህ ይወጣል? ስትለው . . .

– ያንቺ ፍቅር ልቤ ሲገባ፣ ብሎ ጉንጮችዋን በረጃጅም ጣቶቹ እየዳሰሰ ሲሰማት፣ በደስታ አርግዛ፣ ወንድ ልጅ ሰጥታው፣ እሱን ለማስተረት፣ የራስዋ፣ የግልዋ ሊታደርገው እየተመኘች ተያይዘው ከስሜት ሞገድ ውስጥ ሲወድቁ . . .

– እቤት ያን ቀን አብረን ያሳለፍነው ሊሊት፡፡ ብዙ ብዙ የደስታ ሊሊት፡፡ ያሳለፍነው ጊዜ፡፡ እቤት ደስ ማለቱ፡፡ እና፣ አሁን ደህ ደንቃራ መዐሀቱ የት ይሆን የተደበቀው? ብላ ሲታሰብ፣ ያልደረሰችበት ቦታ ትዝ ብሎአት፣ ልብዋ ከበሮ እየመታ፣ ወንበር አቀረበችና ከቁም ሳጥኑ አናት ላይ ብቅ . . . ከእቡዋራና ከጭቃርሻ ሌላ ምንም አልነበረም፡፡ ወዲያውኑ ገረዲትዋ፣ ‹‹እትዬ!›› እያለች ስትሮህ ገባች፡፡

‹‹ምን ሆንሻል? የድቁናው ሚካኤል ይጠብህብሽ እቦ›› በማለት መልሳ ጮኸችባት፡፡

‹‹ዬዬትማ፡፡ ዬዬትማ፣ እትዬ፡፡፡››

@OLDBOOKSPDF



«ምንድን ነው እሱ?»

«ዪዩትማ፡፡ የህንስ የተጫወተበትን እህል፡፡ አሁን ይህን ስራ እግዜር ይወደዋል እትዩ? ጡር ነው እትዩ!» እያለች ተፈትፍቶ የተጣለ እንጀራ አሳየቻት፡፡

ውባንቺ ስትናገር ትንሽ እንቅርትዋ ከፍ ዝቅ እያለ አንገትዋ ላይ ይጫወታል፣ ቀይ ስለሆነች እንቅርታም አንገትዋ ላይ ያለው ንቅሳት ቦግ ብሎ ይታያል፡፡

«የወሎ ረሀብሽ ትዝ አለሽ እንግዲህ» ብላት፣ እጆችዋን እየጠረገች ከወንበሩ ላይ ወርዳ፣ «ልጄን ለእግዜር አትስጪብኝ፡፡ ደግሞ ችጋር አትጥሪብኝ፡፡ እንዲያውም እንቺ እዚህ ቤት ከገባሽ ወዲህ ሌማቱ እየደነገጠ ሄዶአል፡፡ የምን መስገብገብ ነው እሱ፡፡ ልጄን ከማግረር ሌማቱን ከፍ ካለ ቦታ ላይ አታስቀምጪውም ኖሮአል!» አለቻት፣ የሲራክን ረቂቅ ፈልጋ በማጣትዋ ውስጥ ውስጡን እየበገነች፡፡

«ጡር ነው ኧ እትዩ፡፡ እርስዎ ረሀብ ምን እንደ ሆነ ስላላዩ ነው እንዲህ የሚናገሩት፡፡ ሀገር፣ አፈር እንደ ዶሮ ሲጭር፣ እንደ ኩብት ሳር ሲግጥ፣ እንደ ፍየል ቅጠል ሲበጥስ ስላላዩ ነው፡፡ አሞራ የሞት ጥላውን እያጠላ ከሰማይ ላይ ሲያንዣብብ፣ ህፃናት የሬሳ ጡት ሲጠቡ፣ ሰው ሰውን ለመብላት ሲከጅል . . . እትዩ አላዩትም፡፡ እህል ንጉስ ነው» ብላ፣ የተፈተፈተውን እጀራ ባምልኮት ሳም ሳም አደረገችና፣ «ጡር ነው እትዩ፡፡ ከሀገሬ ያወጣኝ፣ ባሌንና ልጄን የነጠቀኝ፣ እናትና አባቴን ባንድ ቀን ያሳጣኝ ምን መሰለዎት እትዩ! እህል ነው፡፡ ያንን መከራ ያንን ጉድ ያላየ የእህልን ጡር እንዴት አ'ርጎ ያውቀዋል?» አለች፡፡

እነዚያ የሚያማምሩ ትላልቅ አይኖችዋ እንባ አቀረሩ፡፡ ከሞቀ ጎጆዋ ውስጥ ጢስ ቡልቅ ሲል — ሲንተከተክ ጎመን — እስዋ ልጅዋን ባንቀልባ አዝላ ቀና ጎንበስ ስትል — ጥገቶችዋ እምቡዋ እያሉ ሜዳውን አቋርጠው ሲመጡ — ጥጃው እምቡዋ ሲል — ዶሮችዋ ሲሰፍሩ — የባልዋ ማሳ — የጉዋሮዋ አትክልት — ጎመን — ቃሪያው — ሽንኩርቱ — የጠጅ ሳሩ — ጤና አዳሙ — ውሀ የምትቀዳበት ምንጭ — እንጨት የምትሰብርበት ጫካ — ሜዳው ሽንተረሩ — ፊትዋ መጥቶ መጥቶ ድቅን አለ፡፡ አንድ ዘለላ እንባ ኮለል ብሎ በጉንጮችዋ አቋርጦ ወረደ፡፡

«ጡር ነው እትዩ፡፡ የህል ጡር አለው» አለችና፣ እንደ ገና እንጀራውን ባምልኮ ሳም ሳም አደረገችው፡፡

 @OLDBOOKSPDF

«ጀመርሽ እንግዲህ፡፡ ጡርሽን ያውጣው እቴ! ይልቅ ልጄን ስጪኝና ቡና አፍይልኝ፡፡ ለራሴ ጤና የለኝም፡፡ ራሴን ያመኛል፡፡ ያዞረኛል፡፡ ኸኸው ኸኸው ይልብኛል» አለች፣ ብሽቅ ብላ፡፡

«ቀብር አይሄዱም?»

«ሁለት ብር እከፍላለሁ፡፡ ሌላ ምን ይመጣብኛል!»

«ቀባሪ አያሳጣኝ ማለት ነው እትዬ፡፡ ቀበሌም ሰብሰባ አለ ብለዋል፡፡»

«አልሄድም፡፡ አሞኛል ስልሽ አይገባሽም፡፡ ከንዴን ስወረውር የምውልበት አቅም የለኝም . . .»

«እህል የከለከሉን እንደሆነ ብዬ ነው . . .»

«እህል ይንሳሽ አቦ! ሂጂ ቡና አፍይልኝ ነው የምልሽ» አለቻት፣ ተቆጥታ፡፡

«እሱስ ፈልቶአል፡፡ ብቻሁን እንዴት ይጠጣሉ ብዬ ነው» አለች፡፡

«ምን ይደረግ? ሃጂ በእርግማን በሬን ዘግተው ይዘጋሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ለምን ከኛ በላይ ትኖራለች? ከኛ ይበልጥ ታጌጣለች? ነው የሚሉት — ሁሉም . . .»

«እረ ሌላ ሌላም ይናገራሉ፡፡»

«እንደ ምን ያለ በይ?»

«ከየሀ ከጎረቤታችን ያሉ ትግሬ በቀደም ለት ጌቶች ሽንት ቤት ሄደው ሲመለሱ አይተው፣ አሁን ይህን የመሰለ የተማረ ወጣት፣ ይህችን አገር አሸንፋ የኖረች ሸርሙጣ ምንዋን አይቶ ነው ያገባው? በመተት ተብትባው ነው እንጂ አይን እያየ አያገባትም ነበር፡፡ ያስታውቃል፡፡ ፈዞአል፡፡ ባህታዊ ይመስል መፅሀፍ ከእጁ አይጠፋም ሲሉ ጆሮዬ ገባ . . .»

«ቆማ የቀረች፣ ያለ ሊቸገሳ የምትነግድ ልጃቸውን ይዳሩለት!»

@OLDBOOKSPDF



‹‹ሌሎቹ ደግሞ ለምን ከዚህ ቤት ለቀው አይወጡም ነው የሚሉት፡፡››

‹‹ለምን?››

‹‹ሃጂ ባለውቃቢ ናቸው፡፡ ውቃቢያቸው ቤቱ ላይ አርፎአል፡፡ በቶሎ ለቀው ካልወጡ አንድ ነገር ይሆናሉ እያሉ ነው የሚያወሩት፡፡››

‹‹እምን እህል ውሀዬን ከዚህ ሰፈር የሚጨርስልኝ ነገር ነው ያጣሁት . . . ምላሳቸው ቀርቶ ደንቃራው፣ እንደርቢ አላስቀምጥ ብሎኛል፡፡ ሲራክ ነው ለዚህ ሁሉ የዳረገኝ፡፡ ተው ይህን ቤት እንልቀቅ፡ ከዚህ ሰፈር እንውጣ ስለው፡፡ ጉድ ነው ብቻ፡፡ ለጉድ ይሆናል እዚህ ጎልቶ ያስቀረን፡፡ ለመሆኑ የኝህ የትግሬዋ ጋለሞታ አለች?››

‹‹ጌቶች ሲወጡ ሲገቡ ብቅ እያለች ታስካካለች . . .››

‹‹አንድ ቀን እናትዋን በመጥረቢያ ነው የምለው አለችና›› ቡናውን ከማቅረብሽ በፊት እትዬ አሊታዬን ቡና ጠጡ ብለሽ ንገሪያቸው›› ብላ አዘዘቻት . . .

‹‹እሳቸው እንደሆኑ ባልነግራቸውም ይመጣሉ፡፡››

‹‹በምን አወቅሽ?››

‹‹ቡና ሲወቀጥ ሳይሰሙ አልቀሩም ብዬ ነዋ›› አለችና፣ ወደ ጉዋዳ ጥልቅ አለች፡፡

የቡናው ጀበና እየፎከረ ሲቀርብ፣ ፅጌ ‹‹አቦል ጀባ፣ በረካ ጀባ፣ ሸረኛውን ምቀኛውን ያገለኝ›› ብላ፣ ባህር እጣን፣ ፍም እሳት ከተጫረበት ገል ላይ ብትን አድርጋ ጢሱ ቡልቅ እያለ ከፍሉን ማጠን ሲጀምር፣ እትዬ አሊታዬ ወርቅ ጥርሳቸውን ብልጭ፣ ብልጭ እያደረጉ፣ ሽበት የወረሰውን ቅርችም ያለ ጎፈሬአቸውን አቁመው፣ ረጃጅም መቀነታቸውን ከትከሻቸውን ወገባቸው ላይ ሸብ አድርገው፣ ረጃጅም ቀሚሳቸውን በረጃጅም ቁመናቸው እየጎተቱ ሲኳኳቸውን በቀይ መሀረም ጠቅልለው ይዘው እየተጎተቱ ብቅ . . .

ሰላምታ ከተለዋወጡ በሁዋላ፣ ‹‹ትንሽ ተሽሎሻል?›› አልዋት፡፡

@OLDBOOKSPDF



«ያመኛል ባክዎን፡፡ ሰሞኑን እዚህ ልቤ ስር እንደ እሳት ያቃጥለኛል፡፡ በሽታዬን ያወቀልኝ የለም፡፡ ሀኪም ቤቱም ሰለቸኝ፡፡ የዘመኑ ሀኪሞችማ በሽታውን ትተው የሚጠይቁት ሌላ ሌላ ነገር ነው፡፡ ከባልሽ ጋር እንዴት ናችሁ . . . ቤትሽ ውስጥ ደስታ ይሰማሻል ወይ . . . ጭንቀት አለብሽ ወይ? ወይ ተአምር! ዘር አባታቸው ይጥፋና እርም ብዬ ትቻቸዋለሁ» አለች ፅጌ፣ የቡና ቁርስ በትንሹ ቆርሳ ላድባርዋ እየወረወረች፡፡

ውባንቺ ያቀረበችላትን ቡና ሳትቀምስ ወደ ውጭ ደፋች ላድባርዋ፡፡ እትዬ አልታዬ በሚጥሚጣ የቀረበላቸውን የቡና ቁርስ እየጎረሱ፣ «ሀኪም ቤት ምን ዋጋ አለው ብለሽ ነው? እነሱ የሚያውቁት ገንዘብ መብላት ብቻ ነው፡፡ ጠበል ነው የሚሻለው ልጄ . . .» ብልዋት ሳይጨርሱ፣ የሁንስ ጨወታውን አቋርጦ ወደ ረከቦቱና ወደ ጀበናው እየሮጠ ስላስቸገረ፣ እትዬ አልታዬ ተናደው፣ «ምን ነው እቴ ይህን ልጅ ብትቆነጥጪው? የምን መቅበጥ ነው እሱ!» አልዋት፡፡

ፅጌ ደስ አላላትም፡፡

«ለስንት ቃልቻ ሰግጄ፣ ለስንቱ ታቦት ተስዬ ያገኘሁትን ልጄን ለቀቅ» አለችና ይዛ አቀፈችው፡፡

«ጀበና ላይ የሚያንገዋብብ ልጅ ደስ አይለኝም» አልዋት፣ ተቆጥተው፡፡

እትዬ አልታዬ ለብዙ ዘመን ሲታወቁ ቃልቻ ቡና ካዳሚ ነበሩ፡፡ አሁን የሚኖሩት በየቤቱ እየዞሩ የቡና ሲኒ እያነሱ በመጠንቆልና በመቀላወጥ ነው፡፡ ሌላ ሥራ የላቸውም፡፡ ቡና የሚወቀጥበትን ቤት ጆሮአቸው ሲያዳምጥ ነው የሚውለው፡፡ ቡናው ተወቅጦ፣ ተጥዶ የሚፈላበት ደቂቃ አይስቱም፡፡ ሲኒያቸውን ይዘው ከተፍ ልክ በሰአትዋ . . .

«ብጠፋ ቡና ቢደፋውስ እትዬ» አለች ውባንቺ፡፡

ውባንቺ ያለቸው ልባቸው ስለገባ፣ «ጉድ ነው ኮ፡፡ ታሪክ ነው፡፡ ቡና ከቡና ሆነር ሲጠፋ፡፡ አድባርዋን ሲያጣሉን፣ ከራማውን ሲያሸሹብን፡፡ የቡናው ሺሂ ዘንግ ደጉን ቀን ያምጣልን - አዎን፡፡ ጀበናን ማስደንገጥ ደግ አይደለም፡፡ የጥቁር ጀበና አምላክ ምሱን ካላገኘ፣ ጋኔሉም አትላውን ካላሸተተ አድባርዋ ትጣላናለች፡፡ ይሄው

@OLDBOOKSPDF



በረሃቡም፥ በኀርፉም፥ በጦርቱም በእርስ በእርስ ፍጅቱም እያሳየን ነው›› አሉና፣ ቡናቸውን ደገሙ።

ውባንቺ ሁለተኛ ቡና ለመጣድ ስትሄድ ፅጌ የሀንስን እያባበለች፡-

‹‹እባክዎ በጣም ተቸግሬአለሁ›› አለች።

‹‹ምን ሆንሽ ልጄ? ባልሽን አውሎ ያግባልሽ እንጂ›› አልዋት።

‹‹ሃጂ ይሀን ቤት ሊያስለቅቁን ይፈልጋሉ።››

‹‹እምን ሰምቻለሁ።››

‹‹ባሌ ደግሞ ከዚህ ቤት ጋር የቀረበ ይመስል ሊለቅ አይፈልግም። ግራ ገባኝ። እርግማኑንም ፈራሁ። ምን እንደማደርግ ነው ያጣሁት›› አለች፣ ጠጉርዋ ላይ በማይረጋው ሻሽዋ ባንድ ፊት እየተበሳጨች።

‹‹ሃጂ ካ እንዴት እንደሆኑላቸው አላውቅም እንጂ ይህን ቤት ለማስለቀቅ ሁጉ አይፈቅድላቸውም። የመረጡት አሁን የሚኖሩበትን ትልቁን ቤት ነው›› አልዋት፣ ወርቅ ጥርሳቸውን ብልጭ እያደረጉ።

‹‹እውነትዎን ነው?››

‹‹እንዴ፣ አልሞትኩ ልጄ።››

‹‹ታዲያ እንዴት ብለው ነው ይገባኛል የሚሉት?››

‹‹ዋ ልጄ። ገንዘብ ብዙ አፍ አለው።››

‹‹እርግማናቸውን ትተውኝ በወጣሁ። ልጄ ላይ እንትፍ ብለው ደጅ ባደርኩ።››

‹‹እምን፣ እርግማን መጥፎ ነው›› ብለው ሲተክዙ ቆዩና፡-

‹‹በጤና ለቃችሁ ብትሄዱ ይሻላል›› አልዋት።

‹‹እኔም ብዬ ነበር፡ እሱ እምቢ አለ እንጂ።››

 @OLDBOOKSPDF

«ለምን ልጄ?»

«አቶዬ አልታዬ፣ እንዲያው በሞቴ፣ ዕህፈት እርግፍ አርጎ የሚያስጥል አዋቂ ይኖራል? እሱ ዕህፈቱን ካልተወ ከዚህ ቤት አይወጣም፡፡ ቤታችንም ሰላም አያገኝም፡፡ ዕህፈት ዕህፈቱን ሲል እኔንም እርግፍ አ'ርጎ እንዳለቀ ቁና ጥሎኛል» አለች፡፡

«ምን አይነቱ በሽታ ነው ደ'ሞ እሱ ልጄ?» አልዋት፡፡

«ባሌን የተጠናወተው በሽታ ነው፡፡ እንደ ደብተራ ሲፅፍ ነው የሚያድረው፡፡ ከዚህ ቀደም ዕፎ ያሳተመው መፅሀፍ እዳ ውስጥ ከቶን በችግር ላይ ነው ያለነው፡፡ ታዲያ ይህንን ምን ይሉታል? መተት ነው እንጂ» ብላ፣ ነገርዋን በመቀጠል፣ «እሱን ዝም ብሎ ሲፅፍ እኔንም ዞር ብሎ አያየኝ፡፡ ሆድና ጀርባ ሆነናል፡፡ እኔ እሱን እንደ እግዜር እምኜው ቤቴን፣ ቤቴን እያልኩ ቀና ጎንበስ ስል እሱ ከመፅሀፉ ሌላ አያስብም፡፡ አለሁልሽ አይለኝም፡፡ ባል አለሁልሽካላለ፣ ከዘመዶቼ ጋር ደብለቅ፣ ደብለቅ ብሎ ካላኮራኝ፣ ባልና ሚስት ሆኖ የመኖር ጣእሙ ምኑ ላይ ነው? አብሮ ለመተኛትማ ከማንም ጋር ተጋድሞ መነሳት ይቻል የለም እንዴ? ታዲያ የዚህ ሁሉ ጠንቅ የሚፅፈው መፅሀፍ ነው፡፡ ሌላ አይደለም» አለችና፣ ልጁን ለማስታገስ ያንገትዋን ወርቅ አውልቃ ሰጠችው፡፡

አቶዬ አልታዬ በነገሩ ተገርመው፣ «ለመሆኑ ስለ ምንድን ነው የሚፅፈው?» ብለው ጠየቅዋት፣ በሚጥሚጣ የቀረበላቸውን እንጀራ ጎረስ ጎረስ እያደረጉ፡፡

«ምናባቴ አውቃለሁ፡፡ ብቻ፣ ስለ አንድ ሞትን የሚሸሽ ሰው ነው የሚፅፈው . . .»

«እንደ ፊታውራሪ ማናለባቸው? እዩ ልጄ፡፡ እኒያ ዐሀይ የመሰሉ ጌታም ሞት አልቀረላቸውም፡፡ አጀባቸውን አስከትለው አለሚቱ በምትባለው በቅሎአቸው ላይ ተቀምጠው . . . አቤት ትከሻ . . . አቤት መልክ . . . አቤት ግርማ ሞገስ . . . ከአደባባይ መልስ እንደ ዐሀይ ብቅ ሲሉ 'የሞተ አለ? የታመመ አለ? መርዶ አልተሰማ?' እያሉ ሲጠይቁ ትዝ ይሉኛል፡፡ ጌቶቹም ጋ እንዳንዴ ብቅ እያሉ፣ 'እድሜ የሚያረዝም መድሀኒት ታውቃለህ?' እያሉ ይጠይቁ ነበር፡፡ ዞሮ ዞሮ ካፈር ማን ይቀራል ልጄ? ጥሪኝ አፈር ነው ራታችን»

@OLDBOOKSPDF



ብለው፣ ሚጥሚጣው ስለ ፊጃቸው ትኩስ ቡና ቶሎ ቶሎ ፉት ፉት አሉበት፡፡

ዕጌ ተገርማ፣ «የሚፅፈው መፅሀፍ ልክ አሁን እንደ ነገሩኝ ነው ታሪኩ» አለች፡፡

«አዎን፣ ስለ ፊታውራሪ ማናለባቸው አጫውቱኝ ይለኛል ሁልጊዜ፡፡ ስለሱ ነው የሚፅፈው? ምን ያደርግለታል ልጄ? ስራ ፈት መሆን ነው፡፡ ውነትም መድሀኒት ያስፈልገዋል» ብለው፣ ትንሽ አሰቡና ትዝ ሲላቸው . . .

«ቀጨኔ አንድ አዋቂ አሉ፡፡ ጌቶቹ ቤት ካዳሚ ሆኜ ያውቁኛል፡፡ እሳቸው ዘንድ ሄደን እንለማመናለን» አሉና፣ ሶስተኛውን ቡና ፉት ብለው መለሱ፡፡

ዕጌም ሶስተኛውን ሳመል ከቀመሰች በሁዋላ የቀረውን ደፍታ ሲኒዋን ሰጠቻቸው፡፡ እትዬ አሊታዬ በልባቸው እቦል ጀባ፣ በረካ ጀባ፣ ከራማው ጀባ፣ የቡናው ሼሂ ዘንግ ምስጢሩን ግለጠው እያሉ ሲኒው ውስጥ የቀረውን የቡና አተላ ሀረግ ሲያነቡ ከቆዩ በሁዋላ፣ «ትንሽ ሀዘን ይደርስብሻል፡፡ ግን ለክፉ አይሰጥም፡፡ ምሱ፣ ጥቁር ቄብ ዶሮ ናት፡፡ አዎን . . . ያንዲት ሴት ልብ ባልሽ ላይ እርፎአል» ሲሉ፣ አቋዋርጣቸው . . .

«ቅርብ ናት ወይስ ሩቅ?» ብላ ጠየቀች፡፡

«ሩቅ ናት» አልዋት፣ ወርቅ ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው፡፡

«ያቺ ሚስቱ ትሆናለች» አለች ብሽቅ ብላ፡፡

«አዎን፣ እሱም አሳብ አለበት . . .»

«ስለዚሁ ደንቃራ መፅሐፍ ይሆናላ» ብላ፣ የት ይሆን ደብቆት የሄደው? እያለች ማሰብ ጀመረች . . .

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፭

ሲንሜንግ ከቤቱ የወጣው ደራሲ እየተንሜነጨ ነበር፤ ቢሮው የገባው፡፡ ስሜቱ ካየሩ ንጭንጭ፥ ጭፍግግ ያለ ጠባይ የተለየ አልነበረም፡፡ ሰማዩ ምድራቱን ለመሳሚን ዝቅ ያለ ይመስላል፡፡ ጥቁሩ ደመና ወተት እንዲጋት የጥገት ጡት በማንኛውም ደቂቃ ዝርግፍ የሚል መስሎ ያስፈራል፡፡ እና፥ ለፈጠራ ፅሁፍ ተነሳስቶ የነበረው ስሜቱ እንደ አየሩ ቀዝቃዛና ጠቋር ነበር፡፡

ጊዜው ከጠዋቱ ዝና ሶስት ሰአት ተኩል ገደማ በመሆኑ፥ ቢሮ ከራሲው መንቀሳቀስ፥ የበለዘ ጥርሱን ማግጠጥ፥ የቦዘ አይኑን ማጉረጥረጥ፣ ተዋጊ ቀንዱን ማሳየት፣ ጣቱን በየቦታው ማስገባት፣ በሰው ቁስል እንጨት መሰደድ አልጀመረም፡፡ ዝም ብሎ ያዛጋል - እንደ ተራበ ጉማሬ፥ ከትናንቱ ምሽት የዞረ ድምሩን ከአይኑ ጥላው ገፎ በመጠኑም ቢሆን መንቀሳቀስ ለመጀመር ገና ብዙ ሲኒ ቡና፣ ማኪያቶና ሻሂ ያስፈልገዋል፡፡ አለበለዚያ የቦዘው አይኑ ወረቀትና ባለጉዳይ ለማየት ከቶ እንዴት አድርጎ . . .

ደራሲው ራሱንም ሆነ ነገር አለሙን ትቶ አኩርፎ ዝም ብሎ ቁጭ ብሎ ነበር፡፡ ከትንሽ ጠረጴዛው ላይ ከፊቱ የተከመረው ያረጀ ፋይል፥ አብዋራውን እያቦነነበት ያፈጥበታል፡፡ እሱም መልሶ ያፈጣል፡፡ የፋይሎቹ አቡዋራ አፍኖ ነፍሱን የሚያወጣ መስሎ ታየውና ተነስቶ ከፋይሎቹ ፊት ለመሸሽ ፈለገ፡፡ ነፍሱ ታፍና ጣእር ሲይዛት ተሰማው፡፡ ግን ወዴት? የት ሸሽቶ ለማምለጥ ይቻላል? ይህን እንደ ነቀርሳ ውስጥ ውስጡን በልቶ የሚጨርስ የሻገተ ህይወት . . .

‹‹እንደምናደርከ ጂል?››

‹‹አ . . . አስከንድር – አላየሁህም ስትመጣ›› አለ፥ ከእንቅልፉ ድንገት እንደ ባነነ ሰው ደንግጦ፡፡

‹‹ባሳብ ተውጠህ ነበር፡፡ ከሚስትህ ጋር ተጣልተህ ነው? ወይስ አዲስ ፍቅር ይዞሃል?›› አለው፥ ሰው ሰራሽ ጥርሱን እያሳየው፡፡ አንድ ጥራዝ ብጤ በእጁ ይዞአል፡፡

‹‹ከሚስቴ ጋር የማይጣላ ማን አለ ብለህ ነው?›› አለ ቢራቡ፥ እየተለደ፡፡

@OLDBOOKSPDF



«ታሳዝኑኛላችሁ ሚስት ያላችሁ ሰዎች፡፡ ሰው በገዛ እጁ ነፃነቱን ሽጦ እንዴት መቀመቅ መግባትን ይመርጣል? በኔ አስተያየት ትዳር የሚሉት ጣጣ የጋራ ስቃይ የምናካሂድበት ተቋዋም ነው፡፡ ወተት በየሜዳው ሞልቶ ላም የምንገዛበት ምክንያት አይታየኝም» አለው ኮስተር ብሎ፡፡

«ለዚህ ነዋ እንደ ባህታዊ ሆቴል ውስጥ ብቻህን ተደፍተህ የምትኖረው!» አለው ሲራክ፣ ፈገግ ብሎ፡፡

«በተግባር!»

እስክንድር ፈረደ ምራቁን መቆዋጠር አይችልም፡፡ ያናገረው ሰው ሁሉ ለካፊያው ጠበል ሳይደርሰው አይለየውም፡፡ ሉጫ ፀጉሩ ብን ብሎ ሳስቶአል፡፡ ፊርስ መሳጣ የሚሆንበት ጊዜ ሩቅ አይመስልም፡፡ ሲናገር ሰው ስራሽ ጥርሱ ወልቆ ዱብ የሚልበት ስለሚመስለው ሳይሆን አይቀርም፣ አስር አስር ጊዜ በመዳፉና በምላሱ ወደ ውስጥ ገፋ ገፋ ያደርገዋል፡፡ በስተቀረ፣ ቁመናው የሰጠ፣ ብስል ቀይ፣ አይኖቹ ጎረጥ ጎረጥ ያሉ መልከ መልካም ነው፡፡ እሱም ይሰማዋል መልከ መልካም መሆኑ፡፡ «የቢሮክራሲው ስራ እንዴት ነው?» አለ፣ የያዘውን ጥራዝ በማገላበጥ የሲራክን አይን ወደ እሱ ለመሳብ እየፈለገ፡፡

«እያፈነኝ ነው፡፡»

«አሁንም የያዘውን ጥራዝ በማገላበጥ የሲራክን ቀልብ ወደዚያ እየሳበ፣ ሰአቱን እየና፣ «መፅሐፍህ ምን ደረሰ?» አለው፡፡

«ኩራዜ አልነድ ብላ ጨልሞብኛል» አለና፣ በረጂሙ ወደ ውጭ ተነፈሰ፡፡

«ግን» አለ እስክንድር፣ «ስለ መፅሀፍህ አንድ ነገር አጠይቅሃለሁ እያልኩ ሳስብ ነበር፡፡»

«ምን?» አለው፡፡

«ምን እንዲህ ያለ ከባድ አር:አስት እንዳስመረጠህ?»

«እንዴት ያለ?»

@OLDBOOKSPDF



«ስለ ህይወትና ሞት፣ ማለት የህይወትን ትርጉም መሻት፣...

ሲራክ ፈገግ በማለት፣ «እንደምታውቀው አርእሱቱ አዲስ ነገር አይደለም። ከሰው ልጅ ጋር የኖረ የቆየ ጥያቄ ነው» ብሎ ጀመረ። «ግን አርእስቱን ስመርጥ አዲስ ትርጉም አገኝለታለሁ ብዬ አይደለም። ስለ ኢጋቶሪ እንደሻው መፃፍ የጀመርኩት ባጋጣሚ ጎረቤታችን የሆኑ አንድ አሮጊት ሞት ከሩቁ ለመሸሽ ይሞክሩ ስለነበሩ አንድ የድር ሰው ሲያወሩ ሰምቼ ነው። ታዲያ ቆይቼ ሳሰብበት የህይወትና የሞት ጥያቄ ስር ነቀል የሆነ አብዮት በሚካሄድበት አገር በያንዳንዱ ሰው አእምሮ ውስጥ የሚጉላላ ጥያቄ ሆኖ ታየኝ። አየህ፣ አብዮት የሞት ሽረት ጉዳይ እንደ መሆኑ መጠን፣ በዚህ የከረረ ትንቅንቅ ውስጥ፣ ምናልባት ብዙዎቻችን፣ እንኖር ይሆን? ወይም ሄሚንግዌይ እንዳለው፣ 'የሚቀጥለው ደወል ድምፅ ማን ይጠራ ይሆን? የህይወት ትርጉሙ ምንድን ነው? ብለን ራሳችንን ሳንጠይቅ አልቀረንም። እና፣ የብዙዎቻችን አቋምም በህይወትና በሞት ላይ ባለን አመለካከት የሚወሰን ይመስለኛል። ደሞም ነው። ሲዘር፣ 'ፈሪዎች ከመሞታቸው በፊት ብዙ ጊዜ ይሞታሉ፣ ጀግኖች ግን ካንዴ በቀር ሞትን አይቀምሱትም' ብሎ የለ። ስንቶቻችን ስንት ጊዜ በቁም ሞተናል . . .

«ግን ይገርምሃል፣ አሳቡ ለብዙ ዘመን አእምሮዬ ውስጥ ሲጉላላ የቆየ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ነገሩ ስለ ሞትና ህይወት አይደለም» አለው።

«ሞትን ከሩቅ ስለሚሸሹ ሰው ነው የምፅፈው ስላልከኝ ነው» አለ፣ እስክንድር እየቸኮለ።

ሲራክ ትንሽ ተከዘና፣ «በመሰረቱ እኔ የምፅፈው ስለ ልበ ሙሉነት፣ ስለ ደፋርነት ነው» ብሎ ሳይጨርስ፣ እስክንድር አቋረጠውና

«ይገርማል! ምንድን ነው አንተ ከድሮ ጀምሮ በዚህ አሳብ ተጠምደህ የምትኖረው? አለው።

ሲራክ አይኖቹን ከእስክንድር ባሻገር ካለው ባዶነት ላይ አሳርፎ፣ «አየህ እስክንድር» አለ — «ልበ ሙሉነትና ደፋርነት በሰው ህይወት ውስጥ መሰረታዊ ነገሮች ናቸው። የሰው ልጅ የሚያስብ ፍጡር ነው። አሳቡን በሥራ ለመተርጎም ድፍረት ከሌለው፣ ልበሙሉ ካልሆነ ከእንስሳ በምን ይሻላል? ድፍረት ከሌለው፣ ቆራጥ ካልሆነ፣

@OLDBOOKSPDF



ለብእዊ ክብሩንና ነፃነቱን ሲጠብቅና ሲያስከብር አይችልም፡፡ ደፋርና ጢስ መውጫ አያጡም ይባል የለ፡፡ እንደዚያ ነው፡፡ ድፍረት ከሌለን ማናችንም ምንም አይደለንም፡፡ ካድሬ ባይ ብእር ባይ ወረቀት ይበልጥ ብዙ ይናገራል፡፡ ብዙ ለፈለፍኩ መሰለኝ፡፡ ለማንኛውም ነገር አሁን እምቢ ብሎኛል›› አለው፡፡

‹‹ስሜቱ ከድቶህ ይሆናል፡፡››

‹‹ሳይሆን አይቀርም፡፡››

እስክንድር፣ ‹‹አዎን፣ አንዳንዴ ኩራቱ አልነሳ ይላል›› ብሎ፣ ሲራክ ፊት የተከመረውን አሮጌ ፋይል ተመለከተና፣ ‹‹ብትለይም የቢሮክራሲ ስራ ሲታከልበት የባሰውን ይጨልማል›› ካለ በሁዋላ፣ የያዘውን ጥራዝ አገላበጠና፣ ‹‹ለኔ ግን የበራልኝ ይመስለኛል፡፡ የምፈራው ግን ብርሃን ነው ያልኩት ጭለማ እንዳይሆን ነው፡፡ የህይወትም ምፀት በስህተት በንጉታዊ ብርሃን እንተረጉመዋለን ያ ጊዜ የታየን ሁሉ ዕልመት፣ ፍፁም የማይዘለቅ ዕልመት መሆኑን ሳንጠረጥር፡፡ ብዙውን ጊዜ ህይወት ስታሾፍብን እውነት ይመስለናል›› አለና፣ ሲጃራውን ልምጥጥ አድርጎ ሰቦ ሲያበቃ፣ ‹‹ለማንኛውም ነገር፣ ያንን ጀምረአለሁ ብዬ አንድ ቀን ያጫወትኩህን መፅሀፍ ጨርሻለሁ›› አለው፡፡

ሲራክ፣ ደስታ ፈንቅሎት ብድግ ብሎ፣ ‹‹እንኩዋን ደስ ያለህ›› እያለ ጨበጠውና፣ ‹‹ምን ይሰማሃል? . . . ማለቴ ስትጨርስ ምን ተሰማህ?›› አለው፡፡

እስክንድር የሚሰጠው መልስ ጠፍቶት ሲያስብ ቆየና፣ ‹‹መቼም ልብ ያሰበውን በወረቀት ላይ አስፍረው ሲጨርሱ ይቀላል፡፡ ደስ ይላል፡፡ አለ አይደል — እሰይ ተወለደ አይነት ስሜት፡፡ ግን መልሰው ሲያነቡት ደግሞ የፃፉት ነገር እንዳሰቡት ሆኖ አይገኝም፡፡ ይህንም፣ ያንንም ለውጡ ለውጡ ያሰኛል፡፡ የመለወጥ ፍላጎት መጨረሻ የለውም፡፡ በመጨረሻ አዲስ መፅሀፍ እንደ መፃፍ ይሆናል፡፡ ይሄ ደግሞ የበኩር ልጅህን እንዲህ ካልሆንክ፣ እንዲያ ካልሆንክ፣ ካልቀነጀህ፣ ጠባይህን ካላሳመርክ፣ እገሌን ካልመሰልክ እያሉ እንደ ማንሳቀል ያህል ይቆጠራል፡፡ ታዲያ ይሄውልህ፣ የበኩር ልጅን እንዳልነበረ አድርጌው ልጅ ገዳይ አባት ከመሆኔ በፊት፣ አንተ አይተኸው አስተያየትክን እንድትሰጠኝ ነው የመጣሁት›› አለው፡፡

 @OLDBOOKSPDF

ሲራክ ይህን አልጠበቀም ነበር። ነገሩ ዱብ እዳ ሆነበት። ውስጣዊ ስሜቱ ኩምሽሽ፣ ኩምትር ሲል ተሰማው። የሰው ድርሰት አንብቦ አስተያየት ላለመስጠት ምሎ ተገዝቶ ነበር። ከዚህ ቀደም ባጋጠመው ልምድ ደራስያን በድርሰታቸው የሠጣ ነባራዊ ሂስ እንደማይቀበሉ ደርሶበታል። ማንኛውንም ሂስ ከምቀኝነት ለይተው አይመለከቱም። እሱ ደግሞ በገዛ እጁ በማያገባው ቦታ ገብቶ የእርጎ ዝንብ በመሆን ምቀኛ ለመባል አይፈልግም። ተፈጥሮው ሆኖ፣ ይበል፣ ግሩም ነው፣ ድንቅ ነው የሚል፣ ልቡ ያሰበውን ምላሱ የምትክድ አይነት ሰው አይደለም። በሒነት ለመጣ ነገር ይሉኝታ አያውቅም። እሺ ብሎ ከተቀበለ ያለውን ነባራዊ ሂስ በሀቅ ለመስጠት ሀሊናው ያስገድደዋል። ታዲያ ትርፉ ምን ነበር? ከዚህ ቀደም የደረሰበት ችግር ትዝ አለው። ሳይቸግር ጤፍ ብድር . . .

አንድ ወጣት ደራሲ ድርሰቱን አንብቦ አስተያየት እንዲሰጠው ጠየቀው። ሲራክም በደስታ ተቀብሎ ካነበበ በኋላ ወጣቱን ደራሲ ጋበዘ፣ «በምሰጥህ አስተያየት ተስፋ እትቁረጥ። ድርሰትህ የልብ ወለድ አፃፃፍን መሰረታዊ ስርአት የተከተለ አይደለም። አንዳንዴ «እኔ» እያልክ በመጀመሪያ ሰው ትተርካለህ። ትንሽ ቆይተህ ደግሞ ተራኪውን ሁሉም ቦታ የሚገባ፣ የሚያይና የሚሰማ ታደርገዋለህ። አስተያየቱ ይምታታል። በዚህ ላይ ደግሞ የመፅሀፍህ ዋና ገፀ ባህርይ ያስራ አራት አመት ልጅ ሆኖ ሳለ፣ የሚናገረውና የሚያስበው እንደ ዩኒቨርስቲ ምሁር ወይም ብዙ ልምድ ከህይወት እንደቀሰመ አዛውንት ነው። ትክክል አይደለም። ንግግሩ ከሁኔታው፣ ከባህርይው ውጭ ያደርገዋል። ሳልነግርህ የማላልፈው ሌላው ነገር ደግሞ ተጨባጭነት የሌላቸው አጠቃላይ አስተያየቶችን መወርወር ታበዛለህ። ወደ ማስተማር ታዘነብላለህ። የምትፈልገው ምንድን ነው? ለማስተማር ነው? አንባቢህን ለማስደሰት ነው? ከሁለቱ አንዱን መምረጥ አለብህ። ሁለቱን ባንድነት ለማቅረብ ከፍተኛ የድርሰት ችሎታን ይጠይቃል። አጨራረስህ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብህ። ለመጨረስ የቸኮልክ ወይም ገፀ ባህርያቱን ምን እንደምታደርጋቸው የጠፋህ ትመስላለህ። ገፀ ባህርይ መቅረፅ በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው። ልብ ወለድ ከሆነ ያለ ገፀ ባህሪይ አይሆንም። ያንተ ገፀ ባህርያት የራሳቸው የሆነ ህልውና የላቸውም። በሚናገሩት የቃላት ኩዋኩዋታና የቃላት ናዳ ይሸፈናሉ። ስለዚህ . . .» ብሎ ሳይጨርስ፣ ወጣቱ ደራሲ ረቂቁን ከእጁ ነጥቆ ደህና ዋል እንኳን ሳይለው ወጥቶ ጭልጥ። ሲራክ አፉን በዳቦ ብሎ ዝም።

ከጥቂት ወሮች በኋላ ያው ወጣት ደራሲ ተመልሶ መጥቶ፣ «ያ መፅሀፍ ያውልህ» ብሎ ይወረውርለታል — ደረቱን ነፍቶ።

@OLDBOOKSPDF



ሲራክ መፅሀፉን እያገላበጠ፣ «አሳትምከው እንዴ? ማለት፡፡

«አዎን፣ እያየኸው!» ብሎ መመለስ፣ ወጣቱ ደራሲ ተኩራርቶ፡፡

«እንዳለ ነው ወይስ . . .»

«እንዳለ፡፡»

የሲራክ አይን ከመፅሀፉ መግቢያ ላይ ያርፋል፡፡ በመግቢያው ላይ የተፃፈው «. . . እንዳንድ ደራስያን ነን ባዮች፣ ወጣት ደራስያን እንዳያብቡ በምቀኝነት ይህን መፅሀፍ አጥላልተው ተስፋ ሊያስቆርጡኝ ቢሞክሩም፣ ጊዜው፣ የትግል ጊዜ ነውና፣ አንባቢ አይቶ እንዲፈርደኝ በተስፋ አቅርቤዋሁ . . .»

በሲራክ አእምሮ ውስጥ ተቀርፆ የቀረ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ከንዴቱ ብዛት፣ «እንኳዋ ደስ አለህ» ከማለት፣ ሌላ ነገር ሊለው አልቻለም፡፡

«ባምላክህ» ካለው በሁዋላ ኩራት እየተሰማው፣ «መታተሙ ብቻ አይደለም፡፡ ባንባብያን ዘንድ መፅሐፉ ተወዶአል፡፡ ተሸጦ ሊያልቅ ነው» ይለዋል፡፡

ሲራክ ስሜቱን ሊቆጣጠር አልቻለም፡፡ በንዴት መፅሀፉን አፍንጫው ላይ ወርውሮለት፣ «የተሸጠ መፅሀፍ ሁሉ ኪነታዊ ዋጋ ያለው አይምሰልህ፡፡ እኔ አንተን ብሆን፣ ባሁኑ ጊዜ እነባለሁ፣ እማራለሁ እንጂ ደፍሬ አልፅፍም» ሲለው፣ ወጣቱ ደራሲ፣ «ግን እኔ አንተን አይደለሁም!» ብሎ ይወጣል፡፡

ሲራክ በድርጊቱ ተፀፅቶ፣ «እኔው ነኝ ሞኙ» ብሎ ገዟ፡፡

የሰው ድርሰት አንብቦ አስተያየቱን ባለመስጠት ምሎ የተገዘተው ከዚያን ቀን በሁዋላ ነበር፡፡

እና . . . አሁን ደግሞ — ነፍሱ መሙዋገት ጀመረች፡፡ እንቢ ብሎ እንዳይመልሰው ቸገረው፡፡ እንዴት አድርጌ እምቢ እላለሁ አለ፡፡ የወለደውን ካላሳመለት፣ የደገሰውን ካልበሉለት፣ . . . ፀሀፊ በተፈጥሮው ደስ አይለውም፡፡ ተዋረድኩ ተናቅሁ ብሎ ይቆጣል፣

@OLDBOOKSPDF



ያከርፋል፡፡ ጠላት ይሆናል፡፡ በቅንአት፥ በምቀኝነት ይተረጉመዋል ብሎ እያሰበ ሲጨነቅ አይቶት፥ «ምንድን ነው ቅር ያለህ?» አለ እስክንድር፥ ቅርታ አድሮበት፡፡

እስክንድር ቅርታ እንደገባው ፊቱ ላይ የሚተራመሰው ስሜቱ ይናገራል፡፡ እኔ እስክንድር፥ የፃፍኩትን መፅሀፍ እንኳ ጠይቆ ሳልጠይቅም፥ አለም ለማንበብ እንዴት አይሽቀዳደምም? የሚል ስሜት ያደረበት ይመስላል፡፡ ለመነበብ የነበረው ፍላጎት ከረሃብና ከጥማት ይበልጥ እንጂ አያንስም ነበር፡፡ መፅሀፉን አንብቦ ስለ መፅሀፉ የሚያነጋግረው ሰው እጅግ አስፈልጎት ነበር፡፡ መፅሀፉ ከመብላት የበለጠ ደስ የሚል ሙዚቃ ያለ አይመስለውም ነበር፡፡

«እ . . . ምንም ቅር ያለኝ ነገር የለም፡፡ ምንነው . . . እንዲያው ከዚህ ቀደም ስለ ደረሰብኝ ታሪክ ነበር ሳስብ የነበረው፡፡ ህይወት ልብ ወለድን ያስንቃል ይባል የለ» አለና፥ በዚያው ቢሉት በዚህ ቅያሜው ሳይቀር፥ አንብቤው ግሩም፥ ሸጋ ነው ብዬ ብመልስለት እሱን ከማስደሰት ሌላ እኔ ምን እጎዳለሁ? ብሎ በማሰብ «ጥሩ ነዋ፡፡ በደስታ» ብሎት፥ ረቂቁን ተቀበለውና ገልበጥ፥ ገልበጥ አድርጎ ከተመለከተው በሁዋላ፥ «ወፍራም ጥራዝ ነው፡፡ እናነበዋለን» አለው፡፡

«ማንበብ ብቻ ሳይሆን ሂስም እንድትሰጠኝ ነው፡፡ ባገራችን አሳታሚ ድርጅት የለም፡፡ እርስ በርሳችን ካልተረዳዳን ማን ይረዳናል? እኛው ፀሐፊ፥ እኛው አሳታሚ ሆነን፥ ችርቻሮም ገብተን እንዘልቀውም» አለ እስክንድር፥ ደስ ብሎት፡፡

ሲራክ ሳይወድ በግድ የምሁት ፈገግታ እመለጠው፥ የወጣቱ ደራሲ ቃላት ትዝ አሉት፡፡

«መረዳዳቱስ ጥሩ ነበር፡፡ ግን ያገራችን የኪነት ሰዎች እይን ሳይን አይተያዩም፡፡ አንዱ የሌላውን ድርሰት፥ 'ትግል የበላው የመቃብር ቤት ቅኔ' ሲል፥ ሌላው መልሶ፥ 'አይ የ'ረኛ ነገር፡፡ ከእበት ላይ የፈላ ትል ሁሉ ውብት ይመስለዋል' እየተባባሉ ማጅራት ለማጅራት ሲተራረዱ ነው የሚኖሩት፡፡ አንዱ የሌላውን ስእል አይቶ 'የሱ የኪነት ሰውነት ካንቀንቀሩና ከሁኔታው ላይ ነው እንጂ ከኪነቱ ላይ አይደለም፡፡ ጥሩ ፎቶግራፍ አንሺ የተሻለ ኪነት ያቀርባል' ሲል፥ ሌላው ደግሞ በበኩሉ፥ 'አይ ጉድ፥ ስርቻ ውስጥ ካልኖሩ ስእሊ ሳይሆን ነው? ቀጋ ያለውን ሸራ እንደ ፊታቸው በቀለም እያዥጎረጎሩ ዋጋ ባያጡት ምናለበት?' ይላል፡፡ አለውና፥ ቡጉሩን አፍርጦ ሲያበቃ ወዳሰበው ጉዳይ በመመለስ፥ «የዚህ ሁሉ ጥላቻ መንሻ ምቀኝነትና ሂስ

@OLDBOOKSPDF



እስመቀበል ነው፡፡ ሚኒስትር በሚኒስትር ላይ፣ አለቃ ባለቃ ላይ፣ ደራሲ በደራሲ ላይ፥ ሰአሊ በሰአሊ ላይ ይቀናል፥ ይመቀኛል፡፡ በተለይም ደግሞ ተፈጥሮአችን ሆኖ ነው መሰለኝ ሂስ ሲባል እንደ ጦር እንፈራዋለን፡፡ ታዲያ በዚህ ሁኔታ መረዳዳት ያስቸግራል፡፡ መሻሻልም አይኖርም›› አለው፥ ፊቱን ጭፍግግ አድርጎ፡፡

እስክንድር ሌላ ሲጃራ አቀጣጠለና፣ ‹‹አዎን፡፡ ያልከው እውነት ነው፡፡ የነገሩ መነሻ ታዲያ ከተፈጥሮአችን ሳይሆን ካስተዳደጋችን ነው፡፡ በህፃንነታችን፣ 'ይህን ያልበላህ እንደሆን ለእገሌ ወይም ለእገሊት እሰጠዋሁ' እያሉ በእልክ ሲያሰበሉን፣ 'እንደ እገሌ ወይም እንደ እገሊ ብትሆን' እያሉ ሲያስቀኑን፣ ሲያስመቀኙን ነው የምናድገው፡፡ ታዲያ ቅናትና ምቀኝነት በአእምሮአችን ውስጥ ተቀርፆ ይቀራል፡፡ በቅናትና በምቀኝነት የተመረዘ አእምሮ ሂስ ለመቀበል ያስቸግረዋል፡፡ አይመስልህም?›› አለውና፣ ሰው ሰራሽ ጥርሱን ብልጭ አድርጎ፣ ‹‹ኪነት ግን ብታስቀና አይገርመኝም፡፡ እንደ ውብ ውሽማ ናት፡፡ ታስቀናለች›› ብሎት፣ ሰአቱን አይቶ ተነሳ፡፡

ሲራክ ፊቱን በመሀረብ ጠረገና፣ ‹‹ልክ ነህ፡፡ ካለፈው ስርአት የተወረሰ የኪነት ሰዎች የህሊና ችግር ነው፡፡ ግን ህዝባዊ ኪነት እንዲያብብ ከተፈለገ ለኪነት ሰዎች አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል›› አለ፡፡

‹‹አዎን›› አለ እስክንድር፥ ‹‹ግን የሚያሳዝነው መንግሥቱም ሆነ ህዝቡ የኪነት ሰዎችን የሚደግፉበት ደረጃ ላይ አልደረሱም፡፡ መንግሥቱ ድሀ ነው፡፡ ዘጠና ሶስት ከመቶ በላይ የሚሆነው ህዝብ ማይም ነው፡፡ በዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ የኪነት ሰዎች ከባህር የወጣች አሳ ናቸው፡፡ የጋን መብራት፡፡ ነደን ነደን ለማንም ብርሃን ሳንሰጥ የምናልቅ ሻማ፡፡ በቢሮክራሲ ሻጋታ ውስጥ ነፍሳችን ታፍና የምትቃትት፡፡ የኪነት ሰዎች ነፍስ ገና አርነት አልወጣችም›› አለ እያቃሰተ፡፡

ሲራክ ፊቱን ጠረገና፥ ‹‹ሆኖም›› አለ፣ ‹‹ብሩህ ተስፋ ሊታየን ይገባል፡፡ የኪነት ሰዎች ህይወት ከህብረተሰቡ ጠቅላላ ኑሮ ተገንጥሎ ብቻውን ሊታይ አይችልም፡፡ ባህላዊ አብዮት የጠቅላላው አብዮት አካል ነው፡፡ በማይምነት ላይ የሞት ሽረት ጦርነት ታውጆአል፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አንባብያን እየተፈጠሩ ናቸው፡፡ ማይምነት ትጥቁን ይፈታል፡፡ እና፣ ያኔ ችቦአችንን አብረን እንቀድማለን – በትግል›› አለ፡፡

@OLDBOOKSPDF



እስክንድር በረጃሙ ተንፈሰና፥ «ይልቅ መራራው ትግል የሚጀመረው ያኔ ነው፡፡ ምክንያቱም ኪነት መቅደምን እንጂ መከተልን አታውቅምና፡፡ ኪነት የነጠረች ህዝባዊ ህሊና ናት፡፡ መሆንም አለባት፡፡ ካልሆነች ዋጋ አይኖራትም፡፡ ውዳሴ ከንቱ ሆና ትቀራለች፡፡ የኪነት ተግባርዋ መጋረጃውን ከፍታ ፀዳሉን ማሳየት ነው» አለ፡፡

«እናሸንፋለን!» አለ ሲራክ፥ እየሳቀ፡፡

«እንጠራጠርም!» ሲል መለሰለት፡፡

እስክንድር ሰአቱን ተመለከተና፥ «መሄድ አለብኝ፡፡ ታዲያ መቼ እንገናኛለን?» አለው፡፡

ሲራክ ጥራዙን እየና፥ «እንግብቤ እንደ ጨረስኩ እደውልልሃለሁ፡፡ ቻዎ! ህዝባዊ ኪነት ታብባለች!» አለው፡፡

«በትግል!» ብሎት ወጣ፡፡

ሲራክ የእስክንድርን መፅሀፍ ይዞ በመቅረቱ ደስ አላለውም፡፡ የሰው መፅሀፍ ማንበብ ሳይሆን የራሱን ለመፃፍ ነበር የፈለገው፡፡ ጠመዝማዛ የህይወት መንገድ! ቶሎ ማንበብ በሳለበት ብስጭት ብሎ ረቂቁን ታቅፎ ቆሞ ቀረ፡፡

ያረጀ ፋይል . . . የሰው ፅሁፍ ረቂቅ . . . ጭፍግግ ያለ አየር . . . በመጥፎ ስሜት የተጀመረ ቀን . . . ለዘለአለም የጠፋ ቀን . . . ኤጭ . . . ሰብለን ማየት ፈለገ . . .

የወትሮ ፀሀያማ ፈገግታዋ ከብ ፊትዋ ላይ አይታይም፡፡ ከየት ይሆን? ይጋባል እኮ፡፡ ያንን ጭፍግግ ያለ ጨንጓታም አየር በትንፋሹ እፍ ብሎ ሰማዩን በማሳቅ የሰዋንም ፊት እንደ መስከረም ሥራ ፈገግ ለማድረግ ቢችል ምን ነበረበት!

በደበሎዋ የነካው የሳቂታ ፊትዋ መጨለም ሳይሆን አይኑን ለመሸሸ የምታደርገው ጥረት ነበር፡፡ እግሬን በሰበረው ኖሮ አላለም፡፡ ፀሀይዋን በኪሴ ይገድላት በመጣሁ ኖሮ የሚል ምኞት ነበር በልቡ ያደረው፡፡ ከጠረጴዛ ላይ ፊት ለፊትዋ ያስቀመጠችውን ያልፈነዳ

@OLDBOOKSPDF



ፅጌረዳ አበባ እምቡጥ ተመለከተ፡፡ ቀጠለና የከንፈርዋን ቀለም አየ፡፡ ከከንፈርዋ ወደ አበባው አይኑን መላልሶ ወረወረ፡፡ አይኑን ለመሸሽ አንገትዋን ደፋ አደረገች፡፡ ጠጉርዋ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ ከንበል ስለሚል ከአናትዋ መሃል ትንሽ ሳዱላ መሰላ ከምትታየው ቦታ ላይ አይኑ ላንዳፍታ ተጫወተ፡፡

‹‹ፈገግታሽ የት ጠፋ?›› አላት፡፡

‹‹በዚህ አለም ፈገግ የሚያደርግ ምን ነገር አለ?! . . .›› አለችው አይኑን እየሸሸች፡፡

‹‹ሞልቶ›› አላት፥ በእጁ አገጭዋን ቀና አድርጎ አይንዋ ለማየት እየፈለገ፡፡

አንገትዋን እንደ ደፋች፥ ‹‹እኔ ግን በኑሮ ውስጥ ምንም የሚያስደስት ነገር አላየሁበትም፡፡ አስተውለህ ስትመለከተው ምን የሚያስደስት ነገር አለ? ምኑ ነው ጥሩ እስቲ? ስለ ኑሮ የማላውቅ ወይም የማይገባኝ አይምሰልህ፡፡ ፈገግ የሚያሰኝ ነገር አይደለም›› አለች፡፡

‹‹ተዪ እባክሽ. . . ህይወት ውብ ናት . . . ብዙ ስቃይ ቢኖርባትም፡፡ ግን ምን ሆንሻል? የማውቃት ሰብለ አይደለሽም›› አለ፡፡

‹‹አዝኛለሁ፡፡ በጣም አዝኛለሁ›› አለች፡፡

ቀና ስትል አይኖችዋ እንባ አቅርረው አየ፡፡

‹‹ምን አገኘሽ›› አላት፡፡

‹‹ስለ መፅሀፍህ›› ብላ፥ ማንባርዋን እጅዋ ላይ አስደግፋ አቀረቀረች፡፡

‹‹ምን ነው? አልወደድሽውም?›› አላት፥ የምትለውን ለመስማት እየጓጓ፡፡ ዝም ብላ ስለቀረች፥ ‹‹ታዲያስ?›› አላት እንደ ገና፡፡

‹‹እንብቤዋለሁ፡፡ ግን ምን ብዬ እንደምነግርህ አላውቅም፡፡ በጣም ነው የማዝነው›› አለች፥ ከጉንቀትዋ ብዛት ድምፅዋ ስልቱን እየሳተባት፡፡

@OLDBOOKSPDF

ከብ ፊትዋ ላይ የሚነበበውን ጭንቀት በመመልከት ግራ ገብቶት፣ «ምንድን ነው እሱ?» አላት።

ሰብለ የወትሮዋ አይደለችም። እንዲህ ያደረጋት አየሩ እንዳልሆነ ገባው። እንዲህ አድርጎ ያሳዘናት ነገር ምን ዕፌ ይሆን? በማለት ራሱን ሲያስጨንቅ፣ «መፃፍክን ማታ ባሲ ቀደደው፣ ቡጭቅጭቅ አድርጎ ነው የጣለው» አለች፣ በሚንቀጠቀጥ ድምፅ።

እንባዋ መውረድ ጀመረ። ቦር ብላ ከቦርሳዋ መሀረብ አወጣችና ስልክክ ብሎ የሚወርደውን እጭር አፍንጫዋን ካባበሰች በሁዋላ፣ «በጣም ነው ያዘንኩት። በውነቱ ምን እንደምልህ ግራ ይገባኛል» ብላ ጠረጴዛዋ ላይ ድፍት አለች።

ሲራክ ድንገት አለ። ጆሮውን ለማመንም አቃተው። ቀልድም መሰለው። ግን እንባዋ በቀልድ እንዳልወረደ ገባው። በግድ ፈገግ ለማለት ሞከረ። ሙከራው አልተሳካለትም። ቂል መስሎ ቁጭ ብሎ ቀረ።

እየተንፋነፈችና እንባ እያነቃት፣ «ሌላ ቅጂ የለህም?» አለችው።

የመጨረሻው ተስፋዋ ነበር። «አለኝ» የሚል መልስ ለመስማት ከፉኛ ጉጉትታ ነበር።

«የለኝም» አላት፣ በደረቀ ጉሮሮ።

«እኔ አላምንም!» አለች።

ቆየችና፣ «ለምን ኮፒ የለህም?» አለችው፣ ማመን እያቃታት።

«በእጁ ስለሆነ የምፅፈው እንደ ገና መገልበጡ ያደክመኛል» አላት፣ የተሰማውን ሀዘን መደበቅ እያቃተው።

«በካርቦን ብታደርገው ኖሮ'ኮ ጥሩ ነበር» አለችው።

«ሞክሬ ነበር። ደስ ስለማይለኝ ነው የተውኩት። አሳብ የሚመጣልኝ አንድ ወረቀት ላይ ነው» አላት።

@OLDBOOKSPDF



‹‹እኔ አላምንም!›› አለች፣ እንደ ገና፡፡

ቆየችና፣ ‹‹ለመሆን ለመጨረስ ምን ያህል ነበረ የቀረህ?›› አለችው፡፡

‹‹አስር ምእራፎች ብቻ ነው የሰጠሁሽ፡፡ ለመጨረስ ገና ብዙ ይቀረኛል፡፡ እሱም እልሄድ ብሎ አስቸግሮኝ ነበር›› አላት፡፡

ሀሊናዋ በደበለጠ በመጨነቁ ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች፡፡ ሰብለ ስታለቅስ በማየቱ ከፋው፡፡ የፈለገው ፀሀያማ ፈገግታዋን ማየት ነበር፡፡ የልቅሶዋ ምክንያት በመሆን የሀሊና ወቀሳ አደረበት፡፡ በእሱ መፅሀፍ የተነሳ ከባልዋ ጋር በመጣላትዋም ከፋኝ አለን፡፡ መዘዘኛ መፅሀፍ! ከኔ ህይወት አልፎ ደግሞ የእሰዋን! እኔን ያንከራተተኝ መቼ አነሰው! ሲል ቆየና ባባቡ፣ ‹‹አታልቅሺ፣ እንደ ከተፃፈ ሁለተኛ ጊዜ ሊፃፍ ይችላል›› አላት፣ ከልቡ ተጨንቆ ሊያፅናናት እየሞከረ፡፡ ትዝ አለውና፣ ‹‹ማስታወሻ የወሰድኩበት ወረቀት ሁሉ አለ፡፡ ችግር የለም›› አላት፡፡

‹‹ግን፣ ልክ እንደ በፊቱ አይሆንማ፡፡ ይሆናል?›› አለችው፣ እንባዋን እየጠረገች፡፡

ፈገግ ብሎ፣ ‹‹ብኔ ይሁንብሽ፡፡ የተሻለ ይሆናል›› አላትና፣ ድንገት ያሳሰበው ደስታ ተሰማው፡፡ ‹‹የመፅሀፉ መቀደድ ሳላሰበው ከሰማይ የወረደልኝ መና ነው፡፡ ይግረምሽና ወደ ፊት አልሄድ ብሎ አስቸግሮኝ ነበር፡፡ ከዳር ሊታደርሰኝ ከፈለግሀ ወደ ሁዋላ እንመለስ ሲለኝ ኖሮአል ለካ፣ ውነቱን ነው፡፡ ባይቀደድም ከስር ጀምሬ እንደ ገና ሳልፅፈው አልቀርም ነበር፡፡ እንደ ገና እፅፈዋለሁ፡፡ ቃል እገባልሻለሁ፡፡ ምንም የሀሊና ወቀሳ ሊሰማሽ አይገባም፡፡ እሺ? ብሎአት፣ ከተቀመጠበት ተነስቶ በእጁ አገጯዋን ይዞ ፊትዋን ወደ ላይ ቀና በማድረግ ጉንጮዋ ላይ ሳም አደረጋት፡፡

ግን፣ የተፃፈውን በተሻለ ሁኔታ እንደ ገና ስለ መፃፉ እርግጠኛ አልነበረም፡፡ በልቡ ጥልቀት ውስጥ ከዚሀ ቀደም የተፃፈውን በዚያ ሁኔታ፣ በዚያው ቀልብ፣ በዚያው ስሜት፣ በዚያው ራእይ እንደ ገና የመፃፉ ነገር ከቶ እንደማይቻል ሳያውቅ ቀርቶ አይደለም፡፡ በዚያን ሲኮንድ አንድን ቃል ሲመርጥ ያደረበት ስሜት፣ ያቺ ቃል የሰጠችው ትርጉም፣ አረፍተ ነገሩን ሲያሳካ ነፍሱ የተሰማት ርካታ፣ የተሰማው ሙዚቃ፣ የታየው ምስል ዳግመኛ ሊከሰት እንደማይችል ያውቃል፡፡

 @OLDBOOKSPDF

ለዘለአለሙ ጠፍተዋል፡፡ ይህን ሁሉ ያውቃል፡፡ ግን አገዟ ሲያሳዝናት አልፈለገም፡፡ እሺን . . . ግን . . . ያንኑ አሳብ ይገፍ ሌላ መፅሀፍ . . . ምናልባትም የተሻለ መፅሀፍ ልፅፍ እችላለሁ በማለት ራሱን አፅናና፡፡ ለጊዜው የታየው የእሰዋ ደስታ ብቻ ነበር፡፡

‹‹እሺ?›› አላት፡፡

‹‹እሺ›› ብላው ፈገግ አለች፡፡ ሳታስበው የሳማት ቦታ ነካች፡፡

ሰውነትዋን አንድ ነገር ውርር ሲያደርጋት ተሰማት፡፡

‹‹እንዲያ ነው፡፡ አሁን ይሻላል፣ የኔ ውብ›› አላት፡፡

‹‹ምናልከ?›› አለችው፡፡

‹‹የኔ ውብ፡፡››

‹‹ማንም እንዲህ ብሎኝ አያውቅም›› አለች፣ በተምታታ ስሜት፡፡

‹‹ባልሽም?››

‹‹ባሌም ቢሆን፡፡››

‹‹እውር መሆን አለበት፡፡››

‹‹ለሚስቶቻቸው ሲሆን ባሎች እውር ናቸው፡፡ በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ እኩል ነው! እንደሱ ነው የትዳር ነገር›› ብላ አዘን አለች፡፡

እዝን ብላ ያደረችውና ያረፈደችው ነፍስዋ ለመተንፈስ ስትወራጭ ተሰማት፡፡ የሚሰማትን የምታጫውተው ሰው ፈልጋ ነበር፡፡ የልቧን የምትነግረው ሰው ይኸውና ብላ አሰበች፡፡ ለምን እንደሆነ ሳታውቅ በሲራክ ላይ እምነት አደረባት፡፡ ‹‹የኔ ውብ›› ያላት ከጆሮዋ ውስጥ አልጠፋም፡፡

‹‹ለምን ቁጭ አትልም?›› አለችውና፣ የታችኛውን ከንፈርዋን ጣል አደረገች፡፡

@OLDBOOKSPDF



ከክንፈርዋ ወደ ዕጌረዳ አበባው፥ ከአበባው ወደ ክንፈርዋ አይኑን እየወረወረ፥ «ስራ አስፈታሻለሁ ብዬ ነው» አላት፡፡

ሆኖም ለመሄድ አልፈለገም ነበር፡፡ እነዚያ ያረጁ አቡዋራም ፋይሎች እንደሚጠብቁት ትዝ አለው፡፡ የስቃይ ቀጠሮ፡፡ መጥተው ያፈኑት ይመስል በሃይል ተነፈሰ፡፡

«አጣዳፊ ስራ የለኝም» አለችና፥ በፀሀያማ ፈገግታዋ አጥለቀለቀችው፡፡ ሞቅ አለው፡፡ ወንበር እየሳበ፥ «አለቃሽ የለም እንዴ?» አላት፡፡

«ስብሰባ ላይ ነው፡፡»

«የውሸት፥ ወይስ የውነት ስብሰባ?»

«አሁን ሳስበው የሚገኝበትን አድራሻ ትቶልኝ አልሄደም» አለች፡፡

«እንግዲያውስ የውሸት ስብሰባ ናት» አለና፥ ተመቻችቶ ተቀመጠ፡፡

«ግን እኮ፥ በጣም ቆንጆ ሚስት አለችው» አለች፥ ሳታስብ፡፡

«በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ እኩል ነው ብለሽ የለ፡፡»

«እውነት ነው» አለችና፥ ከንፈርዋን መጠጠች፡፡

«ለምን ይመስልሻል እንዲህ የሚሆነው?» አላት፡፡

«አመል ሆኖባችሁ ነዋ፡፡ ወንዶች ስትባሉ የሀፃንነት ጠባይ ያጠቃችሁአል፡፡ ሳታድጉ ነው አርጅታችሁ የምትሞቱት» አለች፡፡

«በሴቶች አይብስም?»

«ፍፁም! እዚህ ላይ በጣም ተሳስተሃል፡፡ እኛ ሴቶች አንዴ ከወደድን እንወዳለን፡፡ ሌላ ወንድ ያለ አይመስለንም፡፡ የምታራክሱንም ለዚሁ ነው» አለችና፥ እጅዋን አወናጨፈችበት፡፡

 @OLDBOOKSPDF

እይትን ጨፍኖ ማንባቱን እያሸ ያለችውን ለጥቂት ሲከንድ ሲያስባስል ከቆየ በሁዋላ፥ «እውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሰረተ ጋብቻ ይሆናል፡፡ እውነተኛ ፍቅር ከሆነ ፍቅር የጋራ ስሜትና መተሳሰብ ይሆናል፡፡ እውነተኛ ፍቅር ወንድ ሴት አይልም» ብሎአት ሲያበቃ፥ እይትን ከፍቶ እይን እይንዋን እያየ፥ «ነገሩ ግን፣ ያለ እድል ሆኖ ብዙዎቻችን ጭፍን ስሜትንና ስመመንን በእውነተኛ ፍቅር በመተርጎም ችኩለን እንጋባለን፡፡ አይናችንን ስንከፍት ነገሩ ሌላ ሆኖ ይገኛል፡፡ ያ የሰመመን ጭምብል ሲወልቅ፥ ብቅ የሚለው ያገጠጠ እውነታ ያስቀይማል፡፡ ነገሩ፥ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ነውና፥ ብዙዎቹ ካለው እውነታ ጋር እንደ ምንም ታርቀው እድሜያቸውን ከመግፋት ሌላ ምርጫ የላቸውም፡፡ ህይወት ብዙውን ጊዜ ታዳላለች፡፡ ፍትህ ይጎድላታል፡፡ እድለኞችና ልበ ብርቱዎች ብቻ ናቸው በጊዜ ጊዜ የህይወታቸውን መንገድ በሌላ አቅጣጫ ሲቀይሱ የሚችሉት፡፡ ብዙዎቻችን ዝም ብለን ነው የምንኖረው፡፡ በሌላ አንጻሩ ደ'ሞ ወዴት ነው የህይወትን መንገድ የምንቀለብሰው? እና፥ ለምን? አየሽ፥ ፍቅርና ኪነት አንድም ሁለትም ናቸው – በኔ ግምት፡፡ ማለቴ፥ ፍፁም የሆነ ፍቅር ወይም ኪነት ላይ ለመድረስ ምን ስንማስን ብንውል፣ ምን ስንቡዋጥጥ ብንኖር ልንጨብጣቸው አንችልም፡፡ ተቃረብን ባልን ቁጥር፥ እንደ በረሃ ኩሬ፣ እየራቁን ይሄዳሉ፡፡ ለዚህ ነው ህይወት ታዳላለች የምለው» አላት፥ ልቡ እንደ ድንጋይ እየከበደው፡፡

«አሁን ገና ሆዴ ገባህ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ላነጋግርህ ፈልጌ ነው ቀደ ያልኩህ፡፡ ባሌ መፅሀፍክን ለምን እንደ ቀደደው ሳትጠይቀኝ በመቅረትህ ገርሞኛል» አለች፥ አይኖችዋን እያርገበገበች፡፡

«ልትነግሪኝ ትፈልጊለሽ?» አላት፡፡

እሱ ራሱ ሊያቀርብላት የፈለገው ጥያቄ ነበር፡፡ ግን፥ ስሜትዋን በማጤን፥ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ፥ ምናልባት ልትመልሰው የማትፈቅደውን ጥያቄ ሊያቀርብላት አልፈለገም፡፡ ሆኖም ምክንያቱን ሳይጠረጥር አልቀረም፡፡ የህሊና ወቀሳ ያሳደረበትም ይኸው ጥርጣሬው ነበር፡፡

«ካንተ ጋር የተለየ ግንኙነት ያለኝ መስሎት ነው» አለች፡፡

«ይህን ያህልስ እኔም ጠርጥሬአለሁ» ብሎአት ሲያቅማማ፥

@OLDBOOKSPDF



«ይቀናብሻል መሰለኝ?» ካላት በኋላ፣ ለእሰዋ ያለውን አድናቆት እግረ መንገዱን ለመግለፅ ያህል፣ «ቢቀናብሽም አይፈረድብትም» አለ፡፡

«እንዴት?» አለች፡፡

«ውብ ነሽ» አላት፡፡

«ባሌ ግን አስቀያሚ፣ ደደብ፣ ነው የሚያደርገኝ፡፡ ስድቡ ምሳና ራቴ ነው፡፡ ሞራሌን እየገደለው ነው፡፡ ይልቅ እሱ ነው ሊያስቀናኝ የሚፈልገው» አለች፣ በሀዘን ቅስምዋ ሰበር እያለ፡፡

ልቡ እብሮአት ሰብር ሲል ተሰማው፡፡

«ለምን ይመስልሻል?» አላት፡፡

ከንፈርዋን ጣል፣ እንገትዋን እክት አድርጋ፣ «እኔ እንጃ፡፡ ውሀ ተጠን ብሎ ነው የሚሰድበኝ፡፡ እና፣ ሆን ብሎ ደሞ ሊያስቀናኝ ይሞክራል» አለች፡፡

«ቅናት የፍቅር ጥላ ነው፡፡ ክብት ያልዋለበት ኩበት አይለቀምም» ካላት በሁዋላ፣ አሁንም እያቅማማ፣ «ምናልባት የማታፈቅሪው እየመሰለው እንደሆን?» አላት፣ ዝግ ባለ ድምፅ፡፡

«ልቤ ለፍቅር ቦታ የለውም» አለች፣ ቆጣ ብላ፣ ፍቅር የተባለው ቃል ቆንጠጥ ያደረጋት ይመስል፡፡

«ምልቶት?» አላት ደፍሮ፣ «እንዴት ልቤ ለፍቅር ቦታ የለውም ትያለሽ? ለፍቅር ቦታ የሌለው ልብ የለም፡፡ የሚከፍተው ጥሩ ቁልፍ አጥቶ እንደሆን?» ካላት በሁዋላ፣ ይህን ለማለት መብት የለኝም በሚል መንፈስ፣ ምንነው ባልተናገርኩ ብሎ ተፀፀተ፡፡

እሰዋ ግን፣ «ቁልፍ» የተባለውን ቃል ስታሰላስል ነበር የቆየችው፡፡ በህይወትዋ ውስጥ የደረሰባትን ክፉ ሁኔታ ድንገት አስታወሳትና፣ «ልቤ ተቆልፎ ነው የሚኖረው» አለች፣ የሀዘን ስሜት ፊትዋ ላይ እያጠላ፡፡

«ለምን?» አላት፡፡

 @OLDBOOKSPDF

‹‹ልቤ ተቆልፎ የቀረው ከህፃንነቴ ጀምሮ ነው›› አለችና፣ ትንሽ ከመነታቱች በሁዋላ፣ ‹‹ነገሩ እንዲህ ነው›› ብላ ረጅም ታሪክ ጀመረች።

‹‹እናቴን በጣም አድርጌ እወዳት ነበር፡፡ ከስርዋ አልለይም ነበር፡፡ ቀሚሰዋን ጨምድጄ ይዤ በገባች በወጣችበት ክፍል እከተላት ነበር፡፡ ትዝ ይለኛል፡፡ እንዲህ እስከ መጨረሻው ልንለያይ ወጥታ የምትመለስ አይመስለኝም ነበር. . .! እሰዋም የኔ ነገር አይሆንላትም ነበር›› ብላ ዝም አለች፡፡

ሲራክ ሊያቋርጣት አልፈለገም፡፡ ሰው ብዙውን ጊዜ የልቡን እንደማይናገር ያውቃል፡፡ መናገር ሲጀምር ግን ዝም ብሎ ማዳመጥ ለደራሲ ጠቃሚ ዘዴ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ስለዚህ ዝም ብሎ ጠበቃት፡፡

‹‹ባባቴ ይህን ያህልም ደንታ አልነበረኝም›› ብላ፣ ታሪክዋ ቀጠለች፡-

‹‹ለናቴ ያለኝ ፍቅር ብቻ ነበር የሚያንገበግበኝ፡፡ ቁዋንቁዋ ለቁዋንቁዋ ተግባብተን አልተነጋገርን፡፡ በአይን፣ በስሜት ለኔ የነበራት ልዩ ፍቅር ይገባኝ ነበር፡፡ መልክዋ አይረሳኝም፡፡ ጠይም አፍንጫዋ አጠር ያለ፣ አይኖችዋ ካፍንጫዋ ራቅ ራቅ ብለው ከተሰሩት ጉድጉዋዶች ውስጥ የሚያበሩ ከዋክብት ይመስሉ ነበር፡፡ የጥርስዋ ፍንጭት፣ ትከሻዋ ላይ ወርዶ ከፀሀይዋ ጋር ልዩ ልዩ ብርሃን ይፈነጥቅ የነበረው ሀር መሳይ ፀጉርዋ፣ ድምፅዋ፣ ሳቅዋ፣ ደስታ የተሞላበት ሳቅዋ ትዝ ይሉኛል . . .

‹‹አንድ ቀን በድንገት በሞት ስትለየኝ ለዘለአለም መሆኑ አልገባኝም መሰለኝ አላለቀስኩም፡፡ የሞት፣ የመለየት ትርጉም አልገባኝም፡፡ ተመልሳ የምትመጣ ይመስለኝ ነበር፡፡ ሰዎቹ ሲያለቅሱ ዘፈን መሰሉኝ ባድናቆት ፈዝዤ እመለከት ነበር፡፡ ቤት ሲያስገቡኝም አልተከራከርኩም፡፡ በየትኛው አፉ? እሺ ብዬ ገብቼ እጫወት ጀመር . . .

‹‹የቀብሩ ስነ ስርአት አለፈ፡፡ አርባ፣ ሙት አመት፣ ሁለት ሶስት አመታት አለፉ፡፡ እናት ያላቸውን ልጆች ሳይ የኔስ እናት የት ሄደች? እውን ሞታች? እስከ መጨረሻው ነው የተለየችኝ? በኔ ጨክና? እያልኩ ሁልጊዜ አለቅስ ነበር . . .

‹‹ከጊዜ በሁዋላ የሞት ትርጉም ገባኝ፡፡ ከሚወዱት የመለየት ትርጉም ቁልጭ ብሎ ታየኝ፡፡ ከዚያ ወዲያ ያለውን ታሪክ ማስታወስ

@OLDBOOKSPDF



ያስጠላኛል፡፡ ፍቅር የሌለበት ባዶ ሕይወት ነበር፡፡ ልቤ ተቆለፈ፡፡ ካደግኩም በሁዋላ፥ ያ ከሚወዱት ሰው የመለየት ፍርሃት አልተለየኝም፡፡

‹‹ፍቅሬን ሙሉ በሙሉ ለመስጠት የምፈራው ድንገት እንደ እናቴ የተለዩኝ እንደሆን እያልኩ በመስጋት ይመስለኛል፡፡ መለየት ጠላሁ፡፡ ከምወደው ሰው ለመለየት ስለማልፈልግ ማንንም በሙሉ ልቤ መውደድ አልችልም፡፡ ልቤ ለፍቅር ቦታ የለውም ያልኩህ ለዚህ ነው፡፡ ልቤ ተቆልፎአል›› አለች፥ የሚተናነቃትን እንባ ለመግታት እየታገለች፡፡

ሲራክ ጥልቅ የሆነ ሀዘን ተሰማው፡፡ ሀዘን ሰውነቱን እንደ ጉንዳን ወረረው፡፡ እንዲህ ያለች ውብ ልጅ – ለፍቅር – ብቸኛ ልብ – የሀዘን ሙዚቃ የሚዘፍን ብቸኛ ልብ – እውነትም ይህ ህይወት አድሎአዊ ነው እያለ፥ እዝን ብሎ ሲያስብ፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ አንተ ደካማ ልቤ – ጀመርክ እንግዲህ ልቅሶህን – በማያገባህ ቦታ ገብተህ መጨነቅህን – ለአለም ችግር ሁሉ መፍትሄ ያለህ ይመስል – አብዛኛው በዝምታ የሚያለቅሰው ልቅሶ አይደል – ምን አዲስ ነገር ተናገረች – በአለም ብቸኛ ልቦች ሞልተዋል – በማለት ከራሱ ጋር ሲሙዋገት፥ ሰብለ ከተቀመጠችበት ተነስታ በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከተች፥ ‹‹እየህ ሲራክ›› አለች፥ ‹‹ባል፥ ጤናማ ልጆች፥ ቤት፥ መኪና፥ ጥሩ ደመወዝ፥ አለኝ፡፡ በኑሮ የሚጎድለኝ ነገር የለም፡፡ ይህ ሁሉ አለኝ፡፡ ታዲያስ? – ሰው ይህ ሁሉ ከተሙዋላለት ሌላ የሚፈልገው ምን ነገር አለ? ምናልባት . . . አላውቅም፡፡ እፈራለሁ፡፡ የምፈልገውን – ሊዎን፥ ልቤ የሚፈልገውን ለማወቅ፥ ለማለት፥ ለማመን እፈራለሁ፡፡ ለምን? አላውቅም?. . .

‹‹እስከ መቼ? – እንጃ! ማን ነው ታዲያ ከዚህ ፍርሃት እጀን ይዞ የሚወጣኝ? የሌሎችን ድፍረት ብቻ አድንቆ ዝም ማለት የሚያስተውኝ? ታድለው! ከማለት በስተቀር እኔ ከዚህ ከፈራ ወኔ ራሴን ፈልቅቄ ለማውጣት አልችልም፡፡ ከኔ ከራሴ በስተቀር የሚያድነኝ ማን አለ . . .

‹‹ይህን እያወኩ፥ ሁልጊዜ ከሀሊናዬ ጋር ሙግት – ሙግት፡፡ የሀሊና ሙግት እንዲቀር መቼ ይሆን የሚታወጀው? ምንድን ነው? ከማንስ ጋር? ማንንስ ለመርታት ነው ሁልጊዜ የምሙዋገተው? ተመልሶ እዚያው – እዚያው . . .

@OLDBOOKSPDF


«ህይወት ወደ ፊት፣ ወደ ሁዋላ፡፡ እያሳዝንም የሰው ህይወት፣ አንተ እንዳልከው ህይወት ፍትህ ይጎድላታል፡፡ አድሎአዊ ናት፡፡ የሌሎችን ድፍረት 'ታድለው! ምን ነው እንደነሱ ድፍረት በሰጠኝ' እያልኩ ከማድነቅ ሌላ የራሴን ህይወት መኖር አልችልም፡፡ የራሴን ትቼ በሌሎች ህይወት ውስጥ ነው የምኖረው፡፡ ይገረምህና ለዚህ ነው ልብ ወለድ መፅሀፍ ማንበብ የምወደው» አለች፡፡

በመሀረምዋ ፊትዋን ጠረገች፡፡ ፊትዋን ለማየት ባይችልም አሁንም እንባዋ እንደምታዘራ ታየው፡፡ አሳዘነችው፡፡ በጣም አሳዘነችው፡፡ ከፈራ ወኔዋ ወጥመድ ፈልቅቆ ሊያወጣት ፈለገ፡፡ ግን፣ ግን፣ በዚያ ፍላጎቱ ውስጥ የራሱ ፈሪ ወኔ ታየው . . . እና፣ ደካማ ልቡን ረገመ፡፡

ሰብለ ወደ መቀመጫዋ ተመልሳ፣ «አሰለቸሁህ መሰለኝ!» አለች፣ በደረቀ ጉሮሮ፡፡

«ህይወት ከልብ ወለድ ታሪክ ይልቃል» ብሎ ስሜቱን ለመቆጣጠር እየሞከረ፣ «ልብ ወለድ ከህይወት ጋር ሲነፃፀር ባዶ ነው፡፡ በውነት ባዶ ነው» አላት፡፡

ሰብለ በልብዋ ውስጥ እምቃ ይዛ ለማንም ሳትናገር ያቆየችውን ስሜትዋን በመተንፈስዋ ቀለል አላት፡፡ እንደ ድንጋይ ከብዶአት የነበረው ልብዋ ሸክሙን አራግፎ ሲፈነድቅ ተሰማት፡፡ በረጂሙ ወደ ውጭ ተነፈሰች፡፡ አይን ለአይን ተጋጩ፡፡ ከግጭቱ የወጣው ብልጭታ ያጥበረበረው ይመስል አይኑን ሰበር አደረገ፡፡

«የራሴን ችግር ሳወራ ያንተን መፅሀፍ ረሳሁ» ብላ፣ ብልጭ፣ ድርግም አደረገችና፣ በጣም ነው ያዘንኩት፡፡ በእርግጥ እንደ ከንፈርዋን ግጦ፣ እንገትዋን እንደ እስክስታ ወራጅ እንከት፣ አይንዋን ገና ትፅፈዋለህ?» አለች፡፡

«ቃል እገባልሻለሁ» አላት፡፡

«ወደ ፊት ግን ሰስት፣ አራት ቅጂ ማኖር አለብህ፡፡ በታይፕ እረዳሃለሁ፡፡»

«አብረን እንፅፈዋለን» አላት፡፡

«ታድዬ» አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF



ክብ ፊትዋን ፈገግታ አጥለቀለቀው፡፡ እሱ ቁጭ ብሎ ሲፅፍ እሰዋ ካጠገቡ ተቀምጣ ስታነብ፣ እሱ ስለፃፈው ነገር፣ እሰዋ ስላነበበችው መፅሀፍ ሲጨዋወቱ ታያት፡፡ በመስኮቱ ከሚታየው አድማስ ላይ አይንዋን ጣል አደረገች፡፡ እሳብዋ ግን ከአድማሱ ባሻገር እልፍ ሄደ፡፡ ምንኛ ደስ ይል ይሆን? ብላ አሰበች፡፡

‹‹በንገራችን ላይ›› አላት፡፡

‹‹አቤት›› አለች፣ እንደ መባነን ብላ፡፡

‹‹ወዶ መለየት አዲስ ነገር አይደለም›› ሲላት

‹‹እኔን ግን ያስፈራኛል›› ስትለው

‹‹ያለ፣ ወደ ፊትም የሚደርስ ነገር ነው›› ብሎአት – ማርታን ሳይወድ በግድ እያስታወሰ፣ ‹‹የፍቅር ቅመሙ ታዲያ ከምን ላይ መሰለሽ? መለየት መኖሩን ከማወቅ ላይ ነው፡፡ እንደ ህይወት ማለት ነው፡፡ ሞት ባይኖር የህይወት ጣእም እንዴት እድርጎ እንደሚገባን አላውቅም፡፡ ይገባን እንደሆን ማለቴ ነው›› ካላት በሁዋላ፣ ‹‹ለማንኛውም ነገር ህይወት ብዙ ቁስል፣ ብዙ ጠባሳ ሳትተው እንዲሁ አትለቀንም፡፡ ይህች አጭር ህይወት ጣጣዋ ብዙ ነው›› አላት፡፡

‹‹ልክ እንደምትናገረው በፃፍከ . . .›› አለች፣ ስሜት ፈንቅሎአት፡፡

‹‹እንደምናገረው አልፅፍም እንዴ?›› ብሎ በመገረም፣ ‹‹እስካሁን ድረስ ስለ ድርሰቴ እንደዚህ ያለ ገንቢ ሂስ ሰምቼ አላውቅም ነበር›› አላት፡፡

‹‹ከፃፍከ ገና ብዙ እሰማሃለሁ›› አለችው፡፡

‹‹የምኖረው ለመፃፍ ነው፡፡ እየፃፍኩ ለመኖር ብችል ምንኛ በታደልኩ›› አላት፡፡

አይኖቻቸው እንደ ገና ተጋጩ፡፡

‹‹ከባልሽ ጋር ስትጋቡ እንዴት ነበራችሁ? አላት፡፡

@OLDBOOKSPDF



«እንዴት ማለት?» አለች፡፡

«ተፋትራችሁ ነው ወይ የተጋባችሁት? ማለቴ ነው» አለ፡፡

«ይመስለኛል» አለች፡፡ «በጣም ጥሩ ሰው ነበር፡፡ የሚያስብልኝም ይመስለኝ ነበር፡፡ ስድብ፥ ቁጣ፥ መጠጥ አያውቅም ነበር፡፡...»

«አሁንስ?» አላት፡፡

«ክፉኛ ተለውጦአል» ብላ ስታስብ ቆየችና፥ «አብሬው የኖርኩ ሰው አይመስለኝም፡፡ ፍፁም ተለውጦአል» አለች፡፡

«ምናልባት አንቺ ተለውጠሽበት እንደሆን? አብዛኛዎቻችን ስለ ራሳችን መለወጥ ብዙውን ጊዜ አናውቅም» አላት፡፡

«ፍፁም! እኔ የተለወጥኩበት ምንም ነገር የለም» አለች፡፡

«ታዲያ ምን ሆኖ ነው?» አላት፡፡

«እዲሱን ጠባይ ያመጣው ከአብዮቱ ወዲህ፥ በተለይም የገጠር መሬት፥ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ከተወረሱ ወዲህ ነው» አለችና፥ ፊትዋን በመሀረብ ካባበሰች በሁዋላ፥ «ከወላጆቹ የወረሳቸው የገጠር መሬቶችና ሶስት ቪላዎች ነበሩት፡፡ ብዙ ገቢ ነበረው፡፡ ችግር የሚሉትን አይቶ አያውቅም፡፡ የገጠር መሬት አዋጅ ሲወጣ ይህን ያህልም አልተጨነቀም፡፡ 'ሰስት መቶ ጭሰኛ ባጣ ችግሩ ምንድን ነው? ባቂላ እለቀ ቢሉ ፊስ ቀለለ ይባላል' ብሎ ትቶት ነበር፡፡ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጅ የወጣ ቀን ግን፥ ያለ ልማዱ ጥምብዝ ብሎ እኩለ ሌሊት ላይ መጣ፡፡ 'ምን ነው? ምን ነካህ? አልኩት፡፡ በተተግመደ ጨው ነግዶ ያፈራው ሀብት ሁሉ ሄደ! ምን ነካህ ብሎ ነገር! ከዚህ ወዲያ ምን ይምጣ! አባቴ አዋሉ ምንም ደንታ የለሽም፡፡ ገንዘብ ባይኖረኝ ኖሮ አንቺም ዞር ብለሽ አታዪኝም ነበር' አለኝ፡፡ እንዲህ ሲለኝ በጣም ነበር የተናደድኩት፡፡ ግን በብስጭቱ ላይ ብስጭት ላለመጨመር፥ ንዴቴን ውጬ፥ 'እኔ ለገንዘብ ብዬ አላገባሁህም፡፡ ለገንዘብ ደንታ እንደሌለኝ ታውቃለህ፡፡ እየሰራን እናገኛለን፡፡ ከጆሮ ደግሞ ጥሩ ነው' ብዬ፥ ላፅናናው ስሞክር፥ 'አንቺ ብሎ ለህዝብ አሳቢ፥ በማን ቤት ውስጥ ግን ሊኖር!

@OLDBOOKSPDF



ግን በሰራው ግን ሲገባበት! ደግሞ እየሰራን እንኖራለን! ያንቺ ብጣሻም ደሞዝ ነው እኔን የሚኖረኝ? ችግር ሲመጣ ልጆችሽን ጥለሽ ውልቅ እንደምትዪ ሴቶቹ አጫውተውኛ፣ እያለ ሲነተርከኝ አደረ፡፡ ተበሳጭቶ ይሆናል ብዬ ታገስኩ፡፡ ግን በዚያው አላቆመም፡፡ ነጋ ጠባ ንትርካችን ይኸው ሆነ፡፡ በጣም አዘንኩ፡፡ ለገንዘቡ ብዬ ከእሱ ጋር የምኖር አድርጎ ስለ ቆጠረኝ በጣም ነበር ያዘንኩት፡፡ በእሱ ግምት እኔ እሱ በገንዘቡ ከገዛቻው እቃዎች ውስጥ አንዱ ነኝ፡፡ ያሳዝናል›› ብላ ዝም አለች፡፡

ሲራክ ሰብለ ፊት ላይ ቦግ ያለውን ንዴት አነበበና፣ ‹‹አንቺ እንደምትዪው ሳይሆን፣ ምናልባት አንቺንም ጭምር የሚያጣ መስሎት ይሆናል፡፡ አትፍረጂበት›› ብሎ ሲያበቃ፣ ነገሩን በማራዘም፣ ‹‹እንዲህ አይነቱ ንትርክ በናንተ ቤት ብቻ የደረሰ አይመስለኝም፡፡ ስር ነቀል አብዮት የማይነካው ነገር የለም፡፡ የእንቅንቅር መሰረት ሲለወጥ ትዳር መናጋቱ አይቀርም፡፡ ብዙ ትዳር ሲፈርስ አይተናል፡፡ ግን እንደሚገባኝ የናንተ ኑሮ በጥቅም ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ የአብዮቱ አላማ ሲገባውና ያንቺንም ጥንካሬ ሲረዳ ይመለሳል፡፡ እድል ስጪው›› አላት፡፡

‹‹እስካሁን ሞክሬአለሁ፡፡ ደክሞኛል፡፡ አሁን እፎይ ብዬ የማርፍበት ጥላ ነው የምፈልገው፡፡ ብዙ መንገድ ተጉዣለሁ፡፡ ደክሞኛል›› ስትል፣ እንባዋ ዱብ ዱብ ይል ጀመር፡፡

የሚላት ነገር ጠፍቶት ዝም ብሎ ይመለከታት ነበር፡፡ እንባዋን ጠራረገችና፣ ‹‹የዚህ አብዮት መምጣት እንዳንዳችንን እንዲህ አይነት ሀዘን ላይ ቢጥለንም፣ ለመጭው ትውልድ በጣም ጥሩ ነው›› አለች፡፡

አሳቡዋን ለማወቅ ፈልጎ፣ ‹‹ለምን?›› አላት፡፡

‹‹ጥሩ ነው የምልበት ምክንያት ብዙ ነው›› ብላ ጀመረች፡፡

‹‹በሀብትና በዘር ላይ የተመሰረተ ጋብቻ ሲቀር፣ በባልና ሚስት መካከል የሚኖረው ፊውዳላዊ ጥርጣሬ ይቀራል፡፡ ሁሉም በእኩልነት ሰርቶ በሚኖርበት ሁኔታ ውስጥ የጋብቻ መሰረት ፍቅርና መተሳሰብ ይሆናል፡፡ ለገንዘቤ ነው . . . ለአጥንቴ ነው ብለሽ ያገባሽኝ፣ የሚል ርካሽ አስተሳሰብ አይኖርም፡፡ አይመስልህም? አለችው፡፡

‹‹የመጭው ትውልድ ኑሮ ያስቀናል›› አላት፡፡

 @OLDBOOKSPDF

‹‹በጣም›› ብላ ዝም አለች፡፡

አይኖቻቸው እንደ ገና ተጋጩ፡፡ ሲራክ ብልጭታ ታየው፡፡ ዝም አለ፡፡ ጥልቅ ዝምታ ዋጣቸው . . .

## ምእራፍ ፯

የሲራክ አሳብ አንድ አቅጣጫ ይዞ ሊሄድ አልቻለም፡፡ አሳቡ እንዳልተገራ ፈረስ እሻፈረኝ እያለ ዝም ብሎ ይፈረጥጣል – የትም ሳይደርስ፡፡ ስለ መፅሀፉ መቀደድ ወይም ማስታወሻውን ከያለበት ሰብስቦ እንደ ገና ስለ መፃፉ አልነበረም የሚያስበው፡፡ እንዲያውም ስለ ምን እንደሚያስብ አያውቅም ነበር፡፡

ፊቱ የተከመረውን ፋይል በግማሽ ልብ ያገላብጣል፡፡ የሚያነበው ነገር ምንም ሳይገባው ዝም ብሎ ያነባል፡፡ ከፋይሉ ውስጥ ሰብለ ድንገት ብቅ ትልበታለች፡፡ ትክዝ ብሎ ይቆይና በግማሽ ልብ ማንበቡን ይቀጥላል፡፡ ሰብለ ከፅሁፎቹ መካከል ድንገት ብቅ ትልበታለች፡፡ ትክ ብሎ እያየ ምንም አያይም፡፡ ቀልቡ ተሰልቦ ፍዝዝ፥ ድንግዝ ብሎ ሲቀር ሰብለ ከየትም ብቅ ብላ ፀሀያማ ፈገግታዋን ስታሳየው ፈገግ ይላል፡፡ ሲከፋት ፊቷን እንደ አየሩ ጭፍግግ ያደርገዋል፡፡

አንድ ተሳሳቢ እምጥቶ ከጠረጴዛው ላይ የዘረገፈው ፋይል ነበር ከቀን እንቅልፉ የቀሰቀሰው፡፡ በራሱ ሁኔታ ተገርሞ ራሱን መልሶ ታዘበ፡፡ የቢሮክራሲው መዘውር መንቀሳቀስ ጀምሮአል፡፡ ፋይል ይገባል፥ ይወጣል፡፡ የተሰሳቹ ፀሀፊዎች እርስ በርሳቸው ያወራሉ፡፡ ትእግስታቸውን ለመጨረስ የተቃረቡ ባለጉዳዮች ሌላ ምርጫ ስለሌላቸው የቀራቸውን ትንሽ ትእግስት ያስታምማሉ፡፡

ሲራክ ተገርሞ ለካ አእምሮ ካላየ አይን ብቻውን ባዶ ብልጭታ ኖሮአል? ብሎ አሰበና፥ አሁንም በራሱ ሁኔታ መልሶ በመገረም፥ ማን

@OLDBOOKSPDF



ነው እሱ፥ ስለ ሴት በተከታታይ አምስት ደቂቃ የሚያስብ ወንድ፥ ወንድ አይደለም ያለው? በማለት በራሱ ላይ ሳቀ፡፡ ሳቁን ለማፈን አልቻለም፡፡ እንደ እብድ ብቻውን ከት ብሎ ሳቀ፡፡ ግን የሰማው ሳቁን ሳይሆን ውስጣዊ ልቅሶውን ነበር፡፡ በዚያ ሳቅና ልቅሶ ውስጥ የደረሰበት ታላቅ ጥፋት፣ ሳይታወቀው ያደረበት ስቃይና ንዴት ቁልጭ ብሎ ታየው፡፡ የመዕሀፉ መቀደድ ድንገት እንደ ውስጥ እግር እሳት ያንገበገበው ጀመር፤ ግን ለምን ዋሸሁዋት? አለ፥ ራሱን በመታዘብ ብስጭት ብሎ፡፡

ሳቁን የሰሙ የስራ ጉዋደኞቹ አንገታቸውን ዞር ዞር እያደረጉ ተመለከቱት፡፡ ልባቸው የተስቀለው ባለጉዳዮች፣ ፍንክችም አላሉም፡፡ ከስራ ጉዋደኞቹ መካከል አንዱ በእድሜ ጠና ያለ መላጣ ሰው፥ «እንዲህ ካሳቀህ ቀልድ ለኛም ብታካፍለን?» አለው፡፡

ሲራክ ፊቱ የተከመረውን ፋይል በእጁ ገፋ ገፋ እያደረገ በረጅሙ አየር ወደ ውስጥ ስቦ በሃይል ተነፈሰና፣ «በራሴ ላይ ነው የሳኩት» አለው፥ ዝግ ባለ ድምፅ፥ ሳይፈልገው ጣልቃ በመግባቱ እየተነጫነጨ፡፡

«የትልቅነት ምልክት ነው» አለ ሰውዬው፣ መላጣውን እያከከ፡፡

ሲራክ ሳይወድ በግድ ከንፈሩን አላቆ፥ «እንዴት?» ሲል ጠየቀው፡፡

ጥያቄ ለማቅረብ አልፈለገም፡፡ መልስ ባያገኝ ምንኛ ደስ ባለው ነበር፡፡ በጣም የፈለገው ነገር ቢኖር ብቻውን መሆን ነበር፡፡ ከፋይሎቹ፥ ከሰዎቹ ራቅ ወዳለ ስፍራ ሄዶ ብቻውን መራራ ሳቅ ለመሳቅ፥ ጣፋጭ እንባ ለማፍሰስ ነበር የፈለገው፡፡ ብቸኝነት ናፈቀው፡፡

«በራሳችን ላይ መሳቅ ረስተናል . . .»

«ለምን ይመስልሃል?»

«መራራ ትግል በዝቶ ነዋ! ሌላ ለምን ይመስልሃል?»

«ከመራራው ትግል ባሻገር ደስተኛ የሰው ፊት አይታይህም?» ብሎ ዝም አለ፡፡

@OLDBOOKSPDF

«ሆሆሆ . . . ወዴት? ወዴት? በቀኝ እውለኝ ብለህ አልተነሳህም መሰለኝ!» አለው ሰውዬው፣ የሲራክን መነጫነጭ ተመልክቶ።

«ግራውን እውለኝ ብዬ ነው የተነሳሁት» አለ፣ ክሱ ፊቱን እያሳየው። ሰውዬው የሲራክን ክሶ ፊት አይቶ በመበሳጨት ፊቱ ካለው ፋይል ውስጥ ቆልማማ አፍንጫውን ቀብሮ ዝም ለማለት ቢሞክርም፣ አላስችል ስላለው ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ ሄዶ፣ ከሲራክ ጠረጴዛ ላይ በግዙፍ ቁመናው እያንገዋበበ፣ ሌባ ጣቱን ቀስሮ፣ «ስማ ሲራክ . . . እኔ በተፈጥሮዬ ከመሬት ተነስቶ የሚያኮርፍ ሰው ደስ አይለኝም . . .» ሲል፣ ሲራክ ያቋርጠውና፣ «ለማኩረፍ መብት የለኝም?» ይለዋል።

ሰውዬው መላጣውን እከክ እከክ አድርጎ ሌባ ጣቱን እንደ ገና በመቀሰር፣ «ሰው በቀና መንፈስ ሲያናግርህ ማኩረፍ ደግ አይደለም። አኩርፈሃል ያሉህ ለት ትስቃለህ፣ ስተሣል ሲሉ ደሞ ታኮርፋለህ። መጥኔ አቦ አብረውህ ለሚኖሩ ሰዎች!» ብሎት፣ መላጣውን እከክ እከክ አድርጎ፣ ትክዝ በማለት፣ «ይቅርታ አድርግልኝ። እንዳልከው ማኩረፍ መብትህ ነው። ብቻ፣ ብሩህ የሰው ፊት ማየት ደስ ስለሚለኝ ነው የተናገርኩህ . . .

«ሰው በዚህ አለም ሲኖር ብሩህ ፊት ከማየት ሌላ ምን ትርፍ አለው? ወደዚህ አለም ይዘን የመጣነው ነገር የለም። ከዚህ አለም ስንለይም ይዘን የምንሄደው ነገር አይኖርም። ብሩህ የሰው ፊት ማየት ለኔ የደስታ ምንጭ ነው። እሱቴ እንዲያው በሞቴ ትንሽ ፈገግታ ማንን ይጎዳል! . . .

«እየህ፣ ካባቴ የወረስኩ የገጠር መሬት — አስር ጋሻ ለም መሬት፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ሄዶአል። ይገኘው አልሄደ። ይገኘው አልመጣው፣ ፊቴን አጥቁሬ አላውቅም። ይህ ሁሉ ለኔ ዋጋ የለውም። አንድ ቀን እንኳን ለምን ብዬ ነው? ለኔ ዋጋ ያለው ብሩህ ገፅታ ብቻ ነው» ይለዋል።

ነገሩ ስለ መታው፣ ሲራክ ምልስ ብሎ፣ «ታዲያ እኔ ይህን ያህል ጨጓጓታም ነኝ እንዴ?» ይልና፣ ፈገግታ ብጤ ያሳየዋል።

«ይቅርታ አድርግልኝና በየሰአቱ፣ በየቀኑ ጠባይህ እንደ እስስት ይለዋወጣል። ግን አፍአዊ ሁኔታህ እንደዚህ ቢሆንም ርህሩህ ልብ ያለህ ይመስለኛል?»

@OLDBOOKSPDF



‹‹እንዴት ነው እፍአዊ ሁኔታዬ ባክህ? የሰው መስተዋቱ እኮ ሰው ነው፡፡››

‹‹እርኩም ይመስል እንገትክን ቀብረህ ነው የምትሄደው፡፡ ፊትህ ደስታ አይታይበትም፡፡ ሲያዩት ያሳዝናል፡፡ ግን እንዳልኩህ ልብህ ክፉት ያለው አይመስለኝም፡፡ ከሰው ስለማትቀላቀል ኩራተኛ ነው፣ ሰው ይንቃል ይሉሃል›› ብሎት፣ መላጣውን እከክ እከክ አድርጎ ትኩር ብሎ እየተመለከተው፣ ‹‹ከመፅሀፍ ሌላ ወዳጅ የለህም እንዴ?›› ብሎ ይጠይቀዋል፡፡

‹‹ጥሩ መፅሀፍ ከወዳጅ ይበልጣል፡፡››

‹‹አንተና ሰብለ አንድ ናችሁ . . .››

‹‹በምን?›› ይለዋል ደንግጦ፡፡

‹‹ከመፅሀፍ ጋር ተጣብቃችሁ በመኖር፡፡ ግን እስዋ እንኳን ልብ የሚያሞቅ ፈገግታ አላት›› ብሎ ሲያበቃ፣ ‹‹መፅሀፍክን እንብቤ በጣም ነበር የተደሰትኩት፡፡ እንደ ፊትህ ጭፍግግ ያለ አይደለም፡፡ ንፁህ ልብ እንዳለህ በመፅሀፍህ ነው ያወኩት፡፡ ጥፌ እንኩዋን ይደገማል፡፡ ሌላም በለን እንጂ?›› ይለዋል፡፡

‹‹እዳውን በተወጣሁት! ለማተሚያ ቤት እዳውን እየገፈገፍኩ ነው›› ይላል፣ ራሱን በብስጭት እየነቀነቀ፡፡

‹‹ምን ነው በብዛት ተሸጦ የለም እንዴ?›› ይላል ሰውዬው፣ እየተጠራጠረ፡፡

‹‹መሸጡንስ ተሸጦ አልቆአል፡፡ የመፅሀፍ ቸርቻሪዎች በልተውት ቀሩ፡፡ እኔን የቀረኝ እዳው ብቻ ነው . . .››

‹‹ስሙስ?››

‹‹ባዶ ስም ብቻውን ምን ያደርጋል?››

‹‹ለሰው ልጅ ስሙ እንጂ ዋናው ነገር፡፡ ከመቃብር በላይ ሌላ ምን ሊቀረው?››

@OLDBOOKSPDF

«ተወኝ አቦ» አለ ሲራክ፤ «ሰው የማስታወስ ችሎታው በጣም እጭር ነው፡፡ ከመቃብር ባሻገር ስላለው ጉዳይ ምን ተዳዩ፡፡ ያሰብኩን እዳ በከፈልኩና ስሙ በተረሳኝ» አለው፡፡

ሰውዬው መላጣውን እክኮና፥ «ደራስያን ስትባሉ ፍራንክ ባለቤ የምትዝቁ ይመስለኝ ነበር» አለ፡፡

ሲራክ ሳቀና፥ «እንዲህም እርጎ መዛቅ የለ! የማሳተሚያ ዋጋ ሰማይ ነው፡፡ አንባቢው ደግሞ የመፅሀፍ ዋጋ ርካሽ ካልሆነ አይገዛም - ያውም ቢገዛ፡፡ የተማረውም ከትምህርት ቤት ከወጣ በሁዋላ እንብዛም መፅሀፍ ዞር ብሎ አያይም፡፡ በአጠቃላይ የማንበብ ልምድ የለንም፡፡ የመፃህፍት ሪቂቅ እየገዙ የሚነግዱ ግለሰቦችም ትርፋቸውን እንጂ የደራሲውን ልፋት አይመለከቱም፡፡ ለጊዜው ባገራችን የመፃህፍት አሳታሚ ድርጅቶች በብዛት የሉም፡፡ ያሉትም በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው ሁሉ፥ ለአንድ ደራሲ የሚሰጡት የድርሰት አበል አስር በመቶ ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ የአንድ መፅሀፍ መሸጫ ዋጋ አንድ ብር ቢሆን፥ ለደራሲው የሚደርሰው አስር ሳንቲም ብቻ ነው፡፡ ይግረምህና ከአስርዋ ሳንቲም ላይ መንግስት ደግሞ አርባ በመቶ ይቆርጣል፡፡ እንግዲህ ደራሲው ቤቱ ይዞ የሚገባውን አስብ፡፡ የደራስያን መብረታታት ከህዝባዊ ባህል መገንባት ተነጥሎ ሊታይ ስለማይችል በጥብቅ ሊታሰብበት ይገባል» አለው፡፡

«ይህም አለ ለካ!» ብሎት፥ ባለ ጉዳይ የሚጠብቀው መሆን ስላየ እየተጣደፈ ወደ ጠረጴዛው ሲመለስ፥ ሲራክ በልቡ ግልግል ብሎ በእፎይታ ተነፈሰ፡፡

ባለ ጉዳዩን ቀና ብሎ አይቶ፥ «ፈገግታዎ ድንጋይ ያስፈልጣል» ሲል ሲራክ ሰምቶ ፈገግ አለ፡፡ ግን ፈገግታው ፊቱ ላይ አልቆየም፡፡ እባቡ ርጦ ወደ ሰብለ ተመለሰ፡፡

የተዋወቁበት ጊዜና ሁኔታ ትዝ አለው፡፡ አንደ ገና ባላብ ጓደና ጥላቸ ብሎ ሄደ፡፡ ከሁለት አመት በፊት ነበር፡፡ የመስሪያ ቤቱን ስራ አስኪያጅ ለማየት ፈልጎ ወደ ቢሮው ይሄዳል፡፡ የሄደበትን ጉዳይ አሁን አያስታውሰም፡፡ የቀደሙት ሌሎች ባለ ጉዳዮች ስለነበሩ ተራውን ለመጠበቅ ቁጭ ይላል፡፡ እና፥ ያያታል፡፡ እሰዋ ከምታነበው መፅሀፍ ቀና ብላ፥ የምታውቀው ይመስል ልብ የሚያሞቅ ፈገግታ ታሳየዋለች፡፡ ፈገግታዋ የሚጋባ በሽታ አይደንት ይሆንበታል፡፡ ከገንባርዋ ላይ ደፋ የሚለውን፥ ቡናማ ቀለም የተቀባውን ፀጉርዋን

@OLDBOOKSPDF



ሲመለከት አሻንጉሊት መስላ ትታየዋለች፡፡ ከጠረጴዛዋ ላይ ያስቀመጠችውን ዕጌ ረዳና ከንፈርዋን ያነፃፅራል፡፡

ደስ በሚል ሽቶ ክፍሉ ታጥኖአል፡፡ ምንዋ ላይ ይሆን ሽቶዋን የምታርከፈክፈው? . . . አንገርዋ ስር? ጡቶችዋ መሃል? ብብትዋ ወይስ ጭኖችዋ ውስጥ? እያለ ሲያስብ ይቆይና፡- ሁልጊዜ ቢሮ ውስጥ ታነቢያለሽ? ሲላት፡-

አንገትዋን እንደ እስክስታ ወራጅ እንክት፣ የታችኛውን ከንፈርዋን ጣል ታደርግና፡- ስራ ከሌለኝ፣ ብላ ስትመልስለት፡-

– መፅሀፍ ማንበብ ደስ ይልሻል? ብሎአት፣ ይቺ ልዩ ፍጡር መሆን አለባት በማለት ሲገረም፡-

– በጣም ደስ ይለኛል፣ ብላ፣ ስታነብ የነበረውን መፅሀፍ ስትዘጋ፡-

– ለምንድን ነው መፅሀፍ ማንበብ ደስ የሚልሽ?

አንገትዋን እንክት፣ ከንፈርዋን ጣል ታደርግና፡- እየሁ፣ ሰዎች መፃህፍት የሚያነቡት ለመደሰት ወይም ጊዜ ለማሳለፍ ወይም ትምህርት ለመቅሰም ነው፡፡ እኔ ግን የማነበው ራሴን ለመርሳት ወይም እንዴት ልበልህ? ከራሴ ውጭ ለመሆን ነው፣ ብላው ስታበቃ፡- ያንተንም መፅሀፍ አንብቤዋለሁ፣ ትለዋለች፡፡

– እረ? ብሎ የምትለውን ለመስማት ጉጉት ሲያድርበት፡-

– ጥሩ መፅሀፍ ነው . . .

– ምን ነው ጥሩ?

እንደኛ የመፅሀፉ ስም ደስ ይላል፣ ብላ፣ ትብላይ እንደ ጥላ በማለት የመፅሀፉን ስም በስሜት ትጠራና፡- ድንቅ ነው፡፡ ታሪኩ ደሞ ከስሙ ይበልጥ ደስ ይላል፡፡ ወጣትነት እንደ ጥላ ኮብልሎ ሲጠፋ አይታወቅም፡፡ ያሳዝናል፡፡ ሳነበው በጣም ነው ያዘንኩት፣ ትለዋለች፡፡

የመፅሀፉን ፍሬ አሳብ ለመጨበጥ በመቻልዋ በልቡ እያደነቃት፡-

 @OLDBOOKSPDF

— ግንኮ አላማዬ ለማሳዘን አልነበረም፣ ብሎ እንድትናገር ሲያደፋፍራት፡-

— አዎን፣ ይገባኛል፡፡ አላማውስ የወጣትነት ጊዜ ባዶ ህልማችንን፣ ደመ ፍሉነታችንን፣ ከንቱ ፍቅራችንን፣ ጉረኛነታችንን፣ ለምንም፣ ለማንም ደንታ የሌለን መሆናችንን ለማስታወስ ይመስለኛል፡፡ ብዙ የሚያስቅ ነገር ቢኖረውም፣ ለምን እንደሆነ አላውቅም፣ ሳነበው አዘንኩ፣ ብላ አይንዋን ወደ ሩቅ ስትወረውር፡-

— ሌሎች ግን የወሲብ (የሴክስ) ውዳሴ የሚል ትርጉም ነው የሰጡት፣ ሲላት፡-

— ቢሆንሳ? ብላ አንገትዋን እንከት፣ ከንፈርዋን ጣል በማድረግ፣ ወሲብ ከህይወት ተለይቶ አይታይም፣ ስትለው፡-

— ከህይወት ተለይቶ የማይታይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የህይወትም ምንጭ ነው፣ ሲላት፣ በግልፅነትዋ ተደፋፍሮ፡-

ከት ብላ ስትስቅ፡-

— እውነቱን ነው፡፡

— እንዴት? ብላ ስትጠይቀው፣ ሳቅ እያፈናት፡-

— ከየት ይመስልሻል ታዲያ የተገኘነው?

— እኔ እንጃ?

— ከፍቅርና ፍቅር ከሚያስከትለው ግንኙነት ነው፡፡ ፍቅር የህይወት ምንጭ፣ የህይወት ቅመም ነው፡፡ ለሰው ልጅ ፍቅር እንደ እንጀራ እንደ ውሀ፣ እንደ አየር ያስፈልገዋል፡፡ ስንት ሚሊዮን ሰዎች በየምሽቱ ፍቅርን ፍለጋ በጨለማ ውስጥ እንደሚደናበሩ ማሰብ ትችያለሽ? ስንቱ የፍቅር ርካታ አግኝቶ በደስታ ሲዋኝ? ስንቱ ፍቅር አጥቶ በደረቅ ሌሊት ሲያፈጥ፣ ሲያቃስት፣ ሁሉም ስለ ፍቅር ያስባል፣ ያደርጋል፣ ግን፣ ማንም ስለ ፍቅር መናገርና መፃፍ አይፈልግም፡፡ ጤናማ አመለካከት አይደለም፡፡ ፍቅር ህይወት ነው፡፡ የህይወት ምንጭ ነው፡፡ እኔ ስለ ፍቅር አዜማለሁ፣ እዘፍናለሁ፣ እፅፋለሁ፡፡ ሲላት፡-

እንደ ገና ከት ብላ ስትስቅና፣ ሌላ መፅሀፍ መቼ ነው የምትፅፈው? ብላ ትጠይቀዋለች፡፡

@OLDBOOKSPDF



– ጀምሬአለሁ፡፡

– ታድለሀ፡፡

– ማንበብ ትፈልጊያለሽ?

– አማኝቼ ነው!

ከዚያ ቀን ጀምሮ ዕፎ የጨረሰውን ምእራፍ ከሰር ከስሩ ሲሰጣት... የሚቀጥለውን ምእራፍ ለማንበብ እጅግ በጣም ስለምትጉዋጉዋ፥ ጉጉትዋ ሀይል ሆኖት ሲገፋፋው... እንብባ ስትጨርስ፥ – ይህ ደስ አይልም፡፡ ዝም ብሎ በቃላት ጨዋታ ነው፡፡ እዚህ ላይ ደግሞ ስለ ሴትዮዋ የጻፍከው ትክክል አይደለም፡፡ የሴቶች ስሜት በደንብ አልገባህም፡፡ ሴትዮዋ እንዲህ ከማለት ይልቅ እንዲህ ብትል ይሻል ነበር፡፡ ይሄኛው ክፍል ግሩም ነው፥ እያለች የምትሰጠው ግልፅ የሆነ ገንቢ ሂስ ሁሉ ወለል ብሎ ታየው፡፡

ተነስቶህ ብረር፥ ብረር የሚል ስሜት አደረበት፡፡ ግን ወዴት? ወደ እሰዋ? ምን ብዬ? እና ለምን? ብሎ አሰበ፡፡ ለምን አላያትም? የሚል ስሜት አደረበት፡፡ ባልዋ መፅሀፌን ቀዶ የለም? እኔም የእሱን ልብ እቀድለታለሁ! አለ በልቡ፥ ጥርሱን ነክሶ፡፡ ዞር አድርጎ ሲመለከተው ደግሞ ለቁጭት ብዬ? ፊፅሞ መሆን የለበትም የሚል የሀሊና ሙግት ገጠመው፡፡ የሀሊና ሙግት ያለችው ትዝ አለው፡፡ ታዲያ ለምን? ለምንድን ነው ከቃላቶቼ ውስጥ፥ ከአረፍተ ነገሮቼ መካከል እንደ መስቀል አበባ እየፈካች፥ እንደ መስቀል ምፍ ብቅ እያለች የምታስቸግረኝ? ለምን? ለምን? . . .

ከሩቅ የሚያሳዝን ሙዚቃ ተሰማው፡፡ – ልቤ የሚዘፍነው አሳዛኝ ሙዚቃ ይሆን? ወይስ የሰብለ ልብ የሚዘፍነው አሳዛኝ ሙዚቃ ነው ከሩቅ የተሰማኝ?

የትኛው እንደሆነ አላወቀም፡፡

– ወይስ የሁለታችንም ይሆን? . . .

@OLDBOOKSPDF

ሲራክ ቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ ከሰይጣን ቤት አጠገብ ከሴይቼንቶ ወርዶ በድሮ ቁራ መንገድ ቀኙን ይዞ ወደ ቤቱ ማምራት ጀመረ፡፡ ከብዶ የዋለውን ደመና ከላይዋ ላይ ገፋ የወጣችው ፀሀይ እናት ትበሳለች፡፡

የምሳ ሰአት በመሆኑ ሁሉም ቤቱ ለመድረስ ይጣደፋል፡፡ ሳይታወቀው ከቶኛ ምርመሮት ኖሮ፣ ሲራክም ርምጃውን አፈጠነ፡፡

ብርሌ ደት – ሰው በላው ጎንደሬ – ካንዲት ደሳሳ ሱቅ ደጃፍ ላይ አቀርቅሮ መኪና ይሰፋል፡፡ እጁ፣ እግሩ፣ አይኑ ባንድነት በስልት ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ቀኑን ሙሉ ከስፌት መኪናው ላይ ቀና ሳይል አሮጌ ልብሶችን ሲጥፍ፣ የህፃናት ጥብቆዎችን ሲቀድና ሲሰፋ ይውላል፡፡ ቀኑን ሙሉ ትንፍሽ አይልም፡፡ «ሰው በላው ጎንደሬ» የስፌት መኪናውን ቤት ካስገባ በሁዋላ፣ አፈር ድቤ ጠጅ ቤት አምሽቶ ከዚያ መልስ ነው፣ «ሰው በላው ጎንደሬ፣ የከሱ ሻጪዋ ልጅ፣ ሆኖተ ኩስታራ፣ ጠጥቶ ገዳይ ደመ መራራ፣ ያፈር ዱቤ ጠጅ ቤት፣ ከም ከም – ጠጥቶ የጠገበሽ የለም – ሆይ ሆይ! በአብዮቱ አምላክ፣ በደርጉ!» እያለ አንዘባሳ መሆን የሚጀምረው፡፡

ሲራክ እጅ ነስቶ አለፈ፡፡

ከቤቱ አጠገብ ሲደርስ ሲል እንካሳው፣ ጋሼ ማንደፍሮ፣ ምርኩዙን ተደግፎ እንጥር፣ እንጥር፣ ቅጭ እያለ መጥቶ «ቲቸር» አለው፡፡

ለምን ቲቸር ብሎ እንደሚጠራው ፈፅሞ አይገባውም፡፡ ምክንያቱንም ጠይቆት አያውቅም፡፡

«ጋሼ ማንደፍሮ፣ ስፈሩ እንዴት ነው?

«አድሃሪ ሁሳ!»

ሲራክ ስቆ ሳንቲም ሰጠው፡፡

«የጠላቹ ጌታ» ብሎት፣ በምርኩዙ እንጥር፣ እንጥር፣ ቅጭ እያለ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ «አድሃሪ ሁሳ ይወድማል! በቀይ ሽብር ይመታል!» ይል ጀመር፡፡

@OLDBOOKSPDF



አቶ አያርፍም፡፡ እንካስ እግሩ አያርፍም፡፡ ሁልጊዜ እንደ ተናደደ የሚኖር ሰው ነው፡፡ የማያውቁት አብድ ነው ብለው ከሩቅ ይሸሹታል፡፡

«አድሃሪ ሁላ!» ብሎ እንጥር፣ እንጥር፣ ቅዋ እያለ ይሮጥባቸዋል፡፡ ማንደፍሮ ልመና አያውቅም፡፡ እኔ በጉልበቱ — በማስፈራራት ነው የሚኖረው፡፡

የሰፈሩን ልጆች አይወድም፡፡ «ጋሼ ተራማጁ» እያሉ ስለሚቀልዱበት ሮጦ አይደርስባቸው ነገር፣ ሲያያቸው እርር ይላል፡፡

ሲራክ ወደ ቤቱ ከምታስገባው ኮረኮንች መንገድ ታጠፈ፡፡ የሃጂ ሙስጠፋ ቤት ከራማ ፀጥ፣ እረጭ፣ ለጥ ብሎአል፡፡ ከቆርቆሮ አጥራቸው ላይ በትላልቅ ቀይ ፊደል የተፃፈው፣ «ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይመታል» የሚለው ፅሁፍ አልጠፋም፡፡ ደብዘዝም አላለም፡፡ ቦግ ብሎ ይታያል፡፡ ቤት ተኝተው ምንድን ነው ከራማውን የሚለምኑት? እኔ እንደሆንኩ አልወጣ አለ በልቡ፡፡

«እንደምን ዋሉ?» አሉት አይኑ ሰውሩ ለማኝ ባርኔጣቸውን እንስተው፡፡ የሰፈሩን ሰው በድምፅ ብቻ ሳይሆን በኮቴውም ጭምር ለይተው ያውቁታል፡፡

«ደህና፣ ደህና፡፡ እርስዎስ?»

«ለሱ ምን ምስጋና ይብቃዋል? እንደምታየኝ አለሁ፡፡፡»

ሳንቲም ሰጣቸው፡፡

«እሜቴ ደህና ናቸው? ተሻላቸው? አሉት፡፡

«ደህና ናት፡፡፡»

«በሽታው ጠንቶአል፡፡ ምን ጤና አለ?»

ለማኙ ስለ እያንዳንዱ ቤት የማያውቁት ነገር የለም፡፡ እንዴት እንደሚያውቁ እግዜር ይወቅ ብቻ፡፡ አላፊ አግዳሚውን ሰሌን ባርኔጣቸውን እያነሱ እጅ ከመንሳት ሌላ ብዙ ጊዜ አፍ አውጥተው አይለምኑም፡፡ የልብ ኩራት አላቸው፡፡

@OLDBOOKSPDF

ሲራክ እውሩን ለማኝ እጅ ነስቶ እልፍ ከማለቱ፣ ሃጂ ሙስጠፋ ከቤታቸው ደጃፍ ላይ ቆመው ይጠብቁት ኖሮ፤ በረጂም ቁመናቸው በከፍተኛ አክብሮት እጅ ነሡትና ቤት እንዲገባ ጋበዙት፡፡

ከቤታቸው ጥላ ስር ጠጋ ብሎ ቆመ፡፡ ሀሀይዋ እናት ትብላለች፡፡ ሃጂ ሙስጠፋ በጣም ረጂም፣ ጠይም አፍንጫቸው እንደ ሸምበቆ ቀጥ ብሎ የሚወርድ፣ ጆሮዎቻቸው ትላልቅ፣ አይኖቻቸው ትናንሽ፣ ሸበቶ ሽማግሌ ናቸው፡፡ ጠቅላላ ገፅታቸው ከእንጉሬ እንደኛው ገፅታ ጋር ተማታበት፡፡ ለምን እንደሆነ ባይገባውም፣ እውነታን እንደ አንድ አይነት ቀልድ አድርገው የሚመለከቱ ሆነው ነው የታዩት፡፡

‹‹የላኩት ደብዳቤ ደረሰዎት?›› አሉት፣ ስልል ባለ ድምፅ፣ ትናንሽ አይኖቻቸውን ስለምልም እያደረጉ፡፡

‹‹አዎን ደርሶኛል፡፡››

‹‹ብእላህ፣ ታዲያ ምን ፈረዱኝ?›› አሉት፣ ሴት፣ ቡናና ሱካር ያበለዘውን ፍልጣ ፍልጥ ጥርሳቸውን እያሳዩት፡፡

በዚች የጭቁኖች ጉሮኖ በሆነችው ተረት ሰፈር ውስጥ የጀመርኩትን መፅሀፍ እስከጨርስ ይታገሱኝ፣ ከዚያ በሁዋላ እርስዎ ሳይጠይቁኝ እኔ ራሴ ቤትዎን ለቅቄ እሄዳለሁ ብሎ የእውነቱን ሊነግራቸው አስቦ ነበር፡፡ ግን፣ ሃጂ ስለ ድርሰት ምን ይገባቸዋል? ከሰው ልጅ ኪነታዊ እድገት፣ ለደራሲያን ከያኒ ስሜት ምን ደንታ አላቸው? በማለት፣ ‹‹ቤት አላገኘሁም፡፡ ባሁኑ ጊዜ ቤት ማግኘትም አስቸጋሪ ነው›› ብሎ የተለመደውን ምክንያቱን አቀረበላቸው፡፡

ሃጂም አይኖቻቸውን ስለምልም አድርገው ያው እንደ ተለመደው፣ ‹‹ሰባት መቶ ብር እያገኙ፣ የመንግስት ሰራተኛ ሆነው እንዴት የተሻለ ቤት ያጣሉ? ቤቱም ሆነ ሰፈሩ ለእርስዎ ክብር አይሆንም፡፡ እኔ መቃብር አፋፍ ላይ የቆምኩ አንድ ድሀ ሽማግሌ ስበደል ምን ደስ ይልዎታል? በአላህ ብለው ቢለቁልኝ›› አሉት፡፡

‹‹ሃጂ›› አለ ሲራክ፣ ‹‹እርስዎ የት እንደምሰራ፣ ምን እንደምሰራ፣ ምን ያህል ደሞዝ እንደማገኝ የሚያውቁትን ያህል፣ እኔም ስለ እርስዎ በመጠኑም ቢሆን አውቃለሁ፡፡ እርስዎ እንደሚሉት ምስኪን አይደሉም፡፡ ሰስት ቦታ ላይ ሱቅ አለዎት፣ የቤት እኖጅ

@OLDBOOKSPDF



ሲታወጅ የመረጡት እኔ የምኖርበትን ቤት ሳይሆን አሁን ያሉበትን ቤት ነው፡፡ ሀጉ አይፈቅድልዎትም፡፡ ሳየው የሚሰሩት ሻጥር ነው፡፡ እዩ ሃጂ፣ የቤት ችግርን የሚፈጥረው እንዲህ ያለው ሻጥር ነው፡፡ ቤት አከራይ የነበሩ ብዙ ሰዎች ትርፍ ቤታቸውን በልዩ ልዩ ዘዴ ስለያዙት የቤት እጥረት ተፈጥሮአል፡፡ በዚህ የተነሳ ብዙ ሰዎች ከነቤተሰባቸው በሆቴል ቤቶች ውስጥ ይሰቃያሉ፡፡ ከዚህ የባሰው ስቃይ ደግሞ የደባልነት ኑሮ ነው፡፡ የደባልነት ኑሮ ሲኦል ነው፡፡ ባል ከሚስቱ ጋር ሊገናኝ አይችልም፡፡ የደባልነት ኑሮ ሰላምና ነፃነትን ይነፍጋል፡፡ ባለፈው ጊዜ በደባልነት አብረው የሚኖሩትን ህፃናት በመጥረቢ ፈልጦ ስለጨረሳቸው ሰውዬ አልሰሙም? የደባልነት ኑሮ የመጨረሻ አስከፊ ገፅታው ይኸው ነው፡፡ ቤቱን ለቀህ ደባልነት ግባ፣ ቢሻህ የትም ሄደህ ውደቅ እንደማይሉን አውቃለሁ፡፡»

«ምን በወጣዎት፡፡ እላህ ጠላትዎን ይጣለው!» አሉት፡፡

«ታዲያ ምን ሁን ነው የሚሉኝ?»

«ብእላህ ብለው ቢለቁልኝ፡፡»

«ህጉም'ኮ አይደግፍዎትም፡፡»

«ስለ ህጉ ለኔ ቢተውልኝ፡፡»

«ብለቅልዎት ምን ያደርጉበታል? አያከራዩት ወይም አይኖሩበት» አላቸው፡፡

ሃጂ አይኖቻቸውን ስልምልም አደረጉ፡፡ ትላልቅ ጆሮዎቻቸው ደበልጥ ትልቅ መስለው ታዩት፡፡ ባላብ ጭልጥ ብለው ሄደው ቆዩና፣ «ሚስት ላገባ አስቤአለሁ» አሉት፡፡

«ቤት ያሉት ሁለት ሚስቶችዎስ?» አላቸው እየተገረመ፡፡

«እነሱ መውለድ አቁመዋል፡፡ ቤቱን የምፈልገው ላዲስዋ ሚስቴ ነው፡፡ ቤቱም የተያዘው በእስዋ ስም ነው፡፡ በእኔ አይደለም፡፡ እርስዎ ኖት እንቅፋት የሆኑብኝ፡፡ እንቅፋት የሆኑት ለኔ ብቻ ሳይሆን ለእላህም ነው» አሉት፡፡

«እንዴት?» አላቸው፡፡

@OLDBOOKSPDF

‹‹ለእሳሁ ስል ነው፡፡››

‹‹እኮ?››

‹‹ቤቱን ቢለቁልኝ ቶሎ ሌላ ሚስት አግብቼ ለእሳሁ ተጨማሪ ፍሶች አተርፍ ነበር፡፡››

‹‹እና?››

‹‹ቢለቁልኝ ለእሳሁ ብለው፡፡››

‹‹ትገርሙኛላችሁ እናንተ እስላሞች›› አላቸው፡፡

‹‹እንዴት?›› አሉት፡፡

‹‹እኔ አንድ ሚስት ማኖር አቅቶኛል፡፡ እርስዎ በስተርጅና ሰስተኛ ለማግባት ይፈልጋሉ?›› አላቸው፡፡

ሃጂ፣ ጫት ያበለዘውን ጥርሳቸውን እያሳዩት፣ ‹‹እኛስ በግልፅ ነው፡፡ እናንተ ዘንድ እለ እንጂ ከምታገቡት በሁዋላ የተደበቀው ጉድ የሚወጣው›› አሉት፡፡

‹‹የምን ጉድ?››

‹‹ፍርድ ቤት ወይም ጡረታ ከሚሸን ብቅ ብለው ጉዱን ባየ ሚስት ነን እያሉ ሰማንያቸውን ይዘው የሚመጡት ሴቶች ቁጥር እይጣል ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ እንደኛ በህግ ብታረጉት እሳሁ ደስ ይለዋል›› ብለውት ሲያበቁ፣ ወደ ዋናው ጉዳያቸው መለስ ብለው፣ ‹‹በእሳሁ ብለው ቢለቁልኝ›› አሉት፡፡

‹‹እርስዎም ስእሳሁ ብለው ትንሽ ይታገሱኝ፡፡››

‹‹እስከ መቼ?››

‹‹አንድ መፅሀፍ ጀምሬአለሁ፡፡ እሱን እስከጨርስ ድረስ፡፡››

‹‹የምን መፅሀፍ?››

‹‹ልብ ወለድ መፅሀፍ ነው . . .››

@OLDBOOKSPDF


«ይቀልጻሉ ልበል!»

«ቀልዴን አይደለም፡፡»

አብድ ነው ወይስ ጤና እንደማለት በትናንሽ አይኖቻቸው ትኩር ብለው ተመለከቱትና፣ «ታዲያ መቼ የሚጨርሱት ይመስልዎታል?» አሉት፡፡

«አንድ አመት ወይም ሁለት . . . እኔ እንጃ፡፡ አሳቡ እንደ ተባካልኝ ነው» አላቸው፡፡

«ለምን ሌላ ቦታ ሄደው አይሰሩም?»

«ሰሜቱ ይበላሽብኛል፡፡ እዚሁ እንደ ጀመርኩት እዚሁ መጨረስ አለብኝ፡፡ ይታገሱኝ፡፡ አሳህ እንደ ሆነ ወደ ፊት ለሚወለዱ ቀርቶ ላሉትም ፍትህ ይጎድለዋል» አላቸው፡፡

ሃጂ ትላልቅ ጆሮአቸውን ማመን እያቃታቸው፣ ሲራክ ቤቱን የማይለቅበት ምክንያት አልገባ እያላቸው፣ በልባቸው አብድ ነው ወይስ ጤነኛ፣ ከዘመኑ ነው ወይስ ከእኔ፣ ወይስ ከእኔ ሌላ የሚፈልገው ነገር ኖሮት ይሆን? እያሉ በመጨነቅ፣ «በአላህ ብለው» አሉት፡፡

ጥሎአቸው ሄደ፡፡

ሲራክ አልፍ ሲል ያ መከረኛ ውሻ ሲያላዝን ሰማ፡፡ ተገርሞ ቆም አለ፡፡ ራሱን ነቀነቀና ራመድ አለ፡፡ ነገሩ ከንከኖት እንደ ገና ቆመ፡፡ ወደ ቤቱ መግባት ትቶ ውሻው ከሚያላዝንበት ግቢ ዘው ብሎ ገባ፡፡

ውሻው ከቤቱ ፊት ለፊት በሁዋላ እግሩ ተቀምጦ ወደ ላይ በማንጋጠጥ ሲያላዝን ሲል ነው የደረሰበት፡፡ ጥቁር ወደል ውሻ ነው፡፡ በማንጋጠጥ ሲያላዝን ሲል ነው የደረሰበት፡፡ ብልጣ ብልጥ ደረቱና ጆሮዎቹ ላይ ነጭ ጠጉር ጣል ጣል አድርጎበታል፡፡ ብልጣ ብልጥ አይኖች አሉት፡፡ የሚናከስ መስሎ ጠንቀቅ ብሎ ቆመ፡፡ ፊት ለፊት ተያዩ፡፡ ውሻው ቀስ ብሎ በደረቱ ተኛ፡፡

«ቤቶች! ቤቶች!» አለ ሲራክ፣ በተጠንቀቅ ቆሞ፡፡

«አቤት፡፡»

 @OLDBOOKSPDF

አንድ አጠር ያለች ጠይም ሴት ከቤት ውስጥ ብቅ አለች፡፡ አይን የሚወጋ ቀይ ሻሽ አስራለች፡፡

‹‹ምንነው ደህና?››

ድምፅዋ ጆሮ ይወጋል፡፡

‹‹የለም፡፡ ደህና ነው›› አለ፣ የመጣበት ጉዳይ መልሶ እያስገረመው፡፡ ከመጣ በሁዋላ ምንም ሳይል ተመልሶ ለመሄድ የሚያስችለው ዘዴ ጠፍቶት ዝም ብሎ ቆመ፡፡

‹‹ወይዘሮ ፅጌ ደህና አይደሉም እንዴ?››

‹‹ደህና ናት›› አለ፣ ስላወቀችው ተደስቶ፡፡

‹‹ያማቸዋል አሉ›› ብላ፣ ምን አመጣው? እያለች በመገረም፡፡

‹‹ይግቡ እንጂ ከፀሀይ ላይ›› አለችው፡፡

‹‹የለም አልገባም፡፡ እቸኩላለሁ፡፡››

‹‹ታዲያ በዚህ ጠራራ ፀሀይ፣ የደመና ግላጩ ጥሩ አይደለም፡፡››

‹‹ምንም አይደለም፡፡››

‹‹ታዲያ ምንነው ደህና መጡ? አሁን ቢገቡ ምናለበት?››

‹‹የለም በእውነት፡፡ የመጣሁት. . . እ. . . እንዲያው ይህ ውሻ ሁልጊዜ እያሳዘነ ስላስቸገረኝ ነው›› አለ፡፡

አቤቱታ ለማቅረብ ነው እንዴ የመጣሁ? ብሎ ራሱን ታዘበ፡፡ እብድ ወይስ የመንደር ቂል አድርጋ ትቆጥረኝ ይሆን? ብሎ አሰበ፡፡ ብልጥ አይኖችዋ አሳፈሩት፡፡

ከንፈርዋን መጠጠችና፣ ‹‹እኔም በችሎ ማደር እንዳዘንኩ ነው ያለሁት፡፡ እሱ ባሳዘነ ቁጥር ሳለቅስ እኖራለሁ፡፡ ባሳዘነ ቁጥር ቤተሰቡ ሁሉ ያለቅሳል . . . ይህንኑ ማሳዘኑን ጠልተን ካንድም ሁለት ጊዜ ቁራ ወስደን ጥለነው ነበር፡፡ ስንጥለው ከተሳፈርንበት አውቶቡስ ቀድሞ

@OLDBOOKSPDF



መጥቶ ቁጭ ብሎ ሲያሳዝን እናገኘዋለን፡፡ እኛም የሉ ነገር ግራ ገብቶናል፣ እባክዎን›› አለች፡፡

ካንጀትዋ ያዘነች መሆንዋ ተሰማውና፣ ‹‹ታሪክኛ ውሻ ነው፡፡ እኔ እየራበው የሚያሳዝን መስሎኝ ነበር፡፡ ሳየው ወደል ነው›› አለ፡፡

‹‹ምን ይርበዋል!›› ብላ ቆየችና፣ ‹‹ባለቤቴ ከሄደ ጀምሮ ይኸው እንዳሳዘነ ነው ያለው፡፡ በፊት ባለቤቴ ከስራ ሲመጣ መንገድ ጠብቆ ነበር የሚቀበለው፡፡ ባለቤቴም ቢሆን ችሎ ማደርን ሳያበላው እህል ቢሞት አይቀምስ ነበር›› አለች፡፡

አይኖችዋ እንባ ሲያቀሩ ታዩት፡፡ አንጀቱ በሀዘን ሲላወስ ተሰማው፡፡ ዞር ብሎ ችሎ ማደርን ተመለከተ፡፡ ጠላትነቱ ባንድ ጊዜ ከልቡ ጠፋ፡፡

‹‹ባለቤትዎ የት ነው የሄዱት?››

‹‹ጦር ሜዳ››

የሲራክ ልብ በድብልቅ ተነካ፡፡ የደመና ግላጭ ፀሀይ እናት ትፈልጋለች፡፡ ግን፣ ከምንም አልቆጠረውም፡፡ እግሩን መትከል የጀመረ ህፃን ልጅ ድክ ድክ ሲል መጥቶ የእናቱን ቀሚስ ጭምድድ አድርጎ በመያዝ ሲራክን ይመለከት ጀመር››

‹‹ልጅዎ ነው?››

‹‹አዎን፡፡ አባቱ ሲሄድ ገና የሶስት ወር ህፃን ነበር›› አለች፣ ራሱን እየደባበሰች፡፡

ሲራክ ስሜት ፈንቅሎት ህፃኑን ብድግ አድርጎ ሳመው፡፡ ህፃኑም አልፈራውም፡፡ አንገቱ ስር ሽጉጥ አለ፡፡

‹‹አባቱ በየትኛው ግንባር ነው የዘመቱት?››

‹‹በፊት የዘመቱት በምስራቅ ጦር ግንባር ነበር፡፡ ከፈዲስ ጀምሮ ጅጅጋ ድረስ እየተዋጋ ዘልቆአል፡፡››

@OLDBOOKSPDF



ጀግናው የናት እገሩን ጥቁር አፈር መስሎ ካራ ማራ ተራራ ላይ ከነሙሉ ትጥቁ ቆሞ የማርዳን ሸለቆ እንደ ንስር አሞራ ወደ ታች ሲመለከት ታየው፡፡

‹‹እና፣ አሁንስ?›› አለ፡፡

‹‹አሁን ደግሞ ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ተዛውሮአል፡፡ በምፅዋ እድርጎ ነው ከረን የገባው፡፡››

በጀግናው ደም በደበሏጥ የቀላው የቀይ ባህር ሞገድ ወድቆ እየተነሳ በፊቱ አለፈ፡፡ ዶጋሊ ላይ የወደቁት ሰማእታት አጥንት ከጀግናው የተበሮ ጉድጉዋድ ውስጥ እየለመለሙ ወጥተው እንደ እንጉዳይ በየስፍራው ብቅ ብቅ ሲሉ ታዩት፡፡ እልልታቸው ተሰማው፡፡ የጀግናውን ጉዞ በአይኑ ሀሊናው ተከተለ… ወጣ ጀግናው ተራራውን ወጣ፣ በደም እየዋጀ፣ ደሙን እየጠጣ… ወረደ ጀግናው ተራራውን ወረደ፣ እየፎከረ፣ እያቅራራ ዘርቶ እያጨደ… ወረደ… ወረደ፣ መግደል እንደ ለመደ፡፡ ተግ ብሎ ታየው ጀግናው ከከረን — ምሽግ ላይ ያንድነት አርማውን ይዞ ቆሞ — ከምሽጉ ባሻገር ናቅፋንና ቃሮራን ከሩቅ እየተመለከተ — ዳር ድንበሩን ባይኖቹ ሲቃኝ፡፡ ሲራክ ድንገት የልብ ኩራት ተሰማው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሀፍረትና የሀሊና ወቀሳ እደረበት፡፡ ጀግኖች በጦር ሜዳው በየደቂቃው ከሞት ጋር ተፋጠው፣ ሌሎች በክብርና በነፃነት እንዲኖሩ እነሱ ሲሞቱ፣ የመንደር ደራሲ ሆኖ ያለ አላማ እያውደለደለ መኖሩ አሳፈረው፡፡ ለዚች አገሩና የምታሳዝን ጎድቀሞላ እናት አገር እኔም ከጦር ሜዳ ጀግኖች ጋር ተሰልፌ በሰራሁ በሚል ስሜት ልቡ ተቃጠለ፡፡

በጦር ሜዳ ከጀግናው ጋር የጠላትን ምሽግ ጥሶ ለመግባት፣ ‹‹አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት!›› እያለ ሲሮጥ ታየው፡፡ ያቺ የሰው ልክ የሚታወቅባት ወሳኝ ደቂቃ ጆሮው ውስጥ ሀይወት . . . ሞት . . . ሞት . . . . ሀይወት እያለች ስትሄድ ተሰማችው . . .

ባሩድ ሸተተው፡፡ መድፉ ሲያጉዋራ — መትረየሱ ሲንጣጣ — ጥይቱ ሲዘራ — ቦምቡ ሲፈነዳ — እይሮፕላኑ ከላይ ሲያንዣብብ — ታንኩ ከታች ሲርመሰመስ — ሰራዊቱ ሳንጃውን ተክሎ ሲተም — ሲነድ — ሲጤስ — ሲያጠቃ — ሲጋይ — ሳንጃው ሲሞሻለቅ — ጀግና ወድቆ ውሀ ውሀ ሲል — ጉዋደኛውን፣ ‹‹ስለ ወንድ ልጅ ጨርሰኝ አትለፈኝ››

@OLDBOOKSPDF



ሲል – የህይወት ሀቅ በገሀድ ስትከሰት – ሲታወቅ የወንድ ልጅ ልኩ – ታየው፡፡

የህይወትን ሀቅ መግለፅ ምነው በቻልኩ! አለ በልቡ፡፡

‹‹አይሰቶልዎትም?›› አለ፥ ከሀሳቡ ሲመለስ፡፡

ሴትዮዋ ግራ ገብቶአት ትክ ብላ ትመለከተው ነበር፡፡

‹‹መጀመሪያ እንደ ሄደ ሰሞን በሚሰራበት ማተሚያ ቤት በኩል ደብዳቤ ይደርሰኝ ነበር፡፡ አሁንስ ድምፁ ከጠፋ ቆይቶአል፡፡ ለዚህ ነው ችሎ ማደር ባላዘነ ቁጥር የምንላቀሰው›› አለችና፥ ከንፈርዋን መጠጠች፡፡

‹‹የጀግና ሚስት አታለቅስም›› አላት፡፡

ጀግናው በድል አድራጊነት ሲመለስ፥ ‹‹ጉሮ ወሸባዬ. . .›› እያለች ስትዘፍን፣ ጎረቤቱ ሁሉ ተሰብስቦ፥ ‹‹እንዲያ እንዲያ ሲል ነው ግዳዬ. . .›› በማለት እየተቀበላት እልልታው ሲቀልጥ ተሰማው – ታየው – አሁን አሁን አለው – ከጀግናው አይን የድል ርችት ተተኩሶ በልዩ ልዩ ቀለማት እያሸበረቀ ሲፈንጥቅ ታየው፡፡

ሀሣኑን በልዩ ስሜት እቅፍ አድርጎ ሳመውና ኪሱ ውስጥ ያለችውን አምስት ብር አውጥቶ ሰጠው፡፡

እናትዮው፥ ‹‹አንዴ! ፈፅሞ አይሆንም!›› ብላ፥ ከህፃኑ እጅ ብሩን ነጥቃ ለመመለስ ትታገል ጀመር፡፡

‹‹ለከረሜላ መግዣ ነው፡፡ ምን ሆኑ? እረ እባክዎን›› ሲላት፥ ‹‹ይሙት ብያሁ . . . በእውነት ችግር የለብንም. . . እድሜ ለቀበሌው ህዝብ፡፡ በደንብ ይዞናል፡፡ አባቱን በደህና ይመልሰው እንጂ ምን ጎድሎን›› እያለች ስትከራከረው፥

‹‹ምን ሆኑብኝ? ያባቱ ትግል የኔም ነውኮ›› ብሎ፥ ብሩን በግድ ከልጁ ኪስ ከተተና እየተጣደፈ ወጣ፡፡

በሩ ጋ ሲደርስ ችሎ ማደር እንዴ እላለሁ፡፡ ዞር ብሎ ተመለከተውና የጀግና ውሻ አያላዝንም አለ፤ በልቡ፡፡

 @OLDBOOKSPDF

«እግዜር፥ የልጅዎ አድባር፥ የልጅዎ ጥላ ያርግዎት» ስትለው ከሩቅ ሰማት። ምን ነው ብዙ ገንዘብ በኖረኝ ብሎ ተመኘ።

ቤቱ ሲገባ ዮሀንስን ለመሳም ፋታ አላገኘም።

«ምን ነው እንዲህ አረፈድክ፥ ልጄ» አለች ፅጌ።

«ዶኬው በረደ እንዴ?» አላት፥ ዮሀንስን እየሳመ።

«ይርባቸዋል ብለህም አታስብም?»

ሲራክ ካልገባ ፅጌ ብቻዋን እህል አትቀምስ – እኔ እንደ ሴቱ ብቻዬን መብላት አልወድም፣ ከጉሮሮዬ አይወርድልኝም። ከትፎውን፥ ገንፎውን፥ እጥሚቱን ሲሉ ሁለሙ፥ ያለ እህል ይኖሩ ይመስል፥ ባል ፊት የማይቀምሱ መስለው የሚቀርቡት ሴቶች ይገርሙኛል። እበስሉ ገበርኩ እቱ ትላለች፣ እዘውትራ።

ቢላዎ ተስሎ ቀርቦአል። ጥቁር ዶሮ ከእሊጋው እግር ላይ ታስራለች፥ ርጥብ ሳር ከወለሉ ላይ ተጎዝጉዞአል። ውባንቺ የወደቀ ቁራሽ እንጀራ አይታ ሳይሆን አይቀርም፥ «ዋ ካይ'ኸ ጡር» በማለት እያጉረመረመች አሳት በገል ይዛ መጥታ ከገበቴው ጎን አኖረች።

ሲራክ ሰአቱን እየና፥ «ለምሳ ዶሮ ኅርድ ነው እንዳትዪኝ ብቻ» አላት ፅጌን።

«ዶሮ ማታ» አለችው።

«ዶሮ ማታ፥ አሁን ዶኬውን ቆጥ» አላት እየሳቀ።

«ቀልዱን ተወውና ዶሮዋን እረድልኝ» ብላ በገል ከቀረበው እሳት ላይ እጣን በተነች።

ውባንቺ ዶሮዋን ከፈታች በሁዋላ ይዛ ቀረበች። ፅጌ ተስሎ የተቀመጠውን ቢላዎ እንስታ ሰጠችውና ልጇን ተቀበለችው። ዮሀንስ ካባቱ ለምን ተለየሁ በማለት ጩኸቱን ያቀልጥ ጀመር።

«እረ ኢዲያ!» አለችው ተናዳ።

@OLDBOOKSPDF



‹‹እኔን ከመጠበቅ አንቺ ለምን አታርጂአትም ኖርአል? አላት፥ ደሮዋ ይዞ፡፡

‹‹በስማብ›› አለች፡፡

‹‹የምን በስማብ ነው? ሴት ዶሮ አታርድም ያው ማን ነው? አይ አራታውያን! ደ'ሞ በስማብ ብዬ አሳርድ፡፡ በስመ ሆድ ብዬ ነው፡፡ አንገቱ ላይ ክር ያሰረ ወደ ፊት ይኖራል ብለሽ አታስቢ፡፡ ይልቅ ካሁኑ ብትለማመጂው ይሻላል፡፡ መጣፉም ቢሆን ወደ ሆድ የሚገባ አያረክስም ብሎአል›› አላት፥ ዶሮዋን እንጠልጥሎ፡፡

‹‹ጉድ ነው'ኮ›› አለች፡፡

‹‹ምንድን ነው ጉዱ?››

‹‹ሴት ዶሮ ትረድ ማለት፡፡ ይልቅ በነፍስ አትጫወት፡፡ ቶሎ አረዳት›› አለችው፡፡

‹‹ማረድ አለብሽ፡፡ ሴቶች ዶሮ አያርዱም ማለት እጉል እምልኮ ነው፡፡ ካጉል እምልኮ መላቀቅ አለብን፡፡ እውነቴን ነው›› አላት፡፡

‹‹ወንዶች ሌላም ይገድላሉ፥ እቴ! የምን መንቀጥቀጥ ነው ደ'ሞ ለዶሮ?››

‹‹እኔ ወንድ አይደለሁም እንዴ አንቺ?››

‹‹ወንዶቹን አይተናል፥ እቴ፡፡ ጠላታቸውን ዘርረው የሚያጋድሙ›› አለች፥ ልጁን እያባበለችው፡፡

‹‹እኔን ምን ልትዪኝ ነው ታዲያ?››

‹‹ምናችሁ ይታወቃል?››

‹‹እነማን?››

‹‹ትዳርን ተመራመርን የምትሉት ለምን፡፡ ወንድ አይሉዋችሁ ሴት፥ ቄስ አይሉዋችሁ ደብተራ . . . መላ ቅጣችሁ የጠፋ!›› አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF

‹‹ተኩዋሽ ተኩዋሽ ይልሻል? ገዳይ፣ ገዳይ ያሰኝሻል? የቦረናዪትዋ ልጅ! አይደለም እንዴ! ለማንኛውም ነገር የባህል አብዮት ለዘለአለም ይኑር!›› ብሎ፣ ዶሮዋን በዚያ በሰላ ቢላዎ አንገትዋን በጥሰ ጣላት፡፡

ፅጌ ቶሎ ብላ የዶሮዋን ደም በትንሹ በጎድጉዋዳ ሳህን ቀዳችና ገቡቱውን ደፍታባት ባንድ እግርዋ ቆመችበት፡፡

እጁን ሲታጠብ፣ ለየትኛው ጋኔን በጠራራ ፀሀይ መስዋእት ለማቅረብ ነው ያሰበችው? አለ በልቡ፡፡

ከጥቂት ደቂቃ በሁዋላ ዶሮዋ ፀጥ አለች፡፡ ውባንቺ ከነገቡቱው ይዛት ወጣች፡፡ እጣኑ ቡልቅ ቡልቅ እያለ ይጤሳል፡፡ ልጁን ሰጠችው፡፡ ግን ተቀብሎ አላቀፈውም፡፡ ለተቀው፡፡ ዮሀንስ እየሮጠ ሄዶ እጣን የሚጤሰበትን ገል ደፍቶ እየጨፈረ ሲስቅ፣ እናቱ ብስጭት ብላ፣ ‹‹የድቁናው ሚካኤል ይድፋህ አቦ!›› ብላ፣ እሳቱ እንዳያቃጥለው ዘላ ያዘችው፡፡

‹‹የሰለት ልጅሽን? እንትፍ በዪ›› አላት ሲራከ፡፡

‹‹እጁ፣ እግሩ አያርፍ ታዲያ! ይህ እንዲያው ህፃን አይደለም፡፡ የሰይጣን ቁራጭ ነው፣ እንትፍ? አለች፣ ብግን ብላ፡፡

የእጣኑ መደፋት ጥሩ ምልክት ሆኖ አልታያትም፡፡

‹‹እንደ ተመኘሺው ነው የሆነልሽ. . .››

‹‹ምንድን ነው የተመኘሁት?››

‹‹ረባሽ ልጅ በሰጠኝ ብለሽ. . .››

‹‹ታዲያ እሳት ስጠኝ አልኩት?››

‹‹ሳም እሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈጀት፣ እንዳትተወው ቸገራት. . .››

‹‹ኤድያ! ለወጉ አባት ነህ፡፡ ገስጥ ብታደርገው ምናለበት?›› አለችና አመናጨቀችው፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹ተቢው አባክሽ፡፡ እሱ ስፍራው ካማልክት ጋር ነው – ከነሄርኩሊስ፣ ከነሄክቶር፣ ከነኢጋሎ፡፡ አማልክት በቅናት አይን የሚመለከቱት ልጅ ነው. . .››

‹‹ኦ ኦ እቴ! የምን መቀባጠር ነው እሱ?›› አለችና ሻሽዋን አስተካከለች፡፡

‹‹ተቢው›› አላት፡፡

‹‹ልጁን ቆንጥጠው ካላሳደጉት እንዴት ይሆናል? አባት ታዲያ ጥቅሙ ምንድን ነው?›› አለች፡፡

‹‹እንደ ፈለገው ይደግ፡፡ የኔና ያንቺ ፈንታ እንዲያድግ የሚቻለንን ማድረግ ብቻ ነው፡፡ ሃሳፈንታችን እኛን መስሎ እንዲወጣ ማድረግ አይደለም፡፡ እሱም ሲያድግ የሚገምተን በዚሁ ነው፡፡ ራሱ በሚመርጠው አካባቢውን መስሎ እንዲያድግ ከማድረግ ሌላ ሃላፊነት የለብንም›› አላት፡፡

‹‹ኤዲያ!›› ብላ ልጁን ይዛ ወደ ጉዋዳ ገባች፡፡

ሲራክ ድካም ተሰማው፡፡ የዛለው ሰውነቱ እረፍት ቢሻም፣ ጭንቅላቱ ግን አላርፍም እያለ ያስቸግረው ነበር፡፡ ረሀቡ አለፈለት፡፡ እህል አላሰኘውም፡፡ አይኖቹን ከደነ፡፡ ሰብለ ብቅ አለችበት፡፡ ግን ብዙ አልቆየችም፡፡ መፅሀፉ መጥቶ ትክት. . .

የተረገመ መፅሀፍ አለ፡፡ ድንገት ተነስቶ የአእምሮ ሰላም ሊያሳጣው ለምን እንደ ጀመረ ገረመው. . . እስካለፈው ቀን ድረስ ምንም አይነት ችግር አይሰጠኝም ነበር፡፡ ግን አሁን. . . በድንገት ገሃነም፣ ሲኦል፣ ስቃይ ለምን ሆነብኝ? በቤት ውስጥ የጭቅጭቅ ምክንያት መሆኑ አንሶት፣ ሄዶ ደግሞ ከሰብለ ህይወት ጋር መያያዙ?... ሰው ቤት ገብቶ መነጀሱ?. . . ነጃሳ! ወዴት ነው የሚጎትተኝ? ወይስ?... ብሎ አሳቡን ገታ፡፡

አስፈራው፣ አሳቡን ለማሰብ፡፡ ያሳቡን ፈለግ እስከ መጨረሻው ተከትሎ ለመሄድ አስፈራው፡፡ ግን የመጣበትን አሳብ ለማምለጥ አልቻለም፡፡

 @OLDBOOKSPDF

መፃፍ አልቻልኩም፡፡ ሀቁ ይሀ አይደለም? ታዲያ ሀቁን ለምን ከራሴ አደብቀዋለሁ? መፃፍ አልቻልኩም፥ በቃ፡፡ የምለው አዲስ ነገር የለኝም፡፡ መባል ያለበት ሁሉ ከኔ በተሻሉ ደራስያን ተብሎ ተብሎ አልቆአል፡፡ እና፥ እንዲያው ነው ጊዜዬን በከንቱ የማጠፋው፡፡ የምለው ነገር የለኝም፡፡ ቢኖረኝም ምን እንደሆነ አላውቅም፡፡ ባውቀውም በቃላት ልገልፀው አልቻልኩም፡፡ ቃላት. . . ቃላት መግለፅ ያለባቸውን አይገልፁም – ያሾፋሉ. . .

«ምንድን ነው የምታስበው?» ፅጌ ነበረች፡፡

«ምንም፡፡»

«ስለ መፅሀፉ ነው?»

«እንዴት አወቅሽ?»

«ሌላ ምን ታስባለህ?» አለች፥ ውስጥ ውስጥዋን እርራ እየደበነች፡፡

ቀይና ጥቁር ተፃፈባቸው አዳዲስ ሉክ ወረቀቶች ከከሰል ምድጃ ውስጥ ስትከምር ቆየችና፥ «ጥቅም ያለው ነገር ብታስብ ምንኛ ጥሩ በሆነ?» አለች፡፡

ብስጭት ብሎ፤ «ኪነት በጥቅም ብቻ አይለካም» አላት፡፡

«እንግዲያውስ በእዳ ነዋ የሚለካው!» አለች፥ ነገሩ፥ እንዲገባው ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፡፡

ነገርዋ ከመቀመጫው አስፈንጥሮ አስነሳው፡፡ ሽንጡን ይዞ ትንሽ ተንጎራደደ፡፡ – የኪነት ትርጉም ሊገባሽ አይችልም፡፡ አንቺ የሆድ እንጂ የመንፈስ ምግብ አታውቂም፡፡ ከእንስሳ አትሻዪም፡፡ ጥፋቱ ካንቺ አይደለም፡፡ ከኔ ነው፡፡ አንቺን ከማግባቴ በፊት ማሰብ፥ ማመዛዘን ነበረብኝ! ብሎ ሊሰሀባት ፈልጎ ነበር፡፡

«እዳ የገባሁበት መፅሀፌ ይሀን ያህል መጥፎ ሆኖ፥ ወይም አልሸጥ ብሎ አይደለም. . .» አላት፤ ስሊቱን ባጣ ድምፅ፡፡

«ታዲያስ?» አለችው፡፡

@OLDBOOKSPDF



እጁን በብስጭት እወናጨፈና፣ «እየሽ፥ የኔ እመቤት» አላት፥ «ማይምነት በነገሰበት አገር ውስጥ ነው የምኖረውና የምፅፈው፡፡ ማንበብ ከሚችሉትም ውስጥ አብዛኞዎቹ አያነቡም፡፡ አብዛኛው ለመንፈስ ምግብ ምንም ደንታ የለውም. . .

«ሥጋ ለመቋረጥ፥ አረቄ ለመጠጣት፥ ገንዘብ ካለ፥ እድኦን የሚያሽ ማንም የለም፡፡ መፅሀፍ በሳንቲም ገዝቶ ማንበብ ግን ምን ሲደረግ! ቀድሞስ ማን አሰቦት?»

«ተነበበ አልተነበበ — ፋይዳው ምንድነ ነው?!» አለች፥ ወረቀቱን ከምራ እንደ ጨረሰች፡፡

«ይህን አይደለም የምልሽ፡፡»

«እረ ኤዲያ!»

«ከመንፈስ ድህነት የበለጠ በሽታ የለም፡፡»

«ባለማንበቡ ታሞ የሞተ አላየንም እቴ!»

«እሱስ ነው» አለ፥ «ሲታዩ በቁም ከመሞቱ ላይ ነው፡፡»

ውባንቺ የታረደችውን ዶሮ ጠጉር ነጭታና በቀሰም ነፍታ ይዛ መጣች፡፡ «እምን፥ እዳውን መክፈል በቁም ሊገድለን ነው፡፡ እሱን መቼ አጣሁት? እዳው የተረፈው ለኔና ለልጄ ነው፡፡ ሳይቸግር ጤፍ ብድር አሉ፥ እቴ!» ብላ፥ ከምድጃው ውስጥ የተከመረውን ወረቀት ከብረት ጭራ ለኮሰች፡፡

እሳቱ በግ ብሎ መንበልበል ሲጀምር ዶሮዋን ከውባንቺ ተቀብላ ምድጃውን እየዞረች ትለበልብ ጀመር፡፡ አንድ አይነት ምንቃላ የምትሰራ ቃልቻ መሰላ ታየችው፡፡ ግን እሳቡ አሁንም ከመፅሀፉ ላይ ስለነበረ፥ «እዳ የገባሁት ወድጄ አይደለም፡፡ መፅሀፍ ነጋዴዎችና እንሸጥልሃለን ብለው መፅሀፉን የወሰዱ አንዳንድ ሰዎች ገንዘቡን በልተውት ስለቀሩ ነው፡፡ እና፥ በዚህ ሊታማርሪኝ፡፡ ለማንኛውም ነገር እዳውን ከፍዬ ለመጨረስ ትንሽ ጊዜ ነው የቀረኝ» አላት፡፡

ዶሮዋን እየለበለበች፥ «እሱስ ደህና» አለች፥ «የፈሰሰ ውሀ መቼም አይታፈስ፡፡ ካለፈ ክረምት ቤት አይሰራ፡፡ ያለፈው አለፈ፡፡

 @OLDBOOKSPDF

እኔን የሚገርመኝ፣ የማይም አገር ናት፣ አንባቢ የለም እያልክ ሌላ መፅሀፍ ፅፈህ ሌላ እዳ ልታመጣብኝ መነሳትህ ነው. . .

‹‹እኔ በበኩሌ ይህንን ጤና አልለውም፡፡ የበሽታ ነው፡፡ የተጠናወተህ በሽታ አለ፡፡ ጤና ቢኖርህ ኖሮ ያለ ምንም መተማመኛ መፃፍክን እያነሳህ ለማንም በትነህ እዳ ውስጥ አትነክረንም ነበር›› አለች፡፡

የተለበለበችውን ዶሮ ለውባንቺ ሰጠች፡፡ ውባንቺ በአንድ እጅዋ ዶሮዋን ይዛ በሌላ ጎንዋ ዮሀንስን አቅፋ ወጣች፡፡ ፅጌ ወረቀቱ የነደደበትን ምድጃ በጥንቃቄ ከድና ስታበቃ ከጥግ አስቀመጠች፡፡ ምንድን ነው የምትሰራው? ብሎ እያሰበ፣ ‹‹ከእውነት የበለጠ መተማማኛ የለም፡፡ እኔ በፊርማ ወይም በዋስትና አላምንም፡፡ በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት መወሰን ያለበት እምነት ብቻ ነው›› አላት፡፡

‹‹እዎን - ትርፉ እዳ!›› አለች፣ መሶብ እያቀረበች፡፡

‹‹ቢሆንም በሰዎች ላይ ያለኝን እምነት ሊቀንሰው አይችልም›› አላት፡፡

‹‹ሰውን ማመን ቀብሮ ነው፡፡ ያንተ ግን የበሽታ ነው፡፡ ሌላ አይደለም›› ብላ ወጥ እያወጣች፣ ‹‹ሁዋላ ሌላ መፅሀፍ እፅፋለሁ ብለህ እዳ ብትላክክብኝ እንዳለፈው ጊዜ ዝም ብዬ የማይህ አይምሰልህ፡፡ እኔም መብት አለኝ፡፡ ሆ – ምን አይነቱ ልክፍት ነው ባካችሁ!›› አለች፡፡

‹‹ልክፍቱን ልታስጥዪኝ ነዋ የተነሳሽው?›› አላት፡፡

‹‹ምን ማለትህ ነው?›› አለች፣ ቃላትዋን እየጎተተች፡፡

ያቃጠለችው ወረቀት ትዝ አለው፡፡ ምድጃውን እየዞረች ዶሮዋን ስትለበልብ ታየችው፡፡ የጠንቋዋይ ምስል መጣበት፡፡

‹‹እኔ እንጃ ቀፈፍሺኝ›› አላት፡፡

መልስ አልሰጠችውም፡፡ ቡዳ፣ አለች በልብዋ፡፡

@OLDBOOKSPDF



እሱም በልቡ እይ የድንቁርና ጣጣ ሲል ቆየና፥ «ስሚ ዕንቁ» አላት፡፡

«እኔን ፅሁፍ ለማስጣል ይህ ሁሉ ጣጣ አያስፈልግም፡፡ ብትጠይቂኝ ዘዴውን እኔው እነግርሽ ነበር፡፡ ዘዴው ምን መሰለሽ? ቀላል ነው፡፡ ላንድ ወር በየቀኑ ዶሮ ማረድ፡፡ ታዲያ አንቺ ራስሽ ካላረድሺአቸው አይሆንም፡፡ ደሙን በእርጎ እያደረግሽ ማቅረብ፡፡ ከትፎም ቢጨመርበት ይበልጥ ፍቱን ይሆናል፡፡ በዚያ ላይ ቀዝቃዛ ቢራ፡፡ በቃ፡፡ የፅሁፍ ነገር እርግፍ ብሎ ይቀራል፡፡ አረቦች እንደሚተርቱት፥ 'ሆድ ሲሞላ ጭንቅላት ባዶ ይሆናል'፡፡ ከዚህ የበለጠ ምን ዘዴ አለ? ጠንቁዋዩ እንዲያው ነው የበላሽ!»

«የምን ጠንቁዋይ ነው የምትለው!»

«ክርስቲያን አይሉዋችሁ አረመኔ! ለበንቱ ሰማዳችሁ እንደምትዘልቁ እግዜር ይወቅ!» ሲል፡-

«የምን መቀባጠር ነው እሱ!» ብላ ቱሉ ውልቅ አለች፡፡

አልተናደደባትም፡፡ ይልቅስ፥ ጆሮው ውስጥ የደወለው የባህል አብዮት አስፈላጊነት ነበር. . .

## ምእራፍ ፺

ሀምሌ ግም ካለ ሰንበት ቢልም ምሽት ላይ ዝናብ አልነበረም፡፡ ጥዋት ላይ እንደዚያ ፊቱን ክስ አስመስሎ ሲያስፈራራ የነበረው ሰማይ ኩል መስሎ ተንጣሎአል፡፡ ኩል መስሎ ከተንጣለለው ሰማይ ላይ ከዋክብት ሆጨጭ ብለው ፈሰው፥ ከአድማስ ላይ ዝቅ ብላ የተንሳፈፈችውን ሙሉ ጨረቃ እያባባቁ ይጠቅሰዋታል፡፡ ጨረቃዋ በባህር ዛፎች መካከል ብቅ ብላ ስትታይ ከጫጉላ ቤት የወጣች ሙሽራ ትመስላለች፡፡

@OLDBOOKSPDF

እየሩ ተዝቆዝ ያለ ነበር። በባህር ዛፍ ማገዶ ጢስ፣ ምራቅ በሚያስመጥጥ ጥሩ መአዛ ባለው የወጥ ሽታ፣ በቡናና በእጣን የታጠነ ነፍስ ረጋ ብሎ ይነፍሳል።

ተረት ሰፈር ፀጥ ብላለች። በቀን ደርቶ የሚታየው ጉሊት ገበያ ተበትኖአል። እንጀራ የሚሸጡ ጥቂት አሮጊቶችና ቆሎ የሚቸረችሩ ህፃናት ብቻ ቀርተዋል። የመንደሩ ውሾች ጉሊት ገበያው የዋለበትን ስፍራ እየተዘዋወሩ ያነፈንፋሉ።

መንገዱ ላይ በብዛት የሚታዩት ከስራ የሚመለሱ ሰርቶ አደሮች ናቸው። አገልግላቸውን ይዘው በፍጥነት ይራመዳሉ። አንዳንዶቹ ቆም ብለው ከጉሊትዋ እንጀራ ወይም ቆሎ ይገዛሉ። ስእት የረፈደባቸው አንዳንድ በእድሜ ጠና ያሉ ሴቶችና ወንዶች፣ እንዲሁም ወጣት የቤት ገረዶችና አሽከሮች እርሳስና ደብተር ይዘው ወደ መሰረተ ትምህርት ቤት ለመሄድ ይጣደፋሉ።

በቀበሌው ዕሀፈት ቤት የሚካሄደው ቅስቀሳ ከሰፈሩ ፀጥታ በላይ ነግሶ ከሩቅ ይሰማል፦

ማይምነት ትጥቁን ይፈታል!
ይፈታል!,
ማይምነትን እንታገላለን!
እንታገላለን!
ማይምነት ጠንቀኛ ጠላታችን ነው!
ነው!
በድንቁርና መቃብር ላይ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን እንገነባለን!
እንገነባለን!

ከማይምነት ጋር ትጥቃቸውን የሚፈቱ ብሎ በእሳብ ፈረሰ ጭልጥ አለ – በጠፍ ጨረቃ።

ቺፈና ቁዋቁቻ፣ ላሽና ቁረቁር
ለምፅና ነቀርሳ፣ የራስም ፎረፎር
ቁንጫና ትሁዋን፣ ቅጫምና ቅማል
ትክትክ ተስቦ፣ ኩፍኝና ባል
ሙጀሊና ጭቶ፣ የቆላ ቁስል
ደበሎ ዲሪቶ፣ ቡቱቶና ባና

@OLDBOOKSPDF



ቂጥኝና ጨብጦ፣ ዝሆኔ ቁምጥና
እነ አቶ ጭቅቅት ጋሼ ጉስቁልና
እንቅርት ጆሮ ደግፍ አባጭ ኪንታሮት
ድንቁርና ዕልመት፣ ረሀብ ጣ'ረሞት
አበጋዙም ጭምር፣ ሁዋላ ቀርነት
ጉዋዛቸውን ይዘው ሆነው ባንድነት
ድል ተመተው ኖሮ ሁሉም አቀረቀረው
ታዩት ተሰልፈው፣ የፊጥኝ ተሳሰረው፡፡
ቁመናው ያማረ፣ ግርማው የሚስፈራ
ወዙ ፍልቅ ያለ ከውሀ የጠራ
ጠላት'ሚያሳፍር ወገን'ሚያኮራ
የእኩልነትን፣ ፃዳ ሸማ ለብሶ
በነፃነት ካባ ኮርቶ ተኮፍሶ
ያንድነት አርማውን ጥበቡን ተላብሶ
እንደ ሰሜን ኮከብ እንደ ጠዋት ጮራ
እንዳደይ አበባ እንዳዲስ ሙሽራ
በብሩህ ደስታ ፊቱ እያበራ
ብቅ ብሎ ታየው ቁርጠኛው ያ ኩሩ
የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ – ጀግናው፣ ሰርቶ አደሩ. . .

እና፣ እግረ ህሊናውን በመግታት፣ መለስ ብሎ – ይህን የተረገመ መፅሀፍ መቼ ይሆን የምጨርሰው? አለ፡፡ ገና ስጀምረው ሚስቱ፣ እግዜር ይይላትና፣ አረገዘች፡፡ እና፣ በግድ ስራ መፈለግ ነበረብኝ፡፡ ስራው ተገኘ፣ እንደ ምንም፡፡ የምትወልድበትን ሌላ ጎጆ ፍለጋ አቤት ያጠፋሁት ጊዜ! አዲስ ቤት፣ አዲስ ስራ፣ አዲስ ህይወት – ይህን ሁሉ እስከምላመደው ድረስ መፅሀፉ መቆየት ነበረበት፡፡ እንደ ገና ስጀምረው እያንዳንዱ ቃል እንደ ድንጋይ እየከበደኝ ስቸገር፣ ስፅፍ፣ ስቀድ፣ እንደ ገና ስፅፍ በመጨረሻ አሁን ደግሞ ከነአካቴው መቀደዱ ምን ይባላል? ስቀርበው ይርቀኛል – ክይሲ!

@OLDBOOKSPDF



– እድሜ ለሰብለ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጥሩ ሁኔታ መራመድ ጀምሮ ነበር፡፡ የመተደዱም ምክንያት እስዋ መሆንዋ ያስገርማል፡፡ ዕፊ የጨረስኩትን ምእራፍ ላላያት እንዴት እጣደፍ ነበር? ፍፃሜው ደረሰ መሰለኝ፣ ግቢአቱ መሬቱ... እና፣ ከእሱ ጋር የኔም ኪነታዊ ህይወት...

‹‹እንደምን አመሹ ጋሼ?››

ውባንቺ ነበረች፡፡

‹‹አው፣ አንቺ ነሽ እንዴ!››

‹‹ምንነው ዝም ብለሁ ቆመዋል? ቤት አይገቡም?››

ጨረቃዋን አየ፡፡ ቀዝቃዛ ፈገግታ አሳየችው፡፡

‹‹ለምን ትምህርት ቤት አልሄድሽም?›› አላት፡፡

‹‹ስራ በዝቶብኝ›› ብላ መለሰችለት፡፡

‹‹የምን ስራ?›› አላትና፣ እየተጣደፈ ሄደ፡፡

በሩን ከፍቶ ሲገባ የሆንስ ሮጦ ተጠመጠመበት፡፡ አቅፎ እየሳመው ሄደ፡፡ ከሚፅፍበት የምግብ ጠረጴዛ ላይ የያዘውን ጥራዝ አኖረና፣ ጠረጴዛውን ተደግፎ፣ ‹‹ውባንቺን ለምን ትምህርት ቤት አልሰደድሻትም?›› አላት – ባለቤቱን፡፡

የዕጌ አይን ተወርውሮ ጥራዙ ላይ አረፈ፡፡ ነጠላዋ ከትከሻዋ ላይ አድርጋ፣ ሻሽዋን ገርዳሳ አስራ ቁጭ ብላ ወጥ በከሰል ማንደጃ ላይ ታሞቃለች፡፡ ክፍሉ በዶሮ ወጥ አጥን ብሎአል፡፡ ወስፋቱ ተላወሰ፡፡

‹‹በሰራተኛ ነገር አትግባብኝ ብየሃለሁ!›› ብላ በትላልቅ አይኖችዋ ገረመመችውና፣ ‹‹ከለከለችኝ ብላ ክስ ሄደች እንዴ? ይቺ ጥሬ ካደረች አትቆረጠምም አሉ፡፡ ለዚህም ደረሰች?›› አለች፡፡

‹‹ክስ አይደለም፡፡ እኔ ስመጣ መንገድ አግኝቼ ጠይቃኣት ነው፡፡ ስራ በዝቶብኝ ነው ያልሄድኩት አለችኝ›› አለና፣ ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡ የሆንስን ከጉልበቱ ላይ ቁጭ አድርጎ፣ ‹‹ፈረስ ፈረስ ማጫወት ጀመረ፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹ታዲያስ?›› አለች፡፡

‹‹ምንም ስራ ቢበዛ መሄድ አለባት፡፡››

‹‹ስራውን ማን ሊሰራው?››

‹‹ስትመለስ አትሰራም?››

‹‹ገረድ ሁኚላት ነው የምትለኝ አይደለም? እመቤት አልቀጠርኩም›› አለች፡፡ ‹‹ሰራተኛዋ የምትበላው አጣች ወይ? ለምን ሄዳ አትተኛም? ለምን ትምህርት ቤት አትሄድም? እያልክ እኔን ነጋ ጠባ ከምትጠብሰኝ ከፈለክ ራስህ ላይ አውጥተህ ቁጭ አርጋት፡፡ ከዚህ በፊት የነበሩትን ሰራተኞች እንዲሁ ስታሞላቅቅ ሲጨፍሩብኝ ከርመው ነው እየረገጡኝ የሄዱት፡፡ የከርሞ ጥጃ እቴ፡፡ ውሀ ቢወቅጡት ተመልሶ እምቦጭ፡፡ ምንነው ለኔ አታስብ? የት ወደቅሽ የሚለኝ የለም›› ብላ፣ ድስቱን አወጣችና ውሀ በጣሳ ወዘተች፡፡

ሲራክ ራሱን ይዞ ተክዘና፣ ‹‹እዮሽ ፅጌ፣ ስለዚህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ብዙ ተነጋግረናል፡፡ አሁን ወደዚያ ጭቅጭቅ መመለስ አልፈልግም፡፡ ጭቅጭቅ ሰልችቶኛል፡፡ መማር አለባት ብያለሁ መማር አለባት›› አለ፣ ተቆጥቶ፡፡

የምሩን የተናገረ መሆኑን ከሁኔታውና ከድምፁ አመንችና ነገሩን መለስ አድርጋ፣ ‹‹አሁን እነቡሼና እነ ድንቄ ተማሩ አልተማሩ ምን ዋጋ አለው? ድንቄም ተማረች እቴ፣›› አለች፡፡

‹‹ድንቄና ቡሼም ሰዎች ናቸው፡፡››

‹‹ገረዶች ተሰብስበው ሲያወኩ ነው የሚያመሹት፡፡ የሚማሩ መሰለህ?››

‹‹አሉባልታ ነው፡፡››

‹‹ድንቄም! ለዚያውስ ተምረው የት ሊደርሱ?››

‹‹ለማንኛውም ነገር መማር ይጠቅማል፡፡››

‹‹ያምሳና የስልሳ አመት ሽማግሌዎችና አሮጊቶች ሰብስበው ት ፊደል ቁጠሩ ቢሉዋቸው ምን ጠብ ሊል! እንዲያው ስራ ማስፈታት ነው፡፡››

@OLDBOOKSPDF



«ስራ ማስፈታት አይደለም፡፡»

«ታዲያ ምንድን ነው?»

«ከማይምነት ጨለማ ሰዎችን ማላቀቅ ስራ መፍታት ወይም ማስፈታት አይደለም፡፡ ጥሩ አላማ ነው» አላት፣ ዮሀንስን እያሟሟቀ፡፡

«አይ ጉድ!» አለች፣ «አላማ ብሎ ነገር፡፡»

«ምንም ብሩህ ነገር አይታይሽም ማለት ነው?»

«ህልም እንደ ሆነ ስተኛ ያደርሰኛል፡፡»

«ከጭቁን ቤተሰብ ወጥተሽ እንዲህ ስትናገሪ ይገርመኛል» አላት፡፡

«ድህነቴን ልታስታውሰኝ ነው?»

«እንደሱ ሳይሆን፡፡»

«ነው እንጂ!»

«ያሳልኩትን፡፡»

«አሁንም አላለፈልኝም፣ አባክህ!»

«ያልፍልናል እንጂ፣ ለምን አያልፍልንም?» ብሎ፣ ሩቅ እየተመለከተ፣ «ከህዝቡ ጋር ያልፍልናል፡፡ ብሩህ ተስፋ ሊታየን ይገባል» አላት፡፡

ፅጌ ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ጠረጴዛ ላይ ያኖረውን ጥራዝ እያየች፣ «ጥሩ ነቀ ምናለ! ተስፋ ጳቦ ከሆን» ብላ ሳቀችና፣ «ብዙ አንባቢ አገኛለሁ ብለህ ተስፋ አድርገሃል?» አለችው፡፡

«ለምን?» አላት፣ ባይኑ አይኑዋን እየተከተለ፡፡

«ለመፅሀፍህ፡፡»

@OLDBOOKSPDF



‹‹ለምን ተስፋ አላደረግም? የዛሬ ሀ ሁ ቆጣሪዎች የነገ አንባቢዎች የማይሆኑበት ምንም ምክንያት የለም›› ብሎ፣ ዮሀንስን እየታገለ፣ ‹‹ግን፣ እኔ የምፅፈው ለገንዘብ ብዬ አይደለም›› አለት፡፡

‹‹እዳ ለመግባት ነው?››

‹‹ጀመርሽ እንግዲህ!››

‹‹ታዲያ ለምን ብለህ ነው?››

‹‹ለፍቅር ነው፡፡ የምፅፈው መፃፍ ስላለብኝ ነው፡፡ እያንዳንዷዋ ቃል የመንፈስ ተሀድሶ ትሰጠኛለች፡፡ እያንዳንድዋ አረፍተ ነገር ነፍሴን ታበለፅጋለች፡፡ ይገባሻል?›› አላት፡፡

ውባንቺ መሶብ አቀረበች፡፡

ፅጌ የምፀት ሳቅ ሳቀችና፣ ‹‹አዎን እያንዳንድዋ ቃል ያንተን ሀይወት ስታድስ፣ እኔ ደግሞ ምትን ከምን አድርጌ ስል ሲጋዩ ሲቦጨቅ ይውላል፡፡ አንተ ምን አለብህ? እግዜር ባይጠብቀን ኖሮ እስካሁን ለቃላት መስዋእት ሳታደርገን አትቀርም ነበር›› አለች፡፡

ስሜቱ ሽምቅቅ ኩምትር ሲል ተሰማው፡፡ ንዴትም አፈነው፡፡ ምን ባደርግ ስሜቴ ይገባት ይሆን? ብሎ ሲጨነቅ ቆየና፣ ‹‹እኔ ይህን ያህል ጨካኝ መስዬ እታይሻለሁ? መፃፍ እወዳለሁ ማለት ቤተሰቤን እጠላለሁ ማለት አይደለም፡፡ ለምን አይገባሽም? ካራት አመት በሁዋላ እንዴት ልታውቂኝ አልቻልሽም? እኔ እስከማውቀው ድረስ አብረን ያሳለፍነው ጊዜ ደህና ነበር፡፡ እንዲያውም ደስተኞ ነበርን፡፡ አሁን . . . ድንገት ምን የሚያጨቃጭቀን ጉዳይ ተፈጠረና ነው እንዲህ የምትሆኚው? ኑሮአችንን ሲኦል አድርገሽ የምትመለከችው?›› አለና፣ በረጂሙ ተነፈሰ፡፡

ውባንቺ የጣት ውሀ አቀረበች፡፡

‹‹ከሲኦልም ሲኦል፣ እቴ›› አለች፡፡

‹‹ሲኦል የሆነው ለኔ ነው ላንቺ አይደለም፡፡ ማለቴ፣ ውስጤ እየተሰቃየ ነው፡፡ ይህን መፅሀፍ መጨረስ አለብኝ፡፡ ቀስፎ ይዞኛል፡፡ ላገላገለው የሚያስችለኝ ትንሽ እመቻች ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ ብሎ፣ እጁን እየተጣጠበ፣ ‹‹ከዚያ በሁዋላ ቃል እገባልሻለሁ፡፡ ከራሴም ጋር ሆነ

 @OLDBOOKSPDF

ካንቺ ጋር ሰላም ይኖረኛል፡፡ እንደ ገና ደስተኞች እንሆናለን፡፡ ትንሽ ጊዜ ስጭኝ፡፡ ሌላ አላስቸግርሽም» አላት፡፡

«ባለፈው ጊዜ እንዲሁ ብለኸኝ ነበር፡፡»

«ብዬ ነበር፡፡ ግን. . .!»

«እንዳለፈው ጊዜ ደኸኛውን ስትጨርስ ደ'ሞ ሌላ ትጀምራለህ አይደለም? ፀሁፍ ህይወቴ ነው አይደለም የምትለው?» ብላ፥ ልጁን ተቀበለችውና፥ «እኛ ህይወት የለንም፡፡ ላንተ ምንም አይደለንም፡፡ ህይወትህ መፅሀፍህ ነው፡፡ እኔና ልጂ ደ'ሞ በሚመጣው አዳና ችግር እየማቀቅን እንደሰቃለን – እግዜር ያደለን ህይወት ይህ ከሆነ ምናለ? እግዜር የሰጠውን ሰው አልችል አይል» እያለች፥ ወጥ እየጨለፈች ታሠጣ ጀመር፡፡

ዝም ብሎ ነበር የሚያዳምጣት፡፡ ልክ ናት እሰ በልቡ – ፍፁም ልክ ናት፡፡ የቤተሰብን ደህንነት መሻት ሃላፊነት የሚሰማቸው እናቶች ሁሉ መሰረታዊ ፍላጎት ነው፡፡ ለእሰዋ የኑሮ ዋስትና ከማንኛውም ነገር ይበልጥ ቅድሚያ አለው፡፡ የኑሮ ዋስትና ደግሞ ከገንዘብ በምንም ሁኔታ ተለይቶ አይታይም፡፡ የእስ ምኞት? የእስ ህልውና ትርጉም? የእስ ተልእኮ ትርጉም? ፀሁፍ ህይወቴ ነው፡፡ ከዚያ ውጪ ሌላ ህይወት፥ ሌላ ምኞት የለኝም፡፡ እሺ. . .እውነት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የጻፍኩት መፅሀፍ ዋጋ የሌለው ይሆናል፡፡ አሁን የምፅፈውም ምናልባት ዋጋ ላይኖረው ይችላል፡፡ ግን ነፍሴ ራስዋን ለመግለፅ የምታደርገውን ጥረት መቀጠል አለባት፡፡ አንድ ቀን. . . ምናልባት አንድ ቀን. . . ራስዋን ለመግለፅ ትችል ይሆናል፡፡ ውበትን ለመግለፅ፥ ያውም ቢቻል፥ ትግሉ መጨረሻ የለውም፡፡ ታዲያስ? ሃላፊነቴ ለማን ነው? ለኪነትን? ወይስ ለእሰዋ? ለቤተሰቤ? ይህ ነው መሰረታዊው ጥያቄ፡፡ ኪነት ቀናተኛ ናት፡፡ የተከፋፈለ ታማኝነት አትወድም . . . ከእግዜሩ ይበልጥ ቀናተኛ ናት . . .

መቁዋደሻ አውጥታ ሰጠችው፡፡ መቁዋደሻውን ተቁዋደሰ፡፡

ዘወትር የሚዋትተው አእምሮው እንዲህ አለው – ከዚህች ሴት ጋር ያለህ ህይወት ይብቃ፡፡ አቻህ አይደለችም፡፡ መንፈሳችሁ የተራራቀ ነው፡፡ ከከባቸሁ አይገጥምም፡፡ ከእሰዋ መገላገሉ ላንተም ሆነ ለእሰዋ ይበጃል፡፡ ተዋት፡፡ በቃ፡፡ ምን አስጨነቀህ? መለያየት ብንተ አልተጀመረም፡፡ እግዜር የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም፡፡ እንደ ምንም ትኖራለች፡፡ ለመኖር የማይፍጨረጨር የለም!

@OLDBOOKSPDF



ምናልባትም የሚስማማት ባል ታገኝ ይሆናል – ስራ ውሎ በሰላም ገብቶ የሚተኛ ባል፡፡ አታመንታ፥ ሲራክ፡፡ ልብህ አያመንታ፥ በማመንታት ህይወትክን አታበላሸው፡፡ ከጾር መቁዋደሻ በስተቀር ከሚስትህ ጋር የምትቁዋደሰው መንፈሳዊ ነገር ከቶ የለም፡፡ የተራ ህይወት ቀስትናን የምትፈልግ ተራ ሴት፥ የተራ ህብረተሰብ ልማድ ውጤት ናት፡፡ አንተ ግን ደራሲ ነህ፡፡ ነፍስህ ተልእኮ አላት፡፡ አትሸነፍ፡፡ ወደ እዘቅት መውተቱ ይብቃህ፡፡ ነፍስህ ነፃነትን ትሻለች፡፡ ነፃነትክን የምትጐናፀፍበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ህይወትዋ ውስጥ ዘለህ እንደ ገባህ ሁሉ፥ ዘለህ መውጣት አለብህ፡፡ ሲራክ በውነቱ እኔ የምልህን ስማ፡፡ ይሉኝታና አጉል ርህራሄ ዋጋ የለውም፡፡ ነፃነት! ነፃነት! ነፃነት...

ልቡ ግን ማመንታቱን አልተወም፥ ሚስትህ ወደ ውጭ በኮበለለችበት ሰአት ፅጌ፥ 'እይዞህ፥ እኔ አለሁልህ' እያለች የሰጠችህ የማያወላውል ፍቅር ውሲታው ምንድን ነው?›› አለም ጨልሞብህ፣ ስራ አጥተህ በምትንገላወድበት ሰአት ሰውነትዋን ሸጣ ባጠራቀመችው ገንዘብ ያሳለፈችልህ የመከራ ጊዜ እንዴት አድርጎ ሊረሳህ ቻለ? ላንተ ፍቅርና ክብር ስትል አልነበረም የሞቀ ሱቅዋንና የደራ ገበያዋ የዘጋችው? እስቲ አስበው፥ ላንተ ስትል ባላት አቅም ለከፈለችልህ መስዋእትነት ምን መልሰህ ሰጠሃት? ችላህ የኖረችው እሰዋ ናት፡፡ አንተ አይደለህም፡፡ ካንተ የበለጠ ታላቅ ነፍስ አላት. . .

‹‹ምን ታስባለህ?›› አለች ፅጌ ትኩር ብላ እየተመለከተችው ልጁ ደረትዋ ላይ እንቅልፍ ወስዶታል፡፡

‹‹ምንም›› አላት፡፡

‹‹አትበላም?››
‹‹ጠግቤአለሁ፡፡››

‹‹መሶቡ ከፍ ይበላ?››

‹‹ይበል፡፡››

‹‹ቍልቁ ብለህ ሄደህ እንዴት ምንም አላስብም ትላለህ?››

ሳስብ የነበረውን ልንገራት? የእኔና ያንቺ የእንጀራ ገመድ ትበጥሶአል፤ ከዛሬ ጀምሮ እኔና አንቺ ከህይወት የምንጋራው ነገር የለም፤ እብሮ ከመኖሮማት ሌላ፤ ይብቃን እንግዲህ እንለያይና ህይወት

@OLDBOOKSPDF



ወደ መራን አቅጣጫ እንሂድ ልበላትና ያበጠው ይፈንዳ? እስከ መቼ ድረስ ነው ይህን ቤት የእርስ በርስ ስቃይ የምናካሂድበት ተቋም አድርገን የምንዘልቀው? ሁለታችንም ደስታችንን መሻት አለብን። ህይወት አጭር ናት. . . ስቃይ፡ እጣ ፈንታችን መሆን የለበትም፡ እያለ ሲያስብ ቢቆይም፣ በሀዘኔታ የተሞሉ ትላልቅ ውብ አይኖችዋንና ደረትዋ ላይ የሚያንቀሳቅሰውን ህፃን ባየ ጊዜ መከረኛ ልቡ ሊጨክን አልቻለም። ያሰበውን በማሰቡ የህሊና ወቀሳ ቆንጠጥ አደረገው። ከተቀመጠበት ድንገት ተነስቶ ግንባርዋ ላይ ሳማት።

«ለምን ነው እሱ?»

«ሰርተሽልኝ ለቆየሽው ጥሩ ምግብ።»

«አልመሰለኝም።»

«እሺ፣ ደስ ስላልሽኝ ነው።»

«ደስ የምልህ ከሆንማ እንደ እቃ ቆጥረኸኝ አትዘጋኝም ነበር። አሳብህም ስሜትህም ከኔ ጋር እንዲልሆን ይገባኛል። የማይገባኝ አይምሰልህ፤ የደባል ኑሮ ነው የምንኖረው» አለች ተከዛ።

ውባንቺ መሰቡን ከፍ አደረገች። ድስቱንም አነሳች። የጣት ውሀ አቅርባ አስታጠበቻቸው።

«ከመፅሀፌ ሌላ አሳቤና ስሜቴ ካንቺ ተለይቶ የት ይሄዳል ብለሽ ነው?» ብሎ፣ ቀጠል አደረገና፣ «ስሜቴ ቢገባሽ፣ እንዲያው ብትረጂልኝ፣ ህይወታችን ምንኛ ጣፋጭ በሆን ነበር» አላት።

«የመፅሀፍ ነገር አታንሳብኝ፣ ያመኛል!» ብላ ነገሩን ባጭሩ ቀጨችበትና ተነስታ ልጁን ለማስተኛት ሄደች።

ስሜቱ ላይ ቀዝቃዛ ውሀ እንዳፈሰሰችበት ያህል በለተሰማው ባውነቱ ሽምቅቅ አለ። አፍቅረኝ፣ አለሁልሽ በለኝ፣ አይደለም የምትለው? እሺ። መቼ እምቢ አልኩ? እንዳፈቅራት ከፈለገች እስቀብ ለምን ስራዬን አታደንቅልኝም? ለምን አይዞህ፣ በርታ አትለኝም? ለምን ከኔ ብቻ ያልተከፋፈለ ታማኝነት ትጠይቃለች? እኔ ቢቶች ታማኝ የቤት ባርያ ነው እንጂ የሚፈልጉት'ኮ ባል አይደለም! ነፃና ነፍሴ ለሰንት አመቤት ትገዛ? እያለ የተጨነቀች ነፍሱን ሲያስጨንቅ ቆይቶ ዞር ሲል ከምግብ ጠረጴዛው ላይ ያኖረውን ጥራዝ አየ።

@OLDBOOKSPDF



ማየቱ ብቻ እንደ እሬት ስለ መረረው ፊቱን ኮስተር አደረገ፡፡ ከራሱ አሳብ ርቆ፣ ያውም ባሁኑ ጊዜ፣ ወደ ሌላ ሰው አሳብ መጠጋት፣ በክረምት ወራት ለዛዛ እንሶላዎች መሀል እንደ መግባት ያሀል ሆኖ ስለ ተሰማው፣ ሰውነቱ ቀዝቀዝ አለ፡፡ ማንበቡ ቀርቶ መፅሀፉንም ከፍቶ ማየት አስፈራው፡፡ መጀመሪያውኑ እሺ ብዬ ለምን ተቀበልኩ በማለት ተቆጨ፡፡ ‹‹ቀድሞ ነበር እንጂ አልሞ መደቆስ፣ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ›› አለና፣ መፅሀፉን አንስቶ እየተነጫነጨ ማገላበጥ ጀመረ፡፡ ‹‹የዘመቻው ችቦ ነደደ – በገጠርም ጎህ ቀደደ›› የሚል የመፅሀፍ አርእስት ብቅ ብሎ አይኑ ላይ እንደ መጫ ተጣበቀበት፡፡

– የባዶ ጋን ጩኸት፣ አለ፡፡

– ምክንያት ሰጥቼው ብመልስለትስ? ማሰብ የምፈልገው ስለ መፅሀፌ ነው፤ ስለ ሌላ ሰው መፅሀፍ ምን አስጨነቀኝ? እሺ፣ እንብቤው የጠላሁት እንደሆን ምን ልለው ነው? ሀቁን ልነግረው እችላለሁ? እሱስ ሀቁን ለመስማት ዝግጁ ነው? አርእስቱ ራሱ መባል ያለበትን ብሎ የጨረሰ ይመስላል፡፡ ከዚህ ሌላ ምን ሊል ነው? ፍየል ከመድረስዋ ቅጠል መበጠስዋ! ግን እሱ ከፈለገ እኔ ምን ቸገረኝ? የተሰማኝን ሀቁን እነግረዋለሁ፡፡ እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደር አለና ወደ መቃብር እንደሚወርድ ሰው ራሱን በግድ እየጎተተ ማንበብ ሲጀምር የሽቶ መአዛ አፍንጫውን አወደው፡፡

የእስክንድርን መፅሀፍ ወደ አፍንጫው ጠጋ አደረገ፡፡ ሽቶ ሽቶ የሚሸተው ወረቀቱ ነበር፡፡ ቃላቶቹ አይደሉም፡፡ በውሀ ሰማያዊ ወረቀት ላይ ጥራት ባለው የመኪና ዕፊት የተፃፈው መፅሀፍ በጥሩ ሁኔታ ተጠርዞአል፡፡ ሽቶው ከፀሀፊዋ ይሆን? ወይስ እሱ ራሱ ጥራዙን ሽቶ ውስጥ ነክሮ አውጥቶት ነው? አለና እንደ ገና አሸተተው፡፡ ሽታው ደስ ይላል፡፡

‹‹ሽርሙጣ!›› አለና ማንበቡን ቀጠለ. . .

 @OLDBOOKSPDF

እትዬ አልታዬ ሲኒያቸውን ይዘው፥ ሰአትዋን ጠብቀው፣ ወርቅ ጥርሳቸውን ብልጭ እያደረጉ ኩተፍ ብለው፥ «እንደ ምን አደራችሁ?» ሲሉ ከቡናው ጀበና ጋር ግጥም፡፡

ፅጌ ብድግ ብላ፣ «ውይ እትዬ፥ ልንጠራዎት ስንል» ስትላቸው፡-

«የቡና ሼሂ የት ሄዶ ልጄ? እሱ ይጠራኛል፡፡ የቡናው ክራማ ይነግረኛል፡፡ አቦል ጀባ፡፡ ቀኝን አውለን፡፡ ሸረኛውን ያዝልን» ብለው ቁጭ፡፡

ፅጌ ሞቅ ያለ ፈገግታ እያሳየቻቸው፥ «ቀኝን አውለን ማለት ቀርቶአል እኮ» ስትላቸው፥ እትዬ አልታዬ የወርቅ ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው፥ «እዎን ልጄ» ብለው ትክዝ፡፡

ውባንቺ በእትዬ አልታዬ ነገር እየተገረመች ዝም፡፡

እየገነፈለ የቀረበው ጀበና ቆርቆንዳውን አስፈንጥሬ ልጣል እያለ ይፎክራል፡፡ እጣኑ ቡልቅ ቡልቅ እያለ ይተናል፡፡ ጢሱ ቀጥ ብሎ ወደ ጣሪያው ያንሰራራል፡፡

እትዬ አልታዬ የእጣኑን ጢስ ተመልክተው፥ «ሰምሮአል፡፡ ክራማው ቀጥ ብሎአል» ብለው፥ ወርቅ ጥርሳቸውን ብቅ አደረጉና፣ «ደግ አሰማን፥ ክፉ አታሳየን፡፡ ሸረኛውን ከበሩ ያዝልን፥ መጋኛውን አባርልን፡፡ አቦል ጀባ በለን፥ አትለየን» አሉና፥ ሲኒአቸውን ለውባንቺ ሰጡአት፡፡

የቡና ጀበናው አልቦታ፡፡ እትዬ አልታዬ በፍቅር አይን ጀበናውን ትክ ብለው ሲመለከቱ፥ ዮሀንስ ለቁርስ የቀረበውን የተጠበሰ ቆሎ ለማፍሰስ ወደ ጀበናው ሲሮጥ ውቃቢያቸው ተቆጣና፥ ይህን ቀዛ ከጀበናው ላይ ብትደገፈው ምናለበት!» አሉ፡፡

ፅጌ ተንጠራርታ ልትይዘው ስትል አመለጣት፡፡ ቆሎውን እዘግናለሁ ሲል ሳህንቀ ከንብል አለች፡፡ ቆሎው እንዳለ ሆጨጭ ብሎ ፈሰሰ፡፡ እትዬ አልታዬ እርር ድብን አሉ፡፡ አላስችል ሲላቸው፣

@OLDBOOKSPDF



‹‹ምንነው እቴ!›› ብለው ተነሱና ይዘው በቁንጢጥ ድብን አደረጉት፡፡ የህንስ እርር ብሎ ማልቀስ ጀመረ፡፡ ውብንቺ እንጀትዋ ራሰ፡፡ በሆድዋ የእህል እምሳክ... የእህል እምሳክ... እያለች የፈሰሰውን ቆሎ መጀመሪያ እፍስ እፍስ፣ ቀጥሎም ልቅም ልቅም ስታደርግ፣ ዕጌ ልጇን ሳም ሳም አድርጋ እያባበለች፣ ‹‹ምን ነው እትዬ?›› አለች ተቆጥታ፡፡

‹‹ልጅሽን ከጀበና ላይ መያዝ!›› ብለው ወደ መቀመጫቸው ተመለሱና፣ ‹‹ጀበናን ውቃቤ ማስረቅ ደግ አይደለም›› አሏት፣ እየተንሜነፉ፡፡

ዕጌ ቆሎውን አልረሳችም፡፡ አንድ ሲኒ ቡና ወደ ውጭ ረጨች፡፡ ቆሎውንም ዘግና በተነች፡፡

እትዬ አልታዬ ቡናቸውን ፉት ብለው፣ ከዕጌ ጋር የቀጨነው ቃልቻ ዘንድ የሄዱበትን ጉዳይ እያስታወሱ፣ ‹‹ያንን እንደ ተባልሽው አደረግሽ?›› አሉዋት፡፡

‹‹ምን ያደርጋል ብለህ ነው!›› አለች፡፡

‹‹እንዴት ልጄ?››

‹‹ጠንቋዋይ ለራሱ አያውቅም አሉ! እንኳዋን የሌላውን፡፡ ፋይዳ የለውም›› አለቻቸው፡፡

‹‹እረ ተዪ ልጄ፡፡ ደግ አይደለም፡፡ እንዲህ አትበይ›› አሏት፣ ደንግጠው፡፡

‹‹እረ ኤዲያ! የጠንቋዋይን ነገር ይተውት፡፡ ዋጋ የለውም፡፡ ውሸት ነው›› አለች፡፡

ደ ራ ሲ ው ፻፯

‹‹እንዲያው ፍንክችም አላለ?››

‹‹እረ እሱ እቴ፡፡ ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ መቼ ይለቃል ብለሁ ነው? አለች፣ ተስፋ እንደ መቁረጥ ብላ፡፡

እትዬ አልታዬ የዕጌን ስሜት አላጤኑም፡፡ ስለሚጭሩመሪቸው ሩህብ ነበር የሚያስላስሉት፡፡ ጦም ያደረው ሆዳቸው ይሰማል፡፡ ያረጀው ጥርሳቸው ቆሎ መቆርጠም አልቻል ብሎ እያማረረ ነው፡፡

 @OLDBOOKSPDF

በልባቸው ሰው ከሆዱ የበለጠ ጠላት ማን አለው? እያሉ፣ «የድስት ጥራጊም የለሽ?» ብለው ጠየቋዋት፡፡ ጉድ ጉድ ማለት ጀመረች፡፡

ውባንቺ ቡና ለሁለቱም ደግማ፣ ሁለተኛ ቡና ልታፈላ ጀበናውን ይዛ ወጣች፡፡

እትዬ አልታዬ በዶሮ መረቅ የቀረበላቸውን እንጀራ ጎረስ ጎረስ አድርገው ቡናቸውን ፉት ካሉ በሁዋላ ለምሲጋና ወደ ጣሪያ አንጋጠው፣ «እጅሽ ይስፋ፡፡ ያባትሽ የእናትሽ ከራማ ይታረቅሽ በአለም ኑሪ» ብለው፣ ወደ እንጀራቸው ተመለሱ፡፡

«ያባቴና የናቴ ከራማ ምኑን ታረቀኝ ብለሁ ነው? ሲያንከራትተኝ፣ በሌተኛ አጻረኑት ሲያጉላላኝና ለማንም ሰካራም ጥፌ ሲዳርገኝ ኖረ፡፡ ከዚህ ሁሉ ጣጣ ገላገለኝ ብዬ አመስግኜ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ዞሮብኛል» አለች፣ ምርር ብላ፡፡

«ምን ሆንኩ ነው የምትዪው ልጄ?» ብለው እንጀራ ቆርሰው በመጉረስ፣ እያላመጡ፣ «ከመሬት ተነስቶ ማማረር ደግ አይደለም» አሏዋት፡፡

«አልገባዎትም!» አለች ተብሳጭታ፡፡

«ቅናት ነው፡፡ መቼ አጣሁትና?»

«አዩ እባክዎን. . .»

«የልጃገረድ ባሌን እየቀናሁ በፍልጥ አገላብጠው ነበር» ብለው፣ የወርቅ ጥርሳቸውን ብልጭ አደረጉባት፡፡

ፅጌ ልጇን ገሰፀችና፣ «እትዬ ቅናት አይደለም» ብላ፣ ኮለል ብሎ የመጣውን እንባዋን ዋጥ አደረገችና፣ «እኔ የማዝነው በልጄና በራሴ እድል ነው» አለች፡፡

«ምን ነካችሁና?» አሉ፣ እትዬ አልታዬ እንጀራ እያላመጡ፡፡

«እንደ አሮጌ ቁና አውጥቶ እንደሚጥለን ይሰማኛል» አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF


«አበስኩ ገበርኩ» አሉ፥ «ምን ቆርጦት ልጄ?» ለሰው በጣም ርህሩህ ነው። እንቿና ልጁ ላይ እንዴት ይጨክናል? ተዪ ሀጢአት አትናገሪ።»

በረጂሙ ተነፈሰችና፥ «ይተውት አባክዎን» አለች፥ «እሱ የሚጠባበቀው የሚስቱን መመለስ ነው። እኔና ልጁ ለእሱ ምንም ዋጋ የለንም። እኛ የጊዜ ማሳለፊያዎች ነን። በፊት የቆረጠ ይመስለኝ ነበር። አሁን ግን ሳየው አይደለም።

«አዩ እትዬ . . . የቆረጠ ቢሆን ኑሮአችንን ለማሻሻል ይጥር ነበር። ሰው ሊያደርገን ይታገል ነበር። ግን ደንታ የለውም። ምክንያቱም የማይኖርበት ቤት ነው፣ የማያድሩበትን ቤት አያመሻሹበትም ይባል የለ። እንደዚያ ነው። ጊዜ ነው የሚጠብቀው። እና፥ የሚዕፈው ለምን መሰለዎት? ልጁና ሚስቱ ትዝ ሲሉት ነው። ለሌላ አይደለም። ትርጉም ገብቶኛል።»

እትዬ አልታዬ ጣታቸውን እየጠራረጉ፥ «ካገር ኮብልላ የወጣች ሴት በየት ትመለሳለች ብለሽ ነው? ሬሳ ከወጣበት ቤት ይመለሳል? የእነሱን ነገር እንደዚያ ቁጠሪው» አሉ።

ውባንቺ ሁለተኛውን ቡና አፍልታ መጣች። የጣት ውሀ አቀረበችላቸው። እትዬ አልታዬ እጃቸውን ሲታጠቡ፥ ፅጌ ስታስብ ቆየችና፥ «ውጭ አገር የቀሩ ኢትዮጵያውያን ይመለሱ እየተባለ ይነገር የለ? ብዙዎቹም መመለስ ጀምረዋል አሉ። ሰው ካገሩ ወጥቶ እንዴት ይቀራል? አለች።

«ምንነው እቴ?» አሉ እትዬ አልታዬ፥ «ሞኝ ነሽ ልበል! ጆሌ የከዳ ሰው እንዴት ሰተት ብሎ በበር ይመለሳል? እረ ተዪኝ! ባልዋን የምታፈቅር እውነተኛ ሚስት ብትሆን ኖሮ ድሮውን ለምን ጥላው ትሄድ ነበር? ለወገኖችዋ አድልታ አይደል? እሰዋ አትመለሰም። ይህ አብዮት እስካለ ድረስ... የወንድ ሆድ አይቆርጥምና ይልቅ እሱ ይጠፋ እንደሆን መጠርጠር ያባት ነው። የመጀመሪያ ፍቅር የመጨረሻ ነው ይባላል። የሚያገረሽ ፍቅር ደግሞ አደገኛ ነው» አሉ።

«እይ እሱስ አይጠፋም» አለች፥ «ካገር ወጥቶ መጥፋት ቆርቶ ከተረት ሰፈር አይወጣም። ይዛው ለመሄድ በብዙ መንገድ ሞክራው ነበር። ከሞት በቀር ከዚህ አገር የሚለየው ነገር አለመኖሩን ከተረዳች በሁዋላ ነው ተስፋ ቆርጣ ልጁን ይዛ የጠፋችው። 'አገርን

 @OLDBOOKSPDF

ጥሎ መጥፋት ስር ያጣ ዛፍ መሆን ነው' የሚል ፈሊጥ አለው፡፡ 'ያገሬን ዘፈንና እንጉርጉሮ፣ ሳቅና ሀዘኑን፣ ቀልድና ተረቱን ትቼ ምን ሀልውና ሊኖረኝ?' ይላል ሁልጊዜ፡፡ አገሩን ጥሎ ይጠፋል ብዬ አልጠረጥርም፡፡ በተለይም ይህን አብዮት ካንጀቱ ነው የሚደግፈው፡፡ አንድ ቀን፣ 'ለምን ከሚስትህ ጋር አልሄድክም? ከጭቁን ቤተሰብ ብትሆንም ተጋብተሃል?' ስለው፣ 'ጋብቻ ከመደብ ትግል በላይ አይደለም፡፡ ጭቁኖች ታሪክ ሲሰሩ እያየሁ ወዴት እሄዳለሁ? ታሪክን ባልፅፍም ማየቱ፣ ከትግል ጋር መኖሩና መዋሀዱ የትም ሊገኝ የማይችል ትልቅ ልምድ ነው' ያለኝ ትዝ ይለኛል፡፡ እሱ የትም አይሄድም፡፡ እዚሁ ነው የሚሞተው፡፡››

እትዬ አልታዩ ግራ ገብቶአቸው፣ ‹‹ታዲያ ጭንቀትሽ ምን ላይ ነው ልጄ?›› አሉና፣ ቡናቸውን ፉት ብለው አጣጣሙት፡፡

ፅጌ እንደ መብሸቅ ብላ፣ ‹‹ታዲያ ቤቱን ለምን ዞር ብሎ አያይም? ልቡ ያለው ውጭ ነው›› አለች፡፡

‹‹ምን ነው ልቡ ከመፅሀፉ ጋር ነው ብለሽኝ?›› ብለው በመገረም፣ ‹‹እሱ ከሆነ እርግፍ አድርጎ ባይተወው አልታዩ ምናለች በዪኝ፡፡ ከሌላ ሴት ጋር ፍቅር ይዞት ከሆነ የቡናው ሼሂ ይከሰትበታል›› አልዋት፡፡

ልብዋ ቆሞ፣ ‹‹እንዴት አድርጎ?›› አለች፡፡

ውባንቺ ሶስተኛውን ቡና ለማፍላት ስትወጣ፣ እትዬ አልታዩ ጀበናውን በአይን እየተከተሉ፣ ‹‹ካልሺስ እሱ ከሚሰራበት መስሪያ ቤት የማውቃት ልጅ አለች፡፡ ሁኔታውን ከእስዋ ለማጣራት እሞክራለሁ፡፡ ወላጆችዋ፣ ነፍሳቸውን ይማረውና፣ ጎረቤቶቼ ነበሩ፡፡ ጣልያን ሰፈር፡፡ አይ ደግ፡፡ አይ ደግ፡፡ እነሱንም አፈር በልቶአቸው ቀረ፡፡ ዞር ዞር ላፈር፡፡ ፊታውራሪ ማንአለባቸውም እንዲያ ሞትን ሲሸሹ ያንን የመሰለ ሰውነት ይዘው አፈር ሆነው ቀሩ›› አሉ፡፡

‹‹ማን ትባላለች?›› አለች፣ ስምዋን ለማወቅ ቸኩላ፡፡

‹‹ሳብለ ወርቅ ታፈሰ ትባላለች፡፡ አባትዋ አለቃ ታፈሰ በጣም አስተዋይ ነበሩ፡፡ ይገርምሻል፣ እስዋም ባባትዋ ነው የወጣችው፡፡ አይ መልክ! እግዜር ጥበቡን የጨረሰባት ነው የምትመስለው፡፡››

ፅጌ አሁንም ልብዋ ቆሞ፣ ‹‹ያገባች ናት? ወይስ. . .›› አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF 

‹‹ባለትዳር ናት፡፡ ለዚያውስ የምትኖረው ኑሮ እንዲህ መሰለሽ? ገነት ነው፡፡››

የፅጌ ልብ ረጋ አለ፡፡

## ምእራፍ ፱

አጣዳፊ ስራ ከሲራክ ፊት አልነበረም፡፡ ለለውጥ ያህል ጠረጴዛው ላይ የተከመረ ፋይል አይታይም፡፡ በእፎይታ ነፍሱ ተነፈሰች፡፡ የነሀሴ ቀጭጋግ ገፎ መስከረም የጠባ ይመስላል፡፡ ወጣ ብሎ በሙሉ ግርማ ሞገሰዋ የወጣችውን የጥዋት ፀሀይ ለመሞቅ ነፍሱ ክፉኛ እየከጀለች፣ ደጅ ደጁን በመስኮት እያየ ዝም ብሎ ቀረ፡፡

አንዳንድ ሰራተኞች ስራ የበዛባቸው ለመምሰል ካለቀለት ፋይል ውስጥ ነገር የሚያሸት አፍንጫቸው ቀብረው ይታያሉ፡፡ ከአምስት አመት መራራ ትግል በሁዋላ የፊውዳላዊው ስርአት ርዝራዥ ባህርይዎች ባለመጥፋታቸው ተገረመ፡፡ እንዲያውም በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ስም አንዳንድ ፊውዳላዊ ጠባዮች እስከፊ ገፅታቸውን ብቅ ብቅ ማድረግ የጀመሩ መሆናቸውን አስታወሰና፡- የአብዮት ሂደት ጠመዝማዛ ነው፣ ብሎ ፈገግ አለ፡፡

የትናንቱ ማጋለጥና ቀይ ሽብር ከመቼው ተረሳና ሳይጠቆ አቤት፣ ሳይላኩ ወዴት፣ እያሉ ሽር ጉድ፣ ጠብ እርግፍ የማለት፣ በውሸት ስራ ድካም የጎበጠ ጀርባን ቁና ቁና እየተነፈሱ የማሳየት፣ ሌላው በደከመበት ስራ ለምስጋና የመሽቀዳደም፣ በምላስ ሥጋ የመጥበስ፣ በመሰሪነት የማናከስ፣ የማጋጨት፣ የማምታታትና ከጀርባ በስውር ጩቤ የመውጋት ፊውዳላዊ ባህርይ ማንሰራራት ጀመረ? አይ ቢሮክራሲ! ላብ የለውም እኮ አለና፣ የእስክንድርን መፅሃፍ ገለጠ፡፡ ረጅም የመጨረሻው ምእራፍ ብቻ ነበር የቀረው፡፡ እሱም ቢሆን ረጅም አልነበረም፡፡ ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ማንበብ ጀመረ፡፡

ሲጀምር አሳቡ የተሰበሰበ አልነበረም፡፡ ግን ቀሎ እንዝዞ ጨርሶ የተሰማውን ለደራሲው ገልፆለት ከሰው መፅሀፍ ለመገላገል የነበረው ፅኑ ፍላጎት ብቻ ነበር የሚገፋፋው፡፡ በመፅሀፉ እምብዛም

@OLDBOOKSPDF



እንዳልተደሰተ ያስታውቃል፡፡ የቀረው የመጨረሻው አጭር ምእራፍ ቢሆንም፣ ከማይወጣው ጥቅጥቅ ካላ ጫካ ውስጥ እንደ ገባ ያህል ተሰማው፡፡ እሳቡ ከመፅሀፉ ጋር ጭልጥ ብሎ እስኪጠፋ ድረስ ማንበቡን ቀጠለ፡፡

ከመፅሀፉ ላይ ቀና አለ፡፡ ሰአቱን ተመለከተ፡፡ ከአርባ ደቂቃዎች በላይ አልወሰደም፡፡ አንብቦ በመጨረሱ እፎይታ ተሰማው፡፡ ስለሚቀጥለው ርምጃ ሲያስብ ስቃይ እፎይታውን ተክቶ በክራንቻው ቅርጭጭ ሲያደርገው ተሰማው፡፡ መፅሀፉን ዘጋና ስለ ጠቅላላ ይዘቱ ማሰላሰል ጀመረ፡፡

— በአጠቃላይ መፅሀፉ መጥፎ አይደለም፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ምእራፎች በጣም ግሩም ናቸው ብሎ አሰበ፡፡ በተለይም ቁዋንቁዋው ግሩም ነው፡፡ ነገር ግን የቁዋንቁዋው ጥራትና ውበት ብቻ አንድን ድርሰት የወጣለት ድርሰት ሊያደርገው አይችልም፡፡ ቅርፅ ብቻውን ዋጋ የለውም፡፡ ወሳኝ ጉዳይ መሆን ያለበት ይዘት ነው፡፡ እዚህ ላይ መፅሀፉ ከባድ ድክመት ይታይበታል፡፡

— የመፅሀፉ መሰረታዊ አላማ ግልፅ አይደለም፡፡ የእድገት በህብረት የእውቀትና ስራ ዘመቻ አላማ ለወጣቱ ትውልድ የጀብደኝነት መንፈስ መውጫ ቀዳዳ ለመክፈት ሳይሆን፣ የህብረተሰቡ ትኩስ ሃይል የሆነው ወጣቱ ትውልድ፣ ሰፊውን ህዝብ ትምህርት ቤት አድርጎ፣ ከእሱ እየተማረ፣ በተለይ የአካባቢን፣ በአጠቃላይ ደግሞ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በመረዳት፤ ሰፊውን ህዝብ አቅፎና በሰፊ ህዝብ ታቅፎ፣ መልሶ በማስተማር፣ ሰፊውን አርሶ አደር ለፖለቲካ ንቃት፣ ለድርጅትና ለትግል በማብቃት፣ እኑዋኑዋሩንና አካባቢን ለመለወጥ የሚረገውን ትግል አቅጣጫ ለማስያዝ ነበር፡፡ ይህ መሰረታዊ አላማ መፅሀፉ ውስጥ በግልፅ አልቀረበም፡፡

— ባህርያቱ፣ የሁኔታዎች ተገዥ ሆነው ከመታየት ሌላ፣ ራሳቸውንም ሆነ ሁኔታዎች ለመለወጥ ያደረጉት ጥረት ትኩረት ስላልተሰጠው፤ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አዲስ ስርአትን ለመገንባት ያደረጉት አስተዋፅኦ ደብዛው ይጠፋል፡፡ በዚህ ላይ፣ መፅሀፉ ውስጥ ያሉት ባህርያት ቲዎሪ በማነብነብ አንድ ቁዋንቁዋ የሚናገሩ ስለሆኑ፣ አንዱ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት ልዩ ጠባይ እምብዛም አይታይም፡፡ ስለዚህ፣ አንባቢው፣ ከማይታዩ፣ የተለየ አቋምና ሚና ከሌላቸው፣ ቲዎሪን እንደ ውዳሴ ማርያም ከሚያነበንቡ ባህርያት ጋር ስሜትን እየተጋራ የመጨነቅ፤ የመደሰት፤ የማዘን፤ የመሳቅ ወይም የማልቀስ እድል አያገኝም፡፡ በአጠቃላይ 56 ሺህ ዘማቾች

@OLDBOOKSPDF



የመፅሀፉ ባህርያት ሊሆኑ አይችሉም፡፡ አንድ ልብ ወለድ ታሪክ መነሻው አንድ የተወሰነ ድርጊት ቢሆንም፥ ግለሰብአዊ ባህርያት ከሌሉበት ልብወለድ መሆኑ ቀርቶ የፍልስፍና መጽሀፍ ይሆናል፡፡ የአንድ ልብ ወለድ መፅሀፍ ጥሩነት ወይም መጥፎነት ዞሮ ዞሮ የሚለካው በታሪኩ መጣፈጥ ወይም በቋዋንቋዋው ውበት ብቻ ሳይሆን፥ ደራሲው የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት በማድረግ በሚፈጥራቸው ግለሰብአዊ ባህርያት ነው፡፡ ተራማጆችን በአንድ ፊት፥ አድሃሪዎችን በሌላ በኩል አሰልፎ ማዋጋት ለአንድ ልብ ወለድ ድርሰት መሰረት ሊሆን አይችልም፡፡

– አንድ ልብ ወለድ ድርሰት ጥልቀት እንዲኖረው ደራሲው የሚፈጥራቸውን ግለሰብአዊ ባህርያትንም ሆነ የታሪኩን ሂደት ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ለማየት መሞከር አለበት፡፡ እስከንድር ይህን ለማድረግ የሞከረ አይመስልም፡፡ የዘማቾች ኩተት አዋጅ ሲታወጅ አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው እንዳይዘምቱ ጉቦ በመስጠት፥ አንዳንድ አዝማቾችን አጥብቀው በመማፀን፥ ከሀኪም አስር አይነት የምስክር ወረቀት በማጉረፍ፥ ይህም ባይቻል ዘመድ ወደ አለበት አካባቢ ወይም በአቅራቢያ ወደሚገኝ ከተማ እንዲዘምቱ፥ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በመማለድ የፈጠሩት ሁኬታ አንድም አልተጠቀሰም፡፡ ሰፊውን ህዝብ ከተሰቦ፥ ከተቅማጥ፥ ከቅማል፥ ከሙጃሊ፥ ከጭቆና ከችግር ሰይተው የማይመለከቱ አንዳድ ወላጆች፥ አይናችን እያየ ሀይወታችን እያለች እንዴት ልጆቻችንን ወደ ገሃነመ እሳት፥ ወደ ሲኦል እንልካለን በማለት እመት ሙሉ ጉዋዳ ውስጥ ደብቀው ያኖሩም ነበሩ፡፡ በያለበት የተፈፀመውን ደባ ቤቱ ይቁጠረው! ዘመቻው ሰፊውን ህዝብ በእውነት ለመርዳት የታቀደ ሳይሆን፥ ልጆቻችንን በቅንጨራ ለማስፈጀት ሆን ተብሎ የታሰበ ሰይጣናዊ ተንኮል ነው እያሉ ሲለፍፉ ቆይተው፥ ዞር ብለው ደግሞ ሰፊው ህዝብ መሀል በመግባት፥ ወታደራዊው መንግስት ተማሪዎችን አሰልፎ የሚልክባችሁ፥ ቤተክርስቲያናትንና መስጊዶችን እንዲያቃጥሉና ሃይማኖታችሁን እንዲያጠፉ፥ ሚስቶቻችሁንና የደረሱ ልጆቻችሁን እንዲያባልጉ፥ ክቡር ባህሎቻችሁን እንዲያጠፉና ተሰማችሁ የተባለውን መሬትና ከብቶቻችሁን ቀምተው ወደ እስከፊ የገባርነት ኑሮ ሊመልሱዋችሁ ነው በማለት የነዙት ውዥንብር በልዩ ልዩ ግለሰብአዊ ባህርያት አማካይነት ቢጠቀስ ኖሮ ለታሪኩ ጥልቀትና ውበት በሰጠው ነበር፡፡

– የመፅሀፉ ጉድለት ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ዘማቾች ሁሉ አንድ አይነት አመለካከትና አቋም እንዳላቸው አድርጎ ማቅረብ ትክክል አይደለም፡፡ ተራማጆች ወጣቶች የመኖራቸውን ያህል አድሃሪ አመለካከት ያላቸውም ነበሩ፡፡ ሰፊውን ህዝብ በሀቅ ለማገልገል

@OLDBOOKSPDF



የተሰለፉ ወጣቶች የመኖራቸውን ያህል ከወላጆች ቁጥጥር ነፃነት አግኝተው በመደሰት ሲባልጉ፣ መሸታ ሲያንቃርሩ፣ ሲጃራ ሲያጩ፣ ጫት ሲያኙኩ፣ የእባ ወራ ሚስቶችንና የደረሱ ልጃገረዶችን ሲያማግጡ የከረሙም ነበሩ። ደንፊዎችና ጀብደኞች የመኖራቸውን ያህል አስተዋዮችም ነበሩ። በሰፊው ህዝብ የታፈሩ ዘማቾች የመኖራቸውን ያህል በሰፊው ህዝብ የተተፉም ነበሩ። ለሰፊው ህዝብ ንቃት፣ ድርጅትና ትጥቅ መሰዋእት የሆኑ ሀቀኛ ዘማቾች የመኖራቸውን ያህል በሰፊው ህዝብ ሲነሰገሱና ራሳቸውን ብቻ ሲያገለግሉ ከርመው የተመለሱም ነበሩ። በዘማቾችም መካከል የከረረ የመደብ ትግል ነበር ማለት ነው። ይህ ሁሉ መፅሀፉ ውስጥ በሚገባ አልተንፀባረቀም።

– ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ መፅሀፉ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ቀይ ቃልሮች ከመሬት ከበርቴዎች ጋር የሚለዋወጡት ተኩስ ቢሆንም፣ ታሪኩ የሚሆንበት ሰፍራ በግልፅ አይታይም። ይህም፣ ደራሲው ስለ ሰፍራዎቹ መጠነኛ ምርምር አለማድረጉን ያሳያል።

– እንደ እድገት በህብረት የእውቀትና ስራ ዘመቻ ያለ ታላቅ እርእሰት፣ ታላቅ የድርሰት ችሎታን፣ ታላቅ ትእግስትን፣ ጥንቃቄና ከፍተኛ ምርምርን የሚጠይቅ እንደ መሆኑ መጠን፣ ሀቀኛ የኪነት ሰው በድፍረት አይነካካውም። ከነካውም በዋዛ አይለቀውም። ኪነት ከፍተኛ መሰዋእትነትንና የማያቋርጥ ትግልን ትጠይቃለች፣ እያለ ሲያሰብና ማስታወሻ ሲወስድ ከቆየ በሁዋላ፣ ቀና ብሎ የሌሎችን ሰዎች ድርሰት በነባራዊነት ተመልክቶ ፍርድ መስጠት እንዴት ይቀላል? አለ።

የእስክንድርን መፅሀፍ እንዲህ አበሻቅጦ አራክሶ የተመለከተበት ምክንያት ግልፅ አልሆነለትም። ቀንቼ ይሆን? ብሎ አሰበ። ቅናትም እንዳልሆነ ገባው። የምቀናበት ምን አለ ብሎ ከራሱ ጋር ተከራከረ። ምናልባት በእሱ አይን፣ በእሱ ስሜት፣ በእሱ ርእዮተ አለማዊ አመለካከት ባላየው ቀርቼ እንደሆንስ? የሚል እሳቤ መጣበትና፣ ግን ይህን ለማድረግ እንዴት ይቻላል? በማለት ግራ ነፋስ ቀኝ ወደደም ጠባ፣ ስለ መፅሀፉ የተሰማውን ገልፆለት መገላገሉን መረጠና ስልክ አንስቶ ለእስክንድር ደወለለት።

እስክንድር፣ ብብቱን፣ ጆሮ ግንዱን፣ ግንባሩን፣ ጀርባውንና መቀመጫውን እያላበው፣ ከንፈሩና፣ እጁ እየተርገበገበ፣ ጆሮው እየነጣ፣ አይኑ እየቀላ የሞት ፍርድ ለመቀበል ዳኛ ፊት የቀረበ መስሎ ቢራከ ስለ መፅሀፉ የሚናገረውን ለማዳመጥ በእት ያህል ዝም ብሎ ያዳምጥ ነበር። ቢራክ ንግግሩን አቁሞ ቀና

@OLDBOOKSPDF



ብሎ ባየው ቁጥር በማንኛውም ደቂቃ ሊፈነዳ የሚችል ተዳፍኖ የቆየ እሳተ ገሞራ መስሎ ስለሚታየው፣ ልቀጥል? ወይስ ላቁም? ወይስ በደፈናው ጥሩ ነው ብዬ ልለፈው እያለ ከራሱ ጋር ይሙዋገት ነበር፡፡ የኪነትን ጉዳና የመረጡ ግለሰቦች ስቃይን ለመቀበልም ሆነ የተጠየቁትን መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ አለበለዚያ ቀድሞውኑም ቢሆን ከኪነት ጋር መወዳጀት አልነበረባቸውም፣ በሚል አስተሳሰብ ሂሱን ቢቀጥልም፣ የእስክንድርን አሳዛኝ ሁኔታ በመመልከት ልቡ ውስጥ ውስጡን ሳይደማ አልቀረም፡፡

ቆም ብሎ ራሱ እያደለም የጠየቀው? እኔ አልለመንኩ! እና፣ እስታጥቀዋለሁ፤ ምን አስጨነቀኝ ይልና፣ ደራስያን ስለ ራሳቸው ያላቸው ያበጠ አስተሳሰብና ራሳቸውን አጥብቀው የማፍቀር ዝንባሌ ትዝ ሲለው ወኔው ሲከዳው ይከጅል ነበር፡፡ ለማንኛውም ነገር ከደራሲ ጋር ማን ሰላም ይኖረዋል! ከሰው ጋር ቀርቶ ከራሳቸውም ጋር ሰላም የላቸውም፡፡ ወቸ ጉድ! ለሰው ልጅ ሰላምና ደስታን የሚሹ እንደ ሻማ ነደው እያለቁ ለሌሎች ብርሃን እንኩዋ ባይሆን ጭላንጭል ለመፈንጠቅ የሚሞክሩ ደራስያን ለራሳቸው ሰላም ሲያጡ ያሳዝናል፡፡ ስለዚህ መፅሀፉን እንዲህ እያብጠለጠልኩ በተጨማሪ ሰላም ለምን ልንሳው? ግን... ታዲያ ምን ይሁን? ኪነት ከአፍቃሪዎችዋ የምትጠይቀው ዋጋ ነው፡፡ እውነትን የሚሻ ደራሲ፣ ምን ስቃይ ቢሆንበትም፣ ስለ ድርሰቱ የሚነገረውን ሀቅ መቀበል አለበት እያለ፣ ከራሱ ጋር ሲሙዋገት፣ ሲያመነታ ነበር ንግግሩን የጨረሰው፡፡

እስክንድር ከግንባሩ ላይ ላቡን ጠረገ፡፡ የቀሉት ወፍራም ከንፈሮቹ ተንቀጠቀጡ፡፡ ሰው ሰራሽ ጥርሱ ወልቆ ዱብ እንዳይል የሰጋ ይመስል ወደ ውስጥ ገፋ አደረገው፡፡ የሞት ቅጣት ተፈርዶበት ተስፋ የቆረጠ እስረኛ ይመስል ጆሮውን ማመን አቅቶት ፈዞ ቀረ፡፡

ቢራክ ሰረቅ አድርጎ ተመለከተው፡፡ በሙሉ አይኑ ሊያየው አልቻለም፡፡ በሰጠው አስተያየት የመፀፀት ስሜት በልቡ አደረበት፡፡ እስክንድር ሮጦ የመጣው እንዲህ አይነቱን ነቀፋ ለመስማት እንዳልነበር ገባው፡፡ ያበጠው አስተሳሰቡ ተሸንቁሮ በመተንፈሱ እስክንድር ደረቱ እየሰመጠ፣ ጀርባው እየጎበጠ፣ ተሸማቆ እያነሰ ሲሄድ ታየው፡፡

ፍጥጫው ስላስጨነቀው ቶሎ ለመገላገል አለ፣ «እንዳልኩህ ባጠቃላይ መፅሀፉ ጥሩ ነው፡፡ ያቀረብኩልህን ጥቆማዎች ጠቃሚ ከሆኑ ብትጠቀምባቸው የበለጠ ጥሩ ይሆናል» አለና፣ ረቂቁን መለሰለት፡፡

@OLDBOOKSPDF

እስክንድር የመፅሀፉን ረቂቅ ለመቀበል አልቸኮለም፡፡ የሚያስጠላ ነገር የተሰጠው ይመስላል ቀስ ብሎ ነበር የሚንቀጠቀጠውን እጁን የዘረጋው፡፡ መፅሀፉን ተቀብሎ፣ ስው ሰራሽ ጥርሱን ወደ ውስጥ ገፋ አደረገና፣ «አልቀልኛል ማለት ነው?» አለ፡፡ ጥያቄውን የሰነዘረው ለሲራክ ሳይሆን ለራሱ እንደ ሆነ አድርጎ ነበር፡፡

«ምኑ?» አለው ሲራክ፡፡

«ደራሲ መሆን» አለ፣ እያቃሰተ፣ «ደራሲ ለመሆን የነበረኝ ህልም ፍርክስክሱ ወጣ፡፡ የነበረኝ ጥሩ ህልም ከዚህ ላይ አበቃ፡፡ ባዶ ህልም ነበር ለካ? አሁን ምን እየሚሰማኝ ታውቃለህ?

ሲራክ ቸኩሎ «ምን ይሰማሃል?» አለው፡፡

«ባዶነት»

«ተሳስተሃል፡፡ እንዲህ አይነት ስሜት ሊያድርብህ አይገባም፡፡፡»

«እባክህን ጃል!»

«እውነቱን ነው፡፡ ችሎታው እንደሆን አለህ፡፡፡»

«ችሎታ እንደሌለኝማ ነግረኸኛል፡፡፡»

ሲራክ ተቆጥቶ፣ «ችሎታ የለህም አላልኩም፡፡ አልወጣኝም» ብሎ በረጅሙ ወደ ውጭ ተነፈሰና፣ «የሰጠሁህን ሃሳብ መቀበል ወይም አለመቀበል ያንተ ፈንታ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ደራስያን ለፍፁምነት መጣር አለባቸው» አለው፡፡

እስክንድር ሰው ሰራሽ ጥርሱን ወደ ውስጥ ገፋ አደረገና፣ «ፍፁም ካልሆነ ፍጡር ፍፁም ነገር መጠበቅ እንዴት ይቻላል? ሀሳቡ መሆን ነው» ብሎ ሳቡን ከማንባሩ ላይ ከጠረገ በሁዋላ «ውድምድም ነው ያደረከኝ፡፡ በእውነት ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው፡፡ የነበረኝ አንድ ተስፋ ይህ መፅሀፍ ነበር፡፡ እና፣ አሁን. . . ምን ቀረኝ? ምንም» አለና፣ ረቂቁን ጠረጴዛው ላይ ጣለው፡፡

ሲራክ በነገሩ ተገርሞ ወደ ሁዋላ ተለጠጠና ትኩር ብሎ እያየው፣ «ብል ተወሁ ወንድሜ! አንተን ሆነ ማንንም ተስፋ

@OLDBOOKSPDF



የማስቆረጥ ፍላጎት የለኝም፡፡ እኔ ማንንም አልመቀኝም፡፡ ግልፅ መሆኔ አስቆጥቶህ እንደ ሆነ ይቅርታ፡፡ ለኪነት ያለኝ ፍቅርና አክብሮት ነው ግልፅ እንድሆን ያደረገኝ፡፡ ጆሮህ ለመስማት የፈለገውን ብቻ ከኔ ለመስማት መጥተህ እንደሆን ተሳስተሃል፡፡ የተሰማኝን ነግሬሃለሁ፡፡ ነገሬ አበሳጭቶህ ከሆነ አዝናለሁ፡፡ የኪነት ሰዎች ሲባሉ ስለ ራሳቸው ያላቸው ከፍተኛ አስተያየትና ፍቅር ብዙውን ጊዜ እውር ያደርጋቸዋል፡፡ ቆዳቸው ስስ፣ አመላቸው ቀብጥብጥ፣ ቁጡና አኩራፊ ከመሆናቸውም ሌላ፣ ትንሽዋ ነገር ሁሉ ስሜታቸውን ትጎዳለች፡፡ ነገር ግን፣ ይህም ሆኖ፣ ፍፁምነትን ለመፈለግ የማይጥር ከያኒ ከመወለዱ በፊት የሞተ ነው፡፡ ይህንንም በመናገሬ ይቅርታ፡፡ እዚህ ላይ ብናቆም ይሻላል›› ብሎ ለመነሳት ሲል፡-

‹‹አልገባህም›› አለው፡፡

‹‹ምን ነው ያልገባኝ? ብሎ ተመልሶ ቁጭ አለ፡፡

‹‹ያልከኝን ሁሉ ብጨምር፣ ሳንሱሮች የሚያሳልፉ ይመስልሃል? ለምን ሀሳባዊ ትሆናለህ?›› አለ፡፡

‹‹የሳንሱሮች መቀስ ያንተ ጉዳይ አይደለም፡፡ ምን ይቆርጣሉ? የትኛውን ያሳልፋሉ እያልክ በማሰብ መጣፍ የለብህም፡፡ የደራሲ ፈንታ እውነተኛ ስሜቱን በትክክል መግለፅ ነው›› አለና፣ በብስጭት ብጉሩን ፍርጥ አደረጋት፡፡

እስክንድር የምራቁን ካፊያ ከጠረጴዛው ላይ በእጁ ጠረግና በቀሉት ትላልቅ አይኖቹ ሲራክን እያማተረ፣ ‹‹ለዚህ ነው'ኮ ሀሳባዊ ነህ የምልህ›› አለው፡፡

ሲራክ ተቆጥቶ፣ ‹‹ሀሳባዊ አይደለሁም?›› ብሎ፣ ቁጣውን ጫልሶ በማብረድ ደብዘዝ ያለ ፈገግታ እያሳየው፣ ‹‹ህልም እልማለሁ፡፡ ህልሜ ግን የሰፊው ህዝብ ህልም ነው፡፡ ህልማቸውን ለማለም፣ ተረታቸውን ለመተረት፣ ሳቃቸውን ለመሳቅ፣ ልቅሶአቸውን ለማልቀስ፣ ጭንቀታቸውን ለመጨነቅ ነፍስ ትፈልጋለች፡፡ ነፍስ ለሰው ልጅ ያላትን ፍቅርና ምኞት ለመግለፅ ቃላት ያንሱአታል፡፡ የሰውን ልጅ ደስታና ስቃይ ሊገልፅ የሚችሉ ቃላት... ይህ አለም ከንቱ፣ የሰው ልጅ ህይወት ትርጉመቢስ እንደሆነ የሚገልፅ ቃላት... የሰው ልጅ ይህችን አለም ድል ለማድረግና ለመለወጥ እንጂ ድል ለመሆን ያልተፈጠረ መሆኑን የሚገልፅ ቃላት... በሰው ልጅ፣ መለያዩ ቃላት... ቃላት... ቃላት፡፡ ቃላት ብርቅ እንቁዎች ናቸው፣

@OLDBOOKSPDF



ግን በጥንቃቄ እናጌጥባቸውም፡፡ አዎን፣ በዚህ ከሆነ ሀሳባዊ ነኝ» አለው፡፡»

«ይህን ማለቴ ሳይሆን...»

«ታዲያ ምን ማለትህ ነው?»

«ማለቴ አንተ እንደምትለው ብዕፍ...»

«ገባኝ፡፡ ሳንሱሮች አያሳልፉም ማለትህ ነው፡፡»

«አዎን፡፡»

«ታዲያ ሳንሱር ቢያልፍ ባያልፍ አንተ ምን ቸገረህ? ያንተ ሃላፊነት የሚሰማህን መፃፍ ነው፡፡»

«ደራሲ መነበብ የለበትም? አላማው ዝም ብሎ መፃፍ ብቻ ነው? የጻፍከ ደራሲ ሁን ነው የምትለኝ? ከፃፍኩ መነበብ እፈልጋለሁ፡፡ ይህን ከፈለኩ ደግሞ አንዳንድ ስሜቶችን መግታት አለብኝ፡፡ ይህ ነው ተጨባጩ ነገር» አለው. . .

ሲራክ መቀመጫው ላይ ተመቻቸና፣ «ማንም ደራሲ መነበብ ይፈልጋል፡፡ ግን ዋናው አላማ መፅሀፍ አሳትሞ ማውጣት መሆን የለበትም፡፡ የደራሲ ተቀዳሚ አላማ ለኪነት ሀቀኛ መሆን ነው፡፡ የመጀመሪያውን መፅሀፌን አሳትሜ ሳወጣ የተሳሳትኩ እዚህ ላይ ነው፡፡ ለመነበብ ያለኝ ፍላጎት ስለ ገፋፋኝ አሁን ይቆጨኛል፡፡ በቶሎ ዝናን ለማትረፍና ከስመ ጥር ደራሲያን ጎን ለመሰለፍ የምጉዋጉዋ ከሆነ ስህተት ነው» አለ፡፡

እስክንድር ራሱን አከከ፡፡ ሰው ሰራሽ ጥርሱንም ወደ ውስጥ ገፋ አደረገ፡፡ ከሲራክ ባሻገር መስኮቱን ዘልቆ ሩቅ ተመለከተ፡፡ አይኑ ከአድማሱ ጋር ተጋጨ፡፡ የነበረው ተስፋ ከጉም ጋር በንኖ ሲጠፋ ታየው፡፡ አንድ ወር፣ ግፋ ቢል ሁለት ወር... ሰሙን የያዘው መፅሀፍ ታትሞ... ሰው እጅ ገብቶ ሲነበብ ለማየት የነበረው ተስፋ፣ ይታየው የነበረው ጣፋጭ ህልም... በሲራክ ክፋት ምክንያት... ድንገት መና ቅዠት ሆኖ ሲቀር... ደብዛው ሲጠፋ... ሲጨልም... የጋለው ስሜቱ ከስሎ አመድ ሲሆን ታየው፡፡ ህይወት መራራ ሆነችበት፡፡ ሲራክን ከልቡ ጠላው፡፡ ልቡን በጦር ቢወጋው ምንኛ ደስ ባለው ነበር. . .

@OLDBOOKSPDF



ሲራክ እስክንድርን ትኩር ብሎ ሲመለከተው ከቆየ በሁዋላ፣ «ለመሆኑ ለምንድን ነው የምትፅፈው?» ብሎ ጠየቀው፡፡

«ምን ማለትህ ነው?»

«ማለቴ ምን አላማ ኖሮህ ነው?»

«ድርሰት እወዳለሁ፡፡»

«ጥሩ፡፡ ግን የድርሰት ፍቅር ብቻ አይበቃም፡፡ ድርሰት ተልእኮ አላት፡፡ ያንተ ድርሰት ተልእኮ ምንድን ነው?»

«ከእኔና ካንተ የበለጡ አዋቂዎች ብለውት ብለውት ያልጨረሱትን ነገር እኔን ምን ትጠይቀኛለህ?»

«እኔ ስለ ሌሎቹ አልጠየኩህም፡፡ በድርሰትህ ምን ለመግለፅ ነው የምትፈልገው ነው ያልኩህ!»

«ሀቅ፡፡ ውበት፡፡ በድርሰት ሌላ ምን የሚገለፅ ነገር አለ?»

«የማን ሀቅ? የትኛውን ውበት፡፡»

«ይህን ርእዮታዊ ማጣህን ተውኝ!»

«ዋናው ጉዳይ ምን ሆነና... ቆይ እንጂ፣ አትቆጣ፡፡ እየሀ የደራሲያን አርእስት ጉዳይ የሰው ልጅ ነው፡፡ በዚህ ላይ እንስማማለን፣ አይደለም? እሺ፡፡ እዚህ ላይ የምንስማማ ከሆን የሚቀጥለው ጥያቄ፣ የሰውን ልጅ እንዴት ነው የምንመለከተው? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ነው፡፡ ህይወት ትርጉም የላትም? የሰው ልጅ ህይወት በሚሉአት ወጥመድ ውስጥ ሳይወለድ ተወልዶ እዚያው ውስጥ በግድ ኖሮ የሚሞት ምርጫ የሌለው አሳዛኝ ፍጡር ነው ማለት፣ ወይም፣ የለም፣ የሰው ልጅ ራሱንም ሆነ አለምን ለመለወጥ የሚችል፣ በስራው ለህይወት ትርጉም የሚሰጥ ጠንካራና ተስፋ ያለው ፍጡር ነው ብሎ ማመን፤ ከነዚህ ሁለት ተቃራኒ እምነቶች ውጪ ሌላ አመለካከት ሊኖረን አይችልም፡፡፡ ድርሰት ያንዱ ወይም የሌላው አመለካከት ነፀብራቅ ከመሆን ሌላ ምን ልትሆን ትችላለች?» ብሎ በልቡ እያዘነ፣ ነገር ግን እስክንድር ጥሩ መፅሀፍ እንዲፅፍም እየተመኘ፣ «በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ አይነት ሰው አትመስለኝም ነበር...» ሲል፡-

@OLDBOOKSPDF



እስክንድር አቀርቅሮ መሬት መሬት እያየ፣ «ባንድ ቃል፣ ምንም መፅሀፍ አልፃፍክም በለኝ!» አለው፡፡

ሲራክ ውሀ ቢወቅጡት ተመልሶ እምቦጭ እንደሚሉት ነገር ሆኖበት፣ ተበሳጭቶ ጠጉሩን እየነጨ፣ «እንደሱ አላልኩም!» አለ፡፡

«ታዲያ ምንድን ነው ስትል የቆየኸው?»

«እየህ እስክንድር፣ ለድርሰት ከወረቀት፣ ከብእርና ከቀለም ሌላ ተጨማሪ ነገር አለው፡፡ የኔ ፍላጎት ጥሩ መፅሀፍ ፅፌህ እንድታወጣ ነው፡፡ ጥሩ መፅሀፍ ፅፎ ለማውጣት ምን ምን ያስፈልጋል? አንደኛ፣ ደራሲው ነገሮችን ዘልቆ በማወቅ በመካከላቸው ያለውን ልዩነትና አንድነት የማሳየት ችሎታ እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ በሌላ አነጋገር፣ የደራሲ ተግባር አዲስ ነገር መፍጠርና ያንኑ ሰፋ አድርጎ ማስረዳት ማለት ነው፡፡

«ምን አዲስ ነገር ፈጠርኩ? ምን አዲስ ነገር ሰራሁ? ከዚህ ቀደም በሌሎች ያልተሞከረ ነገር ምን ሞከርኩ? በእያንዳንዱ ደራሲ አእምሮ ውስጥ መቀረፅ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ ይህ ወደ ሁለተኛው ነጥብ ያመራል፡፡

«ሁለተኛ፣ ያንድ ደራሲ የመፍጠር ችሎታ ብቻውን አይበቃም፡፡ ማንበብ፣ መመራመር፣ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ማን? ምን? ከዚህ ቀደም ሰርቶአል፡፡ ማን በምን ጉዳይ ላይ ምን አለ? ለአንድ ደራሲ ሰፋ ያለ እውቀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እውቀት ስል ከመፃህፍት የምናገኘው እውቀት ብቻ ማለቴ አይደለም፡፡

«ከህይወት በተግባር የምናገኘው እውቀት ሶስተኛው ነጥብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚገኘው ህይወትን—የሰዎችን ህይወት በማስተዋል፣ አነጋገራቸውን፣ አመለካከታቸውንና ጠቅላላ ሁኔታዎችን በመቅሰም ነው፡፡

«አራተኛ፣ ይህ ሁሉ ሆኖ፣ አንድ ደራሲ ለማንኛውም ነገር ጥሩ ልብና ስሜት ከሌለው ድርሰቱ ዋጋ አይኖረውም፡፡ ሆሬስ፣ 'ሊያስለቅስ የሚችል ደራሲ መጀመሪያ እሱ ራሱ ማልቀስ አለበት' እንዳለው ነው፡፡

«አምስተኛና የመጨረሻው ነጥብ፣ የደራሲው ነገሮች አሳምሮ የማየት ችሎታ ነው፡፡ ያንድን ነገር ተቃራኒን ማወቅ ካልቻለ፣

@OLDBOOKSPDF



ውበትንና ሀቅን ለማሳየት አንችልም፡፡ አንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች አሉዋት፡፡ ህይወትም እንደዚሁ ነች፡፡ 'ያንድ ህዝብ ህይወት፣ የሀቀኛ ከያኒ ልጆች ህይወት ነው' ያለው ማነው?›› አለና፣ በረጂሙ ተነፈሰ፡፡

‹‹አንድ ደራሲ ምናልባት ዘላቂነት ያለው ድርሰት ለማቅረብ የሚችለው፣ አንዳንድ የሚያጋጥሙት ነገሮች አሳዛኝ ቢሆኑበትም፣ ማንኛውንም ነገር እንዳመጣጡ በማወቅና ሰላገኘው ልምድ ያለ ፍርሃትና ያለ ይሉኝታ በመፃፍ ብቻ ነው፡፡ ሀቅን ከመሻት የበለጠ አደገኛም ሆነ አስደሳች ነገር የለም፡፡ ለዚህም ነው ሀቀኛ ደራሲ ምናልባት አድናቂዎች ቢኖሩት እንጂ ወዳጅ የለውም የምለው፡፡

እስክንድር ሰው ሰራሽ ጥርሱን በምላሱ ወደ ውስጥ ገፋ አደረገና፣ እሺ, አሁን ምን አድርግ ነው የምትለኝ?›› አለው፡፡››

‹‹የድርሰትህ ተልእኮ ምን እንደ ሆነ ማወቅ የመጀመሪያ ጥበብ ነው…››

‹‹እና?››

‹‹እና፣ እንደ ገና ፃፈው…››

‹‹ይህን መፅሀፍ?››

‹‹አዎን፣ ይህን መፅሀፍ፡፡››

‹‹ከሁለት አመት ልፋት በሁዋላ?››

‹‹እኔ ባንድ መፅሀፍ ላይ ሶስት አመት ሙሉ ስለፋ አለሁ፡፡ ምናልባት ሌላ ሶስት አመት ይወስድብኝ ይሆናል፡፡ የኪነት ምስዋ ላብና ደም ነው…››

እስክንድር ከተቀመጠበት ድንገት ብድግ ብሎ፣ ‹‹እኔ አላደርገውም! ለምን ገደል አይገባም!›› አለ፣ ላብ እያሰመጠው፡፡

ሲራክ ወንበሩ ላይ ወደ ሁዋላ ተለጠጠና፣ ‹‹እኔ አንተን ብሆን እንደ ገና ልፅፈው እሞክራለሁ፡፡ ጥሩ እርእስት ነው የመረጥከው፡፡ እና፣ ችሎታውም አለህ፡፡ በዚህ አለም በምንም ሁኔታ ተስፋ መቁረጥ የለብንም›› አለው ፡፡

@OLDBOOKSPDF

እስክንድር በመስኮቱ አሻግሮ ሩቅ ተመለከተ፡፡ አይኖቹ ከእድማሱ ጋር ተጋጭተው ተመለሱ፡፡ ፑርሱን ወደ ውስጥ ገፋና፣ «እድሜ ላንተ ከእንግዲህ ደራሲ አይደለሁም፡፡ ደራሲው እስክንድር ሞቶአል» ብሎ፣ በቡጢ ደረቱን መታ መታ እያደረገ፣ «በድን ነው የቀረው» አለና፣ ሬቂቱን እንስቶ... ላብ እያሰመጠው... በስቃይ እያጉዋራ... ቀዶ... ቦጭቆ... ሸርክቶ... ጣለው...

## ምእራፍ ፲

«ምን ሆንሃል?» አለችው ሰብለ፣ ሲራክ የቢሮዋ በር ከፍቶኝ ከመግባቱ፡፡

«ምን ሆኛለሁ?» አላት እያወቀ፡፡ ከንፈሮቹን በግድ አላቆ ፈገግ ለማለት ቢሞክርም አልሆነለትም፡፡ የሆነውን አጥቶት አይደለም፡፡ ወደ ሰብለ ቢሮ ሲመጣ እንደ እመቤት ሆይ ማከቤዝ በእሳብ እየተንሳፈፈ፣ ይህን ጉድ የአረቢያ ሽቱ ሁሉ አጥቦ ሲያጠፋው አይችልም፣ ግን የሆነው ሆኖአል፣ የሆነው ነገር ሳይሆን አይችልም እያለ፣ የእስክንድር ሁኔታ ከፊቱ አልጠፋ ብሎ ሲጨንቅ ነበር የመጣው፡፡

«ጣእረ ሞት መስለሃል» አለችው፣ የታችኛውን ከንፈርዋን ጣል አድርጋ፡፡

ወንበር ስቦ ተቀመጠና ስለ እስክንድር አንድ በአንድ ከነገራት በሁዋላ፣ «ነፍስ የገደልኩ ያህል ነው የሚሰማኝ፡፡ በጣም አዝናለሁ» ንገሩ ከቶኛ ፀፀቶኛል» አላት፣ እያጉተመተመ፡፡

ሰብለ በነገሩ ተገርማ ራስዋን እየነቀነቀች፣ «ምን ያሳዝንሃል?» አለችው፡፡

«አንድ ተስፈኛ ደራሲ እንደ መግደል ያህል ነው» አላት ተክዞ፡፡

@OLDBOOKSPDF 

‹‹ስለ ራሱ ሀቁን ማወቅ ካልፈለገ የራሱ ጉዳይ ነው፡፡ ምን ቸገረህ ታዲያ!›› አለችና፣ ጠረጴዛዋ ላይ ያለውን ዕጌረዳ አበባ አስተካከለች፡፡

ቀና ብሎ ዕጌረዳ አበባውንና የከንፈርዋን ቀለም ሳንጻጽር እንዳወረና፣ ‹‹ማንም ስለ ራሱ ሀቁን መስማት አይወድም፡፡ የእርጎ ዝንብ መሆን ምን ያስፈልጋል? ሀቁን ነገርኩትና ምን አተረፍኩለት? ገደልኩት በቃ፡፡ ተስፋ የቆረጠ ሰው ከሙት አይሻልም፡፡ በዚህ አለም የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር ተስፋ ብቻ ነው፡፡ ያለ ተስፋ መኖር አይቻልም፡፡ ይህችን መራራ አጭር ህይወት በመጠኑም ቢሆን ለማጣፈጥ ትንሽ ተስፋ በያንዳንዳችን ልብ እንዲያድር ማድረግ ያስፈልጋል›› አለ፣ ግንባርዋ ላይ የሚደፋውን ጠጉርዋን እየተመለከተ፡፡

የጠጉር አበጣጠርዋን ብትለውጥ ምን ትመስል ይሆን? ብሎ አሰበ፡፡ አበጣጠርዋን ለውጣ አይቶአት አያውቅም፡፡ ጠጉርዋን ግንባርዋ ላይ ከንበል ማድረግ ነው የሚቀናት፡፡

ቀና ብላ ሰፊ ፊትዋን አሳየችው፣ ‹‹ትምህርት እግኝቶበት እንደሆን በምን ታውቃለህ? እንዲያው ነው የምትጨነቀው›› ብላ፣ በአይንዋ ገረፍ አደረገችው፡፡

‹‹ሬቲቁን ቀድዶ ሲወጣ ብታዪው እንዲህ አትዪም ነበር፡፡ እብድ ሆኖ ነበር የወጣው፡፡››

‹‹ራሱን ይገድላል ብለህ ነው?››

ያልጠበቀው ጥያቄ ስለ ሆነበት ደነገጠና፣ ‹‹ያደርገዋል ብለሽ ነው? ጉዳዩን ከዚህ አንፃር አላየሁትም ነበር›› ብሎ፣ እየተከዘ የሚያፈርጣትን ብጉር በጣቱ ሲፈልግ ቆየና፣ ‹‹አሁን ሳስበው በጣም ብቸኝነት የሚሰማው ሰው ነው፡፡ ከዕሁፍና ከምግብ ሌላ ወዳጅ የለውም፡፡ ሲበላ ብታዪው፣ እያንዳንድዋን ጉርሻ በጥንቃቄና በፍቅር እያጣጣመ ነው፡፡ አቤት ጊዜ ሲወስድ! ቀስ ቀስ የሚበላ ሰው ያየ እንደሆን ይጣላል፡፡ አንድ ቀን ምን አደረገ መሰለሽ? እዚህ ቸርቺል ጎዳና ካስቴሊ አንድ ቀን ምሳ ጋብዞኝ ስንበላ ከጎናችን ካለው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠው ሰው ያዘዘውን ፓስታ ቀስ ቀስ እየጠቀለለ ጎረሰ ዋጥ ሲያደርግ አይቶ ተነስቶ ወደ ሰውዬው ሄደና፣ 'ወንድም፣ ጥድፊያው የት ለመድረስ ነው?' አለው፡፡ ያላበው ሰውዬ ጉንጮቹን በፓስታ እንደ ሞላ ከሳህኑ ላይ ቀና ብሎ አየው፡፡ በጥያቄው ግራ እንደ

 @OLDBOOKSPDF

ተጋባ ያስታውቃል፡፡ በእውነትም ያስመጠውን ሳብ ሲመለከቱት ከባድ ስራ ላይ እንጂ ምግብ ላይ ያለ አይመስልም ነበር፡፡ እስክንድር በጥያቄ አይን እያየው፣ 'አበላልህን ማለቴ ነው' አለው፡፡ 'ካበላሉ ምን አለው? አለ ሰውዬው፣ ቆጣ ብሎ፡፡ 'ቶሎ ቶሎ የሚበላ ሰው ላይ ወስፋቱ ይዘጋል' አለው፡፡ ሰውዬው ተናዶ ጠብ ያንሳል ብዬ ስጠብቅ፣ ቅባታም ከንፈሮቹን አላቆ በፈገግታ፣ 'ታዲያ ወስፋትህ እንዲከፈት ጀርባህን ዞር አድርገህ ለምን አትቀመጥም? ልትበላ ነው እንጂ ሰው ልትመለከት አልመጣህ! ወይስ የትራማጆች አበላል አለ እሉህ? ሆ ሆ... ወቾ ጉድ' አለው፡፡ እስክንድር በዚያው ሊያቆምልሽ ነው! 'በሰዎችና በእንስሳት መካከል ካሉት ልዩነቶች አንዱ አመጋገብ ነው፡፡ እንስሳት ይግጣሉ፣ ያግበሰብሳሉ፣ ያመሰኳሉ፡፡ ሰዎች ግን ይባላሉ፣ ይመርጣሉ፣ ያጣጥማሉ' ብሎ ወደ ጠረጴዛው ተመለሰና ምግቡን ትቶ ቁጭ አለ፡፡ 'ብላ እንጂ' አልኩት፡፡ 'በቃኝ አባክህ፡፡ ወስፋቴ እንዲ ከተዘጋ ለመብላት አልችልም' ብሎ በማንኪያው እየተጫወተ ሲያስብ ቆየና፣ 'እየህ' አለኝ፣ 'ያንድን ሙዚቃ ጣእም ለማድነቅ በርጋታ ሙዚቃውን ማድመጥ ያስፈልጋል፡፡ የተፈጥሮን ውበት በተመሰጦ ካላዩት ለማድነቅ አይቻልም፡፡ ማንኛውም ኪነት ትኩረትን ይጠይቃል፡፡ ምግብ ከቀረበ በሁዋላ የሚቀረው ነገር አግበስብሶ መዋጥ አይደለም፡፡ እያደነቅነው፣ እያጣጣምነው ልንደሰትበት ይገባል፡፡ እለዚያ ሰው የመሆን ትርጉም ምንድን ነው?' ብሎ እንደ ጨረሰ፣ ያ ሰውዬ ጆሮውን ጥሎ ያዳምጥ ኖሮ፣ ምግቡን ጨርሶ መጣና፣ 'ወንድም ለመብላት ሳይሆን ለመፈላሰፍ ነው የመጣኸው መሰለኝ? የደላው ሙቅ ያኘካል አሉ፡፡ የተራብ ሆድ ለአጉል ፍልስፍና ቦታ የለውም' አለና፣ መልስ ሳይጠብቅ ጥሎን ወጣ፡፡... የተነሳበት እርእስት ስለ ጠፋው፣ «ምን ነበር ልነግርሽ የፈለኩት?» ብሎ ጠየቃት፡፡

እርስዋም ሲታሰብ ቆየችና፣ «ብቸኝነት ያጠቃዋል ብለህ ነው የጀመርከው?» አለችው፡፡

«አ፣ አዎን፡፡ ብቸኝነት የሚሰማው ሰው ለራሱ እድኛ ነው፡፡»

«የኪነት ሰዎች ስትባሉ ብቸኛነታችሁን የምትወዱ ይመስለኝ ነበር፡፡»

«ሙዚቃችን ነው፡፡»

«ታዲያ ስለ እስክንድር ያሲጋህ ምንድን ነው?»

@OLDBOOKSPDF 

«ሲጋቴ» ብሎ፥ ቆም ካለ በሁዋላ፥ «የኪነት ሰዎች መፍጠር ሲያቅታቸው ማፍረስ ይጀምራሉ፡፡ ህይወት ምስጢርዋን ከጉያዋ ውስጥ ደብቃ አልበገር ስትላቸው ከሁሉም ነገር ጋር መጣላት ይቀናቸዋል፡፡ በመጀመሪያ አደገኛ ጠላት የሚሆኑት ለራሳቸው ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ጠጪዎች ይሆናሉ፡፡ አንዳንዶቹ ቁጭታቸውን በምግብ ይወጣሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ቤሰኞች ይሆናሉ፡፡ የባሰባቸውም ራሳቸውን ይገድላሉ፡፡ እንደ እብድ ተነስተው የሚጠፉም አሉ፡፡ በያይነቱ ነው፡፡ የኪነት ሰዎች ልዩ ፍጥረት ናቸው፡፡ በፈጠራ አለም ውስጥ ስለሚኖሩ ያምላክነት ስሜት ያጠቃቸዋል፡፡ ራሳቸውን ከሰው በላይ አድርገው ይገምታሉ፡፡ ስለ ራሳቸው ያላቸው አመለካከት በጣም ያበጠ ነው፡፡ አብዛኞቹ ሂስ አይቀበሉም፡፡ መንፈሳቸው ቁጡና ብስጩ ነው፡፡ ምን ልበልሽ? አብዛኞቹ የኪነት ሰዎች በመሰረቱ የህፃንነት ጠባይ አለባቸው» አላት፡፡

«እስክንድር የትኛውን መንገድ የሚመርጥ ይመስልሃል ታዲያ?» አለችው፡፡

«በየሆቴሉ እየዞረ ጥሩ ምግብ ማሳደድ ይጀምር ይሆናል፡፡ በዚህ ከተማ እሱን የማያውቅ የሆቴል ወጥ ቤት ሃላፊ የለም፡፡ እሱም የሚኖረው ሆቴል ቤት ውስጥ ነው፡፡»

ሰብለ ግንባርዋ ላይ ከንበል የሚለውን ጠጉርዋን በእጅዋ ነካ ነካ አድርጋ አስተካከለችና፥ «ስለ ኪነት ሰዎች ባህርይ ስትነግረኝ የማስበው ሌላ ነገር ነበር» አለችው፡፡

«ምን?»

«የሚግባቡዋችሁ ሚስቶች እንደሚያስፈልጉዋችሁ፡፡»

«አይምሰልሽ፡፡»

«እንዴት?»
«ራሳችንን በጣም ስለምንወድ ከማንም ጋር አንግባባም፡፡»

«ዝምታ ስትፈልጉ ዝም የምትል፥ ጨዋታ ሲያምራችሁ የምትጫወት፥ ልጆችዋን በጊዜ አስተኝታ፥ ቤትዋን አስተካክላ፥ ጥሩ ምግብ አዘጋጅታ፥ ለፈጠራ ስራ ጥሩ ሁኔታን ፈጥራ የምትጠብቅ ሚስት ብትኖርስ?» አለች፣ ድምፅዋን በመጠኑ ከፍ አድርጋ፡፡

 @OLDBOOKSPDF

ሲራክ በአሉታ ራሱን ነቅንቆና፣ «በዶራሲና በድርሰቱ መካከል በደስታ ለመኖር የምትችል ሴት የለችም፡፡ የዶራሲ ደስታው የብእሩ ቀለም እንደ መስከረም ጅረት ጠርቶ ያለ እክል ኮለል እያለ መውረድ ሲጀምር ብቻ ነው፡፡ የኪነት ሰዎችን ለሚያገቡ ሴቶች አዝናለሁ፡፡ የኪነት ሰዎችን ደስታና ስቃይ ለመካፈልም ሆነ የእሳማቸው አካል ለመሆን የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ፍፁም አስቸጋሪ ፍጡራ ናቸው» ብሎ እንደ ጨረሰ፣ ድንገት ስሜትዋ ሲለወጥ ታየው፡፡

ፊትዋ ላይ የነበረው ፈገግታ ጠፋ፡፡ ትኩር ብሎ ይመለከታት ስለነበረ፣ ያደረባትን ስሜት ለመደበቅ ዝም ብላ አቀረቀረች፡፡ ጠጉርዋ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ የሚከፋፈልበት ቦታ እናትዋ ላይ ካለችው ባይ ከብ ላይ አይኖቹ ሳንጻፍታ ተሜወቱ፡፡ ስሜትዋን የሚጎዳ ምን ነገር ተናገርኩ? ብሎ ራሱን ጠየቀ፡፡ መልስ ሊያገኝ አልቻለም፡፡ ወይም አስልቺቻት ይሆናል ብሎ አሰበ፡፡ በራሱና በእስክንድር መካከል በደረሰው ሁኔታ አእምሮው ተጨንቆ ስለነበረ እንደ ሌላው ጊዜ ሁሉ መፅሀፍ በእጅዋ ውስጥ ወይም በጠረጴዛዋ ላይ አለመኖሩን አሳጤነም፡፡ ስለ እስክንድር ሊያዋያት ወደ እርስዋ ለምን ሮጦ እንደ መጣ ሲያስብ የተጨበጠ ምክንያት ሊያገኝለት አልቻለም፡፡

ከእስዋ ጋር ፍቅር ይዞኝ ይሆን?... ሊሆን አይችልም... ወይም... ሲራክ ቂል አትሁን እንግዲህ፣ እያለ ሲያስብ ቀና ስትል አይን ለአይን ተጋጨ፡፡

«ማንበቡን ትተሽል እንዴ?» አላት፣ አይኑን ሰብሮ፡፡

«ህይወቴ ራሱ ልብ ወለድ ታሪክ ሆኖብኛል» ብላ፣ የታችኛውን ከንፈርዋን ግል አደረገች፡፡

«እና?» አለ፡፡

«እና፣ ህይወት ራሱ እንደ ልብ ወለድ ታሪክ እየተወሳሰበ ሲመጣ ልብ ወለድ ማንበብ ምን ያስፈልጋል? ዶራሲ ብሆን ፅፌው በወጣልኝ ነበር» አለች፣ በተሰባበረ ድምፅ፡፡

«ታዲያ ለምን አትሞክሪም?» አላት፣ በጋለ ስሜት፡፡

«ያልተሳካለት ዶራሲ መሆን አልፈልግም፡፡ ስቃዩ ይበዛል ብለኸኛል አኮ» አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF 

‹‹ግን እኮ፣ ደስታው የሚመነጨው ከስቃዩ ነው›› አላት፡፡

‹‹የኔን ተወውና ይልቅ ያንተ ከምን ደረሰ?›› ብላ ጠየቀችው፡፡

ከወንበሩ ላይ ተመቻቸችና፣ ‹‹ግድ የለሽም፡፡ እንደ ገና እጀምረዋለሁ፡፡ እንዴ ከጀመርኩት ማቆም የለም፡፡ ስራዬ ይኸው ብቻ ቢሆንም ምንኛ ጥሩ ነበር፡፡ ግን ዋናው ችግር እንደ ገና መጀመሩ ላይ ነው፡፡ የደራስያን ዋና ችግር መፅሀፉን ከመጀመርና ከመጨረሱ ላይ ነው፡፡ ምን ላይ ልጀምረው? የሚለው ጥያቄ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ የት ላይ ልጨርሰው? የሚለውም ጥያቄ እንደዚሁ ነው፡፡

‹‹ግን ጭንቅላቴ ውስጥ አንድ ነገር እንደሚፈላ ይሰማኛል፡፡ ምን እንደ ሆነ ገና ለማወቅ አልቻልኩም፡፡ የመፅሀፉ ጠቅላላ አሳብ ጥሩ ሆኖ ሳለ፣ አንድ መሰረታዊ ነገር አልጨበጥ እያለ ያስቸግረኛል፡፡ አንድ ቀን ቁልጭ ብሎ ሲታየኝ በቃ–በገዛ ራሱ መንቆርቆር ይጀምራል፡፡ እና፣ ያኔ፣ ገፀ ባህርያቱን መንገድ እያሳየሁና እየተከተልኩ ዝም ብዬ ከእነርሱ ጋር መንጎድ ነው›› አላት፣ በሚቱ እየተነሳሳ፡፡

‹‹ቶሎ በጀመርክና ደስ ባለኝ›› አለችው፡፡

‹‹አታስቢ፣ እጀምረዋለሁ፡፡››

‹‹ለምን መሰለህ ቶሎ እንድትጀምረው የፈለኩት?››

‹‹ለምንድን ነው?››

‹‹የመጀመሪያው ረቂቅ በእኔ ምክንያት ስለ ተቀደደ ብቻ አይደለም፡፡ እርግጥ ሃላፊነት ይሰማኛል፡፡ ዋናው ምክንያቴ ግን ስሜቱ የተቀጣቀሰበት መፅሀፍ ተጀምሮ ሲያልቅ ለማየት ስለጓጓሁ ነው›› ብላ፣ አይንዋ ሰበር አደረገችና፣ ያላባት ይመስል ፊትዋን በመሃረም ጠረገች፡፡

‹‹ይልቅ አሁን ከባድ ሃላፊነት ጣልሺብኝ›› አላት፣ ቁም ነገር በተመላበት ድምፅ፡፡

ቀና ብላ ፊት ለፊት እያየችው፣ ‹‹ባሌ ሳይገድልህ ፊጠን ብለህ ብትጨርሰው ይሻላል›› አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF

እየሳቀ፣ «ለምን ብሎ ይገድለኛ ልጄ?» አላት፡፡

እሰዋ ግን አልሳቀችም፡፡ በሚንቀጠቀጥ ድምፅ፣ «ፍቅረኛዬ የሆንክ መስሎት» አለች፡፡

«በሆንኩና በገደለኝ፡፡ ዕድሌ ነው» አላት፡፡

ዝም ብላ ቀረች፡፡ ዝምታው ስላላዋጣት ቦርሳዋን ከፈተች፡፡ የማትፈልገውን ነገር ነበር የምትፈልገው፡፡ ቦርሳዋን ዘጋችና መልሳ አስቀመጠችው፡፡ ከወንበርዋ ለመነሳት ቃጣት፡፡ ግን አልተነሳችም፡፡ ከንፈሮችዋ ሲንቀጠቀጡ ታዩት፡፡ –እፏን በቆረጠው ኖሮ፣ አለ፡፡

«ማን ከለከለህ» አለች፣ ከንፈርዋን ጣል አድርጋ፡፡

ጆሮውን ማመን አቃተው፡፡ –ይህን ያህል ጊዜ ለካስ ጅል ኖረሃልና ሲራክ፣ አለ በልቡ...

## ምእራፍ ፲፩

– ቀኑ ምን ነበር? አለ፡፡

ጠዋት ሲወጣ ከቤቱ አጠገብ መንገድ ላይ ቁጭ ብሎ ምፅዋት የሚጠይቅ ለማኝ፣ «ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ አለሞቼ» እያለ አላፊና አግዳሚን የሚወተውተው መጥቶ ጆሮው ስለ ገባ ረቡእ ነሐሴ 23 ቀን መሆኑ ትዝ አለው፡፡ ቅዳሜ እንደ አመት ርቆ ታየው፡፡

ሲራክ ስለ ጊዜ ተጨንቆ አያውቅም፡፡ ጊዜን የሚለካው በየቀኑ በሚፅፋቸው ገፆች ቁጥርና በወረቀት ላይ በሚያሰፍራቸው ቃላት ብዛት ሲሆን፣ ጊዜውን እንዴት እንዳሳለፈም ሆነ መጥቶ የሄደው ቀን ምን ትርጉም እንደ ሰጠው የሚመዝነው በፅሁፉ ሂደት ነበር፡፡ ከዚያ ውጭ ለጊዜ የተለየ ትርጉም ሰጥቶት አያውቅም፡፡ አሁን ግን... ጊዜ ድንገት የፊጥኝ ታስሮ የቆመ መሰለው፡፡ ቅዳሜ በጣም ራቀው፡፡ ጊዜን እንደ ፈለገው ወደፊት መግፋት ቢቻል ምን ነበረበት? ሲል ራሱን ጠየቀ፡፡ ጊዜ ጨቋኝ ጌታ ነው፣ ከጊዜ ጭቆናና ነውጥ የምናመልጠው በሞት

@OLDBOOKSPDF



ብቻ ነው ወደ ዘለአለማዊ ጭለማ ዘሎ በመግባት፡፡ እና+ ፍፃሜ ይሆናል፡፡

ደህና ሰንብት ጊዜ አለ፡፡

ቅዳሜ፡፡

– ወቸ ጉዱ! ለቅዳሜ ቀጠሮ ደህ ሁሉ ስልቻ ሙሉ ፍልስፍና! ብሎ ራሱን ነቀነቀና፦ ለመሆኑ ምን አይነቱ እውር ኖሬአለሁ በፈጠራችሁ! አለ፡፡

ሰብለ መጥታ ከፊቱ ድንቅ አለች፡፡

– ማን ከሰከሰህ?

– ማንም፡፡

– ወይስ እኔ ሴትዋ እንውጣ ብዬ እስክምጠይቅህ ድረስ ነው የምትጠብቀው?

– ምን ቀርጦሽ? መቼ እንውጣ?
– ቅዳሜ፡፡ ከሰንት በሁዋላ በሰምንት ሰዓት፡፡

– ቅዳሜ በጣም ራቀብኝ፡፡ ቆይ እስቲ፡፡ ሰስት ቀን ተኩል፡፡ ሰስት ሌሊት ተኩል፡፡ ሰንት ሰአት ይመስልሻል? ሰማንያ አራት ሰአት፡፡ ደቂቃው ሰከንዱ ሲቆጠር ደግሞ አቤት ቅዳሜ መራቁ! መአት አመት ነው የሆነብኝ…

– ሰንት ዘመን ታውሮ የኖረ ሰው ነገ አይንህ ይበራልሃል ቢሉት…

– እምን፣ ዛሬን እንዴት እድሬ አለ ይባላል፡፡

– ግን እስከ ዛሬ ድረስ እንውጣ ብለህ ያልጠየከኝ ለምንድነው ክርተህ ነው?

@OLDBOOKSPDF



– ወኔ እጥቼ ነው፡፡

– ምን ነው፣ አስፈራሰሁ?

– የለም አታስፈሪም፡፡ ከዕሁሌ ውስጥ ብቅ እያልሽ ታስቸግሪኝ ነበር፡፡ ወኔ እጥቼ ነው ያልነገርኩሽ፡፡ ወኔ እግኝቼ ብነግርሽም ምን እንደሚሰማሽ አስቀድሜ ስለማውቅ ተናግሬ ጥሩ ግንኙነታችንን ላበላሸው አልፈለኩም፡፡

– እውነትክን ነው? ብላ ችርችም ያሉትን ውብ ጥርሶችዋን እያሳየችው ስትስቅ ከቀን እንቅልፉ ነቃ፡፡ ሰብለ አጠገቡ የለችም፡፡

ሰባት ሰአት ሆኖ ሰው ሁሉ ለምሳ ሄዶአል፡፡ ባዶ ቢሮ ውስጥ ብቻውን ነበር፡፡ የቆየ የሲጃራ ጢስ ትንፋግ አፈነው፡፡ ሳይጠይቃት የቀረው አንድ ነገር ትዝ አለው፡፡ ቅዳሜ፡፡ በስምንት ሰአት ፡፡ ግን የት? ከስሜቱ የተነሳ የሚገናኙበትን ቦታ አልጠየቃትም ፡፡ ከሰአት በሁዋላ እጠይቃታለሁ ብሎ ተነስቶ ወጣ፡፡ ሩቅም አልሄደ፡፡ ሌላ ችግር ብቅ ብሎ ታየው ፡፡ የምንገናኝበትን ቦታ ብትነግረኝስ ከዚያ በሁዋላ የት እወስዳታለሁ ብሎ አሰበ፡፡ ያውም በጠራራ ፀሀይ!

ምን አይነት አለም ነው? ሰው የሚዕፍበት ቦታ ሲያጣ... ፍቅረኛውን የሚያፈቅርበት ቦታ ሲቸግረው... ቡና ቤት ሲኒማ ቤት? አልበርጎ? ... በቀን? ... ፈፅሞ አይሆንም ... በፈጠረሀ አስብ ቢራክ አለ፡፡ ወዲያውኑ አንድ ሀሳብ ድንገት መጥቶ ጭንቅላቱን መታው፡፡ አለክንድር... እውነትም... ግሩም ቦታ ነው... ግን እንደዚያ ተቀይሞኝ ሄዶ አሁን እንዴት አድርጌ አይኑን አየዋለሁ?... ያውም የመኝታ ቤቱን ቁልፍ እንዲሰጠኝ?... ከቶ አይል... ግና ምናባቱ፣ ችግሬ ይገባዋል፡፡ ደራሲ ነው፡፡ እኔም ደራሲ ነኝ፡፡ በመካከላችን የምንጋራው ስሜት አለ፡፡ ቢቀየመኝም ቅሉ... ግን እኮ እርስዋስ ብትሆን በጠራራ ፀሀይ መውጣቱን ምን አስመረጣት... አይ ሴቶች፣ ከፈለጉና ከመሰላቸውኮ የማያደርጉት ነገር የለም! እንደ ወንድ አይደሉም፡፡ ደፋሮች ናቸው፡፡ አንዴ ከቆረጡ የሚመልሳቸው ሃይል የለም፡፡ በል ቢራክ፣ ልብህ በርታ ይበል፡፡ ከአለክንድር ሌላ ምርጫ የለህም፣ እያለ ሲያስብ ቆየና ሲይቸንቶ አስቁሞ «ፒያሳ» አለው፡፡

«ሃምሳ ሳንቲም ይከፍላሉ»

@OLDBOOKSPDF


«ምነው ቅርብ አይደለም እንዴ»

«መኪናዋ በሙሉ አይደለምካ የምትሄደው» ብሎት ጥሎት ሊሄድ ሲል፣ «በል እሺ ወንድሜ» አለውና ገባ፡፡

– ከርካሳዋ ሲይቼንቶ እየተንከራከሰች፣ እያማረረች እያቃሰተች ስታዘግም፣ በዚህ አለም ምን ምርጫ አለ? የሲይቼንቶ ነጂዎችን ፈቃድ መፈፀም፣ የሚስቶችን፣ የቢሮ አለቆችን፣ የቀበሌ ሹሞችን ፈቃድ መፈፀም – ሁልጊዜ፣ ከእንቀልባ ጀምሮ እስከ መቃብር ድረስ፣ በሌሎች ፈቃድ መገዛት፡፡ ለመሆኑ ነፃነት የሚባል ነገር አለ? ምርጫ አለን? አንድን ነገር መርጠን ሌላውን የምንተውበትን ምክንያት በእርግጥ እናውቃለን? ለመኖር ለመሞት ምርጫ አለን? በማናውቀው ምክንያት እንኖራለን፣ በማናውቀው ምክንያትና ጊዜ እንሞታለን፡፡ በህይወትና በሞት መካከል ያለችውን ጊዜ ምንም ምርጫ አትተውልንም፡፡ ህይወት የሚባል ነገር ምንኛ ትርጉመ–ቢስ ነው? ግን ምንኛ ጣፋጭ፣ ምንኛ መራራ፡፡ ቅዳሜ ምንኛ ሩቅ፣ እያለ ሲያስብ ጭልጥ ብሎ ሄዶ ኖሮ ሲይቼንቶዋ ከመብራት ሃይል ህንፃ አጠገብ ደርሳ ስትቆም አላወቀም፡፡

ሲራክ ደንገጦ ለመውረድ ሲርበተበት ሲይቶንቶ ነጂው አይቶ «ምነው ባሳብ ክበለሉ» አለው ጫት ያበለዘውን ጥርሱን እያሳየው፡፡

«የዋጋ መናር አሳስቦኝ ነዋ» አለ ሲራክ፣ ኪሱ ውስጥ ሳንቲም እየፈለገ፡፡

«ባይከፍሉኝ ይቅር...»

ሃምሳ ሳንቲም አውጥቶ ሊሰጠው እጁን እየዘረጋ፣ «እንዴ ለምን ተብሎ? ወይስ መኪናህ በሙሁ ነው የምትንቀሳቀሰው?» አለው፡፡

ሳንቲሙን ሳለመቀበል ድርቅ ብሎ፣ «ኮብላይ እንደ ጥላ» የተባለው መፅሀፍዎ የሰጠኝ ደስታ ይበቃኛል፡፡ ግሩም መፅሀፍ ነው፡፡ ለምን ሌላ አይፅፉም?» አለው፣ ከመፅሀፉ ጀርባ ላይ ያለውን የሲራክን ምስል እያስታወሰ፡፡

ሲራክ ሞቅ አለው፡፡ የማያውቃቸው ሰዎች በመፅሀፉ ምክንያት አውቀውት አድናቆታቸውን ሲገልፁለት ሁልጊዜ ሞቅ ይለዋል፡፡ ልቡ በደስታ ይፈነድቃል፡፡

«መፃፉንስ እፅፍ ነበር...»

@OLDBOOKSPDF



‹‹ታዲያስ?››

‹‹ትርፉ ኪሳራ… እዳ ብቻ ነው›› ብሎት፣ ሳንቲሙን ሊሰጠው እንደ ገና እጁን ዘረጋ፡፡

‹‹እርም፡፡ ይሙት ስልዎት…››

‹‹በል ደንበኛ እንሁን– በነፃ የምታጉዋጉዘ ከሆነ›› ብሎት፣ አመስግኖት ተለየው፡፡

በመብራት ሃይል ህንፃ አድርጎ ወደ ሰራተኛ ሰፈር ማሽቆልቆል ሲጀምር ጥሩ ቀን ነው ብሎ አሰበ፡፡ ሰብለ ለሰጠችው ቀጠሮ፣ አሁን ደግሞ የማያውቀው ሰይቼንቶ ነጂ ያሳየው አድናቆትና ያደረገለት ውለታ ልቡን በደስታ አሞቀው፡፡ –ዝነኛ መሆን ጥሩ ነው፡፡ ግን፣ ዝና የሚጠይቀው ዋጋ ቀላል አይደለም፡፡ ጥቂቶች ናቸው ዝናን የሚያተርፉት፣ ምክንያቱም መስዋእት ለመሆን በቁርጠኝነት የሚቀርቡት ጥቂቶች ናቸው፣ እያለ በዘውዲቱ ህንፃ አልፎ ወደ ቀኝ ሲታጠፍ እስክንድር የሚኖርበት ሆቴል ፊት ለፊት ታየው፡፡

ድንገት ወኔው ከዳውና ቆም አለ፡፡ ለመመለስ ቃጣውና ሲራክ ስለ ትዳሟ አስብ ብሎ በቀጥታ ወደ ሰማንያ አንድ ቁጥር አመራ፡፡ ፎቁን ሲወጣ በጣልያን ጊዜ የተሰራው ጣውላ ከሚያሰማው ማቃሰትና የመረረ ሰሞታ ሌላ ድምፅ አይሰማም፡፡ ልቡ እንደተንጠለጠለ ሄዶ በሩን አንኳኳኳ፡፡ መልስ አጣ፡፡ እንደ ገና ሞከረ፡፡ አሁንም መልስ የለም፡፡ –ራሱን እንዳልገደለ ተስፋ አለኝ፣ አለና ለሶስተኛና ለመጨረሻ ጊዜ ሲያንኳኳኳ፣ ‹‹ማን ነው?›› አለ እስክንድር ከውስጥ በጎረና ድምፅ ፡፡

ሲራክ በልቡ ተመስገን እያለ ‹‹ሲራክ ነኝ›› አለው፡፡ ከውስጥ ዝምታ፡፡ ፍፁም ዝምታ፡፡ እስክንድር ልከፈትለት ወይስ ልተወው እያለ ከራሱ ጋር ክርክር ሲሟገት በአይኑ ህሊናው ታየው፡፡ ባልበ ‹‹ሚርድ›› ሲለው፡፡

‹‹ምንነው አትከፍትልኝም?›› አለ፣ ጥርጣሬና ልመና በተቀላቀለበት ድምፅ፡፡

ከውስጥ ኮቴ ተሰማው –ሚርድ –ሚርድ –ሚርድ –ሚርድ በሩ ተከፈተ፡፡

@OLDBOOKSPDF



ሲራክ እግሩን ሲያስገባ ሙስኪ ትንፋሽ ገፈተረው። ከቡና ጠረጴዛው ላይ ግማሽ ጠርሙስ ሙስኪ፣ እምቦ ውሀና ጭላጭ ያለበት ብርጭቆ ይታያሉ። በእንግሩ አረንጉዋዴ ሰፋፊቹና ተንጣለው የሚታየው አረንጉዋዴ ምንጣፍ ከብጫ መጋረጃዎቹ ጋር ተዋህደው መንፈስ ተገዘተገዘ፣ ረጋ ያደርጋሉ።

ሲራክ የሙስኪውን ጠርሙስ እየተመለከተ፣ «ከመቼ ወዲህ ነው ሻል በተን ከሙሲኪ ጋር መጋተር የጀመርከው?» አለው።

ባሙና «እያገባህም! ብሎ መለሰለትና፣ «ስለ መፅሐፉ እንደሆን የመጣኸው ምንም ነገር ለመስማት አልፈልግም። ይበቃል። የሞት ጉዳይ ነው። ሙት መቀስቀስ አይቻልም። እንዲያውም በጣም ሳስብበት ነበር። ልክ ነበርክ። ደራሲ አይደለሁም። ነኝ ብዬ ራሴን ሳታልል ነው የቆየሁት። ሀቁን ስለ ነገርከኝ አመሰግናለሁ።ስለ አድራጎቴ አዝናለሁ። ጅል ነው የሆንኩት። አሁን ስለ እሱ ምንም መስማት አልፈልግም» አለው ቁና ቁና እተነፈሰ።

ሲራክ ራሱን ነቀነቀና፣ «የእውነተኛ ደራሲ ንዴት ነው የያዘህ። ጥሩ ምልክት ነው» አለና፣ እቅፍ አድርጎ ለመያዝ ተዘጋጅቶ የሚጠብቅ አረንጉዋዴ ሶፋ ላይ ሰውነቱን ወረወረና እግሮቹን ዘረጋ።

«ስለ ድርሰት፣ ስለ ደራሲ ምንም ነገር መስማት አልፈልግም ብዬሃለሁ። ያንተም ሆነ የማንም ርህራሄ አያስፈልገኝም። የተናገርከው ሁሉ ሀቅ ነው። ሀቁን ፊት ለፊት እያየሁት ነው» አለና፣ ሙሲኪውን አንስቶ ባንዴ ትንፋሽ ጨለጠው።

ሲራክ የሚያፈርጣትን ብዙር በጣቱ እየፈለገ፣ «በመጠጣት ነው ሀቁን ፊት ለፊት የምታየው?» ብሎት ራሱን ነቀነቀ።

ሌላ ሙስኪ እየቀዳ፣ «ሀቁን እንዴት እንደማየው የራሴ ጉዳይ ነው። አንተን አያገባህም» ብሎ፣ ከቡና ጠረጴዛው ስር ብርጭቆ አወጣና፣ «አንተም ዘፈለክ ጠጣ። ራስክን ሙስኪ ውስጥ አስጥመው። እና፣ ድርሰት ጀሀንም ይግባ!» አለና፣ የሙስኪ ብርጭቆውን አነሳ።

ሲራክ ራሱን እየነቀነቀ ለራሱ ሙስኪ ቀዳና፣ «አስክንድር እኔ ችሎታ የለህም አላልኩም። ጥሩ የድርሰት ችሎታ አለህ... እውነቱን ነው። የጠቆምኩህ አንዳንድ ቴክኒካዊ ጉድለቶችን ነው... ቆይ እንጂ!» አለ፣ ትከሻውን ሲሰብቅ እያዬ፣ «እየህ፣ ስለ ራሳችን መፅሐፍ ንባራዊ አስተያየት ይኖረናል ማለት ዘበት ነው። ጉድለቱን

@OLDBOOKSPDF


ማየት ያስቸግረናል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እውር እንሆናለን፡፡ ፍቅር እውር ነው ይሉ የለም? እንደዚያ ነው፡፡»

እስክንድር ራሱን ከስተር አድርጎ የቀሉትን አይኖቹን በብስጭት እያጉረጠረጠ፣ «አባክህን ተውኝ! አሁን ሰላም ነው የምፈልገው፡፡ ተውኝ፡፡ ስለ መፅሀፍ መስማት አልፈልግም፡፡»

ሲራክ ቆጣ ብሎ፣ «እሺ፡፡ ለማንኛውም ነገር እኔ የመጣሁት ስለ መፅሀፉ ላነጋግርህ አልነበረም» አለ፡፡

«ሬሳዬን ልታይ ነው የመጣኸው፡፡»

«ራስክን ልትገድል አስበህ ኖሮአል?» አለው ፍርጥም ብሎ፡፡

«እሱም ታላቅ ድፍረትን ይጠይቃል፡፡ እኔ ወኔ የለኝም፡፡»

«እብደትን ብትል ይሻል ነበር» ብሎ፣ አቀማመጡን ለወጠና፣ «ሬሳህን ለማየት አልመጣሁም፡፡ እኔ የመጣሁት የክፍልህን ቁልፍ እንድትሰጠኝ ልለምንህ ነው፡፡ ፈቃድህ ከሆነ» አለው ፡፡

እስክንድር ነገሩ ግራ አጋብቶት ትኩር ብሎ እያየው፣ «ለምን ትፈልገዋለህ» አለው ፡፡

ሲራክ ውስኪውን ተጎነጨና አልኮል ደረቱን እየሰነጠቀ ሲወርድ እያጣመመ፣ «ለምን ይመስልሃል? ፍቅረኛዬን የምወስድበት ቦታ ስላጣሁ ነው፡፡ የምዕፍበት ቦታ የለኝም፡፡ አሁን ደግሞ ለፍቅር ቦታ ቸገረኝ፡፡ ለዚህ ነው የመጣሁት» አለው፡፡

እስክንድር በልቡ ሜርድ አለ፡፡ ከሲራክ ያልጠበቀው ነገር ነበር፡፡ ደግሞም ስለ መፅሀፉ መስማት አልፈለገም፣ ስለ እሱ እያነሳብኝ ቢለውም ከልቡ ጥልቀት ውስጥ እንዲያበረታታውና በራሱ ላይ ያለውን እምነት ለማደስ እንዲያስችለው ነበር የሚፈልገው፡፡

«ሸርሙጣ ቤት የማካሄድ መሰለህ?» አለው በድንገት፡፡

ሲራክ በጥፊ እንደ ተመታ ያህል ጆሮው ጮኸበት፡፡ ቃላቱ እንደ ሰለት ልቡን ሰነጠቁት፡፡ በሚንቀጠቀጥ እጁ የውስኪ ብርጭቆውን ለማንሳት ሲል ከነበለው፡፡ ውስኪው ከዙና ጠረጴዛው ላይ ተደፋ፡፡ «አዝናለሁ» ብሎ ለመሄድ ተነሳ፡፡

@OLDBOOKSPDF



እስክንድር ከት ብሎ ይስቅ ጀመር —«ሆ ሆ ሆ… እሂ ሂ ሂ ሂ»

«ምን የሚያስቅ ነገር ገጠመህ?» አለ ሲራክ አኩርፎ፡፡

«ፍቅረኛውን የሚወስድበት ቦታ አጥቶ የሚዞር ሰው ታይቶኝ ነው…እሆ ሆ ሆ —እሂ ሂ ሂ….»

«ጅል አትሁን!» ብሎት ወደ በሩ ሄደ፡፡

እስክንድር ሳቁን አቆመና፣ «ለመቼ ነው የምትፈልገው?» አለው፡፡

ሲራክ አላመነታም፡፡ ሃፍረቱንና ንዴቱን ዋጥ አድርጎ፣ «ለቅዳሜ፡፡ በስምንት ሰአት» አለ፡፡

« እሺ፡፡»

ሲራክ፣ ትንሽ ቀደም ብዬ እመጣለሁ» ብሎት በሩን ከፍቶ ሊወጣ ሲል፣ «ለምን እሺ እንዳልኩት ታውቃለህ?» አለው፡፡

ሲራክ ቆም ብሎ፣ «ለምንድን ነው?» አለው፡፡

«ቦታ አጥተህ እንዳትቀር ነዋ!»

ሲራክ በሩን ዘግቶ ወጣ —እሆ ሆ ሆ —ኢሂ ሂ ሂ…

## ምእራፍ ፲፪

…ሲራክ ከእስክንድር ክፍል ውስጥ ሆኖ በመስኮት ፊት ለፊት ከሚታየው አውራ መንገድ ላይ አይኖቹን በመትከል የሰብለን መምጣት በተንጠለጠለ ልብ ሲጠባበቅ የቅዳሜ መምጣትና የቀጠሮው ሰአት መድረስ እውን ያልሆነ እየመሰለው መንፈሱ ይዘበር ነበር፡፡

ሰአቱን ተመለከተ፡፡ ስምንት ሰአት ከአስር ደቂቃ ሆኖአል፡፡ ከፈችው አስር ደቂቃ የምዕተ አመት ያህል ነበር ያዘገመችበት፡፡ የልቡ

@OLDBOOKSPDF



ቅርፃ መፍጠንና የሥንዳንድዋ ደቂቃ ማዝገም አልጣማም ስሳሴት የተቀላቀለበት ነበር።
ተጨነቀ። ጭንቀቱ ስቃይና ደስታ

ትመጣ ይሆን? ወይስ አልመች ብሎአት ቀርታ ይሆን? ብሎ አሰበ። የመትረትዋን ነገር አእምሮው ሊቀበለው አልቻለም። የመስኮቱን መጋረጃ ገለጥ አድርጎ መንገድ መንገዱን ይመለከት ጀመር። የውሀ ሽታ—የአይን ሰቀቀን—የልብ ስመመን—ሰብለ ብቅ አላለችም—ባዶው መንገድ ባዶ ነበር — የባሰውን ባዶ ሆነበት።

ደጅ ያከፋል። ስሜቱ ማንባሩን ቁዋጥሮአል። ግን ሲራቡን ያልበው ነበር። እንገቱን እጁን፣ ብብቱን ያልበው ነበር። እንደ ከበሮ የሚመታውን ልቡን ማዳመጥ አስጠላው። ትርፍሮው ደርቆ ሲሰነጠቅ ተሰማው። ደስታውና ስቃዩ ባሰበት። ፊቱን ተጣጠበ። ከተዝታው ውሀ ተጎንጨና ጉሮሮውን አራሰ። ክራቫቱን አላላ። ተጠራራገና ፊቱን ግድግዳው ላይ ካለው መስታወት ውስጥ አየ። ወጣት የሆነ ሰው ከመስታወቱ ውስጥ መልሶ አፈጠጠበት።

በመዳፉ ወደ ታችና ወደ ላይ እያየ ሁሉቱንም ጉንጮቹን በማፈራረቅ አሸ። ጢሙን ከመምጣቱ በፊት በመላጨቱ ጉንጮቹ ለስልሰዋል። ከተላጨ በሁዋላ ጉንጮቹን ያሸበት ሽቶ መአዛ ገና ከላዩ ላይ አልጠፋም።

ቡላ ሱሪ፣ ጥቁር ኮት፣ ሰማያዊ ሸሚዝ፣ ጥቁር መስመር ጣል ያለበት ቀይ ክራቫት — የክት ልብሱን ነበር የለበሰው። ለመግደል፣ ድል ለመንሳት ተዘጋጅቶ ነበር ከቤት የወጣው። እና፣ የሚፈልጉትኖትን ሴት ልብ ድል ከማድረግ የበለጠ የሚያረካ ድል ምን አለ? ሲል ራሱን ጠየቀና የብብቱን ላብ እየጠላ፣ ከመስተዋቱ ውስጥ መልሶ የሚስቅበትን ወጣት ሲመለከት፦ ማፍቀር ወጣት ያደርጋል ለካ አለና፣ ክራቫቱን እስተካክሎ ከመታጠቢያ ቤቱ ወጣ።

ሰአቱን እንደ ገና መመልከት አስፈራው። ግን አላስቻለውም፣ ተመለከተ። ስምንት ሰአት ከሩብ ይላል። የልብ እንደ ከበሮ መምታት፣ የጉሮሮው እንደ ገና መድረቅና የሰውነቱ በላብ መስመጥ የባሰውን እያበሳጨው ከፍሉ ውስጥ ሲንጎራደድ ከቡናው ጠረጴዛ በር የተቀመጠው ግማሽ ጠርሙስ ውስኪ ታየው። ጠርሙሱ ላይ ዘለለበት። በአንዱ ትንፋሽ ወደ ውስጥ የጠረጠረው ውስኪ ደረቱን እየሰነጠቀ ሲወርድ ሞቅ ብሎት በረጅሙ ወደ ውጭ እየተነፈሰ ሲቀዳ፣ በሩ ሲንኳኳ ድንገት ስለ ሰማ፣ መለኪያው ከእጁ ሊወድቅ ምንም አልቀረውም ነበር። ጆሮውን ለማመን ስላቃተው ዝም ብሎ

@OLDBOOKSPDF 

ቀረ፡፡ በሩ እንደ ገና ተንኩዋንኩዋ፡፡ ልቡ ቀጥ አለ፡፡ ትንፋሽ አጠረው፡፡ መለኪያውን ከጠረጴዛው ላይ አስቀምጣለሁ ብሎ ሲርበተበት ከንብል አለበት፡፡ ዘሎ በሩን ከፈተ፡፡ አይኑን ማመን አቅቶት በሃይል ከፈተው፡፡ ትልቅ፣ ጥቁር የሀበሻ መነፀር... ፊት የሚሸፍን ጥቁር ሻሽ... ነጭ፣ ረጅም የዝናብ ልብስ—ከጥቁር መነፅሩና ከጥቁር ሻሹ መሀል ብቅ ብሎ የሚታይ ደካማ ፈገግታ፡፡ ከጥቂት ሴኮንድ በሁዋላ ነበር ሰብለ መሆንዋን ያወቀው፡፡

ሰው ከሁዋላ የሚከተላት ይመስል ሮጣ ወደ ውስጥ ገባች፡፡ በሩን ድርግም አድርጎ ዘጋና ከውስጥ ከቆለፈው በሁዋላ በእግሩ መቆም ያቃተው ይመስል ጀርባውን ከበሩ ላይ አስደግፎ ቆሞ ቀረ፡፡ ሰብለ መነፅርዋን አውልቃ ሮጣ ተጠመጠመችበት...

«በፈጠረሽ፣ ልብሽ እንዴት ነው የሚመታው? አላት፣ አንገትዋ ስር ተወሽቆ፡፡

«ያንተም ከሩቅ ይገፋተራል» አለችው፡፡

ለቀአት፣ ሁለቱን እጆችዋን ይዞ ፊት ለፊት እያያት፣ «እያንዳንድዋን ደቂቃ ምእተ አመት ሆናብኝ ነበር» ብሎአት፣ ሰፊ ደረቱ ላይ ለጠፋትና በጆሮዋ፣ «ቤቱም መቃብር ሆና ሲመስለኝ ትንሽ ቀርቶት ነበር፡፡ እንኩዋን መጣሽልኝ፡፡ ይህችን ቀንና ሰአት ምን ያህል በናፍቆት እንደቆየሁ ለመግለፅ ቃላት ይቸግሩኛል» አላት፣ ቁርጥ ቁርጥ በሚል ትንፋሽ፡፡

«ሴይቼንቶ አጥቼ ነው» አለችው፡፡

የዝናብ ልብስዋንና ሻሽዋን አውልቃ አንዱ ሶፋ ላይ ጣለች፡፡ ግንባርዋ ላይ ከንበል የሚለውን ጠጉርዋን ነካ ነካ አድርጋ አስተካከለች፡፡ አንገቱ ከፍት ሆኖ የጡት መያዣዋን በትንሹ ብቅ አድርጎ የሚያሳይ ነጭ እጅ ጉርድ ሸሚዝ፣ ጉርድ ሰማያዊ ቀሚስ ለብሳ ታኮው ወፈር ብሎ ረዘም ያለ ነጭ ጫማ አድርጋለች፡፡ ውበትዋ ከቶ ማረከው፡፡

ዞር ብላ በሚስቁ አይኖችዋ እያየችው፣ «ሸክ ብለሃል» አለችና፣ ከንፈርዋን ጣል አደረገች፡፡

«አንቺም ውብ ሆነሻል» ብሎአት ጎዶ አቀፋትና፣ «አሁን አለም ነው» አላት፡፡

@OLDBOOKSPDF

ጥብቅ አለችበት፡፡ ግን አልቆየችም፡፡ የገዛ ስሜትዋ አስፈራት፡፡ እና፣ ቶሎ ብላ ለቀቀችውና ክፍሉን እየዞረች ትቃኝ ጀመር፡፡ ክፍሉ አንድ ሆኖ መኝታ ቤቱና እንግዳ ማረፊያው የተለየው ከእንጨት በተሰራ ተጣጣፊ ማካለያ ነበር፡፡ ከበሩ አጠገብ ወደ ግራ ሲል መጠነኛ የሆነ የዕህፈት ጠረጴዛ ይታያል፡፡ በተለይም ማረፊያ ቤቱን የሞሉት፣ ግድግዳውን እየታከኩ ዙሪያውን፣ በፈረንሳይኛ መፃህፍት ታጭቀው የቆሙት የመፃህፍት መደርደሪያዎችና የእርጌ ጋዜጦች ክምር ነበሩ፡፡ ሲራክ ውስኪውን እየተጎነጨ በአይኑ ተከተላት፡፡

ክፍሉ ብርሃን እምብዛም አይገባውም፡፡ ብጫው የመስኮት መጋረጃ ወርቃማ ቀለም ይፈነጥቃል፡፡ ክፍሉ ሆን ተብሎ ለፍቅረኞች የተዘጋጀ ይመስላል፡፡

ከመፃህፍት መደርደሪያዎቹ በላይ ያለው ግድግዳ እስክንድር በየጊዜው ባገኛቸው ዲፕሎማዎችና የምስክር ወረቀቶች አጊጦ ይታያል፡፡ ሰብለ ዞር ብላ፣ «ጉደኛህ ዲፕሎማና የምስክር ወረቀት የሚያጠራቅም ፕሮፌሽናል ተማሪ ነበር መሰለኝ?» አለች፡፡

«ሁሉ አማረሽን ገበያ ኢታውጡዋት እንዲሉ፣ ያልለካከፈው ትምህርት የለም» አላት፣ እስክንድር የክፍሉን ቁልፍ ሰጥቶት ሲሄድ ሲል፣ «እንደ ቆመብህ ስትዞር ከምትሞት ብዬ ነው» ያለውን አስታውሶ ፡፡

ሰብለ አላዳመጠችውም፡፡ እስክንድር በልዩ ልዩ የወታደርና የሲቪል ልብስ የተነሳው ፎቶግራፍ ማርኮአት ትመለከት ነበር፡፡ መለስ ብላ፣ «ወታደር ነበር እንዴ» አለች፡፡

«አስተርጓሚ ሆኖ ኮንጎ ዘምቶ ነበር» አላት፡፡

«ራሱን ያመልካል መሰለኝ?» አለች፣ በልዩ ልዩ አቀማመጥ የተነሳቸውን ፎቶግራፎች እየተመለከተች፡፡

«የኪነት ሰው አይደል!»

«ቢሆንስ?»

«የፈጣሪን ሚና ይጫወታል፡፡»

«ታዲያ እግዜር ራሱን ያመልካል ልትለኝ ነው?»

@OLDBOOKSPDF



«እሱማ የሚያመልኩትን ፈጥሮአል፡፡»

«እንዴት? እንዴት?»

«ሰው ከሌለ እግዜር የለም ማለት ነዋ፡፡ እግዜር የሚባል ነገር የተፈጠረው ከሰው በሁዋላ ነው፡፡ በፊት አይደለም» ብሎአት ሄዶ ትከሻዋን ያዘ፡፡

ብርድ የመታት ይመስል ሰውነትዋ ሲንቀጠቀጥ ተሰማው፡፡ ማጅራትዋ ላይ ሳማት፡፡ ዝም ብላ ቀረች፡፡ ፊት ለፊት ሊያያት ፊልጎ ወደ እሱ አዞራትና አይን አይንዋን እየተመለከተ፣ «የኔ ውብ» አላት፡፡

ከንፈርዋን ጣል አደረገች፡፡ ወፍራም ከንፈሮችዋ ሊፈነዱ የደረሱ የፅጌረዳ እንቡጦች መስለው ታዩት፡፡ የሚያቃጥለው ትንፋሽዋ ገረፈው፡፡ እና፣ አይኖችዋ ውስጥ አየ... ምን ታየው? ... እልፍ አእላፍ ከዋክብት? ራሱን ለመቆጣጠር አቃተው፡፡ የእርስዋን ስሜት ከእርሱ የተለየ አልነበረም...

የኪሩቤል ዋሸንት — የመላእክት ዜማ — የሊቃነ መላእክት ውዝዋዜና ሽብሸባ — የዎፎች ዝማሬ — የገነት አየር — የማርያም መግደላዊት ሽቶ — የኔፈርቲቲ አንገት — የክሊዮፓትር አፍንጫ — የትሮይቱዋ ሄለን አይን — ዳዊትና ቤርሳቤህ — ሰለሞንና ሳባ — ከሰማይ ከዋክብት ሲረግፉ — ባህር ሲናወጥ — ሞገድ ሲነሳና ሲወድቅ — የራሄል ጩኸት — አደይ አበባ ሲፈካ — ሲፈነዳ — ምድራቱን ሲሞላ — ሁሉቱም ዝም — ዝምታ፡፡

ከረጅም ዝምታ በሁዋላ ሰብለ ቀና ብላ ፀጉርዋን እያስተካከለች፣ «ይችን ጊዜ ለዘለአለም የምትቆይ ብትሆን ምንኛ ጥሩ በነበር» አለች፡፡

«ለዘለአለም የሚኖር ነገር የለማ፡፡ ደስታው ያለው ባለን ጊዜ ከመጠቀም ላይ ነው ብሎ፣ ጉንጭዋን እየዳበሰ፣ «ውብ ነበርሽ፡፡ ውብ ነሽ» አላት፡፡

አንገቱ ስር ውሽቅ ብላ፣ «እጋፋሪ እንዳሻው ምስጢሩን ቢያገኙስ» አለችው፡፡

«የምን ምስጢር»

@OLDBOOKSPDF



‹‹ስለ ዘላለማዊ ህይወት፡፡››

‹‹እ! ያ ምስጢር›› ብሎ፣ እየሳቀና ፀጉርን እየዳሰሰ፣ ‹‹ሄዋን እዳምን ያልበሰለች እፀ በለስ ባታተምስው ኖሮ ስለ ህይወት የተሙዋላና የላቀ እውቀት ይኖረን ነበር፡፡ እዳም ያልበሰለ እፀ በለስ በልቶ ለዘር ማንዘሩ ያልበሰለ እውቀት አውርሶ ቀረ፡፡ ለማንኛውም ነገር ኢጋፋሪ እንዳሻው ሞትን ለማሸነፍ ለሰው ልጅ ተሰውሮ የቆየውን የህይወት ዛፍ ፈልገው ከእሱ ለመብላት እየተመኙ ነው፡፡ የህይወትን ዛፍ አግኝተው የበሉ እለት ጉድ ይፈላል›› አለ፡፡

‹‹ለምን?››

‹‹ለምን?›› ብሎ ጥያቄዋን ደገመና፣ ‹‹ምክንያቱም ከህይወት ዛፍ ማን በልቶ ማን ሊቀር? የማን ህይወት ረዝሞ፣ የማን ሊያጥር? የህይወትን ዛፍ በሞኖፓል ለመያዝ ከዚህ ቀደም ታይተው የማይታወቁ ጦርነቶች ይጀመራሉ፡፡ እና፣ እልቂት ይሆናል፡፡ ምፅአት ይመጣል፡፡ ነገር ግን ለማንኛውም ነገር ላንድ ፈላስፋ አንድ የህይወት ዘመን በቂው ናት፡፡ ሞኝ ዘለአለማዊ ህይወትን ቢያገኝ ምን ይሰራበታል?›› አላትና ግንባርዋ ላይ ሳማት፡፡

‹‹መቼ ነው የኢጋፋሪን ታሪክ የምትቀጥለው?›› አለችው፡፡

‹‹ምናልባት ዛሬ ወይም ነገ፡፡ በቅርቡ፡፡››

‹‹እስካሁን አልጀመርከም?››

‹‹ገና ነኝ፡፡››

‹‹ለምን? ለምን?›› ብሎ ቀለደባትና፣ ‹‹ስለ አንቺ ሳስብ ነዋ! ሌላ ለምን ይመስልሻል››

ቀና ብላ አይን አይኑን እያየችው፣ ‹‹ትድም ዝም ብዬ ምን ሳስብ ነበረ መሰለህ?›› አለችው፡፡

የከንፈሮችዋን ቅርፅ በሌባ ጣቱ እየተከተለ፣ ‹‹ምን ነበር የምታስበው?›› አላት፡፡

@OLDBOOKSPDF


ምንም ሳታመነታ፣ «ቤታችን ሆነን አንተ ቁጭ ብለህ ስትፅፍ፣ እኔ ደግሞ አጠገብህ ቁጭ ብዬ ሳነብ፣ ሁዋላ ፅፈህ የጨረስከውን ምእራፍ ስጥተኸኝ፣ ስለ እሱ ያለኝን አስተያየት ስትጠይቀኝና ስሰጥህ፣ እንደ ህልም ይታየኝ ነበር፡፡ ውብ አለም፣ የሰላምና የፍቅር አለም ይታየኝ ነበር» አለች፣ ህልምዋን በእውን የምታይ ይመስል አይኖችዋን ፊት ለፊታቸው ካለው ግድግዳ ላይ ተክላ፡፡

«ውብ ነው» አላት፡፡

በአሳብ ጭልጥ ብላ ከሄደችበት ተመለሰችና፣ «ምን?» አለችው፡፡

«አሳብሽ፡፡»

«አንተ ስትፅፍ እኔ አጠገብህ ቁጭ ብዬ፣ ጉልበትክን ተደግፌ ሳነብ አይታይህም?»

«ይታየኛል፡፡ ውብ ሆኖ ይታየኛል፡፡»

«ሲጠማህ የምትጠጣውን ሳቀብልህ፣ ሲበርድህ ጋቢ ስደርብልህ፣ ሲርብህ የምትበላውን ሳመጣልህ፣ አይታይህም?» አለች፣ ሩቅ ሩቅ እየተመለከተች፡፡

«ይታየኛል» ብሎ አይንዋን እየተከተለ፣ «ግን፣ ለደራሲ ይህ ብቻ አይበቃም» አላት፡፡

«ፍቅርና ታማኝነት ይቀርሃል ልትለኝ ነው?»

«ከፍቅርና ከታማኝነት ሌላ» ብሎ ፊትዋን በእጁ ዳበሰና፣ «ደራሲ ከሁሉም ነገር በላይ ነፃነቱን ይወዳል፡፡ እውነተኛ ደራሲ መፅሀፉን ከፀነሰበት ደቂቃና ሰአት ጀምሮ ፅፎ እስከ ጨረሰበት ቀን ድረስ ነፃነቱን ይመርጣል፡፡ ደራሲ አንድ መለኪያ ብቻ ነው ያለው እንከን የማይወጣለት ኪነታዊ ውበት ደራሲ ከፍቅረኛው ይልቅ በይበልጥ የሚያስበው ስለ ድርሰቱ ነው፡፡ እዚህ የተባለው ባለቅኔ ያለው ትዝ ይለኛል፡፡ ምን ብሎ ነበር መሰለሽ? 'ባለቅኔ ፍቅር ሲይዘው የፍቅረኛውን ሞት በልቡ ይመኛል' አለ ይባላል» አላት፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹የኪነት ሰዎች ስትባሉ ለሰው ስሜት ወይም ፍቅር ደንታ የላችሁም ማለት ነው!?›› አለች፣ በአባባሉ ተገርማ፡፡

‹‹ስራችን ሁሉንም ያጠቃልላል፡፡ ግን፣ ከሁሉም ነገር በላይ ነፃነት ያስፈልጋል፡፡››

‹‹አላማህ ከገባኝ ለምን ነፃነት ልሰጥህ አልችልም? እችላለሁ፡፡ አሳብህ ከድርሰትህ እንዳይለይ ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡ መፃፍ ሰልችቶህም ከወጣህ፣ ዞር ዞር ብለህ እንድትመጣ እፈቅድልሃለሁ፡፡ ፍቅርህ ጥላ ስር ቁጭ ብዬ እስክትመለስ እጠብቅሃለሁ፡፡ ከዚህ የበለጠ ነፃነት ምን ያስፈልጋል?››

ሳቀና፣ ‹‹ላንድ ሁለት አመት ታደርጊው ይሆናል፡፡ ግን›› ሲል፡-

‹‹ከዚያ በሁዋላ ምን እሆናለሁ?››

‹‹ከዚያ በሁዋላማ›› አለ፣ ‹‹ያው እንደ ሌሎቹ ሴቶች መሆንሽ አይቀርም፡፡ ስለ ልጆችሽ ደህንነት፣ ስለ ትዳርሽ መቃናትና መሙዋላት ማሰብ ትጀምሪያለሽ፡፡ ያኔ ደራሲው የሚታገልለት ኪነታዊ ውበትና ይህ ትግል የሚጠይቀው ነፃነት ጤና ይስጥልኝ! ደራሲ ደግሞ ለነዚህ ነገሮች ደንታ የለውም፡፡ ርግጥ ቢጋጣሚ የሚበለፅጉ አሉ፡፡ ግን የደራሲ አላማ ሀብት ማፍራት አይደለም፡፡ ኪነታዊ ውበትን መሻት ነው፡፡ ታዲያ ያኔ መፋጠጥ ሲመጣ፣ መግባባት ጠፍቶ ንትርክ ቦታውን ይወርሳል፡፡ ሚስቶችም እውነት አላቸው፡፡››

በጥሞና ስታዳምጠው ቆየችና፣ ‹‹እስተሳሰብህ እንዲህ ከሆነ ታዲያ ለምን ካንዴም ሁለት ጊዜ አገባህ?›› አለችው፡፡

ላቀረበችለት ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ቶሎ አልመጣለትም፡፡ ቆየና፣ ‹‹እኔ እንጃ፡፡ አለ አይደለም የህይወት ቅራኔ፡፡ እሱ የሚያስከትለው የህይወት እንቆቅልሽ ነው፡፡ ደራሲ በመሠረቱ ብቸኛ ሰው ነው፡፡ ብቸኛነቱን ይወዳል፡፡ ያኔ ነው ከልቡ ውስጥ የሚመነጨውን አሳብ ለማዳመጥና ለመፃፍ የሚችለው፡፡ ደራሲያን ፍፁም የሆነ ነፃነትን እንፈልጋለን፡፡ ግን፣ ግጁታም የዚሁ ነፃነት አካል ነው›› አላት፡፡

‹‹ተፈጥሮ ጨካኝ ነች›› አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹የሰው ልጅ አንድ ቀን ምስጢርዋን ያውቅባት ይሆናል›› ብሎአት፣ ወደ ተነሳሱበት አሳብ መለስ በማለት፣ ‹‹የደራስያን ፍላጎት የሚመዋባበት ስርአተ ማህበር ይመጣ ይሆናል፡፡ ከያንዳንዱ እንደ ችሎታው፣ ለያንዳንዱ እንደ ፍላጎቱ፣ የተባለው መርህ በተግባር በሚተረጎምበት ጊዜ፣ የኪነት ሰዎች ለዘመናት ሲናፍቁዋት የቆየችው የገነት በር ትከፈታለች፡፡ የማትከፈትበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ የሰው ተፈጥሮ እየተለወጠና እየተሻሻለ ይሄዳል፤ ከሚሉት አማዎች ውስጥ አንዱ ነኝ ግን፣ ምድራዊ ገነት ቢፈጠርም፣ የኪነት ሰዎች ረክተው የሚኖሩ አይመስለኝም፡፡ በደራሲ ልብ ውስጥ ርካታ የሚባል ነገር የለም፡፡›› አላትና፣ ሰብለን ትኩር ብሎ በዝምታ ይመለከታት ጀመር...

## ምእራፍ ፲፫

መስከረም ጠባ፡፡ የመስከረም ሥራ እንቁጣጣሽ ብላ ተግ አለች፡፡

ልጃገረዶች ሳዱላቸውን አሳመሩ፡፡ አደስ ተቀቡ፡፡ እንሶስላ ሞቁ፡፡ ወንዝ ወረዱ፡፡ ቄጠማ ለቀሙ፡፡ ዐዳዲስ ልብሳቸውን ለብሰው፣ አሸንክታባቸውን አጥልቀው፣ ‹‹አበባዬ ሆይ — ለምለም›› በማለት ተሰብስበው ብቅ አሉ — እንደ ሥራዴቱ፡፡ የወርሀ መስከረም ብሩህ ተስፋና ስሜት በምድሪቱ አስተጋባ፡፡

ጠፍ እያለ መጣ ምድሩ፡፡ ወንዙም እየጠራ፡፡ ኩል መሰለ ሰማዩ፡፡ ሜዳው፣ ጋራው፣ ሸንተረሩ ወርቃማ የአደይ አበባ ካባ ለበሰ፡፡ ደመራ ተደመረ፡፡ ተቀጣጠለ ችቦ፡፡ ‹‹እዮሃ አበባዬ — መስከረም ጠባዬ›› ተባለ፡፡

ከመጀመሪያ የቅዳሜ ቀጠሮአቸው በሁዋላ ሲራክና ሰብለ ወደ አሌክሳንደር ሆቴል እንደ መስቀል ዎፍ አንድ ጊዜ ብቅ ብለው ከህይወት ጋር አብረው ቀስመዋል፡፡ ሰሜታቸው የመስከረም ሥራ የአደይ አበባ፣ ኮለል ብሎ የሚወርድ የወርሀ መስከረም የጠራ ውሀ፣ ኩል መስሎ የተንጣለለው ሰማይ፣ የመስቀል ዎፎች ዝማሬ፣ የቢራ ቢሮዎች ውርውርታ፣ የአበቦች ማበብ፣ መፈንዳት ነበብራት ነበር፡፡ ሲራክ እንደ ተጋደመ በዛሬው እለት፣ በተለመደው ሰአት አዚያው ቦታ ከሰብለ ጋር

@OLDBOOKSPDF

ስላደረገው ቀጠሮ አሰበ፡፡ ስልክ ደውሎ፣ ‹‹ነገ በስምንት ሰአት ሊጠጣ እችላለሁ?›› ሲለው፣ እስክንድር፣ ‹‹ያልጋዉን ኪራይ ከከፈልክ ምናለ›› ያለውን አስታወሰ፡፡

‹‹በዱቤ ቢያዝልኝስ?››

‹‹ዱቤ ክልክል ነው፡፡››

‹‹እግዜር ራሱ ያልከለከለውን!››

‹‹እንዴት ቢባል?››

‹‹እሳ! ህይወት ምን መሰለችህ? በዱቤ ነው የምንኖራት!››

‹‹ሜርድ!››

ድምፁ ከወትሮው ለውጥ ነበረው፡፡ ለምን ይሆን? ብሎ አሰበ፡፡ ምክንያቱን በማሰላሰል የሚያጠፋው ጊዜ ስላልነበረው ተነስቶ መተጣጠብ ጀመረ፡፡ በመተጣጠቡ ላይ ጊዜ አልቆጠበም፡፡ ለባብሶ እንደ ጨረሰ ዕጌ ዮሀንስን እንደ ታቀፈች ገባች፡፡ ውባንቺ በትልቅ ትሪ ቃተኛ ይዛ ተከትላት ነበር — ለቁርስ፡፡

ሲራክ የሚወደውን ቃተኛ እየጎረሰ ሻሂውን ፉት ሲል፣ ዕጌ ልብ አድርጋ እያየችው፣ ‹‹ይህን ሰሞን መሽቀርቀር አባበዛህም እንዴ?›› አለችው፡፡

‹‹እጥላለሁ?›› ብሎአት ክራቫቱን እያስተካከለ፣ ‹‹እስቲ በሞቴ ንገሪኝ›› አለ፡፡

‹‹ድንቄም!›› ብላ፣ ዮሀንስን እያጎረሰች፣ ‹‹መሽቀርቀሩ ብቻ ሳይሆን ጠባይህም ተለውጦአል›› አለች፡፡

‹‹የንጭንጩና የኩርፊያው አባዜ ለቆሃል፡፡ መቁነንም እርግፍ አርገህ ትተሃል፡፡ የስራ ሰአትክንም ማክበር ጀምረሃል፡፡ ምን አግኝተህ ነው ልጄ?›› አለችው፡፡

ሻሂውን ፉት ብሎ ብርጭቆውን አስቀመጠና፣ ‹‹ምንም›› ካለ በሁዋላ፣ ‹‹ወጣትነት ይሰማኛል፡፡ እና፣ አንድ ሰው ወጣትነት ሲሰማው ደስ ደስ ይለዋል፡፡ በያለበት ሙዚቃ ይሰማዋል፡፡ ውበት ይታየዋል፡፡

@OLDBOOKSPDF


ወደ ውስጡ መመልከት ትቶ ወደ ውጭ ማየት ይጀምራል፡፡ ምን ልበልሽ—ከዘይዉት ጋር ፍቅር ይወድቃል›› አላት፡፡

ዮሀንስን ለማጉረስ እየታገለች፥ ‹‹ልብሰና ጌዋ የሰው ማንነት መለኪያ አይደለም የምትለኝ ትዝ ሲለኝ ይገርመኛል›› ብላ፥ ልጁ አልጎርስ ብሎ በማስቸገሩ ብስጭት ብላ፥ ‹‹ምን ነው ብትቆጣው?›› አለች፡፡

‹‹አንቺስ ምናለ ብትተዪው፡፡ ማስገደድ ጥሩ አይደለም፡፡ ህፃን ካልወፈረ ህፃን አይሆንም ማለት ነው?›› ብሎአት፥ ተነስቶ ሄዶ እጁን እየታጠበ፥ ‹‹አዎን—ልብሰና ጌዋ የሰው ማንነት መለኪያ አይደለም፡፡ የስሜት ነፀብራቅ ነው›› አላት፡፡

‹‹ታዲያ ስሜቴ ምንድን ነው ልትል ነው?››

‹‹የደስታ እያልኩሽ!›› አላትና፥ ዮሀንስን ግንባሩ ላይ፥ እሰዋን ደግሞ ጉንጭዋ ላይ ስሞ ሊወጣ ሲል፡-

‹‹የጤና ያርግልህ›› አለችው፡፡

ከሁሉም አብዮታዊ መዝሙሮች ደስ የሚለውን፥ ‹‹አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት›› የተባለውን እያዜመ ወጣ፡፡ ከቤቱ ወጣ እንዳለ ችሎ ማደር ሲያላዝን ሰማ፡፡ የጠር ሜዳው ጀግና ትዝ ብሎት፥ በዘይዉት ይኖር ይሆን?... ወይስ?... በማለት እያሰበ ሲሄድ፥ ኩሩው የመንደር ለማኝ ባርኔጣቸውን አንስተው እጅ ነሱትና፥ ‹‹እሜቴ ደህና ናቸው? ጤንነታቸውስ?›› ሲሉት፥ ሳንቲም ሰጣቸው፡፡ ሳንቲሙን እየተቀበሉ፥ ‹‹ጠበል ቢሄዱ ደግ ነበር፡፡ ሚጣት ወይም ጎርዶማ፡፡ ደግሞ ከራታቸው ኪዳን ምህረት ወይም እንጦጦ ማርያም፡፡ የገብርኤልም ጠበል ተአምር ይሰራል ይላሉ፡፡ ሲሉት፥ እንካሰው፥ ጋሼ ማንደፍሮ በምርኩዙ እንጥር እንጥር እያለ መጥቶ፥ ‹‹ቲቸር›› አለው፡፡ ለእሱም ሳንቲም ሰጠው፡፡ ማንደፍሮ፥ ‹‹አድሃሪ ሁላ!›› እያለ ሄደ፡፡ ‹‹ባሰው ባሰው ጊንደሬ›› ሁዋ ብሎ መኪናውን ይሰፋ ነበር፡፡

ሲራክ የሚወዳትን መዝሙር እያዜመ ሲደቸንቶ ለመያዝ ወደ ሰይጣን ቤት ሲያመራ፥ በእርግጥም ከዘይዉት ጋር ፍቅር እንደ ያዘው ይሰማው ነበር፡፡ ፍቅር ይዞኝ ይሆን? ብሎ ራሱን ጠየቀ፡፡ እርግጠኛ አልነበረም፡፡ የገረመው ነገር ቢኖር ሚስቱንም በልዩ የፍቅር አይን መመልከት መጀመሩ ነበር፡፡ ሁለት ሴቶች በአንድ ጊዜ እኩል መውደድ እንዴት ይቻላል? የሚል የዘይዉት እንቆቅልሽ ግጥሞች እንደ

@OLDBOOKSPDF



መብራት ምሰሶ ተገትሮ ሲያስብ ከየት መጡ ሳይል፥ «በእሳባ ብለው ምን ፈረዱኝ?» አሉት ሃጂ ሙስጠፋ ጠጋ ብለው፥ በረጃጅሙ ቁመናቸው ላዩ ላይ እያንገረበቡ።

ወደ ላይ እንጋጦ እያያቸው፥ «ሃጂ በእሳባ ብለው ቢተውኝና መፅሀፌን ቢያስጨርሱኝ ምናለበት!» አላቸው።

«እርስዎስ ቢለቁልኝና ልጃገረድ አግብቼ ለእሳባ ነፍስ እንዳበረክት ቢያደርጉኝ ምናለበት? የእሳባን ፈቃድ ከመፈፀምና አንድ መፅሀፍ ከመፃፍ የቱ እንደሚበልጥ እስቲ ፍረዱኝ። በእሳባ ብለው ፍረዱኝ» አሉት።

«ሃጂ!» አላቸው ተቆጥቶ፥ «የኔ ስሜትና ፍላጎት ሊገባዎት አይችልም። ቤትዎን ለቅቄ ብሄድ ደስ ይለኛል። ግን ተልእኮዬን መፈፀም አለብኝ። ግን እንደሚገባኝ ከሆነ፣ ልጃገረድ አግብተው የሚያስቀምጡበት ቤት አጥተው አይደለም የሚያስቸግሩኝ። ያፈራሁት ንብረት፥ የሰራሁት ቤት ለምን ባዳ እጅ ገብቶ ይቀራል? ለምን ሚስት አግብቼ፥ ልጅ ወልጄ እሱ አይወርሰውም? ብለው ነው። አይደለም? ለእሳባ ተጨማሪ ነፍስ ለማስገኘት ነው የሚሉት ይህን ነው። ሌላ አይደለም። እና፥ ተልእኮዬን እስከምፈፅም ቢታገሱኝ ምናለበት» አላቸው፥ በአይኑ ሊይዟቸው እየፈለገ።

«አቶ ሲራክ፥ በእሳባ ብለው። ከሰል እየተሸከምኩ ነግጄ የሰራሁት ቤት ነው። በድህ እቅሜ ጥሬ ግሬ የሰራሁ ስለሆነ ለእሱ ቤት ልዩ ትዝታ አለኝ። ለእሱ ቤት ልዩ ስሜት አለኝ። እንዳሉም ከስጋዬ የተከፈለ ልጅ ይዞት አይቼ ብሞት የምገባበት ጉድጓድ አይቆረቁረኝም። እንዲያው ለእሳባ ብለው፥ እሳባንም ባይፈሩ ሽበቴን አክብረው ቢለቁልኝ። ከእኔ የሚፈልጉት ሌላም ነገር ካለ ቢነግሩኝ» አሉት።

«ከእርስዎ የምፈልገው ትንሽ ትእግስት ብቻ ነው» አላቸው።

«ግድ የለዎትም። እንደሚያውቁት እኔ የገንዘብ ችግር የለብኝም። እሳባ ክብሩ ይስፋ እዱዬ ሞልቶኛል። የምፈልገው ቤቴን ብቻ ነው...» ሲሉ፥

«እና?» አላቸው፥ ቅንድቡን ከፍ ዝቅ እያደረገ።

«አንድ ሽህ ብር ልስጥዎትና ይልቀቁልኝ።»

@OLDBOOKSPDF 

«ሃጂ! እኔ የገንዘብ ፍላጎት የለኝም!»

«እሺ አምስት መቶ ብር ልጨምር...»

«በአላህ ብለው» እያሉ ሲለምኑበት፣ ጥሎአቸው ሲይቹንቶ ውስጥ ገባ...

መሥሪያ ቤቱ ሲደርስ ከወትሮ ለየት ብሎ የታየው ነገር ቢኖር የቢሮ ግድግዳዎች መዝጊያዎችና መስኮቶች በልዩ ልዩ መፈክሮች ማጌጣቸው ነበር፡፡ ምንድን ነው ነገሩ? በማለት እየዞረ ያነብ ጀመር፡፡ ከውይይት ክበብ መሸሽ አድሃሪነት ነው—ከውይይት ክበብ የሚሸሹ አለብዋሌተኞች በትግላችን ይመነጠራሉ—ውይይት ክበብ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርእዮተ አለም የምንታጠቅበት ብቻ ሳይሆን ታጥቀንም የመደብ ጠላቶቻችንን የምንታገልበት መድረክ ነው—የውይይት ክበቡን ማጠናከር አብዮቱን ማጠናከር ነው— ፀረ—ውይይት ክበብ አቋም ከፀረ—አብዮተኛነት ተነጥሎ አይታይም! የሚሉ ነበሩ፡፡

ወደ ቢሮው ሲያመራ አንድ ተላላኪ ከማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ማዘገር ሲለጥፍ አይቶ ለማንበብ ጠጋ አለ፡፡ «የውይይት ክበብ አባልነት ምንም እንኳዋን በግለሰቦች ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው ቢባልም፣ መማር የውዴታ ግዴታ መሆኑ ታውቆ ከዛሬ ጀምሮ ውይይት ክበብ በማይገባ በመስሪያ ቤቱ ሰራተኛ ላይ ርምጃ የሚወሰድ መሆኑን እስታውቃለሁ» ይላል ማዘገሩ፡፡ የባለስልጣኑ ፊርማ የተፈረመበት ቀለም ገና አልደረቀም፡፡

«ምን ታነባለህ? የሚል ድምፅ ከበስተኋላው ሰምቶ ዞር ሲል የመስሪያ ቤቱ ባለስልጣን መላጣ ራስ አፈጠጠበት፡፡ ከላይ ቀጥ ብሎ ወርዶ ከስር እንደ ጎራዴ ወደ አንድ ጎን ቆልመም የሚለው አፍንጫው አሽሙቀጠጠው፡፡ ስስ ሹል ከንፈሩ አሾፈበት፡፡ የሰውን ደካማ ጎን እንጂ በጎ ነገር ለማየት የተፈጠሩ የማይመስሉ ወደ ውስጥ የተጎለጎሉት ትላልቅ ቀይ አይኖቹ እንደ ጦር ወጉት፡፡

ቢራክ የአለቃውን አሽሙቀጣጠጥና አሾአፈ ፊት ለመሸሽ እየሞከረ፣ «የእርስዎን ማዘገር ነበር የማነበው» አለው፡፡

በገለጣ ግንባሩ፣ በቆልማማ አፍንጫው፣ በስስ ሹል ከንፈሩ፣ በማሽሙቀጥ እንደ ሽንኩርት እየላጠው፣ «ላብዮቱ መጠናከር መታገል ያስፈልጋል፣ አይመስልህም?» አለው፡፡

@OLDBOOKSPDF

ሲራክ የአለቃውን ጠባይ ስለሚያውቅ ጭጭ ብሎ ቀረ። አለቃው ሰውን በነገር ማጥመድ እንደሚወድ ያውቃል። ሰውን በነገር ማጥመድና ማማት፣ ስለ ሰው እንቃቂር ማውጣት፣ ስለ ሌላው ድንቁርናና ስለ ራሱ ትልቅነት ማውራት ልማዱ ነው። እንዜጥን ተጠግተውት ከሩቅም እንደ አንኮበር ቅጠል— እንደ ሳማ ይለበልባል። እንደ እቶን ምላሱ ይጋረፋል። እንደ እጋም እሾህ ይዋጋል። እንደ አሳቴ ሳሙና ሙልጭልጭ ስለሚል ጭራው አይያዝም። እሺም ሆነ እምቢ ማለቱ ስለማይታወቅ፣ ይህን ነው ያለው ብሎ ተወራርዶ የሚረታ የለም። እንደ ጊዜው አጎንብሶ፣ ከባለ ጊዜ ጋር ቀና ብሎ፣ መስሎና አስመስሎ በመኖር እጅ አይገኝለትም።

‹‹ዝምታው ምንድን ነው? ወይስ በማነጋገሩ አላመንክበትም?›› አለው፣ ሹል ስስ ከንፈሩን እያሾለበት።

ሲራክ ቀና ሲል ከግድግዳው ላይ፣ ‹‹ከውይይት ክበብ የሚሸሹ ፀረ–ማርክሲስቶች ብቻ ናቸው›› የሚል በትላልቅ ቀይ ፊደሎች የተጻፈ መፈክር ቦግ ብሎ ታየው። ቦግ አለበት።

የአለቃውን አሹአፈ አፍንጫ በነገር ለመምታት ፈለገ፣ ‹‹ትግል በማዘዝ መቼ ይሆንና!›› አለው፣ ኮስተር ብሎ።

‹‹ታዲያ ከውይይት ክበብ በመሸሽና የብዙሃኑን መድረክ በመናቅ ነው?›› አለው፣ በስስታም ቀይ ፊቱ እሽሙጥ እየላጠው።

ሲራክ ብሽቅ ብሎ፣ ‹‹ሀቀኛ ኮሚዩኒስቶች በማዘዝና በማስፈራራት ሰዎችን በግድ እንዲሰባሰቡ አያደርጉም ብዬ ነው›› አለው።

አለቃው እንደ ለመደው ሰሚነቱን ደብቆ፣ ‹‹ታዲያ በመለማመጥ ነው? ወይስ ለዘብተኛ በመሆን? ሲለው፣–

ሲራክ አሁንም ውስጥ ውስጡን እየበሸቀ፣ ‹‹ምሳሌ በመሆን ነው። ለህብረተሰቡ ደህንነትና ደስታ የሚጠቅመውን ነገር ሁሉ በማድረግ መስዋእት በመሆን፣ በተግባር በማሳየት ነው። በተግባር ካዩና ከተረዱ በኋ አላማን የማይከተል ፍጡር አለ ብዬ አላምንም። ለዚህም ነው ሀቀኛ ኮሚዩኒስቶች ጉዞአችን ረጂም፣ ግባችን ሩቅ ነው ብለው በመነሳት፣ ትእግስትን፣ ቆራጥነትንና መስዋእትነትን በተግባር እያሳዩ የማግባባትና የማስተማርን ረጅምና መራራ መንገድ የሚመርጡት። በኔ ግምት አርጩሜ ቆረጣንና የስልጣን ጦር ሰበቃን

@OLDBOOKSPDF



የሚመርጡት አወናባጆች ወይም ለስልጣን የሚቋምጡ አድርባዮች ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነቶቹ ሰዎች ለሶሻሊስታዊ ግንባታ ከሚሰጡት ጥቅም የሚፈጥሩት ጉዳት ይበልጣል፡፡ አብዮት የማካሄድና ሶሻሊስታዊ ስርአትን የመገንባት ታሪካዊ ተልእኮ ምን ጊዜም ቢሆን ሙሉ ፈቃደኝነትንና ነፃነትን ይጠይቃል›› አለው፡፡

‹‹እንዴት! እንዴት!?››

‹‹እንዴት ማለት፣ በግድ የዋጡት ነገር ያቅራል ማለቴ ነው፡፡ አብዮትና ሶሻሊዝም የነፃ ህዝብ ተግባራዊ ስራ ነው፡፡››

‹‹እና?››

‹‹እና፣ በግድ ማስገደድ ጥሩ አይደለም፡፡ በማስፈራራትና በማስገደድ ብዙ አድርባዮች ከማፍራት በሙሉ ፈቃደኝነትና ነፃነት ማርክሳዊ ጎዳናን የመረጡ ጥቂት ሀቀኞች ማግኘት ይሻላል፡፡ ኮሚዩኒስቶች በጥራት እንጂ በብዛት የማያምኑት ለዚሁ ነው፡፡ አይመስልዎትም?››

አለቃው መልስ አልሰጠውም፡፡ በስሊታም ፊቱ ሽምጥጥ አድርጎት ሲያበቃ ትክሻውን አሳይቶት ጥሎት ሄደ፡፡ አለቃው የአህያ ውሀ ጠጭ፣ የጭቃ ውስጥ እሾህ መሆኑን ስለሚያውቅ፣ በመናገሩ ባንድ ፊት እየቆጨው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ያለ ምንም ፍርሃት የተሰማውን በመግለፁ ደስ እያለው ሲያስብ፣ ሃጂ ሙስጠፋ ትዝ አሉት፡፡

የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጅ የደነገገውን ህግ ለመጣስ ከመሞከር አልፈው በገንዘብ ሊደልሉት ያደረጉት ሙከራ አናደደው፡፡ ባጋልጣቸውስ የሚል አሳብ መጣበት፡፡ ለምን አላደርገውም? አለ፡፡ የማጋለጡ ጥቅም አንድም ካለበት አብዮታዊ ግዴታ፣ አንድም የሃጂን ጭቅጭቅና ልመና አስወግዶ በቤቱ ውስጥ በሰላም እየኖረ መፅሀፉን ከመጨረስ እንግር ቁልጭ ብሎ ታየው፡፡ በዚሁ አሳብ ፀንቶ ቢቆ ብሎ ሊወስን ሲል፡- አሁን ሃጂን የመሰሉ ምስኪን ሰው የሚጋልጠው በእርግጥ ለአብዮቱ ብዬ ነው? ወይስ ለራሴ ጥቅም ስል ነው? የሚል ምግባራዊ ጥያቄ መጥቶበት፣ ካደረበት የህሊና ጭንቀት ባሻገር፣ ከሁሉም በላይ ሀቀኛ ሰው፣ ሁሉም ነገር ለሰው የሚል ሰብአዊ አመለካከት ያለው ሀቀኛ ሰው፣ ትንሰቱ አንድን ሰው የሚጋለጥ ተግባር ምን ያህል አስቸጋሪና ከባድ እንደ ሆነና ከፍተኛ መደባዊ ንቃት ህሊናን እንደሚጠይቅ ታየው፡፡ —ማን ነው እውነተኛው ጠላት? አለ፡፡

@OLDBOOKSPDF



ሃጂ በድንቁርናቸው እንጂ በአቋቋማቸው ከአብዮቱ እውነተኛ ጠላቶች ሰፈር ተሰልፈው አሊታዩ አሉት፡፡ ይልቅ አብዮቱ የመጣላቸው መሆኑን ባለማወቅ፣ የመጣባቸው እየመሰላቸው የሚያለቅሱት በሽህ ከሚቆጠሩ ምስኪን ሰዎች መካከል ረጂም ቁመናቸው ብቅ ብሎ ታየው፡፡ የድንቁርና ፍቱን መድሀኒቱ ማጎሳቆል ሳይሆን፣ የአብዮቱን ሰፈር ማጠናከር፣ ማስተማር፣ አሁንም ማስተማር፣ ብሎም ማስተማር— እዩ ሃጂ በማለት ሲተክዝ፣ ትካዜውን አቁሞ ሲሰራ፣ ደግሞ ስራውን አቁሞ ሲተክዝ፣ ለዘብተኛ ነኝ? ወይስ?... እያለ ሲያስብ የሰአቱ ቅልጥ ብሎ መሄድ አሊታወቀውም ነበር፡፡

ከሰብለ ጋር ያደረገው ቀጠሮ በስምንት ሰአት ስለሆነና የቀረው ጊዜ አጭር በመሆኑ ወደ ቤቱ ከመሄድ በቀጥታ ወደ እስክንድር ሆቴል አመራ፡፡

ሲደርስ እስክንድር በጥሩ ስሜት ነበር የተቀበለው፡፡ ክፍሉ ውስጥ ተዝረክርከው ይታዩ የነበሩት አሮጌ ጋዜጦችና መፅሄቶች ደርዝ ይዘዋል፡፡ ክፍሉ ፀድቶ አምሮአል፡፡ እስክንድር ፊት ላይ የደስታ ስሜት ይነበባል፡፡ ሲራክ የእስክንድርን ሁኔታ አጢኖና፣ «ደስ ያለህ ትመስላለህ፡፡ ያደረብህ ደስታ ይሰማኛል፡፡ ምን አገኘህ እባክህ?» አለውና፣ በክፍሉ ፅዳት እየተገረመ ሄዶ ተቀመጠ፡፡

«እንደ ገና መኖር ጀምሬአለሁ፡፡ ከራማው ታርቆኛል፣ ጉዋዴ» አለው፡፡

«የምኑ ከራማ?»

«የኪነት፡፡ ፊቱዋን ወደኔ መልሳለች፡፡ ያንን መፅሀፍ እንደ ገና ጀምሬዋለሁ፡፡ ትክክለኛውን ፈር ያገኘሁ ይመስለኛል፡፡ ይዘቱም ሆነ ቅርፁ ተዋህደው ቁልጭ ብሎ እየታየኝ ነው፡፡ ጉዋዴ፣ አሁን የቀረኝ ነገር ቢኖር መፅሀፉ ህይወት እንዲዘራ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ ጊዜ... ጊዜ... ሌላ ችግር የለኝም፡፡ ህይወት እንደ ገና እየተንቀሳቀሰች ነው» አለ በስሜት፣ እጁን እንደሚታጠብ ሰው እጆቹን እያሻሸ፡፡

ሲራክ በልቡ እየተደሰተም እየቀናም፣ «ግሩም ነው» አለው፡፡

«አመሰግንሃለሁ፡፡ ያንተ ድል ነው» አለና፣ ሄዶ በጋለ ስሜት ከጨበጠው በሁዋላ፣ ጉንጩንና ጉንጩን እያገላበጠ ሳመው፡፡

@OLDBOOKSPDF



«ምን ስላደረኩ?» አለ ሲራክ፥ የእስክንድርን ስሜት እየፋ እየመሰሰ፡፡

«አይኔን ስለ ከፈትክልኝ፡፡ ያኔ የገደልከኝ መስሎኝ ነበር፡፡ ጅል ሆኜ ነው እንጂ ህይወት ነው የሰጠኸኝ፡፡ ህይወት ፈገግ ማለት ስትጀምር እቤት ደስ ማለትዋ!» ብሎ ወደ ዕህፈት ጠረጴዛው እንደ መዝለል እያደረገው ሄደና፥ ብጫ ወረቀቶች አንስቶ ካርታ እንደሚደረደር ሰው ኮልኩሎ ከተመለከታቸው በሁዋላ፥ ቀና ብሎ፥ «ይዘቱን ልንገርህ?» አለው፡፡

እስክንድር መፅሀፉን እንደ ገና በመጀመሩ ሲራክ ደስ ቢለውም፥ ስለ ይዘቱ አሁን ለመስማት አልፈለገም፡፡ ግን እስክንድር ስለ መፅሀፉ ይዘት ለመናገር ያደረበት ጉጉት ጠንካራ ሆኖ ስላገኘው ከመስማት በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም፡፡ ሰአቱን ተመለከተና፥ «እሺ» ብሎ እግሮቹን አጣመረና እስክንድር የሚለውን ለመስማት ተመቻችቶ ተቀመጠ፡፡ ጆሮውን ቢያዘጋጅም ልቡ ስለ ሰብለ ነበር የሚያስበው፡፡

እስክንድር የጠረጴዛውን መብራት አበራና ቁጭ ብሎ፥ «አርእስቱን ምን ብየዋለሁ መሰለህ?» አለ፡፡

«ምን አልከው?»

«መሬት ላራሹ፡፡»

«ግሩም ነው፡፡»

«ወደኸዋል?» አለና፥ ሲራክ በአዎንታ ራሱን ሲነቀንቅ ሰላየው ምንም ጊዜ ሳያጠፋ፥ «ታሪኩን የምጀምረው በምን መሰለህ?» አለና ሰው ሰራሽ ጥርሱን ወደ ውስጥ ገፋ አደረገ፡፡

«እንዴት ልትጀምረው አሰብሃል?» አለ ሲራክ፥ በተከፈለ ልብ፡፡

«የገጠርን መሬት የህዝብ ያደረገው አዋጅ ሲወጣ የነበረው ሁኔታ ትዝ ይልሃል?»

«ትዝ ይልሃል ወይ ብሎ ነገር! አዋጁ አሁንም ጆሮዬ ውስጥ ያስተጋባል» ብሎ፥ አዋጁን ያነበበውን ራዲዮ ተናጋሪ ድምፅ

@OLDBOOKSPDF

በማስመሰል፥ «የገጠርን መሬት የህዝብ ለማድረግ የወጣ አ—ዋ—ጅ! ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በገጠር የሚገኘው መሬት በሙሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆ—ኗ—ል—ል! በገጠሩ ኢትዮጵያ ከሞቱት በላይ ካሉት በታች ሆኖ ሲማቅቅ የኖረው ጭሰኛ እንደ ገና የተወለደበት ቀን እንዴት ይረሳኛል?» አለው።

እስክንድር ሞቅ እያለው፣ «ልክ አዋጁ ሲነገር በየቤቱ የነበረውን ሁኔታ— ባለመሬቶች ከንፈራቸውን ሲነክሱና ሲመጡ— ጭማይሆን ነገር! ህልም ነው ቅዠት፤ ሁለት ቀን የማይቆይ አዋጅ ነው' ሲሉ— ተስፋ የቆረጡት ራዲዮኖቻቸውን ሲሰብሩ— ሌሎች ጆሮዎቻቸውን አላምን ብለው ጉድ ነው! ጉድ ነው! በማለት አይኖቻቸውን አፍጥጠው ሲተክሉ— የኢ.ህ.አ.ፓ ጥንስሶች ደግሞ 'ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ሳይቋቋቋም፣ የገጠሩ ህዝብ ሳይነቃ፣ ሳይደራጅና ሳይታጠቅ፣ እንዲህ አይነቱን ስር ነቀል አዋጅ ማውጣት ትክክል አይደለም። ጭሰኛውን ቢታጠቀው ነፍጠኛ ለማስመታት፣ ወይም ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት የመሬትን ጥያቄ መለሰኩ በማለት እድሜውን ለማራዘም እስቦ ካልሆን በቀር ዋጋ የለውም። ያልተደራጀና ያልታጠቀ ጭሰኛ መብቱን ለማስከበር አይችልም። ስለዚህ አዋጁ፣ ጋሪውን ከፈረሱ በፊት እንደ ማስቀመጥ ነው' በሚሉበት ጊዜ ነው የታሰሩ ባለቤት— ደጀኔ ብቅ የሚለው...»

«እሺ» አለ ሲራክ፥ ሰአቱን እያየ።

«ደጀኔ የጭሰኛ ልጅ ነው። የከብት ጭራ ሲከተል የኖረና ዘግይቶ ትምህርት በመጀመሩ በእድሜ ጠና ያለ የሶስተኛ አመት ኮሌጅ ተማሪ ነው። ታዲያ የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ለዘመናት የታገለለት የመሬት ላራሹ ጥያቄ የማያዳግምና የማያሻማ ቁራጥ ምላሽ በማግኘቱ የወጣቱ ትውልድ ታሪካዊ ሚና አዋጁን ተግባራዊ ማድረግ ነው የሚል መደባዊ አላማ ይዞ ይነሳል...»

ሲራክ አቀማመጡን ለወጠና፥ «ህዝባዊ ጀግና ተከሰተ ማለት ነው። እዚህ ላይ፥ የደጀኔን ባህርይ ለማሳየት፣ ሲጋ፣ ደምና ህይወት ያለው ሆኖ እንዲታይ ለማድረግ ከፍተኛ ጥንቃቄና ችሎታን ይጠይቃል። አብዮታዊ ቃላት ማንበልበሉ ብቻ አርአያ ለመሆን የሚችል ህዝባዊ ጀግና ሊያደርገው አይችልም። ሲከፋው አንዢዚ አብሮት የሚከፋ፣ ሲደሰት አብሮት የሚደሰት፥ ውድቀቱንና ድሉን አብሮት የሚካፈል ህልውና ያለው ባሕርይ መሆን አለበት» አለው።

@OLDBOOKSPDF


እስክንድር ሰው ሰራሽ ጥርሱን ወደ ውስጥ ገፋና፣ «አዎን ልክ እንዳልከው ነው፡፡ የደጀኔን ባህርይ በደንብ የማውቀው ይመስለኛል፡፡ አየዋለሁ፡፡ እንጋግሬዋለሁ፡፡ ስሜቱ ይገባኛል፡፡ አላማው ይታየኛል፡፡ ይገረምሀና፣ እንደፈለኩ የምመራው ሰው ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ እስከዚህ ድረስ ነው የማውቀው» አለ፡፡

«ግሩም ነው» አለ ሲራክ፡፡

«እንግዲህ የታሪኩ ይዘት ባጭሩ፣ ደጀኔ አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ፣ የአዋጁን አላማ ተግባራዊ ለማድረግ፣ የእድገት በህብረት፣ የስራና የእውቀት ዘመቻን ጥሪ በአብዮታዊ ስሜት ተቀብሎ እንዴት እንደ ዘመተ፣ የሰፈሩን ህዝብ ኑሮ በመኖር፣ የልብ ትርታውን በማዳመጥ ከተጨባጩ ሁኔታ ምን መማር እንደ ቻለና ህዝቡን መልሶ በማስተማር፣ በማንቃትና በማደራጀት ረገድ ምን አስተዋፅኦ እንዳደረገ፣ ያጋጠሙን ችግሮች፣ ከመሬት ከበርቴዎች ጋር ያካሄዳቸውን መራራ ትግልና ያሳየውን ቆራጥነት በተለይም አብረውት ከዘመቱት ከኢ.ሀ.አ.ፓ ጥንስሶች ጋር ያደረገውን ብርቱ ትግልና ፀረ-አብዮተኛ ተብሎ የደረሰበትን መከራና እስራት፣ ህዝቡ በሁዋላ እንዴት አድርጎ እንዳስፈታውና እንዳቀፈው መፅሀፉ ለማሳየት ይሞክራል...

«ታሪኩ የሚፈፀመው ያንቃው፣ ያደራጀውና ታግሎ የታገለው ህዝብ በገበሬዎች ማህበር የተደራጀበትን የመጀመሪያውን አመት ሲያከብር ነው» ብሎ፣ ከተቀመጠበት ተነሳና፣ «ምን ታስባለህ? አለው፡፡

«ግሩም ነው፡፡»

«እውነቱን ንገረኝ፡፡»

«እውነቴን ነው፡፡ ብቻ ውጤቱ የሚመሰነው በገፀ ባህርያቱ ጥንካሬና ድክመት ነው፡፡ በታሪኩ አይደለም» አለው፡፡

«በዚህ ሁኔታ ሶሻሊስታዊ እውነታን ለማንፀባረቅ የምችል ይመስልሃል?» ብሎ ጠየቀው፡፡

«አሳምረህ» ብሎት ለጠቀና፣ «ግን ሶሻሊስታዊ እውነታ፣ ህይወትን እንዳለች ገልብጦ ማሳየት ማለት አይደለም፡፡ አላማው ከዚህ ይልቃል፡፡ ምን ልበልህ? በኪነታዊ ፈጠራ ውስጥ የሶሻሊስታዊ እውነታ

@OLDBOOKSPDF



ከአስከሬ ገፅታው ጋር እንዲናድ አላማ አርጌው የታሪክ ግድግዳ ክአስከሬ ገፅታው ግን ሶሻሊስታዊና አብዮታዊ መዋጋት ሲሆን፣ አይነተኛ ተልእኮው ግን ሶሻሊስታዊና አብዮታዊ መዋጋት ሲሆን፣ እይነተኛ ተልእኮው እንዲተረፅ ከማድረጉ ላይ ነው፡፡ አመለካከት በአንባቢ አእምሮ ውስጥ እንዲተረፅ ከማድረጉ ላይ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ጎርኪ እንደሚለው፣ ድርጊትን ከፈጠራ ጋር አጣምሮ ማሳየት ማለት ነው፡፡ ሀልውና የድርጊትና የፈጠራ ነፀብራቅ መሆንዋን ማሳየት ማለት ነው፡፡

‹‹እየህ፣ የሰው ልጅ ስለ አካባቢው በሚሰጠው ገለፃ አእምሮው ከማይረካበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ ሰው አካባቢን ከቁጥጥሩ ስር በሚያውልበት ወቅት፣ የጊዜአችን በማዋል ብቻ ሳይወሰን፣ ለመለወጥ በሚታገልበት ወቅት፣ የጊዜአችን ኪነት የትግሉ አካልና ነፀብራቅ እንድትሆን ይፈለጋል፡፡ መሆንም አለባት፡፡ ለዚህ ነው በሶሻሊስታዊ ኪነት ውስጥ እውነታ ህይወትን እንዳለች ገልብጦ በማሳየት ተግባር መወሰን የለበትም የሚባለው፡፡ ተልእኮ አለምን ለመለወጥ የሚረገው ትግል አካል መሆን ነው፡፡ ማለትም የሞራል ለውጥና የህይወት ተሃድሶ ነፀብራቅ፣ የሰፊው ህዝብ እስትንፋስ መሆን አለበት፡፡ ሶሻሊስታዊ እውነታ በሰው ልጅ የማያቋርጥ የሞራል ለውጥ መሻሻል ፍፁም እምነት ማሳደር ማለት ነው፡፡ በህይወቱ፣ በኑሮው ፍፁም የረካ ሰው፣ ሰው አይደለም፡፡ እዳም ከገነት ባይወጣ ኖሮ ዝንጀሮ ሆኖ በቀረ ነበር፡፡ በኔ ግምት፣ ሰው መሆን በዲያሌክቲካዊ ሁኔታ ውስጥ መኖር ማለት ነው፡፡ የኪነት ተልእኮ ይህን ሁኔታ ውስጥ መኖር ማለት ነው፡፡ የኪነት ተልእኮ ይህን ሁኔታ መተርጎም ነው፡፡ ቀላል አይደለም›› አለውና፣ በረጂሙ ተንፍሶ ስእሉን እንደ ገና ከተመለከተ በሁዋላ፣ ‹‹ሊመሆኑ ታሪኩ የሚፈፀምበትን ቦታ በደንብ ታውቀዋለህ?›› ሲል ጠየቀው፡፡

‹‹በሚገባ›› አለ፣ ‹‹እንዲያውም እሳቡን ያለቀልኝ ታመነ የሚባል ዘማች ነው፡፡ እንዴት ያለ ልጅ መሰለህ! ግሩም ወጣት ነው፡፡ ባጋጣሚ ነው የተዋወቅነው፡፡ በነገራችን ላይ፣ ኩብላይ እንደ ጥላን እንገብቦአል፡፡ በጣም ያደንቅሃል፡፡ እርሲ ክፍለ ሀገር... ኩፈሌ ነው የዘመተው፡፡ በዘመቻው ወቅት ስላገኘው ልምድ፣ ስላካሄደው ትግልና ስለ ደረሰበት መከራ ሁሉ አንድ ባንድ አጫውቶኛ፡፡ የኢ.ህ.አ.ፓ ጀሌዎች ፀረ አብዮተኛ ነው በማለት እወናብደው እንዴት እንዳሳሰሩትና ገበሬዎች እንዴት እንዳዳኑ ሲያጫውትህ እፍ ያስከፍታል፡፡ ይግረምህና ሁዋላ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን የሚለውን መፈክር በመቃወም የለየለት ኢ.ህ.አ.ፓ ነው ተብሎ እንዴት እንደ ታሰረና ከሞት አፋፍ እንዴት እንደ ዳነ ሲነግርህ ያሳዝናል፡፡ ይህ ሁሉ መከራና ፍዳ ከደረሰበት በሁዋላ አሁንም በአብዮቱ ላይ ስላለው እምነትና ተስፋ ሲናገር ያስደንቃል፡፡ ‹በአብዮቱ ወቅት ባንድ ግለሰብ ላይ የሚደርሰው ማንኛውም መከራ ግምት

@OLDBOOKSPDF



ሊሰጠው አይገባም፡፡ ሲሾሙ፥ ሲሸልሙ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አብዮቱ የሚሉ፣ ትንሽ 'ሲንሸራተቱ ደግሞ ኤጭ! የታባቱ' ብለው የሚጥሉ አሉ፡፡ እኛ ሰርተን፣ ተቃጥለን፥ ተጋፍጠን፥ ተማግደን ምን አገኘን? በማለት አኩሩፈው ቁጭ ያሉ አሉ፡፡ ግን ነገሩ እንዲህ መሆን የለበትም፡፡ ማግኘት ወይም ማጣት፥ መሾም ወይም መሻር ዋጋ የለውም፡፡ የአብዮት ችቦ ከነደደ ከተንቀለቀለ ለኔ ምን ጊዜም ቢሆን ስርጌ ነው' ያለኝ አይረሳኝም፡፡ በሚመጣው ሳምንት አብረን ኮፈሌ ለመሄድ ወስነናል፡፡ በጣም ተባባሪ ነው፡፡ ከኔ ይበልጥ በጉዳዩ ያሰበበት ስለ ሆነ የጣለብኝን እምነት ለማጉደል አልፈልግም፡፡ ሁሉም በእጄ ሁሉም በደጄ ነው፡፡ መፅሀፉ ተፅፎ እንዳለቀ ቁጠረው›› አለው፡፡

‹‹አንተን ባደረገኝ›› አለ ሲራክ ቀንቶ፡፡

‹‹ያንተ መፅሀፍ ከምን ደረሰ?›› ብሎ ጠየቀው፡፡

ሲራክ እጁን በብስጭት አወናጭፎ፥ ‹‹የትም አልደረሰ፡፡ ባለበት ይረግጣል›› አለው፡፡

‹‹ፍቅር ይዞህ ይሆናል...››

‹‹የምን ፍቅር?›› አለ፥ ድምፁን ከፍ አድርጎ፡፡

እስከንድር ሳቀና፥ ‹‹የያዘህ ፍቅር ነዋ›› ብሎ ትንሽ ተከዘና፥ ‹‹እውነት ፍቅር ይዞሃል? ወይስ እንዲያው ለቀልድ ነው? ማለቴ ከእውነታ ለመራቅ? አንድ አይነት ፅላል ውስጥ ያለህ ይመስለኛል›› አለው፡፡

‹‹ምንድን ነው እንዲህ ለማለት ያበቃህ?›› አለ ሲራክ፥ ኮስተር ብሎ፡፡

‹‹እንዲያው መሰሎኝ ነው...››

‹‹እኮ በምን ምክንያት?›› አለው፥ ቆጣ ብሎ፡፡

‹‹እንዴት ልበልህ? ኪነታዊ ስራህን በቀዛ ፈዛዛ የምትመለከት አትመስለኝም፡፡ ሚስትና ልጅ አለህ፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ጠንካራ ሰው ትመስለኝ ነበር...››

‹‹ማፍቀር ደካማነት ነው?››

@OLDBOOKSPDF

«እንደሱ ማለቴ አይደለም፡፡ ፅላል የሚያጠቃው ሰው አትመስለኝም ነበር፡፡ ያሰብክበት አይመስለኝም» አለና፣ እስክንድር ጥርሱን ወደ ውስጥ ገፋ አደረገ፡፡

«ምኑን?»

«አንተ ለቀልድ ወይም ቅድም እንዳልኩት ከእውነታ ለመራቅ ብለህ ይሆናል፡፡ ግን ሰብለ ፍቅር ቢይዛትስ? በዚህ የተነሳ ቤትዋ ቢፈርስስ? ያኔ ምን ታደርጋለህ? ሚስትህን አባረህ እስዋን ታገባለህ? ምን ልታደርግ ነው? ከባድ የሞራል ጥያቄ ነው፡፡

«ላንተም ሆነ ለእስዋ ሃላፊነት አለብህ፡፡ ልትጎዳት እንደማትፈልግ እርግጠኛ ነኝ፡፡ እስቲ አስብበት፡፡ በኔ ግምት ቀልዱን አቁመህ ብእርህን ብታነሳ ይሻላል፡፡ ላንተም ሆነ ለእስዋ የሚበጀው ይኸው ነው፡፡ ብቻ በግል ጉዳይህ ገብቼ ስለ ዘባረኩ ይቅርታ» አለውና፣ «እንዲያውም የመውጫዬ ሰአት ደርሶአል፣ እኔም ቀጠሮ አለኝ» ብሎ ክፍሉን ጥሎለት ሲወጣ፣ ሲራክ በልቡ «ሜርሲ» አለ፡፡

እስክንድር ወጥቶ ከሄደ በሁዋላ፣ የተናገረው ነገር ሙሉ ትርጉሙ ቁልጭ ብሎ ታየው፡፡ ከዚህ በፊት አስቦበት የማያውቀው ጉዳይ በመሆኑ ተጨነቀ፡፡ ከሰብለ ጋር ፍቅር ይዞኝ ይሆን? ወይስ እስክንድር እንዳለው ፅላላዊ ስሜት ነው? እና ይህ ፅላል ወዴት ነው የሚያመራው? ብሎ አሰበ፡፡ በመካከላቸው የተፈጠረው ግንኙነት ወዴት እንደሚያመራ ሊታየው አልቻለም፡፡ ዝም ብሎ አቀርቅሮ ቆመ፡፡ ወጥመድ ውስጥ እንደ ገባ ያህል ተሰማው፡፡ ግን በይበልጥ የሚያስበው ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ሰብለ ነበር፡፡ —አስርቱ ቃላት በህይወታችን ውስጥ ቦታ አላቸው ብለህ ነው? እንወያይባቸዋለን፣ እናቀላጽላቸዋለን፣ ግን ማናችንም አናምንባቸውም፡፡ እነዚህን ህጎች በተግባር የሚያውል የለም፡፡ በህይወታችን ውስጥ ቦታ የላቸውም፣ እያለ ሲያስብ፦ በሩ ሲንኩዋኩዋ አሳቡን እርግፍ አድርጎ ጥሎ ዘሎ በሩን ከፈተ...

«ልክ በሰአትዋ ከች» አለችና አንገቱ ላይ ተጠምጥማ...

«እኔም ናፍቄሽ ነበር» ብሎአት፣ አንገትዋ ውስጥ ሽጉጥ...

ወፎች ዘመሩ፡፡ ተራሮች ማህሌት ቆመው ቅዳሴው ሰመረ፡፡ የቤተመቅደስ ጡዋፍ ተንቀለቀለ፡፡ ጉሞች ወደ ከርቤ፣ ወደ ባህር እግ

@OLDBOOKSPDF


ተለውጠው ተነን፡፡ የባህር ሞገድ ተነስቶ ወደቀ፡፡ ስትንሳፈፍ የቆየች ህይወት መልሀቋዋን ጣለች፡፡ ዝም – ዝምታ፡፡

‹‹ይህች ህይወት!›› አለችና ቀና ብላ፡፡

‹‹ውብ ናት›› አላት፡፡

‹‹ግን እጭር ነች›› አለች፡፡

‹‹መሆንዋ በጄ...››

‹‹ለምን ልጄ?››

‹‹እጭር ባትሆን ኖሮ እንዲህ አትጥመንም ነበር...››

ትንሽ ቆየችና፣ ‹‹ለምንም ነገር ደንታ ያለህ አትመስልም›› አለችው፡፡

‹‹እንዴት ማለት?››

‹‹ስለ ፍቅር፣ ስለ ሰው፣ እንዴት ልበልህ?››

‹‹ደራስያን አድገው እያበቁም፣ ለዚህ ነው፡፡››

‹‹ስለኔ ምን ይሰማሃል?›› ስትል ጠየቀችው፡፡

ቀጥታ መልስ አልሰጣትም፡፡

‹‹እየሞቀች የምትሄድ የጠዋት ፀሀይ ነሽ›› አላት፡፡

‹‹ፍቅርህ እሳት ውስጥ ለምትገባ ሴት ይብላኝ!›› አለችው፡፡

‹‹ለምን?››

‹‹የእሳት ራት ሆና ትቀራለች፡፡ ታቃጥላለህ እንጂ አትነድም፡፡ ፍቅር ታስይዛለህ እንጂ ፍቅር የሚይዝህ አትመስልም፡፡››

ግንባርዋ ላይ ሳማትና ዝም አለ፡፡

ክንዱን እንዳንተራሳት በጀርባው ተጋድሞ ከዚህ በሁዋላ ወዴት? ህይወት በእውነት እየሳቀችልን ነው ወይስ እያሾፈችብን?

 @OLDBOOKSPDF

እውነታ ነው ወይስ ዕባል? ወይስ የጥንቆች ግኝት ውስጥ ነው ያለነው? እያለ ማሰብ ሲጀምር፣ ሰብለ ድንገት ከሰንዱ ላይ ቀና ብላ፣ «እትዬ አልታዬ የሚባሉትን ሴት ታውቃቸዋለህ?» ስትል ጠየቀችው።

«ማን አልሽኝ?» አላት።

«እትዬ አልታዬ...»

«ኡ-እትዬ አልታዬን?» ብሎ የወርቅ ጥርሳቸው ብልጭ ሲል እየታየው፣ ጎረቤት ቡና ሲወቀጥ የሚቆመው ትልቁ ጆሮአቸው በአይነ ህሊናው እየመጣበት፣ እጣን ሲጤስ ከሩቅ የሚያሸተው ረጅም አፍንጫቸው ከፊቱ እየተደቀነበት፣ የቡና ጀበና ከትሪሻ ላይ ገና ዱብ ሲል ሲኒአቸውን በቀይ መሀረብ ጠቅለው በረጅም ቁመናቸው ጉትት እያሉ ብቅ የሚሉት ትዝ እያለው፣ «አውቃቸዋለሁ። ጎረቤቴ ናቸው። እንዲያውም ይገረምሽና ያጋፋሪ እንደሻውን አሳብ ያገኘሁት ከእሳቸው ነው።» ብሎአት፣ ትራሱን አመቻችቶ ከአንገቱ ቀና ካለ በኋላ፣ «በምን ተገናኛችሁ ልጄ?» አላት።

«እትዬ አልታዬ» አለች። «ከህፃንነቴ ጀምሮ ነው የማውቃቸው። ድሮ ጎረቤት ነበርን። ሲኒ ይዘው ቡና በፈላበት ሲዞሩ ነበር የሚውሉት። አሁንም አልፎ አልፎ ይጠይቁኛል። አይ አማርኛ፣ አይ ለዛ፣ አይ ቀልድ! የደረሰ ጎረምሳ ሲያዩ ምን ይላሉ መሰለህ? 'ይኸ ሎጋ ወይ ህይወት፣ እኔ አልታዬ ወደ መቃብር። በመንገድ ተሳለፍን እቴ' ብለው እንትፍ እንትፍ ይሉበታል።» አለችው።

«በጣም የሚደነቁ ሴት ናቸው። በቀደም ለት ሰፈራችንን አረብሸው ነው የዋሉት። የሚገርም ነው። እንደዚያን ቀን ልቤ ተነክቶ አያውቅም። ጥዋት ከቤት ልወጣ ስል ጩኸት ሰማሁ። ዕጌ ብቅ ብላ ጩኸቱ ከየት አቅጣጫ እንደሚመጣ ከዳመጠች በኋላ፣ 'እትዬ አልታዬ ናቸው' አለችኝ። 'መርዶ ሰምተው እንደሆን?' አልኩዋት። 'የማንን መርዶ? በዚህ አለም ላይ ምን ዘመድ አላቸውና!' ብላኝ፣ ለማንኛውም ነገር ተያይዘን ሄድን። ጎረቤቱ ሁሉ መጥቶ ግጥም ብሎአል። እትዬ አልታዬ ራሳቸውን ይዘው፣ 'ጉዴን አየሁት! ዛሬ ገና የህይወት አመድ አፋሽ መሆኔ ታወቀኝ' እያሉ እጅጁአቸውን ያቀልጣሉ። በስንት ግልግል ተይዘው ምን እንደሆን ሲጠየቁ ጉዱ ምን ሆና ተገኘ መሰለሽ? አንዲት ርግብ ከቤታቸው ታዛ ስር ጫጩት ፈልፍላ ኖሮ እየበረረችና እየ መጣች የለቃቀመችውን ለጫጩቶችዋ ስታቀብል አይተው ነው በመካንነታቸው እንባቸው እጅጁአቸውን ያቀለጡት። ታዲያ እንዲህ ገረመኝና፣ 'ወፍ ጫጩቶቹዋን ስትመግብ

ሣኛ ዛሬ ነው ያዩት?' ስላቸው ጊዜ፣ 'አዩ ልጄ፣ ሳይ የኖርኩት ጉዳይ ነው። ትርጉሙ ግን የገባኝ ዛሬ ነው' አሉኝ፣ እንባቸውን እያዘሩ። ' ምን ትርጉም?' አልኳቸው። 'የህይወቴ። ያለዘር አፈር፣ ትቢያ ሆኜ መቅረቴ። ከመቃብር ባሻገር ምን ስም አለኝ? ምንስ ይቀረኛል? እንደ ሰው ማህፀን ሰጥቶኝ ነበር። እንደ ድንጋይ ዘረ-ቢስ ሊያደርገኝ! ሌሉ የሰማ ጎረቤት ሁሉ ተጂው... እንባ በእንባ ይራጭ ነበር›› ብሎ፣ ‹‹ለመሆኑ መቼ ነው ቤትሽ የመጡት?›› ሲል ጠየቃት።

‹‹ትናንት።››

‹‹ስለኔ ምን ጠየቁሽ ታዲያ?››

‹‹ስላንተ ምን ለማወቅ እንደ ፈለጉ አላውቅም። ምናልባት ስላንተ የጠየቁኝ እንኳ መስሪያ ቤት ውስጥ መስራታችንን በማወቃቸው ይሆናል። ጥሩ ዶራሲ ነው። አውቀዋለሁ። ብዙ ጊዜ እንገናኛለን አልኳቸው›› አለች፣ ፀጉርዋን እያስተካከለች።

ግንባርዋ ላይ ሳማትና፣ ‹‹ምን አሉሽ ታዲያ?›› አላት።

‹‹ሌላ ምንም አላሉኝ። ብቻ 'ሚስቱ ዶራሲ እንዲሆን አትፈልግም' አሉኝ። 'ለምን?' ብዬ ብጠይቃቸው፣ 'እሰዋ በሰላም ወጥቶ በሰላም ስራውን ሰርቶ፣ ሙሉ የወር ደሞዙን አምጥቶ ቤቱን የሚያቀና ባል ነው እንጂ እንደ፣ ዶብተራ ቀለም የሚለቀልቅ ሰው ደስ አይላትም' ሲሉኝ፣ 'ምን አስብኩ መሰለህ? በልቤ 'ምን ነው ባል ቢተለዋወጥን?' አልኩ›› አለችና፣ እቅፍ አደረገችው። ቀየችና፣ ‹‹ዶራሲ እንዳትሆን ለምንድን ነው የምትፈልገው?›› ብላ ጠየቀችው።

በፊት ያሳተመው መፅሀፍ በሙሉ ተሸጦ ቢያቅም፣ ባላመጣበት እዳና በኑሮው ላይ በላደረሰው ችግር አወራላትና፣ ‹‹በዚህ ብቻ ሳይሆን፣ እንድፅፍ የማትፈልገው ፖለቲካ ውስጥ ገብቼ የታሰርኩ እንደሆን በማለት እየሰጋች ነው። 'ጊዜው አስተማማኝ አይደለም። ለምን ዕሩህ ራስክን ታጋልጣለህ? ወረቀት የያዘው አይለቅም። ጌታዋን ያመነች በግ ላትዋን ደጅ ታሳድራለች አሉ። ምኞትን ነው። አይምስልህ። ደሞ የቤተሰብ ሃላፊ መሆንክን አትርሳ። አንተ አንድ ነገር ብትሆን እኛንም ቀምር ይዘህ ነው የምትሞተው፣ ብቻህን አለመሆንክን እወቅ' ትላለች። ታዲያ በመጥፎነት አይደለም ይህን ሁሉ የምትለው። ከቤተሰብዋ ደህንነት የሚበልጥባት ነገር እንደ ሌለ በማሰብ ነው›› ብሎ፣ ካሜዉታት በሁዋላ፣ ሰብሰ አቀርቅሬ ሲታበብ ቆየችና።

‹‹የድሮ ሚስትህስ?›› አለችው፡፡

‹‹እንዴት ማለት?››

‹‹ማለቴ፣ እንዴት ነበረች?››

‹‹ከምን አንፃር?››

ጥያቄዋን በጥያቄ እየመለሰ ስላስቸገራት ብሽቅ ብላ፣ ‹‹ከሁሉም አንፃር!›› አለች፡፡

‹‹ምን ያደርግልሻል?››

‹‹ማወቅ እፈልጋለሁ!››

የሁኔታዋ መለወጥ እያስገረመው፡፡ ‹‹ከየት ልጀምርልሽ?›› አላት፡፡

‹‹ከመጀመሪያው›› አለች፣ ፍርጥም ብላ፡፡

ሲራክ ስለ ድሮ ሚስቱ ስለ ማርታ አንስቶ መናገር አይወድም፡፡ በእስዋ ላይ ቂሞ ኖት፣ ወይም ከእስዋ ጋር የወደፊት ተስፋ ስላለው አይደለም፡፡ የሞተ፣ የተዳፈነ ትዝታ ነው ብሎ ስለሚያስብ ነው፡፡ ሆኖም ያንን የሞተ ትዝታ እንደ ገና ለመቀስቀስ እየተጨነቀ፣ ‹‹የኔና የማርታ ጋብቻ የዘመኑ ታላቅ መደባዊ ጋብቻ ነበር፡፡ በኔ ያልቀና በእስዋ ያልተገረመ አልነበረም›› ሲል ከእፉ ነጠቀችና፦

‹‹ለምን?›› አለችው፡፡

‹‹ምክንያቱም›› አለ፦ ‹‹እኔ ያጣሁ የነጣሁ መናጢ ድሀ፣ እስዋ የስንት ባላባትና መኩዋንንት ዘር በመሆንዋ ነው፡፡ የስንቱ መኩዋንንትና መሳፍንት ልጆች፣ የንጉሰም ቤተሰቦች ጭምር ወርቅ እናንጥፍልሽ እያሉ ደጅ ሲጠንዋት እኔን መርጣ በማግባትዋ፣ ምን አይነትዋ ሃይማኖተኛ ናት ያላለ አልነበረም፡፡››

‹‹መጀመሪያ እንዴት ነው የተገናኛችሁት?››

‹‹አንድ ፓርቲ ላይ ነው የተገናኘነው›› አለ፣ ሁኔታውን እያስታወሰ፦ ‹‹አንድ እሩጫ ነበራት፡፡ ፓርቲው ላይ እስዋን ትቶ፣ ለማስቀናት ነው መሰለኝ፣ ከሌሎች ጋር ይዳራ ነበር፡፡ እጠገቤ ስለ

@OLDBOOKSPDF


ነበረ የተቀመጠችው መነጋገር ጀመርን፡፡ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ መፃህፍት አለም ውስጥ ገባን፡፡ ድርሰት የምትወድ መሆንዋን ተረዳሁ፡፡ ሰው ሁሉ ሲጨፍር ሁለታችን ስላነበብናቸው አንዳንድ መፃህፍት እንስተን ስንወያይ አመሸን፡፡ በመጨረሻ፣ 'እንደ ዛሬ ጥሩ ጊዜ አሳልፌ አላውቅም' ብላኝ፣ የስልክ ቁጥርዋን ሰጥታኝ ተለያየን፡፡

«ከስንት ሳምንት በሁዋላ አንድ ቀን ትዝ ብላኝ ደወልኩላት፡፡ በቀጠሮ ተገናኘን፡፡ 'ቤትህን ካላየሁ' ብላ ድርቅ አለች፡፡ አንዲት ቢጋባ ውስጥ ነበር የምኖረው፡፡ በሽንጣሙ መኪናዋ በስንት መከራ ከምኖርበት መንደር ገብታ ቤቴን ካየች በሁዋላ፣ 'ከዚህ የበለጠ ሀብት በዚህ አለም ምን አለ?' ያልኩዋት ትዝ ይለኛል፡፡

«በስንተኛው ቀን እንደ ሆነ አላውቅም፣ ተመልሳ መጥታ ቤትዋ ወሰደችኝና ከወላጆችዋ ጋር አስተዋወቀችኝ፡፡ ትንሽ ቆይተው አባትዋ ስለ አባቴ ጠየቁኝ፡፡ 'ምን ያደርግልዎታል፡፡ አያውቁትም' አልኩዋቸው፡፡ 'እንዴት?' አሉኝ፡፡ 'የሚታወቅ አይደለም፡፡ ስም፣ ክብር፣ ማእረግ የለውም' አልኩዋቸው፡፡

«'አባባልህ አልገባኝም' ሲሉ ጊዜ ነገሩን ለማሳጠር፣ 'ጭሰኛ ነው፡፡ ስም የለውም' አልኩዋቸው፡፡ ውይይታችን ቀስ በቀስ ወደ ፖለቲካ አመራ፣ ለአገሪቱና ለህዝቡ ስለ ፈፀሙት ስራ አንድ ባንድ ንግግር ካደረጉልኝ በሁዋላ፣ 'አሁን ስላለው የፖለቲካ ሁኔታ ምን ታስባለህ?›› አሉኝ፡፡ 'ከር—ንቀል የሆነ ለውጥ፡፡ ሌላ የማስበው የለኝም' ስላቸው ጊዜ፣ ተቆጥተው 'ለምን?! እስቲ ንገረኝ?' አሉኝ፡፡ ስለ መሬት ስሪት፣ ስለ ማይምነት፣ ስለ ትምህርት እቅዋም መዛባት ሳጫውታቸው ሲያዳምጡኝ ቆዩና፣ 'ስለ አገርህ ምንም አታውቅም፡፡ እንደ ሌሎቹ ወጣቶች ሁሉ የተሸነቆረ ወጪት ነህ፡፡ እኛ ስንት ዘመን በጥበብና በትእግስት ታግለን በመከራ የገነባነውን ስርአተ ማህበር ባንድ አዳር ልታፈርሱ ነው የምትፈልጉት፡፡ አገራችሁንና ህዝቡን አታውቁትም፡፡ ስር የላችሁም፡፡ ወፍ ዘራሽ፣ የውሀ ላይ ኩበት ናችሁ' ሲሉኝ፣ እኔም ሞቅ አለኝና፣ 'ለምን አናውቅም? እናውቃለን እንጂ!' አልኩዋቸው፡፡ 'ምንድን ነው የምታውቀው' አሉኝ፡፡ 'የጥቂት ጉልተኞች፣ የብዙሀኑ ጭሰኞች አገር መሆንዋን ለማወቅ ምን መመራመር ያስፈልጋል? ያለ፣ የሚታይ ተጨባጭ ነገር ነው' እያልኩ ለማስረዳት ስሞክር፣ 'ልጅ ለእናትዋ ምጥ አስተማረች አሉ፡፡ ምንም አታውቅም፡፡ ለዚህ ነው የተሸነቆረ ወጪት ነህ የምልህ፡፡ ከሰላሳ አመት በላይ በስልጣን ላይ ኖሬአለሁ፡፡ ደንቆሮ ደግሞ አልምሰልህ፡፡ የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ምሩቅ ነኝ— በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ፡፡ ልንገርህ፡፡ በደፈናው ጭሰኛ ትላለህ እንጂ ስንት አይነት የመሬት ስሪት ባገራችን እንዳለ እንኳዋን አታውቅም፡፡

@OLDBOOKSPDF



ምንም የምታውቀው ነገር የለም፡፡ የማገበው ለዚች አገር ያለኝ ከፍተኛ ተስፋ እንዳንተ ባሉ ሰዎች እጅ መውደቁ ነው፡፡ በከንቱ ነው ስለ የኖርኩት ማለት ነው፡፡ ያሳዝናል' እያሉ ቢነጫነጩብኝ እኔም እልክ ይዞኝ፣ 'ምን ያሳዝናል ክቡርነትዎ፡፡ እያንዳንዱ ትውልድ የታሪክን ህግ ተከትሎ ጊዜውን በራሱ አምሳል እንደ ገና መፍጠሩ የማይቀር ሂደት ነው፡፡ አሮጌው ስርአት ለአዲሱ ቦታ መልቀቅ አለበት' በላቸው፣ ዱላ ቀረሽ ጠብ ተፈጥሮ ካሁን አሁን ከቤታቸው ያስወጡኛል ስል፣ ማርታ መጥታ ገላገለችን፡፡

‹‹በሌላ ቀን ቤቴ መጥታ፣ 'ቤት እንሂድ' ስትለኝ፣ 'አብደሻል እንዴ?' አልኩዋት፡፡ 'ለምን?' ብላ ጠየቀችኝ፡፡ 'እንዴ፣ አባትሽን እንደዚያ ደፍሬ ተናግሬአቸው ሁለተኛ ቤታቸው ብደርስ አያስደበድቡኝም? አሽከሮቻችሁ እንኳዋን ተማተው እንዲሁም ሲያዩዋቸው ያስፈራሉ፡፡ ምኔ አብድ ነው!' አልኩዋት፡፡ ሳቀችብኝና፣ 'አይምሰልህ፡፡ ዳዲ ባንተ ላይ ያሳደረው ግምት ጥሩ ነው፡፡ እኔም ገርሞኛል፡፡ እንዲህ አይነቱን ግትር ከየት ነው ያገኘሽው? እዚህ እንደምታመጪአቸው ሌሎች ጎረምሶችሽ ዝም ብሎ፣ እምን፣ እሺ፣ የሚል አይደለም፡፡ ብዙ አንብቦአል፡፡ ግን የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው ያለው፡፡ እሱን ልክ ማግባት አለብኝ፣ ብሎ እልክ ይዞታል' አለችኝ፡፡ እሺ ብዬ ሄድኩ፡፡ እንደ መጀመሪያ ቀናችን ክርክር ተነስቶ ስለ ሜናርድ ሌንዝና ስለ ካርል ማርክስ አንስተን ስንከራከር ዋልን፡፡

‹‹ከዚያ በሁዋላ እየተገናኘን ስለ ኢኮኖሚ፣ ስለ ፍልስፍና መከራከር የተለመደ ነገር ሆነ፡፡ አንድ ቀን የተናገሩኝ ሁልጊዜ ትዝ ይለኛል፡፡ የታሪክን ሂደት የሚያንቀሳቅሰው የመደብ ትግል ነው፣ ታሪክ ሰሪውም ሰፊው ህዝብ ነው በሚል እርእሰት ስንከራከር ከቆየን በሁዋላ፣ ተናደው፣ 'እኔ፣ ሰላሳ አመት ሙሉ ምንም ታሪክ አልሰራሁም ማለት ነው፤ አይደለም? ሰፊው ህዝብ የምትለውን ተወው፡፡ ህዝብ እንደ መንጋ ነው የሚሄደው፡፡ ጌታኖ ሞስካ የፃፈውን The Ruling Class አላነበብክም? 'The trait of civilization is determined by the elites in any given society' ይላል፡፡ ሰፊውን ህዝብ ተወው፡፡ ታሪክ ሰሪው ሰፊው ህዝብ ነው ብሎ ነገር የለም፡፡ ንጉሱም እንደኔ ታሪክ አልሰሩም፡፡ ለኢትዮጵያ ሞቼአለሁ፡፡ ሰርቻለሁ፡፡ ግን ወጣቱ ትውልድ ውለታ ቢስ ነው፡፡ ከምን ላይ እንደ በቀላችሁ አላውቅም' እያሉ ደም ብዛታቸው እስኪነሳባቸው ድረስ ሲጮሁብኝ ሰማሁና፡፡ 'ታሪክ ሰሪው ሰፊው ህዝብ ነው ሲባል'ኮ ግለሰቦች በታሪክ ውስጥ ሚና የላቸውም ማለት አይደለም፡፡ ወሳኙ ነገር ለየትኛው መደብ ነው የቆሙት? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ነው' ስላቸው፣ 'ለመሆኑ ለምንድን ነው እዚህ የምትመጣው?' ብለው ጠየቁኝ፡፡ ጥያቄው ስላልገባኝና ዱብ

@OLDBOOKSPDF



እዳ ስለሆንብኝ 'አልገባኝም' አልኩ፡፡ ኢንቡሲን ዋጡና፣ 'ሚለቴ፣ ሰዎች እዚህ ቤት የሚመጡት ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ጡት ለመጥባት የሚመጡ አሉ፡፡ ሚስቴ እያለች እኔን ይጠይቁኛል፡፡ የኔ ጡት ደረት ነው፡፡ ልጅን ክርስትና አንሳልኝ ብሎ የሚመጣው ሰው ቁጥር አይጣል ነው— ስንት ስራ የፈታ ቄስ እያለ፣ የበላይ ጠባቂ እንድሆንላቸው፣ ለሹመት፣ ለሽልማት እንድደግፋቸው፣ እንዳማልዳቸው ደጄ የሚኮለኮሉ ብዙ ናቸው፡፡ ያንተ አመጣ ግን የተለየ ነው' ሲሉ ምን ሊሉኝ ይሆን? ብዬ እያሳብኩ ሳስብ፣ 'ልታናድደኝ ነው የምትመጣው አይደለም? ስለ እስም ታሪክ በተለይም ስለ ኢትዮጵያ ከኔ ብዙ የምትማረው ነገር አለ፡፡ ግትርነትና ጥራዝ ነጠቅነት እውቀት አይደለም፡፡ ከመፅሀፍ ይልቅ አድማጊ ብዙ አስተምሮኛል፡፡ ይህን መቀበል አለብህ፡፡ እንድትቀበል ባሳደርግ ደግሞ እኔ ሰው አይደለሁም' አሉኝ›› አላትና፣ ነገሩን አቋርጦ፣ ሰብለን ይቅርታ ጠየቃት፡፡

‹‹ይቅርታው ለምንድን ነው?››

‹‹ዶራቢንቴ ስቦኝ ብዙ ነገር ተናገርኩ፡፡ ግን ይህን ሁሉ ያመጣሁት በእና በአባትዎ መካከል በተፈጠረው ፍልሚያ፣ የእኔና የማርታ ግንኙነት እየጠነከረ ሲሄድ እንዴት እንደ ቻለ ለማሳየት ነው›› አላት፡፡

‹‹ከማርታ ጋር ፍቅር፣ ከአባትዎ ጋር ፍልሚያ መሆኑ ገብቶኛል›› ብላ ቀሪውን ታሪክ ለመስማት በመጉዋጉዋት፣ ‹‹እሺ፣ ከዚያ በሁዋላስ ምን ሆነ?›› አለች፡፡

‹‹ከዚያ በሁዋላማ›› ብሎ፣ ታሪኩን ቀጠለ፣ ‹‹እኔና ማርታ እያዘወተርን አብረን መውጣት ጀመረን፡፡ ከአባትዎ ጋር ያለን ፍልሚያም ቀጠለ፡፡ ከጊዜ በሁዋላ ከማርታ ጋር ስለ ጋብቻ መወያየት ጀመርን፡፡ 'የመንግሥቱ ለማን አሳቻ ጋብቻ እንገባበኛል? ጉዋደኛች መሆናችን ያበቃል፡፡ ስለ ጋብቻ ማሰብ ግን ከንቱ ነው' ስላት 'ለምን እንዲህ ትላለህ? እኔ ገንዘብ ወይም ማእረግ አይደለም የማገባው፣ ሰው ነው፡፡ ያ ሰው አንተ ነህ፡፡ ገንዘብ አለኝ፡፡ የራሳችን ቤት ይኖረናል፡፡ ካንተ የሚጠበቀው ቁጭ ብለህ መፃፍና እኔን መውደድ ነው፡፡ ከዚህ የበለጠ ደስ የሚል ስራ ምናለ? ምናልባት እኔንና ድስትን እኩል የበለጠ ደስ የሚል ስራ ምናለ? ምናልባት እኔንና ድስትን እኩል ላትወድ ትችል ይሆናል፡፡ ግድ የለም፡፡ ድስት የመጀመሪያ ፍቅርህ እንደ ሆነች ይገባኛል፡፡ ይህን ያህልም ራሴን ወዳድና ቀናተኛ ስላልሆንኩ ፍቅርህን አልሻማም፡፡ ለሁለታችንም ጊዜ እንድትኖርህ ተስፋ አደርጋለሁ' ትለኝ ነበር - ሁልጊዜ፡፡

 @OLDBOOKSPDF

«ፍቅራችን እየጠነከረ ሄደ። ግን ቀላል አልነበረም። እኛን ለመለያየት የማይደረግ ሙከራ አልነበረም» ሲል፣ ሰብለ ንግሩን አቋረጠችና፣ «ቤተሰቦችዎ?» አለች።

«ቤተሰቦችዎስ አይደሉም» አለ። «ለጋብቻ የሚፈልጉዋት ሌሎች ሰዎች፣ የመጥፎንታቸው ብዛት፣ 'ውቤ በረሃ ዘውትር ከሚያድር ርካሽ ሰው ጋር እየወጣሽ ለምን ራስሽንና ቤተሰብሽን ታሰድቢያለሽ?' እያሉዋት ሊያጣሉን ይሞክሩ ነበር።»

«እውነት ውቤ በረሃ ታድር ነበር?»

ሳቀና፣ «አዎን፣ ውቤ በረሃ አድር ነበር» አለ። «ግን ለብልግናና ስል ብቻ አይደለም። ስለ ውቤ በረሃ ህይወት አንድ ልብ ወለድ እፅፍ ነበር። ስለ አንድ ነገር ሲፅፉ በተቻለ መጠን ህይወቱንም ጭምር እየኖሩ መፃፍ ጥሩ ነው። አለበለያ መፃፉ የህይወት ትክክለኛ ነፀብራቅ ሊሆን አይችልም።»

«ታትሞ ወጥቶአል?» አለች።

«አይደንጋ ሰሊቱ? አልታተመም። ተፅፎ ቁጭ ብሎአል። አንድ ቀን ይታተም ይሆናል» ብሎ የነገሩ መንስኤ ምን እንደሆነ ሲያስብ ቆየና፣ «ማርታ ስትጠይቀኝ አልደበቅኩዋትም። ምክንያቱን ነገርኩዋት። ስለ መፅሀፉም አጫወትኩዋት። እሰዋ ነገሩ ሲገባትም፣ አባትዋ በጉዳዩ በጣም እንዳሰቡበት ነገረችኝ። 'ከዚህም ከዚያም ከፍተኛ ተፅእኖ እየተደረገበት ነው' አለችኝ። 'ምን የሚያደርጉ ይመስልሻል ታዲያ?' አልኩዋት። 'ውጪ አገር ሊልኩኝ ካሁን ወስነዋል' ብላ፣ እያለቀሰች ነገረችኝ። ወር በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ወደ እንግሊዝ አገር ሄደች። እልህ ያዘኝ፣ ተከትያት ለመሄድ ወሰንኩና የነፃ ትምህርት እድል መፈለግ ጀመርኩ። ኬምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ያለ ምንም ችግር ማመልከቻዬን ተቀብሎ መልስ ላከልኝ። የአርፕላን ቲኬቱም መጣልኝ፣ ፓስፖርት ላወጣ ሄድኩ። ከነገ ወዲያ ተመለስ አሉኝ። የተባለው ከነገወዲያ ደረሰና ሄድኩ። ሌላ ሳምንት፣ ሌሎች ሳምንታት አለፉ። ነገሩ ገባኝ» አለ።

«ምን?» አለች ሰብለ።

«እንግሊዝ አገር እንድሄድ የማይፈለግ ሰው እንዳለ» አላት።

«አባትዋ?»

@OLDBOOKSPDF



«ምናልባት...»

«እንዴት አወቁና?»

«ባለስልጣን ብዙ አይንና ጆሮ አለው፡፡»

«ምን አደረክ ታዲያ?»

ሲራክ ትከሻውን ነቀነቀና፣ «ምን ላደርግ እችላለሁ ብለሽ ነው!» አለ፡- «ለተንኮሉ አልኩና የእንግሊዝ አገሩን ትቼ አሜሪካን አገር መፃፃፍ ጀመርኩ፡፡ ሚቺጋን ዩንቨርሲቲ እንደሚቀበለኝ አረጋገጠልኝ፡፡ ፓስፖርት ጠየቅሁ፡፡ በሶስተኛው ቀን ተሰጠኝ፡፡ ሄድኩ፡፡ ግን አሜሪካን አገር ለመቆየት አልቻልኩም፡፡»

«ለምን?»

«ልቤ እንግሊዝ አገር ሆኖ እንዴት አድርጌ! እዚያው ሆኜ እንግሊዝ አገር ነፃ ትምህርት ለማግኘት ሞከሬ ነበር፡፡ አልሆነልኝም፡፡ ጥዬ ተመለስኩ» አላት፡፡

«ድግሪህን ሳታገኝ?»

«ለድግሪ ደንታ አልነበረኝም፡፡ ደራሲ ለመሆን ለሚፈልግ ሰው ድግሪ አያሻውም፤ የሚያስፈልገው ታላቅ ድርሰት ብቻ ነው፡፡»

«እሺ?»

«እዚህ ተመልሼ አንድ አመት ያህል ከቆየሁ በሁዋላ፣ ቀስ ብዬ ፈረንሳይ አገር ነፃ ትምህርት አገኘሁና ማንም ሳይነቃብኝ ሄድኩ» ብሎ እየተከዘ፣ «ኤክስ፣ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ተሰብስበው እለተ ሞታቸውን የሚጠብቁባት ከተማ ናት፡፡ ቆዬ ብለው ሞት ያሸታሉ፡፡ ትከ ብለው የሚመለከቱት መቃብር ነው፡፡ እርጅናቸው የሚጋባ ይመስላል፡፡ ግን የኤክስ ሰማይ ሁልጊዜ የጠራ ነው፡፡ ለመሬት የቀረበ ይመስላል፡፡ ማታ ጨረቃዋና ከዋክብቱ የተንጠራራ ሰው በእጁ የሚነካቸው ይመስላሉ» አላትና፣ «ደስታዬ ግን ይህ አልነበረም፡፡ ስለ ትምህርቱም ግድ አልነበረኝም፡፡ ማርታ ቅርቤ መሆንዋ ነበር የደስታዬ ምንጭ፡፡ እንደ በፊቱ በመካከላችን ያለው ውቅያኖስ አይደለም፡፡ ስርጡን እንግሊሽ ቻነል የተባለው የባህር ስርጥ ነበር የሚለየን፡፡ ስርጡን አቋርጣ መጥታ ትጠይቀኛለች፡፡ እኔም እየሄድኩ አያታለሁ፡፡

@OLDBOOKSPDF



ለእረፍት ሲዘጋ ጀኖዋ፥ ፍሎሬንስ፥ ቬኒስ እየሄድን አብረን ያሳለፍናቸው ጊዜያት አሁን ትዝ ይሉኛል፡፡ በአይኔ ይመጣሉ» ሲል፡-

«እረ!» አለች ሰብለ፥ ልውጥ ብላ፡፡

ስሜትዋን ሳያጤን ታሪኩን ቀጠለ፡- «እንዲሁ እያልን አራት አመት አለፈ፡፡ ክፍል የገባሁበት ጊዜ ቢቆጠር ካንድ አመት አይበልጥም» ሲል፡-

«ምን ትሰራ ነበር ታዲያ?» አለች፥ ከንፈርዋን ጣል አድርጋ፡፡

«እፅፍ ነበር፡፡ 'መዶሻና ማጭድ' በሚል አርእስት አንድ ልብ ወለድ ድርሰት ጀምሬ ነበር፡፡ ፈረንሳይ አገር በነበሩት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ህይወት ላይ የተመሰረተ ታሪክ ነው፡፡ ፈረንሳይ አገር በደረሱ በስድስተኛው ወር ውስጥ ሁሉም ማርክሳዊ ይሆናሉ፡፡ 'የካፌ አብዮተኞች' ይበዙ ነበር፡፡ በተለይም አዲስ የተሰወጡት ከኛ ወዲያ ማርክሳዊ ላሳር ነው በማለት ያስቸግሩ ነበር፡፡ ትንሽ እውቀት አደገኛ ነው፡፡ ታዲያ ድግሪያቸውን አብዛኛዎቹ ተራማጅ፥ አብዮተኛ፥ ማርክሳዊ የሚሆኑት ድግሪያቸውን እስኪያገኙ ድረስ ብቻ ነበር፡፡

«ድግሪአቸውን እንዳገኙ ማርክሳዊ ቆምብላቸውን አውልቀው ጥለው በሚቀጥለው አይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ቁልቁ ያገራቸውን ዘፈን እየዘፈኑ፡፡ የምን ማርክስ! ግን ጥቂት ሀቀኞች ነበሩ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ 'ጉዋድ መዶሻና ማጭድ' የምንለው ነበር፡፡ ከደረቱ ላይ የመዶሻና ማጭድ ምልክት አይጠፋም፡፡ የሚተኛበት መኝታ ቤት ግድግዳ በሙሉ በመዶሻና ማጭድ ስእል የተሸፈነ ነበር፡፡ እሱም እንደኔ ለድግሪ አይጨነቅም ነበር፡፡ 'እዚህ የመጣነው ብጣሽ ወረቀት ለማግኘት ሳይሆን እውቀት ለመገብየት ነው' ይለኝ ነበር እዘውትሮ፡፡ ታዲያ ፈረንሳዮችን አይወድም፡፡ ስለ ቋንቋቸው ያላቸው ትምክህት ያናድደዋል፡፡ የድመት አይን የሚመስለው አይናቸው ያስጠላዋል፡፡ ነጭ ፊታቸው ለምፅ ይመስለዋል፡፡ 'እኛ ያከሱምን ሀውልት ስንሰራ ነጮች ሲባሉ ዋሻ ውስጥ ነበር የሚኖሩት፡፡ እኛ ክርስትናን በተቀበልንበት ጊዜ እነሱ ካውሬ የባሱ «ሰጃጅ» ነበሩ' ይላል ከጥላቻው የተነሳ፡፡

«በዚህ የተነሳ ፈረንሳዮችን ቢጥሉ አይጠጋም፡፡ ኢትዮጵያውያኖችም አይወድም፡፡ 'ኢትዮጵያዊ ከፍንጫው አርቆ የሚያስብ ፍጡር አይደለም' የሚል ፊሊጥ ነበረው፡፡ የሚያስጠጋው

@OLDBOOKSPDF



እኔን ብቻ ነበር፡፡ 'አንተ ድግሪ አሳዳጅ አይደለህም፡፡ እውቀት ፈላጊ ነህ፡፡ የሰው ነገር ይገባሃል' ስለሚለኝ ያምነኛል፡፡ አለበለዚያ ብቸኛ ነበር፡፡ ከዚዜ በሁዋላ እኔ ካላጀብኩት ከቤቱ መውጣቱን ተወ፡፡»

ስብለ፣ «ለምን ልጄ?» አለች፣ ተገርማ፡፡

«ልነግርሽ አይደል» ብሎ ታሪኩን ቀጠለ፡- «እያጀብኩ ራቱን አበላው ጀመር፡፡ መኝታ ቤቱ ስመልሰው በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘግቶ ካፌ፣ ካፌ ይላል፡፡ አራት አምስት ሲኒ ቡና ይጠጣል፡፡ የመኝታ ቤቱ መስኮት አይከፈትም፡፡ መጋረጃውም አይገለጥም፡፡ ክፍሉ ይሸታል፡፡ ያልታጠበ እግር ሽታ፣ የሲጃራ፣ የቡና አተላ ሽታ አያስገባም፡፡ ወለሉ ሁሉ የሲጃራ ቁራጭ ብቻ ነው፡፡ መስኮቱን ልከፍት ስሄድ 'ተው! ተው!' ይለኛል፡፡ መስኮቱ መከፈት አለበት ብዬ ስቆጣ፣ 'ባክሉም ሀውልት ይገፔሃለሁ' ይለኛል—ትንበርከክ፡፡ ሰውነቱ መንቀጥቀጥ፣ እንባው መፍሰስ ይጀምራል፡፡ ቆይቶ እንዲያውም ትቶኸኝ አትሂድ ማለት ጀመረ፡፡ ልሄድ ስነሳ እንደ ህፃን ልጅ ስቅስቅ ብሎ ስለሚያለቅስ እያዘንኩ መቆየት ጀመርኩ፡፡

«አንድ ቀን ክፍሉ በጣም ስለ ቀረናኝ ጨክንኩና ከፈትኩ፡፡ ሮጦ አልጋው ስር ገባ፡፡ 'ምን ሆንሃል? ና ውጣ ካልጋ ስር' አልኩት፡፡ 'መስኮቱን ዝጋና' አለኝ፡፡ 'ለምን'? ስለው፣ 'የህይለሰላሴ ቅጥረኞች ይገድሉኛል፡፡ ከዚህ የሄዱት ተማሪዎች አደገኛ ኮሚዩኒስት ነው ብለው ዘገባ አቅርበውብኛል፡፡ የፈረንሳይ መንግስትም እየፈለገኝ ነው፡፡ ብቻዬን ካገኙኝ አይለቁኝም፡፡ ይገድሉኛል' እያለ ይሪሀ ጀመር፡፡ መስኮቱን ዘጋሁና እንደ ምንም አባብዬ አስተኛሁት፡፡

«ጠዋት ረፋዱ ላይ ቁርስ ላበላው ስሄድ ክፍሉ ሁሉ ፀድቶ አገኘሁት፡፡ ግን ክፍሉን በጣም የለወጠብኝ መፅዳቱ ሳይሆን ሌላ ነገር ነበር፡ ምንድን ነው? እያልኩ ሳስብ ነገሩ ገባኝ፡፡ ግድግዳዎቹን የሞላው የመደሻና የማጭድ ስእል የለም፡፡ 'ምን ነው? ምን መጣ? አልኩት ግድግዳውን እያሳየሁት፡፡ 'አዎ፡፡ በቃ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ኮሚዩኒስት አይደለሁም፡፡ የሀይለ ስላሴ ቅጥረኞች ቢመጡ ምንም ማስረጃ አያገኙብኝም፡፡ ክፍሉን በጥዋት ተነስቼ ያፀዳሁት ደግሞ መስኮቱን እንዳትከፍትብኝ ነው' አለኝ እየሳቀ፡፡ ሲስቅ ደስ ይላል፡፡ ግሩም ጥርሶች ነበሩት፡፡

«ያደረበት ፍርሃትና የመንፈስ ጭንቀት ከዚዜ ወደ ጊዜ እየባሰበት ሄደ፡፡ የሚያገርመው ነገር ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች እንደ መርዳት ይሸሹት ጀመር፡፡ እኔም በጣም ተቸገርኩ፡፡ አንድ ቀን

@OLDBOOKSPDF


ጨርሶውን ለየለት፡፡ ዩኒቨርሲቲው ምግብ ቤት ራቱን ባባለው ወሰድኩት፡፡ ተማሪው ሁሉ ግጥም ብሎአል፡፡ 'እሳማ ሁሉ! ፈረንጅ ሲባል ያለ ሆድና ምችቱ ሌላ ምንም አያውቅም፡፡ ሰሻኸር ናቸው' እያለ ሲበላ ቆየና ድንገት ብድግ ብሎ ድምፁን ከፍ በማድረግ በፈረንሳይኛ፣ ፈረንጆች ሲትባሉ ሰሸኸር ናችሁ!! ካረመኔ ምንም አትሻሉም፡፡ እናንተ ቆዳ ለብሳችሁ፣ በጥርብ ድንጋይ አውሬ በምታድኑበት ዘመን እኛ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ስልጣኔ ላይ ነበርን፡፡ ለዚህም ያክሱም ሀውልቶችና የላሊበላ አብያተ ክርስቲያን ምስክሮች ናቸው፡፡

«ቁሳዊ ስልጣኔአችሁ የተገነባው በጥቁሮች ደምና ወዝ ነው፡፡ ደማችንና ወዛችንን ነው በልታችሁ የምትጠጡት፡፡ የእንጀራ ገመዳችሁ እንዳይበጠስ የእብድ ገላጋይ ሆናችሁ እርስ በእርሳችን ታፋጁናላችሁ፡፡ በመጨረሻም እኛን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ቦምብና መርዝ እያካበታችሁ ነው፡፡

«'አውቶማቲክ ቦምብ መቼ በናዚ ጀርመን ላይ ጣላችሁ?! ዘረኞች ስለ ሆናችሁ አውቶማቲክ ቦምብ የጣላችሁት በሂሮሽማና በናጋሳኪ ላይ ነው፡፡ አዳዲስ የጦር መሳሪያችሁን የምትፈትኑት በቬትናም ህዝብ ላይ ነው፡፡ ወደ ፊት ለጥቁሮች ያቀዳችሁትን ያዝዝ ዘደቤ በደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች ላይ እየሞከራችሁ ነው፡፡ ግን አይሆንላችሁም! ጥቁር ህዝብ ያሸንፋል፡፡ በመዶሻ ይቀጠቅጣችሁአል፣ በማጭድ ይቆራርጣችሁአል፡፡ መዶሻና ማጭድ ለዘለአለም ይኑር! እያለ ሲለፈልፍ፣ ሀበሾች፣ 'አዋረደን፡፡ ውርደት አከናነበን'፣ እያሉ፣ ፈረንሳዮች ደግሞ እብደቱ ለይቶለታል እያሉ ወጡ፡፡

«ይህ ከሆነ ከሳምንት በሁዋላ ነው መሰለኝ፣ የፈረንሳይ መንግስት ወደ አገሩ ባስቸኩዋይ እንዲመለስ ወሰነ፡፡ ጨርሶ አእምሮውን ስቶ ስለነበረ ማን ይዞት ይሂድ? የሚል ጥያቄ መጣ፡፡ እንደዚያ ሆና እያየሁት ዝም ማለት አልቻልኩም፡፡ ይዤው ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ፡፡፡»

«ማርታስ አላሳበበችህም?

«ብስብም ምርጫ አልነበረኝም፡፡፡»

«እሺ፡፡፡»

«ይዤው መጣሁና ለዘመዶቹ አስረከብኩዋቸው፡፡ ደህና ሆኖ ነበር፡፡ አሁን የት እንዳለ አላውቅም» አላትና ዝም ብሎ ቀረ፡፡

«ከዚያስ?» አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF



ሌላ የሚላት ነገር አልነበረውም፡፡ እንዲህ ያለው ውብ ግንኙነት ምንም አይነት የወደፊት እድል የለውም ሊላት አልቻለም፡፡ እንደ ሊለውም እርግጠኛ አልነበረም፡፡ ለሁለት የተከፈለ ልብ ይዞ ዝም አለ፡፡ አእምሮው ውስጥ የሚንላላውን አሳብ የምታነብ ይመስል ትኩር ብላ ታየው ነበር...

ምእራፍ ፲፬

ሲራክ ከሰብለ ከተለየ ወዲህ ተናዳጅና ነጭናጫ ሆኖ ነበር ያመሸው፡፡ ተናዳጅና ነጭናጫ ያደረገው የልቡ ለሁለት መከፈል ነበር፡፡ ቀድሞንም ቢሆን ምን ሲያቀብጠኝ እዚህ ጣጣ ውስጥ ገባሁ? እያለ ባሰበ ቁጥር የተረገመ መፅሀፉን መልሶ ከመርገም አያልፍም፡፡ ከሰብለ ጋር መገናኘቱ ደስ የሚለውን ያህል ከእስዋ መለየቱን ባሰበ ቁጥር፣ አሳቡ ራሱ የማይችለው ስቃይ እየሆነበት፣ በዚያ ላይ ደግሞ መፅሀፉን እንደ ገና የሚጀምርበት ጊዜ ሩቅ፣ በጣም ሩቅ ሆኖ እየታየው መንፈሱ ሲጨነቅና ሲታወክ ነበር ቤት የገባው፡፡

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ሚስቱም ጤነኛ አልነበረችም፡፡ ፅጌ ከፉኛ ኩፍ ብላለች፡፡ ከመሬት ተነስቶ ምንቅረ፣ ምንቅር ያደርጋታል፡፡

፡፡እህህ፣ አለም ዘጠኝ አለ፡፡ አለች፣ ፅጌ በድንገት፡፡

ልጁ በጊዜ ተኝቶአል፡፡ ዛሬ ጦርነት በዚህ ቤት ጣሪያ ስር ፈንድቶ፣ እሽናፊም ተሸናፊም የሌለበት እልቂት ሳይደርስ አይቀርም አለ በልቡ፡፡

በማንኛውም ደቂቃ፣ በትንሽ ምክንያት፣ ፈንድቶ ምድርና ሰማይ የሚደባለቅ ተጠምዶ የተቀመጠ ቦምብ ትር ትር ቢል ተሰማው፡፡ የነገር ሚሳይሎች ሲወረወሩ ታየው፡፡ የተቀጣጠለው እሳት ነጎ ምድርና ሰማዩን ሲለበልብ፣ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች እንደ ባዜሉን ንገብ ተደርምሰው ሲወድቁ፣ የሰው ልጅ ስልጣኔ ወደ አመድ ክምር ሲለወጥ በአይኑ-ህሊናው መጣበት፡፡ እና፣ ይህ ሁሉ ተቁት ለገዝቢ ውይይት መድረክ ካለመከፈት የሚመጣ ነው፣ አለ፡፡

@OLDBOOKSPDF


‹‹እኔ በተመለስኩ በወሩ ማርታም ተመለሰች፡፡ እንዲጋጣሚ ሆኖ ልክ በተመለሰችበት ቀን አባትዋ የዘውድ አማካሪ ተብለው ተሾመው ነበር፡፡ ቤታቸው ሄድኩ፡፡ ከመቃብር አምልጠው የመጣሁ ይመስል ለረጅም ጊዜ ትክ ብለው ሲያዩኝ ቆዩና የት ጠፍቼ እንደ ከረምኩ ጠያየቁኝ፡፡ ነገርኩቸው 'ፈረንሳይ አገር!' አሉኝ ሙክ ብለው፡፡ ሲያስቡ ቆዩና፥ 'ሰይቶልሃል!' አሉኝ፡፡ ምን ሲያስቡ እንደነበሩ ቢገባኝም፥ 'ምኑ?' አልኩዋቸው፡፡ 'አብዶቱ' አሉኝ፡፡ 'እንዴት?' ስላቸው ጊዜ፣ 'ፈረንሳይ ተማሪዎች ምን ጤና አላችሁ?' አሉኝ፡፡ የፈረንሳይ ተማሪ አይወዱም፡፡ የአክሊሉ ካብኔ ያበሳጫቸው ነበር፡፡

‹‹'ለማንኛውም ነገር እንኩዋን ደስ አለዎት' አልኩቸው፡፡ 'ስምኑ?' አሉኝ፡፡ 'የዘውድ አማካሪ ሆነው ስለተሾሙ'... ብዬ ሳልጨርስ፥ 'ተወኝ እባክህ፡፡ የዘውድ አማካሪ አያስፈልግም፡፡ ዘውድ የሚቀማው ጉልበት ያለው ነው አሉኝ፡፡' 'ቢሆንም ለእርስዎ እረፍት ነው' ስላቸው፥ 'አዎን፥ ለወይዛዝርቱ የሽቱ መግዣ እየተባለ የሚታዘዘውን ገንዘብ መፈረም ስልችቶኝ ነበር' አሉኝና፥ እንግዶች ለመቀበል ትተውኝ ሄዱ፡፡

‹‹ከማርታ ጋር ተገናኘን፡፡ ከዚያ በሁዋላ የድሮው ህይወታችን ቀጠለ-ከእስዋ ጋር መውጣት፡፡ ከአባትዋ ጋር ያስተሳሰብ ፍልሚያ መግጠም፡፡ ሁለት አመት አለፈ፡፡ አንድ ቀን፣ 'ሙሉ ጊዜህን ደራሲ መሆን ትፈልጋህ?' ብላ ጠየቀችኝ፡፡ 'በማን እድሌ' አልኩዋት፡፡ ከፈረንሳይ አገር ከተመለስኩ በሁዋላ የድሰቱን ነገር እርግፍ አድርጌ ትቼው ነበር፡፡

‹‹ከእኅትዋ ጋር ፀደይ አለመጭና ባኪ ድርጅት እቁዋቁመው ነበርና ድርጅቱ ውስጥ ትንሽ ትንሽ ስራ እየረዳሁ ሙሉ ጊዜዬን ድርሰት ስራ ላይ ለማዋል እንደምችልና ደሞዜም የተሻለ እንደሚሆን ነገረችኝ፡፡ ህይወቴን በሙሉ ስመኘው የነበረ እድል ቢሆንም፥ እሳቡ ከእስዋ እንዳልመጣ ገባኝ፡፡ ከእኅትዋ የመጣ አሳብ ነበር›› ብሎአት፥ ታሪኩን አቁዋረጠና፥ ‹‹እኅትዋን ሳስታውስ ከ1960 እስከ 1966 ዓ.ም የነበረው ጊዜ ትዝ ይለኛል›› አላት፡፡

‹‹ምኑ?›› አለችው ስብለ፡፡

‹‹ጊዜው፥ የጊዜው መንፈስ›› አላት ለማስታወስ እየሞከረ፡፡

‹‹እንዴት?›› አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF



ቦምቡ ከመፈንዳቱ በፊት ወጥቶ ለመሄድ አስቦ ነበር፡፡ ግን ከተቀመጠበት መነሳቱ ራሱ የፈራውን ነገር መጋበዝ ይሆናል በማለት የቦምቡን ትርታ በተንጠለጠለ ልብ እያዳመጠ ቁጭ ብሎ ቀረ፡፡

በድንገት፣ ‹‹አ ሃ ሃ ሃ — ኦ ሆ ሆ›› ብላ ስቃ፣ ‹‹ታሪክ ነው እቴ —እንደ ምጣድ ቂጥ መጠበስ! ማሽላ ሲያር እየሳቀ ነው አሉ›› አለች፡፡

ሲራክ ደንግጦ አይኑን ጨፈነ፡፡ የፈራው ጦርነት! ደግነቱ በነገሩ አልገፋችበትም፡፡ አይኑን ሲከፍት ውባንቺ እርሳስና ደብተርዋን ይዛ ስትገባ አየ፡፡ የሰላም ርግብ የደረሰችለት ይመስል ተደስቶ፣ ‹‹የፈተናው ነገር ከምን ደረሰ?›› አላት፡፡ፈተና የወሰደች መሆንዋን ባለፈው ጊዜ ነግራው ነበር፡፡

‹‹አለፍኩ›› አለችው፡፡

‹‹ውነትሽን ነው?›› አላት ስሜት ፈንቅሎት፡፡

‹‹ገብርኤልን!›› አለች፡፡

‹‹ጎበዝ የኛ ልጅ!›› ብሎ ተነሳና የጋለ ሰላምታ ሰጣት፡፡ በዚህ ስሜቱ አልረካ ስላለው በጭቃ ቀለም የሚሰራ ‹‹ፓርከር›› ብእር ከደረት ኪሱ አወጣና፣ ‹‹እንኳዋን ደስ ያለሽ›› ብሎ ከሰጣት በሁዋላ፣ ‹‹ደሞዝ ሲመጣ ደ'ሞ ጥሩ ቀሚስ›› አላት፡፡

ፅጌ ቀና ብላ እንደ ጦር በሚወጋ አይን አየችው፡፡

ውባንቺ እጅ ነሳችና ብእሩን እያየች፣ ‹‹ምን አደርግበታለሁ?›› ብላ ጠየቀችው፡፡

‹‹ትፅፈበታለሻ›› ብሎአት፣ ‹‹ቆይ እንዴት እንደሚሰራ ላሳይሽ›› አላትና፣ ብእሩን ከእጅዋ ተቀብሎ እንዴት ልትሰራበት እንደምትችል ደጋግሞ ካሳያት በሁዋላ፣ ብእሩን መልሶ ሰጣትና፣ ‹‹ታዲያስ? ከማይምነት መላቀቅ ደስ ይላል? አሁን ምን ይሰማሻል?›› አላት፡፡

ውባንቺ እየተሽኮረመመች፣ ‹‹ደስ ይላል›› አለች፡፡

‹‹እንደ ገና የመወለድ ያህል ነው፣ አይደለም?›› አላት፡፡

@OLDBOOKSPDF

«ወጣት ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች፣ ጠበቆች፣ እየቆጠቆጡ የመጡበት ጊዜ ነበር። ትዝ ይልሻል ያ ጊዜ?» አላት።

«ከሁሉም ትዝ የሚለኝ በቦሌው ጎዳና ባንድ አዳር የሚሊዮን ብር ጌታ ይሆኑ የነበሩት ሰዎች ናቸው» አለችው።

«ይህን ያዩ ብዙ ሰዎች ደህና ሁኚ አራዳ እያሉ ወደ እርሻ በመሮጥ ለአያቶቻቸው ገባር፣ ለአባቶቻቸው ጭሰኛ ሆነው የኖሩትን ደሀ ገበሬዎች በግፍ እየነቀሉ በማባረር ሰፋፊ የንግድ እርሻዎች መፍጠር ጀምረው ነበር። መሬት የለቀቁ ጥቂት ከበርቴዎች ብቅ ባሉ ቁጥር፣ ከስር እንደ አሸን ይፈላ የነበረው ቦዘኔ ሰቶድ ነበር። ግን፣ ያን ጉድ ማን ዞር ብሎ ሊያይ! ሰማይ ነበር ጣራቸው» ብሎአት ጊዜውን በደበልጥ እያስታወሰ፣ «ከሁሉም ትዝ የሚለኝና ሲያስቀኝ የሚኖረው አዲስ የተፈጠሩት ከበርቴዎች በመካከላቸው ያካሂዱት የነበረው ውድድር ነው።

«ደህናው ሜዳ አስጠልቶአቸው ተራራ ላይ በመውጣት የእንጦጦን ጋራ እየቦረቦሩ፣ ያዩ ፋሲልን ግንብ፣ አየር ላይ የሚንሳፈፍ መርከብ፣ አቆብቁቦ ለመነሳት የተዘጋጀ አይሮፕላን የሚመስሉ ቪላዎች ሰርተው፣ የሳሎኑን መስኮት ከፈት አድርገው ሲያበቁ፣ ቪቫስ ሪጋል ውስኪ በበረዶ ጨብጠው፣ ትኩስ አየር እየሳቡ፣ ጉብልዬን እየሰሙ፣ አዲስ አበባን ከናቱ ቁልቁል ማየት በቃ —ምናባቱ! የዘመኑም ወሬ ይኸው ብቻ ነበር። 'እገሌዬ በመቶ ሃምሳ ሺህ ብር የሰራውን ቪላ አይተሻል? መኪናው ሰተት ብሎ ሳሎን ድረስ ነው የሚገባው።' ሌላዋ ደግሞ፣ 'ውይ፣ እንትንዬ የሰራውን ቤት ባየሽ? አባይን ያላየ ምንጭ ያደንቃል አሉ። በሁለት መቶ ሺህ ብር የሰራው ቤት ታይቶ አይታወቅም። የቤቱ እቃ አንድም ሳይቀር ከኢጣልያን አገር ነው የመጣው። የሳሎኑን እቃ ከየት እንዳስመጣው አላውቅም። ገና ሄደው ቁጭ ሲሉበት እንቅልፍ ያስወስዳል። ደ'ሞ የቤቱ አሰራር የሚደንቅሽ ነው። ሳሎን ሆነው ደጅ አበባ ውስጥ ቁጭ ያሉ ይመስላል። አቤት መኝታ ቤቱ? ገነት ነው' ስትል፣ ሶስተኛዋ ደግሞ፣ 'እንትና የገዛውን አዲስ ባለ አውቶማቲክ ማርቼዲስ አይታችሁአል? ግሩም ነው፣ እግዱ ትመጡት' ስትላቸው፣ 'እገሌዬ ውሀ የመሰለች ቢኤም ደብሊው አስመጥቶልሻል' ከማለትዋ፣ ሌላዋ ቀበል አድርጋ፣ 'የእንትናዬን ጃጉዋር ባየሽ' ሲባባሉ — ይኸው ነበር የዘመኑ ወሬ። ሁኔታው ድቡሽት ላይ ቤት እንደ መስራት ነበር» ካላት በሁዋላ፣ ንግግሩን አቋርጦ ሲያስብ ቆየና ወደ፣ ተነሳበት ጉዳይ በመመለስ፣ «የማርታ አባት ዘመኑ ካስገኛቸው ከበርቴዎች ውስጥ አንዱ ነበር። ግሩም ጭንቅላትና ከምላሱ የሰላ ብልጠት ነበረው። እንደ ሌሎቹ የእሱም ጣራ ሰማይ

ነበር፡፡ በተሰማራበት ንግድ አለም ስማይን ከመንካት ሌላ አላማ አልነበረውም፡፡

«ለማንኛውም ነገር እኔ የንግድ ሰው ባልሆንም፣ እንደኛ፣ ልምዱን ለማግኘት፣ ሁለተኛ፣ ጊዜ አግኝቼ የድርሰቱን ስራ በሰላም ለመቀጠል ከቻልኩ ምን ችግረኝ በማለት እሺ አልኩዋት፡፡

«ስራዬን ለቅቄ ወደዴ አሰመጭና ላኪ ድርጅት ገባሁ፡፡ድርጅቱ እያደገ ሄደ፡፡ ግን እንዳሰብኩት አልሆነልኝም፡፡ ለድርሰት ጊዜ አልነበረኝም፡፡ ማርታን ሳይ ወጥመድ ውስጥ መግባቴ ታወቀኝ፡፡ እነትዋም የፈለገው ይህንኑ ነበር፡፡ ካንድ አመት በሁዋላ በቃኝ ብዬ ለመውጣት ተነሳሁ፡፡ እነትዋ፣ ደሞዝ፣ ተጨማሪ ስልጣን ቢሰኝ እሻፈረኝ አልኩ፡፡

«ከጥቂት ቀናት በሁዋላ ማርታ ቤት መጥታ፣ 'እንጋባ እንግዲህ' አለችኝ፡፡ 'ምን የሚያስቸኩል ነገር መጣ?' አልኩዋት ተገርሜ፡፡ እንደምወዳት እውቃለሁ፡፡ ግን ታገባኛለች ብዬ ስለማላስብ፣ ከሌሎች ወንዶች ጋር ስትወጣ እያየሁና እየሰማሁ፣ ፍቅርዋ ቢቀርብኝ፣ በልቤ ያሳደረችው ቅናት ይበቃኛል ብዬ እኖር ነበር፡፡ የቅናትን ትርጉም ያሳወቀችኝ እሰዋ ናት፡፡

«'አልቸኩልኩም፡፡ ሰባት አመት ጠብቄሃለሁ፡፡ ወይስ ሰባት አመት እጭር ሆኖብህ ነው?' ብላኝ ልታገባኝ የቆረጠች መሆንዋ ነገረችኝ፡፡ ተጋባን፡፡ የሰርጋችን እለት ትዝ ይለኛል፡፡ ሰርክ ልብሴን እንኩዋን አልለወጥኩም፡፡ እሰዋ በሙሽራ ልብስ ንግስት መስላ እጠገቤ ቆማ፣ በልኡላን፣ በመሳፍንትና በመኩዋንንት ተከበን ሳይ ሀልም ይመስለኝ ነበር፡፡ አባትዋ መጨነቄን አይተው ነው መሰለኝ መጥተው፣ 'አይዞህ፡፡ እኔም እናትዋን ሳገባ በመሳፍንትና በመኩዋንንቱ መካከል እንተን እመስል ነበር' አሉኝና፣ ቀስ ብለው በጆሮዬ፣ 'ማርታን ለምን እንደ ሰጠሁህ ታውቃለህ ወይ?' አሉኝ፡፡ ስለ ወደደችኝ ነዋ! ደግሞ እርስዎ አይደለም የሰጡኝ፡፡ እሰዋ ናት ያገኘችኝ አልኩዋቸው፡፡ ቆጣ ብለው፣ 'ሞኝ አትሁን፡፡ ፖለቲካዊ ጋብቻ ነው' አሉኝና ሄዱ፡፡

«በማግስቱ የጋብቻችን ዜና በጋዜጦች ወጥቶ አየሁ፡፡ ዜናው፣ ሰርጋችን በጣም መጠነኛ እንደነበር ይገልፅና በዘዶ የመደብ ጀርባዬን ይጠቁማል፡፡ ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑ ገባኝ፡፡ ጋዜጦቹን ያነበበ ሁሉ፣ 'እርሳቸው ግን ድሀን አይንቁም፡፡ ቢፈልጉ ላንዱ ልኡል ሊድሩዋት ይችሉ አልነበረም? አይ ሰው!' ሲል እንደ ከረመ ሰማሁ፡፡ የፖለቲካ ጋብቻ ነው ያሉኝ ትርጉሙ ገባኝ፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹እንደሱ ነው የሚሰማኝ፡፡ አሁን ሰው የሆንኩ ይመስለኛል›› አለች፡፡

ሲራክ ወደ ወንበሩ ተመለሰና ‹‹አይዞሽ፡፡ የማይምናን ወገኖቻችን አይናች የሚያነቡበት፣ እጆቻቸውም የሚፅፉበት ጊዜ ቅርብ ነው፡፡ እና፣ እንዳልሺው ያኔ ሁሉም እንዳንቺ ሰው መሆኑ ይሰማዋል፡፡ ውብ ነው፡፡ ማን የተማርሺውን እንዳትረሺ ቶሎ ቶሎ ለማንበብ ሞክሪ፡፡ እኔም አንዳንድ መፅሀፍ አመጣልሻለሁ፡፡ እሺ?›› ሲል ፅጌ ከንፈሮችዋን በማሞጥሞጥ እያሽሙዋጠጠችው፣ ‹‹ድንቄም ፊደል ቆጠረችና ሰው ሆና ልብ ውልቅ አቱ!›› ብላ ወደ ውባንቺ ዞር በማለት፣ ‹‹ይልቅ ይህን የከሰል ምድጃ አውጥተሽ አራግቢ፡፡ ቀን የወጣውም እህል አልተበካም፡፡ በሣታው አፉን ከፍቶ የሚጠብቀው እኔን አይምሰልሽ፡፡ ደግሞ ቡና ቶሎ ገንብተሽ ነይ›› በማለት በትእዛዝ ናዳ ስታጣድፋት ከቆየች በሁዋላ ጣቶችዋን አንቋቆቆዋችና፣ ‹‹ከዘመኑ መፈክር አንጀቴ የሚገባው፣ 'ሰውን ሰው ያደረገው ስራ ነው' የሚለው ነው ልጄ!›› አለች፡፡

– መልካም ቃል ማንን ገደለ፣ ወይስ እኔን የጎዳች መስሎአት ነው? በማለት ውስጥ ውስጡን ቢበሽቅም፣ ለምን ጦርነት ላስነሳ? በቀዝቃዛው ስነልቦናዊ ጦርነት ቢቆይ ይሻላል ብሎ ፈርቶ ዝም በማለት፣ ቀድሞውንም ምን ሲያሮጠኝ በጊዜ መጣሁ? እያለ ማሰብ ሲጀምር ከጎረቤት እልም ያለ እልልታ ሲቀልጥ ሰማና ቀና አለ፡፡

‹‹ተረት ሰፈር እልል የሚያሰኝ ምን ነገር አለ ብለው ነው? ወገኞች! ላቃችንም ልቅሶ ነው የሚመስለው›› አለች ፅጌ፡፡

ምንስ የሚያሳዝን ነገር አለ? ሊላት ፈልጎ ነበር፡፡ አፉን በዳቦ ብሎ ዝምታውን መርጦ ዝም አለ፡፡ ውባንቺ ስትንደረደር መጣችና፣ ‹‹አቶ በቀለ መጡ!›› አለች፡፡

‹‹ማን ነው አቶ በቀለ?›› አላት፡፡

‹‹እኝህ ጦር ሜዳ የሄዱት›› አለችው፡፡

‹‹እረ እባክሽ!›› ብሎ ብድግ አለ፡፡ ችሎ ማደር ትዝ አለው፡፡ ሲያስበው ሰሞኑን ሲያሳዝን አልሰማውም፡፡ ሄዶ ደስታውን ከመግለጡ ሊላ፣ ከቆየበት ውጥረት መውጫ ቀዳዳ በማግኘቱ በይበልጥ ደስ ብሎት በልቡ ሳይደግስ አይጣላም እያለ ወደ በሩ ሲሄድ፣ ‹‹የት ለመሄድ ነው?›› አለችው፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹ይግረምሽና፣ ጉዋደ መደሻና ማጭድ፣ ፈልጎኝ መጥቶ፣ እንከኑዋ ደስ ያለህ ይለኛል ብዬ ስጠብቅ፣ ‹አይ የኛ ታጋይ፡፡ ይህን የበሰበሰ ስርአት ትታገላለህ ብዬ ስጠብቅ፣ ትጋባ ይገርማል፡፡ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ካፍንጫህ ትንሽ ራቅ አድርገህ የማታስብ ፕሪሃልናየ ብሎኝ ጥሎኝ ሄደ፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ ተገናኝተን አናውቅም፡፡

‹‹ድርጅቱ እየሰፋ ቢሄድም ለመፃፍ እሞክር ነበር፡፡ ማርታ ምኞቴን ስለምታውቅ ታበረታታኝ ነበር፡፡ አንድ ቀን ጥሩ ደራሲ እንደምሆን እምነት ነበራት፡፡ ግን ምንም የሚረባ ነገር ለመፃፍ አልቻልኩም፡፡ ውስጥ ውስጡን ልቤን የሚበላው ነገር ነበር፡፡ ምንድን ነው ብዬ ሳስብ ምን ሆኖ አገኘሁት መሰለሽ? ያ ቅናት ስለቀረ ማሰቤ መሆንዋ ብቻ የማያረካኝ ሆኖ አገኘሁት፡፡ አይገርምሽም እንዲህ ያለ ስሜት?›› አላት፡፡

‹‹በሽታ ነው እንጂ እኔ እንዲህ አይነቱን ነገር ስሜት አልለውም›› አለችው ሰብለ፡፡

‹‹ቅናት የፍቅር ጥላ ነው፡፡ ፍቅር ያለ ቅናት ጥላ቞ ቢስ ይሆንብኛል›› አለና፣ መልስዋን ሳይጠብቅ፣ ‹‹ባጠቃላይ ጥሩ ኑሮ ነበር፡፡ የጎደለን ነገር አልነበረም፡፡ ግሩም የሆነ ልጅም አገኘን፡፡ ጉዋደኛ መሆን ጀምረን ነበር ከልጁ ጋር›› አለና ዝምታ ዋጠው፡፡

አይኖቹ እንባ አቀረሩ፡፡ ሰብለም ዝም አለች፡፡

‹‹አሁን እሱን እንርሳው›› ብሎ ታሪኩን ቀጠለ፡-

‹‹በየማብሪያው ከመኪዋንቱና ከመሳፍንቱ ጋር ትክሻ ለትከሻ እየተጋፋሁ፣ ስለ ደም ብዛትና ሪሀ ማውራት ደስ ባይለኝም፣ ከማርታ ጋር ያሳለፍነው ጊዜ ጥሩ ነበር፡፡ ቀን ስራ፣ ማታ ግብዣ፣ በየሞቹው ቤት ልቅሶ መድረስ፣ ደም ብዛትና ሪሀ የተጠናወታቸውን መሳፍንቶች፣ መኩዋንንቶችና ሚኒስትሮችን ነጋ ጠባ መጠየቅ፣ ቀብር መድረስና ሀዘን ላይ መቀመጥ – ይህ ነበር የሚያስጠላኝ፡፡ የራሴ ነው የምለው ጊዜ ትንሽ ነበር፡፡

‹‹ከማርታ ጋር በዚህ ነበር ዘወትር የምንጣላው፡፡ ግብዣ፣ ወይም ልቅሶ ወይም ቀብር ካልሄድን ብላ ድርቅ ትላለች፡፡ እኔ ደግሞ አልሄድም ብዬ ድርቅ እላለሁ፡፡ ከሁሉም ነገር ይበልጥ የሚያስጠላኝ ለግብዣ ልብስ መለወጡ ነበር፡፡ የተገነዝኩ ይመስለኛል፡፡ ምን ማለትህ ነው? የማኅበራዊ ኑሮ ግዴታችንን ማክበር አለብን፡፡ ብቻችንን

@OLDBOOKSPDF



ቆም ብሎ፥ «እቶ በቀለ ቤት» አላት፡፡

ብስጭት ብላ፥ «ላነጋግርህ ፈልጌ ነበር» አለችው፡፡

ቆጣ ብሎ፥ «ታዲያ እስካሁን ምን ዘጋሽ?» አላት፡፡

ድሮ ቢሆን ገና ቤት ገብቶ ቁጭ ሳይል እስትዶድማ ትሯሯጥበት ነበር፡፡

«ከእንግዲህ የሚያጣድፍ ነገር የለም፡፡ ስትመለስ ያደርሰናል፥ የጆብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል አሉ» አለችው፡፡

«ደህና» ብሎ፥ በልቡ ዛሬ፥ እውነትም እምርራ ተነስታለች እያለ ወጣ፡፡ ቀጥታ ወደ ጉዋድ በቀለ ቤት አልሄደም፡፡ ወደ መንገድ ወጣ ብሎ መጠጥ ቤት ጎራ አለና አንድ ጠርሙስ እናትና ልጅ አረቄ ከገዛ በሁዋላ ነበር ተመልሶ ወደ ጉዋድ በቀለ ቤት ያመራው፡፡

ቤቶች ብሎ ሲገባ ጎጆዋ ከአፍ እንከ ገደፍዋ በሰው ጢም ብላ ሞልታ ነበር ያገኛት፡፡ የሰፈሩ ሰው አንድም የቀረ አይመስልም፡፡ የእትዬ አልታዬ ወርቅ ጥርስ ከሩቅ ብልጭ ሲል ታየው፡፡ «ሰው በላው ጎንደሬ» ሞቅ እንዳለው ያስታውቃል፡፡ የበቀለ ባለቤት፥ «ወይ በሞትኩት፡፡ ምን አሳሰበዎት» እያለች አረቄውን ስትቀበለው፥ እንካላው ጋሼ ማንደፍሮ «ኖር ቲቸር» አለው፡፡ ሁሉም ተነስተው ቆመው ነበር፡፡ የእውሩ ለማኝ ዘንግ ብቅ ብሎ ታየው፡፡ ግን የሲራክ እድን ያረፈው በችሎ ማደር ላይ ነበር፡፡ የሚሲሺያ ደንብ ልብስ ከለበሰ አንድ ረዘም ያለ ጥቁር፥ ወገቡ እንደ ሀረግ ከሚመዘዝ ሰው እግር ስር የፊት እግሮቹን ዘረግቶ በደረቱ ተኝቶአል፡፡ በውዬው ልጅ ታቅፎ ቆሞአል፡፡ በቀለ ግን እንደ ሆነ አወቀና ሄዶ፥ «ጉዋድ እንኩዋን ለቤትህ አበቃህ» ብሎት ሰላምታ ሰጠውና ጉንጭና ጉንጩን አገላብጦ ሳመው፡፡ ከበቀለ አጠገብ የክብር ስፍራ ተሰጠውና እንደ ተቀመጠ፥ የበቀለ ባለቤት፥ «ቅድም አላቸውን ነበር ያነሳነው» አለችው ባልዋን፡፡

«ስለ ችሎ ማደር ማላዘን የጠየቁሽ? አላት እየሳቀ፡፡ ሲስቅ ከጥቁር ፊቱ ጋር የሚያንፀባርቀው ነጭ ጥርሱ በጠፍ ጨረቃ እንደ ተመዘዘ ጎራዴ ብልጭ እያለ እይን ይመታል፡፡ ጥቅጥቅ ያለ ሪዝ የላይኛውን ከንፈሩን ከዳር እስከ ዳር ሸፍኖት ይታያል፡፡ የራስ ጠጉሩም እንደ ሪዙ ጥቅጥቅ ያለ ሜካ መስሎ ከወደግንባሩ በራው ገለጥ ብሎ ይታያል፡፡

አልተፈጠርንም፡፡ ወደድንም ጠላን የህብረተሰቡ አካል ነን፡፡ እባቴ በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ ያለውን ስምና ቦታ ደግሞ መርሳት የለብህም ስትለኝ እናደድና፣ 'እኔ 'ኮ ያገባሁት መደባችሁን እንዳለ በሙሉ አይደለም፡፡ ያገባሁት እንቺን ነው፡፡ እና፣ ነፃነት እንድትኖረኝ እፈልጋለሁ፡፡ ግብዣችሁ ባፍንጫዬ ይውጣ! አንቺ ህብረተሰብ የምትዪው የትኛውን ወገን እንደሆነ ታውቂያለሽ? ሪሀና ደም ብዛት ያበሰበሳቸውን የገዥውን መደብ አባላት ነው፡፡ ሰልችቶኛ! እንገፍግፎኛል የናንተ ግብዣ! ጣሳ ቤት ብሄድ ነፍሴ ይበልጥ ትደሰታለች፡፡ እፎይ ትላለች' እያልኩ ስጮህባት፣ 'ሂዳ! ታዲያ ማን ከለከለህ? ሮጠህ ጣሳ ቤት ሂድ እንካላ ደሮ ሳትቀድምህ፡፡ ድሮውኑም ቢሆን ትንሽ ነፍስ ምኞትዋ ትንሽ ነው!' ትለኝና እያለቀሰች ወጥታ ትሄዳለች፡፡

«እኔም ተናድጄ ብቻዬን እወጣለሁ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሲኒማ ነበር የምሄደው፡፡ አንድ ምሽት እንዲሁ ተጣልተን ተለያየን፡፡ ሲኒማ ቤት ሰለቸኝና ዝም ብዬ ወደ ከተማ ወጣሁ፡፡ የጥንቱ ውቤ በርሃ ትዝ አለኝ፡፡ ግን ባስበው ሞቶ እንዳልነበረ ሆኗአል፡፡ ለለውጥ ያህል ወደ ሰራተኛ ሰፈር አመራሁ፡፡ ዝም ብዬ ስዞር አንድ ቄሮ ያለ ቤት አገኘሁና ገባሁ፡፡ ጠይም፣ ቆንጆ፣ አይኖችዋ ቦግ ቦግ ያሉ ወጣት ሴት ብቻዋን ቁጭ ብላ ጫት ትበላ ነበር፡፡ አይኖችዋ ትላልቅ ከመሆናቸው የተነሳ፣ ሁለመናዋ አይን መስሎ ታየኝ፡፡ እንደ ነገሩ ሸብ ያደረገችው ሻሽ ከሉጫ ጠጉርዋ ላይ ስለማይረጋ እስር እስር ጊዜ ታስተካክለዋለች፡፡ ቀጭን ኩታ ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋ ነበር፡፡ ገለጥ ብሎ የሚታየው ደረትዋ ትኩስ የተሳጠ ሽንኩርት ይመስላል፡፡ ፈገግ ስትል ሀሞት የሚመስለው ንቅሳትዋ ወተት ከሚመስሉት ትላልቅ ጥርሶችዋ ጋር እየተነፃፀረ ልብ ይማርካል፡፡ ጫት ጋበዘችኝ፡፡ እያኘኩ ስሙጥ እየቸና እየሳቀችብኝ እንዴት እንደሚበላ አሳየችኝ፡፡ 'እንዳንቺ ያለች ውብ፣ ወጣት ሴት እንዲህ ያለ ቦታ ምን ታደርጋለች?' አልኩዋት፡፡ 'ትምህርት፣ ወገን፣ ወይም ሀብት የሌላት እንደ እኔ ያለች ውብ፣ ወጣት ሴት ከዚህ ኑሮ ሌላ የት ልትሄድ ትችላለች?' አለችኝ፡፡ 'ሰው ቤት ተቀጥሮ ሰርቶ መብላት ሀጢአት ነው?' ስላት ጊዜ፣ 'ሀጢአት ብቻ አይደለም፡፡ ገሃነም ነው'፡፡ ብዙ ጊዜ ሞክሬዋለሁ፡፡ ትቁት ወር አልደርስ ሲል፣ በርበሬውና ቅቤው ሲያልቅ ብቻ ማፍጠጥ፣ ለምን በውነቱ እልቅ ይበል! ቆጥበው አይኖሩ ሲያልቅ ይሻለኛል' አለችኝ፡፡ ሌባ ነች ማለት፡፡ እኔ ሌባ ነች ከመባል ሞት ይሻለኛል' አለችኝ፡፡ 'ሴተኛ አዳሪ መባልስ?' አልኩዋት፡፡ 'እኔ እዚህ የተቀመጥኩ መጠጥ ለመሸጥ ነው እንጂ ራሴን ለመሸጥ አይደለም፡፡ ግርድና ተቀጥሬ ባጠራቀምኩት ገንዘብ ነው ይህን ቡቅ የከፈትኩት፡፡ ግን፣ ደስ ከሚለኝ

@OLDBOOKSPDF



«እምንተ እያሳዘነ ሰፈሩን በጥብጦ ነበር» አለ ሲራክ፥ አይኑን ከበቀለ ላይ አንስቶ ወደ ችሎ ማደር እየወረወረ፡፡

አትዬ አሊታዬ፥ «የሰው ልጅ ከማሳደግ ውሻ ማሳደግ ይሻላል» አሉ፡፡ ሁሉም በእምንተ ከንፈሩን እየመጠጠ ራሱን ነቀነቀ፡፡

በድንገት ህፃኑ ምርር ብሎ ማልቀስ ሲጀምር፥ አባቱ፥ «ይሄ ልጅ ምን ነክቶታል? ከትድም ጀምሮ ይነጫነጫል» ብሎ ሲያባብለው ሲሞክር፥ አትዬ አሊታዬ እንደ ገና የወርቅ ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው፥ «ናፍቆት፡፡ ናፍቆት ነው የሚያነጫንጨው የህፃናት ናፍቆት ሃይለኛ ነው» ሲሉ፥ እናቱ መጥታ ስትወስደው ሄዶ እንገትዋ ስር ውሽቅ አለ፡፡ አባቱ እንደ ገና፥ «አብዮት ና!» ብሎ እጁን ሲዘረጋለት ደግሞ እሱም ለመመለስ እጁን ዘረጋ፡፡ «አላልኩችሁም!» አሉ አትዬ አሊታዬ፡፡ ችሎ ማደር የልቅሶ ድምፅ ያሰማ መሰለው – ሲራክ፡፡ ጎንበስ ብሎ አየው፡፡ ከጌታው እግር ስር አልተንቀሳቀሰም፡፡ ቀንቶ ይሆን? አለ በልቡ፡፡

በቀለ ልጁን ጉልበቱ ላይ ቼ ቼ እያጫወተ ወደ ሲራክ ዞር ብሎ «ላደረጉልን ውለታ በጣም ነው የማመሰግነው፡፡ ከመምጣትዎ በፊት ባለቤቴ አጫውታኛለች» አለው፡፡

«እዬ፥ ምን አደረኩ ብለህ ነው?» አለ ሲራክ በተቃውሞ ድምፅ፡፡

«ከዚህ የበለጠ ውለታ ምን ሊኖር!» አለው፡፡

«ይልቅ ደማችሁን ለማፍሰስ የቆማችሁት እናንተ አላችሁ አይደል...»

«ያለ ጠንካራ ደጀን መቼ ይሆናል ብለው ነው!?» ብሎት ሲያበቃ፥ እንግዶቹን አንድ በአንድ በአይኑ ከጎበኘ በሁዋላ፡-

«ይግረምዎትና እኝህ እሙር ለማኝ እገኩዋ በሊመና የቃረሙዋትን ሳንቲም ቁዋጥረው እየመጡ ባለቤቴን ችግርሽ እንደሆንን? እያሉ ይጠይቁዋት ነበር፡፡ ጋሼ ማንደፍሮና «ሰው በሌለበት» ከቤቱም ተለይተው እያውቁም አሉ፡፡ በ'ውነት ለዚህ ህዝብ አንዲ ቀርቶ አስሬ ቢሞቱም አይቆጭም» አለው፡፡

ጠላው በማንቆርቆሪያ ቀርቦአል፡፡ አረቄውና ካቲካላው በጠርሙስ በጠርሙስ ተደርድሮአል፡፡ ቢራውም አልቀረ፡፡ ሁሉም

@OLDBOOKSPDF


እንዳቅሙ የሚችለውን ይዞ መጥቶአል፡፡ ሲራክ በበቀለ አነጋገር ልቡ በጣም ስለተነካ፣ «እንደኛውን ነው የመጣኸው ወይስ ተመልሰህ ትሄዳለህ?» ብሎ ጠየቀው፡፡

«ለስራ ጉዳይ ነው የመጣሁት፡፡ በቅርቡ ተመልሼ እሄዳለሁ፡፡ እንዲያውም ለመሄድ ቸኩያለሁ» አለው፡፡

«ለምን ቸኮልክ?»

«ቀበሮ ጉድጉዋድ ውስጥ ያሉትን ጉዋዶች ሳስታውስ ልቤ ይሰቀላል» ብሎት ነጭ ጥርሶቹን ብልጭ አደረገበትና፣ «ተልእኮዬም ቢሆን ገና አላለቀም» አለው፡፡

«ለቤተሰብህስ ልብህ አይሰቀልም?»

«ለማን የምዋጋ መሰለህ?» አለ፡- «ለእነሱ ነው፡፡ ለአብዮቱና ለአገሪቱ አንድነት ዛሬ የምሞተውና የምደማው እነሱ ነገ ብሩህ ተስፋ እንዲኖራቸው ነው፡፡ እዚህ ተቀምጬ ምን አደርግላቸዋለሁ? ደግሞ እኔ እዚህ ሆንኩ አልሆንኩ ምን ችግር ይገጥማቸዋል? እድሜ ለሰፊው ህዝብ ደጀንነትና ላብዮታዊው መንግስት፡፡ የሚጎላቸው ነገር የለም፡፡

ሲራክ በበቀል አስተሳሰብ እየተገረመና በይበልጥ የማወቅ ፍላጎት እያደረበት፣ «እስቲ በሞቴ ንገረኝ! ሁሉም እንዳንተ ነው የሚያስቡት!?» አለው፡፡

ልጁ እንቅልፍ ወስዶት እንድታስተኛው እናቱን ጠርቶ፣ አንገላብጦ ከሳመው በሁዋላ፣ ለጣትና፣ ፈገግ በማለት ውብ ጥርሱን ብልጭ አድርጎ ሲያበቃ፣ «እኔ ስለ ራሴ ስሜት ነው የተናገርኩ» አለ፡- «ግን አብዛኛዎቹ የኔ አይነት አስተሳሰብ ያላቸው ይመስለኛል፡፡ ብቻ እርግጥ፣ 'እኛ ብቻ ለምን እንዋጋለን? ሌላው ተራ ይድረሰው፡፡ አገሪቱ የኛ ብቻ አይደለችም፡፡ መመለስ አለብን' የሚሉ ጥቂት ሰዎች አይጠፉም፣ ግን በኔ ግምት ያብዮትና ያገር ጥበቃ ሃላፊነት ተራ የመግባት ጉዳይ አይደለም፡፡ ሁሉም እንዳቅሙና እንደ ችሎታው በያለበት ዘብ የመቆም ጉዳይ ነው፡፡ የተያያዙትን የድል ጎዳና ከግቡ ሳያደርሱ፣ ሌላው ተራ ይድረሰው በማለት ከግማሽ መንገድ መመለስ ልክ አይመስለኝም፡፡ የጀመሩትን ከግቡ ማድረስ ወይም መሞት፡፡ እኔ የሚታየኝ ይሄ ነው» ሲል፣ «ሰው በላው ጎንደሬ» ሞቅ ብሎት ኖሮ፣ «ሰው ሁሉ ሜዳይ ሲሸለም ያንተ የት አለ?» አለ፣ ድምፁን ከፍ አድርጎ፡፡

 @OLDBOOKSPDF

ወንድ ጋር ለማደር የሚከለክለኝ ታቦት የለም አለችኝ፡፡ ካሁኑዋ ሚስቴ ጋር የተዋወቅነው በዚህ ሁኔታ ነበር። አለና ሲአቱን ተመለከተ፡፡

‹‹አረ ይመሽብኛል›› አላት፡፡

‹‹ክፈለን ይጋ›› አለችው፡፡

‹‹ብማን እድሴ!›› አላትና ግንባርዋ ላይ ሳማት፡፡

‹‹እሺ ከዚያስ?›› አለች፡፡

በልቡ ይህች ሴት ዛሬ አልለቀቀችኝም አለና፣ ‹‹ከዚያማ በድንገት አብዮት ፈነዳ፡፡ አብዮት መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ሆነ፡፡ ያልተጠበቀ ዱብ እዳ ነበር፡፡ የማርታ አባት አንድ ቀን ቤቴ ድረስ ሲገሰግሱ መጡና፣ 'ይህ ህዝብ ምን የሚፈልግ ይመስልሃል?' አሉኝ፡፡ የመደናገጥና ግራ የመጋባት ሁኔታ ፊታቸው ላይ ይነበባል፡፡ በጣም አርጅተው ታዩኝ፡፡ 'ለውጥ ነዋ፡፡ ሌላ ምን ይፈልጋል?' አልኳቸው፡፡ 'እዋቂ ትመስለኝ ነበር፡፡ ህዝብ ያለ መሪ ምን ለውጥ ያመጣል? ዋኝ፡፡ ይልቅ አሁን የሚያስፈልገው የገዥው መደብ ብልህ መሆን ነው፡፡ የእንግሊዝ የገዥ መደቦች ሰንቱን ህዝባዊ ንቅናቄ አልፈው እዚህ የደረሱት በብልህነታቸው ነው፡፡ አመራር ሰጥተን የተነሳው ማእበል ወደ ጎንቢ ሁኔታ እንዲያመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ያልሆነ እንደሆን ብቻ ነው አደገኛ የሚሆነው፡፡ እኔ የሚያሰጋኝ የተነሳው ህዝባዊ ንቅናቄ ሳይሆን፣ በቤተመንግስት አካባቢ የሚደረገው የእርስ በርስ መጠላለፍ ነው፡፡ ሰውዬው ጃጅተዋል፡፡ ታዲያ፣ ልዑላኑ ባንድ ፊት፣ ሚኒስትሮቹ በሌላ በኩል፣ ጀኔራሎቻችን በየአቅጣጫው፣ ራሶቻችንና ደጃዝማቾቻችንም በፊናቸው ሁሉም ስልጣን ፈላጊዎች ሆነዋል፡፡ እርስ በእርሳችን ስንጠላለፍና ስንበላላ ጀምበር እንዳይጠልቅብን ነው የምፈራው፡፡ በራሳችን ላይ ጥፋት በመጋበዝ ላይ ያለነው እኛው ራሳችን ነን፡፡ ሕዝቡ አይደለም፡፡ አሁንም የደረሰውን ሁኔታ የፈጠረው፣ በደህናው ጊዜ አለ እኛ ማን አለ ይሉ የነበሩት ወይ ቢስ ሚኒስትሮች ተደናግጠው ስራ መልቀቅ ነው፡፡ ሌላ አይምሰልህ፡፡ እኔ ይህን ህዝብ እንደ እጄ መዳፍ አውቀዋለው፡፡ ወታደሩ ወደ ጦር ሰፈሩ ከተመለሰ ሌላው ወደ ወጣበት ጎሬ እየተሽሎከሎከ ይመለሳል፡፡ ምናለ በለኝ፡፡ ወታደሩ የሚፈልገው የደመወዝ ጭማሪ ነው እንጂ የፖለቲካ ለውጥ አይደለም፡፡ እና፣ አፍክን ዋልተህ ህዝቡ የሚፈልገው ለውጥ ነው አትበለኝ' አሉኝ፡፡

‹‹ግን ኮ እርስዎ ያላዩት የህዝቡን አይን መከፈት ነው፡፡ ከእንግዲህ የህዝቡን አይን መልሶ መጋረድ የሚቻል አይመስለኝም፡፡

@OLDBOOKSPDF


አረቄው፣ ኩቲካላው፣ ጠላውና ቢራው በገፍ ይቀዳል።

«አይ ያንተ ነገር» አለ በቀለ እየሳቀ፣ «ግና ምን ሰራሁና!»

«ታዲያ ሌላው ምን ሰርቶ ነው ያገኘው?» አለው፣ መልሶ።

አሁንም በቀለ በይበልጥ እየሳቀ፣ «ጀብዱ። ጀብዱ ነዋ። ኢትዮጵያ ስንት የሚያኮሩ ጀግኖች ልጆች እንዳሉዋት ባየህ» ብሎት ትርትም ብሎ የበቀለውን ራሱን በሌባ ጣቱ ግራና ቀኝ እየነካካ፣ «የኔ ሜዳይ ያብዮቱ መጠናከር ነው፣ ጉዋድ። ሌላ ሜዳይ አልሻም። የላቀ ጀብዱ ሰርተው የተሸለሙት ያኮሩኛል። እኔም የላቀ ጀብዱ ለመስራት እድል ካገኘሁ ወደ ሁዋላ አልልም። አይዞህ» አለው።

ጋሼ ማንደፍሮ በድንገት፣ «አድሃሪ ሁላ ይደመሰሳሉ!» አለ ሎክ ብሎ።

ከጦር ግንባር የተመለሱ ብዙ ወታደሮች በየጦር ሜዳው ስለፈፀሙት ጀብዱ አጋንነው ማውራትን በጣም ስለሚወዱ፣ «ሰው በላው ጎንደሬ» ያቀረበው አይነት ጥያቄ ቢሰነዘርባቸው፣ ከቁጡነት አልፈው ለዱላም የሚጋበዙ መሆናቸውን ስለሚያውቁ፣ በቀለም ይቆጣል ብሎ ሲራክ ሰግቶ ነበር። ቆራጥነቱን ብቻ ሳይሆን ትህትናውንም ጭምር በልቡ በሚያደንቅበት ጊዜ፣ ሊዮ ቶልስቶይ አንድ ጊዜ፣ «ያንድ ሰው ማንነት የሚታወቀው፣ የሰውዬውን መልካም ጠባዮች ከሚያሳየው ትእቢት መጠን ጋር በማካፈል በሚገኘው ውጤት ነው። በሌላ አነጋገር፣ ሰውዬው የሚደነቅ ችሎታ ቢኖረውም፣ ትእቢተኛ ከሆነ፣ የሞኝ ልቅሶ መልሶ መልሶ እንዲሉ፣ ከማሰልቸቱም በላይ ጎጂነቱ ያመዝናል» ብሎ የተናገረው ትዝ አለው። በቀለ የሲራክን መለኪያ አንስቶ እንዲጠጣ ስለ ጋበዘው፣ ተቀብሎ የመለኪያውን ጠርዝ በከንፈሩ ቀስ ብሎ እየዳሰሰ አረቄውን ሲጎነጭ፣ ዝም ብለው የቆዩት እውሩ ለማኝ፣ «ጦር ሜዳ እንዴት ነው?» አሉ።

ጥያቄው ለእሱ የተሰነዘረ መሆኑ ገባውና፣ «እንዴት ማለት?» አላቸው በቀለ።

ድምፁን ወደ ሰጡበት አቅጣጫ በንቃት ዞር ብለው፣ «ያስፈራል ወይ? ማለቴ ነው» አሉት።

ሲራክ፣ ጥያቄው ያስገረመውን ያህል በቀለ የሚሰጠውን መልስ ለመስማት ጉጉቱ ቀና አለ። በቀለም በበኩሉ በቀረበለት ጥያቄ ተገርሞ ሲያሰላስል ከቆየ በሁዋላ፣ ሳይሆን አይቀርም፣

@OLDBOOKSPDF



በዚህ ላይ ደግሞ መሪን የማይፈጥረው ሁኔታ ነው፡፡ እንደ ሙሴ ዕዳት ከበግይ እየወረድም ስላቸው፣ 'አንተ ስለ ፖለቲካ ምንም አታውቅም፡፡ ያው የድሮ የተሸነቆረ ዉጅት ነህ!' ብለውኝ ውጡ፡፡

«ከሄዱ በሁዋላ አባቴን ሆን ብለህ ነው የምታናድደው በሚል መንሻ ከማርታ ጋር ዱላ ቀረሽ ጠብ ገጥመን ዋልን፡፡

«ከዚያ በሁዋላ አባትዋ ስራ ስለ በዛባቸው እሳቸውን ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ ነበር፡፡ ጥዋት፣ ቀን፣ ሌሊት ከዘውድ ምክር ቤት አይለዩም፡፡ ሽማግሌው አንድ ነገር ነክሰው ይዘዋል ብዬ አሰብኩ፡፡ ከጊዜ በሁዋላ ወታደሩ ወደ ጦር ሰፈሩ ተመለሰ፡፡ የእንዳልካቸው ካቢኔም እየተጠናከረ መጣ፡፡ ብሄራዊ ፀጥታ ኮሚሽን ተቋቁሞ ፀጥ ያደርግ ጀመር፡፡ ለሁሉም ነገር መፍትሄ የሚሆነው አዲስ ህገ መንግስት ይወጣል፣ እስከዚያ ድረስ ፋታ ተባለ፡፡ ወጣት አልጋ ወራሽም ተሾሙ፡፡ እውነትም የገኘው መደብ ማአበሉን በብልህነት ሊያልፈው ነው ብዬ ዝም አልኩ፡፡

«ነገሩ ሁሉ ከተረጋጋ በሁዋላ የማርታ አባት ጠርተውኝ፣ 'ኛ ፖለቲካ አዋቂ! ታዲያስ?' አሉኝ፡፡ ራሴን ለመከላከል ያህል፣ 'የተዳፈነው እሳት ውስጥ ውስጡን መቀጣጠሉ ይቀራል? ህዝቡ ካለፈው ምን ያህል ሃይል እንዳለውና በአንፃሩም ይህ መንግስት ምን ያህል ደካማ እንደሆነ ገምቶአል፡፡ ሁሉም በልቡ ለካ እንዲህ ኖሮአልና እያለ ነው፡፡ ህዝቡ እንደ በፊቱ መገዛት ሰልችቶታል፡፡ መንግስትም እንደ በፊቱ መግዛት አቅቶታል፡፡ የላላ ነገር አለ፡፡ የተነቃነቀ ጥርስ መውለቁ አይቀርም ይባላል፡፡ ወታደሮች የራሳቸውን መብት አስከብረው ወደ ሰፈራቸው ከተመለሱ ወዲህ የህዝቡን አይን ማየት አልቻሉም፡፡ ጠላ ቤት አይገቡም፡፡ ሁሉም አይናችሁ ላፈር ብሎአቸዋል፡፡ አንድ ጥያቄ አለኝ? የሚለው አምድ አዘጋጅ 'ከእም ኤ ወይም ከኤም ዋን የትኛው ይበልጣል?' ብለው ቢጠይቁት ምን መልስ ሰጠ መሰለዎት? 'ደሞዝ የሚያስጨምረው ኤም ዋን ይበልጣል' ብሎ ነው መልስ የሰጠው፡፡ የመንደር መልሱ የጊዜውን መንፈስ የሚገልፅ ይመስለኛል ስላቸው፣ 'ወታደሩ በህዝብ ግፊት ወሬህን ተወኝ' አሉኝና ተነስተው ሲሄዱ ቢሉ፣ 'ከት ብለው ሳቁና፣ ተባብሮ እንደገና የወጣ እንደሆንስ?' አልኩዋቸው፡፡ ሸርሸር 'አንድ ቀልድ ልንገርህ' ብለው ጀመሩ 'አባትና ልጅ ተያይዘው ይህ ሲሄዱ ካማኑኤል ሆስፒታል አጠገብ ይደርሳሉ፡፡ አባት ለልጁ ሆስፒታል ነው ብሎ ያሳየዋል፡፡ ብዙ እብዶች ከሩቅ የእብዶች ያታያሉ፡፡ ልጅ ለአባት ማን ነው የሚጠብቃቸው? ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ቢር ላይ የቆሙትን ሁለት ኮሰማና ዘበኞች ያሳየውና፣ እነሱ ናቸው ይሉታል፡፡ ልጁ ይገረምና — ይህ ሁሉ እብድ ተባብሮ ቢመጣባቸው

@OLDBOOKSPDF

‹‹የመጀመሪያዋን የጥይት ተኩሴት ከሰሙና የመጀመሪያውን የወደቀ ሬሳ ካዩ በሁዋላ... እንዴት ልበልዎት?... ስትርበደበድ የቆየችው ሰጋ በድን ትሆናለች፡፡ ከዚያ በሁዋላ ሞት ያለ አይመስልም፡፡ ማለቴ – እንዴት ነው? ...የራስ መሞት ፈፅሞ ይረሳና ጠላትን ተሸቀዳድሞ የመግደል አልክና ስሜት ያይላል፡፡ ታዲያ የሚገርመው ነገር፣ ተኩስ በሚተፋፋምበት ሰአት ሳይሆን ከበረደ በሁዋላ ነው ትንሽ ፍርሃት ፍርሃት የሚለው፡፡ ይህም ቢሆን፣ አንድ ሁለት ጊዜ የተፋፋመ ውጊያ ውስጥ ገብተው ከወጡ በሁዋላ ይለመድና የመሞት ነገር ይረሳል፡፡ ከዚህ በሁዋላ ጠላትን ገድዬ እመለሳለሁ የሚል ስሜት ይጠነክርና እሞታለሁ ብሎ ማሰብ ይቀራል፡፡ እንጃ... እኔ እንዲህ ነበር የሚሰማኝ›› አላቸው፡፡

ሞት ያለ ነገር ቢሆንም የሰው አእምሮ በምንም ሁኔታ እሺ፣ አሜን ብሎ እንደማይቀበል ገባው፡፡ ሞትን አሜን ብለን ከተቀበልን በተስፋ ምን ቦታ ይኖራል? ብሎ አሰበ፡፡ በዚያ አሳብ ውስጥ አጋፋሪ እንደሻው ከነሽበታቸው ብቅ ብለው ታዩት፡፡ ይገርማል፣ አጋፋሪ እንደሻው ለካ ከማንም የተለዩ ፍጡር አይደሉምና፣ የሚል ግምት ቢወስድም በሞት ላይ ድል የሚቀዳጅ ነገር ካልሰፋና ወይም ለኦስራት በመጣጣር ለሰው ልጅ ብፋህ ተስፋን ካላባዩ፣ የሰው ልጅ አእምሮ ሞትን አይቀበልም በሚል ሰበብ ብቻ፣ ሞትን መሸሽ ምግባራዊ ፈሪነት ነው ባለበት ቅፅበት ውስጥ የራሱ ምግባራዊ ፈሪነት ታየው፡፡ መላ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ፡፡ አጋፋሪ እንደሻው ይህን ሁሉ ጊዜ ሌላ ሰው ሳይሆን እሱ ራሱ ሆነው ባገኛቸው ጊዜ ደግሞ የባሰውኑ ደንግጦ ከው ሲል፣ እውኑ ለማኝ፣ ‹‹ዘለአለማዊ ጨለማ ኑሮ ውስጥ ከመኖር ይበልጥ የሚያስፈራ ነገር ያለ አይመስለኝም፣ ወንድሞቼ! አይጣል ነው፡፡ በማያለልስ ጨለማ ውስጥ በፍርሃት ተውጦ መኖር›› ሲሉ ሰማቸው፡፡ በዚያው ሳያበቁ ቀጠሉና፣ ‹‹አይናማ ሆኖ ጠላትን ፊት ለፊት ገጥሞ ሲዋጉ መሞት ምን ያስፈራል! ይልቅ የሚያስፈራው ሚዳውንና ገደሉን ሳይለዩ መሪ እያባበሉ መኖር ነው›› አሉ፡፡ ከመንገድ ዳር ቁጭ ብለው ስለ ጨለማ ኑሮ የሚደረድሩት ግጥም ትዝ አለው፡፡

‹‹አባቴ›› አላቸው፣ ባዶ የሆኑትን የአይኖቻቸውን ጉድጓዶች በሩቁ እያየ፡፡

ድምፁ ወደ ሰሙበት አቅጣጫ ቀና ዞር ብለው፣ ‹‹ልጅ ሲራክ ደህና?›› አሉት፡፡

@OLDBOOKSPDF

ምን ያደርጋሉ? ብሎ እንደ ገና ይጠይቀዋል፡፡ አባት የኮረኮሩትን ያህል ይስቅና፣ አብዶች ምን ጊዜም ቢሆን ሊተባበሩ አይችሉም ብሎ መለሰለት ይባላል፡፡ ነገሩ ገባህ?' ብለውኝ ሄዱ፡፡

፡፡ማርታ ግን ከየካቲት 1966 ዓ.ም. በሁዋላ 'ይህ ህዝብ አንድ ቀን ሳይጨርሰን አይቀርም' እያለች ትሰጋ ነበረና መንፈስዋ ሁሉ ጥሩ አልነበረም፡፡ እየደጋገመች፣ 'የተሻሻለ ህገ መንግስት ከተሰጣቸው ምን ይፈልጋሉ? የተቀረው ምቀኝነት ነው፡፡ ምቀኝነት ልማዳችን ነው' ትለኝለች፡፡ የለም አልገባሽም፡፡ ምቀኝነት አይደለም፡፡ የመደብ ትግል ነው፡፡ ህዝቡ የሚፈልገው የተሻሻለ ህገ መንግስት አይደለም፡፡ በእኩልነት፣ በነፃነትና በፍትህ ላይ የተመሰረተ የተሻሻለ ኑሮ ነው ስላት፣ 'ታዲያ ማን ከለከላቸው?' እያለች ስትበሳጭ፣ ወታደሩ እንደ ገና ከሰፈሩ ወጣ፡፡ ፍፃሜው መድረሱ ለማንም ግልፅ ነበር፡፡ ሲወጣ ሲገባ የቆየው ጠብመንጃ ከእንግዲህ ለመጨረሻ ጊዜ የወጣ ይመስለኛል እያልኩ ሳስብ፡-

፡፡የማርታ አባት ጠሩኝ፡፡ በየቀኑ እያረፉ ይሄዱ ነበር፡፡ 'ፍፃሜው የደረሰ ይመስለኛል፡፡ ልጄን አደራ፡፡ ግን አሁንም ቢሆን ለዚህ ያደረሰን ምኝነታችንና እርስ በእርሳችን የመጠላላፋችን ሁኔታ ነው' ብለውኝ ዝም አሉ፡፡ እኔም ዝም ብዬ ቀረሁ፡፡ የማርታ እናት፣ 'ንጉሱ እያሉ ምን ይመጣል ብለህ፣ ነው?' እያሉ ሲያፅናኑአቸው፣ ሲሞክሩ፣ 'እኔ የታሰረ ንጉስ አላውቅም፡፡ አልቆላቸዋል፡፡ እኛም አልቆልናል፡፡ ኢትዮጵያን ማስቀደም እንዲህም አድርጎ የለ፡፡ ይህን ህዝብ እንደ ራሴ የማውቀው ይመስለኝ ነበር፣ ተአምር ማስቂያ የለውም፡፡ በእግዜሩም ዘንድ ተፈርዶብን፣ ሰውም እንዲህ ጠልቶን፣ እዩ ጉድ፣ ያንዳንድ ሰው የመጨረሻ እድል ያሳዝናል እያሉ ሲተክዙ እዚያው አደርን፡፡ ጥዋት ወታደሮች በታንክ መጥተው ሲወስዱአቸው ትንሽም ፍርሃት አይታይባቸውም ነበር፡፡ 'ይህ ሁሉ ወታደርና ታንክ ምን ያስፈልጋል? ምሽግ አለው አሉአችሁ እንዴ?' ብለው ካቦርታቸውን ደርበው ወጡ፡፡ መኪና ውስጥ ሊያስገቡአቸው ሲሉ በእጅ ጠቀሱኝና፣ 'ጊዜ ሲል አብድም ይተባበራል፡፡ ግን አብዶች እኛ ነበርን' ብለውኝ የቀረባለቸው መኪና ውስጥ ገብተው ሄዱ፡፡ መለስ ብለው ቤተሰባቸውን እንኳዋን አላዩም፡፡

፡፡ማርታ ከዚያን ቀን ጀምሮ ከሰውነት ወጥታ ነበር፡፡ 'አባቴን የሚገድሉት ይመስልሃል?' እያለች ደጋግማ ስትጠይቀኝ ለማፅናናት ያህል፣ 'ፈፅሞ አታስቢ፡፡ ምንም አይነካቸውም' እላት ነበር፡፡ መለስ ትልና፣ 'ለምን ይገድሉታል? ሳገሩ እንደሱ የደከመ የለም፡፡ ለድሀ

@OLDBOOKSPDF


‹‹ለመሆኑ መቼ ነው አይኑ ስውር የሆኑት?›› አላቸው፣ ሰው የጎጋትን ሥራ፣ የምሽትን ጀምበር የከዋክብትን ጥቅሻ፣ የሙሉ ጨረቃን ድምቀት፣ የሰውን ልጅ ፈገግታና ኪነታዊ ጥበብ፣ የተፈጥሮን ፀጋና ውበት በአይኑ ስጋው አይቶ ለማድነቅ ካልቻለ፣ የህይወት ጣእም ምን መሆኑን አውቆ ነው መኖር አለብኝ የሚለው በማለት ሲያስብ፡-

‹‹ከህፃንነቴ… ገና ጡት ስጠባ፡፡ ፈንጣጣ ነው እሉ እንዲህ ጉድ የሰራኝ፡፡ ጨለማውን ስዳስስ ይሄውና ሰልሳ አመት አለፈኝ፡፡ አሁን ከምለምንበት ቦታ ላይ እንኳዋን መቀመጥ ከጀመርኩ አርባ አመት ሳይሆነኝ አይቀርም፡፡ ሙሴ ቴሬስ የሚባል የፈረንሳይ ተወላጅ እዚች ሰፈር በነበረበት ዘመን ሁሉ እዚሁ ነበርኩ፡፡ በእሱ ስም ነው ተረት ሰፈር መባል የጀመረችው›› አሉ፣ በተጨማሪ፣ ‹‹ያኔ እንደ ዛሬው በበሽታም ላይ ጦርነት ቢታወጅ ኖሮ በጨለማ ተውጨ አልቀርም ነበር፡፡ ግና ምን ያደርጋል! ጊዜውም እውር ነበር›› አሉት፡፡

ሲራክ አእምሮው ውስጥ ሲጉላላ የነበረውን ጥያቄ የግድ መጠየቅ ነበረበት፡፡ ‹‹ስለ ተፈጥሮ ውበት ምን ይሰማዎታል ሲያስቡት?›› አላቸው፡፡

‹‹የማያውቁት አገር ምን ይናፍቃል ብለህ ነው ልጄ? የኔ ብርሃን እናንተው አይናማዎቹ ናችሁ፡፡ የሰው ብርሃን ሰው ነው፡፡ አይን ብቻ አይደለም፡፡ የሰው መድህኒቱም ሰው ነው›› አሉት፡፡

‹‹ታዲያ ለምን ያስፈራል?›› አለ፡፡

‹‹ምኑ?›› አሉት፡፡

‹‹ጨለማው፡፡››

‹‹እኔ ፈርቼ አልሞትኩ ታዲያ! እዘንፈው ስኖር እያየኸኝ ምን ነው?›› አሉት፡፡

እንደ እርስዎ ምግባራዊ ድፍረት በኖረኝ ምን ነበረበት ሲል ሲል፣ ‹‹ሰው በላው ጎንደሬ›› ቀደመውና፣ ‹‹እድሜ ለመንደር ቡቱቶ እኛም እንኖራለን፡፡ ዘራፍ! ሰው በላው ጎንደሬ፡፡ ባብዮቱ፣ በደርጉ ብያለሁ!›› አለ፡፡

ሁሉም ሲስቁ እትዬ አልታዬ ብቻ የወርቅ ጥርሳቸውን ብቅ ሳያደርጉ ቀርተው፣ ‹‹ዋ እቴ፣ ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል›› ብለው ከንፈራቸውን መጠጡ፡፡

@OLDBOOKSPDF 

ያበባል፣ ያጠግባል፣ ያለብሳል፣ ይረዳል፡፡ ሀብት ያፈራው ሰርቶ ነው፡፡ ሰርቶ አይደለም፡፡ ብቻ ነገሩ ምቀኝነት ነው' ትለኝ ነበር–ምርር ብላ፡፡

‹‹ክፉኛ ተስፋ መቁረጥዋ የታወቀኝ ስድሳዎቹ ከፍተኛ ባለስልጣኖች ርምጃ የተወሰደባቸው ቀን ነው፡፡ አባትዋ አልተነኩም፡፡ ከስድሳዎቹ አንዱ ግን ያክስትዋ ባል ነበር፡፡

‹‹ልቅሶው ላይ ተቀምጠን፣ ማርታ ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች፣ 'አላልኩህም ነበር? ያልኩት አልቀረም፡፡ ሊፈጁን ነው የተነሱት፡፡ ያለ ምንም ደም፣ ኢትዮጵያ ትቅደም ማለት ትርጉሙ ይህ ነው? እነዚህን ሰዎች ነው ሀቀኞች ናቸው የምትለኝ? ዛሬ እነዚህን ምስኪን ሰዎች ጨርሰዋል፡፡ የነገ ተረኞች እኛ ነን፡፡ ግን የማዝነው ለአገሪቱ ነው፤ አልቆላታል፡፡ ልዩ ልዩ ጎሳዎችንና በሃይማኖት የተለያዩ ህዝቦችን አቅፎ በአንድነት የያዘው ዘውድ – ያንድነታችን ምልክት – ከወደቀ፣ አገሪቱን የሚመሩና የሚያስተዳድሩ ሰዎች ካለቁ፣ ምን አገር ትሆናለች? ፍጅት ነው የሚሆነው፡፡ አገሪቱም የእምቡዋይ ካብ መሆንዋ አይቀርም' በማለት ምን ያህል ተስፋ እንደቆረጠች ስትነግረኝ፦

‹‹ይህን ያህል ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር የለም፡፡ ከዚህም የባሰ ሊደርስ ይችላል፡፡ የትግል ጊዜ ነው፡፡ አገሪቱም ምንም አትሆንም፡፡ ምንጊዜም ቢሆን የአንድነትዋ መሰረት ህዝቡ ነው፡፡ አብዮቱን ያመጣው ህዝቡ ራሱ ስለሆነ የተጠየቀውን መስዋእት ከፍሎ ራሱ ይጠብቀዋል፡፡ እምነት ሊኖረን ይገባል፡፡ እኛ የትናንትናዪቱ ሳይሆን የነገዪቱ ኢትዮጵያ ልጆች ነን፡፡ ለኔ የነገዪቱ ኢትዮጵያ ጨለማ የሰማይ ጉድጓድ ሆና አትታየኝም፡፡ በመደረግ ላይ ያለው ነገር ሁሉ ጥሩ ነው፡፡ እያልኩ ላበረታታት ስሞክር፦

‹‹'የምትለውን ሁሉ በርግጥ ከልብ ታምንበታለህ?... እውሬ ነህ፡፡ ሰው ያለ ፍርድ ሲገደል እንዴት ጥሩ ነው ትላለህ? የሚገርም ነው፡፡ ይህን ጊዜ ያህል አብረን ስንኖር ምን አይነት አውሬ እንደሆንክ አላውቅም ነበር ማለት ነው፡፡ ለሰው ህይወት ደንታ የለህም፡፡ አንተ የምታስበው ስለ ድርሰትህ ብቻ ነው' እያለች ስትጮህብኝ የትዳራችን ፍፃሜ እየተቃረበ መሄዱ ይታየኝ ነበር፡፡

‹‹አንድ ቀን ከምናውቃቸው እንግሊዞች ቤት ራት ተጋብዘናልና እንሂድ ብላ ጠየቀችኝ፡፡ እንደ ሌላው ጊዜ የማስገደድ ጠባይ

@OLDBOOKSPDF



«ሰው በላው ጎንደሬ» ወደ ጋሼ ማንደፍሮ እያየ፥ «አንተም እድሜ ለምርኩዜ በል፥ እ» አለው፡፡

«አድሃሪ ሁላ!»

«አንተማ ተራማጅ፡፡»

ጋሼ ማንደፍሮ ምርኩዙን ከእግሩ ስር እየመዘዘ፥ «አንተም ለመንደር ቡቱቶ በል!» አለው፡፡

«እውነትክን ነው፡፡ አንድ ቀን አንድ አዲስ ልብስ ሰፍቼ ብሞት ደስ ይለኝ ነበር፡፡ የመንደሩን ቡቱቶ ስሰፋ የሚታየኝ አዲስ ጨርቅ ነው፡፡ ታዲያ ያበሳጨኛል፡፡ የተረት ሰፈር ሰዎች ቡቱቶ በየጊዜው ከማስመታት ለምን አዲስ ጨርቅ አያመጡልኝም? ወይስ ችሎታዬን እየተጠራጠሩ ነው? እላለሁ፡፡ እና፥ እበሳጫለሁ፡፡ ነጋም ጠባም ቡቱቶ!» አለ ብስጭት ብሎ፡፡

በቀለ በሀዘን ተውጦ ሲያዳምጠው ቆየና፥ «ተረት ሰፈር አዲስ ልብስ የሚያሰፋ ማን አለ ብለህ ነው? የጭቁኖች ሰፈር መሆኑን አጣኸውና ነው! በነፍስ ይማር ልበስ ነው የምንኖረው፤ ግን አይዞህ አንድ ቀን የምንለብስበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል፡፡ በነገራችን ላይ ካስመራ ለባለቤቴና ለልጄ ያመጣሁት ጨርቅ አለ፡፡ ወስደህ እንድትሰፋላቸው» አለው፡፡

ሲራክ ስሜት ፈንቅሎት፥ «ወር ላይ እኔም ለራሴና ለልጄ የሚሆን ጨርቅ አመጣልሃለሁ» አለው፡፡

ጋሼ ማንደፍሮ ምርኩዙን እየሰበቀ፤ «አድሃሪ ሁላ!» ሲል፣ የሲራክ ባለቤት በቀይ ጨርቅ የተሸፈነ ትልቅ መሶብ ውብንቿን አስይዛ ስትገባ፥ ጨዋታው ተቋርጦ፥ ሁሉም ሊቀበልዋት ብድግ አሉ፡፡

«በማዜር፣ በማዜር» ስትል እውሩ ለማኝ የፅጌን ድምፅ ሰምተው፥ «ፅጌ ማርያም፣ የድሀ እናት፣ መጣሽ?» አልዋት፡፡

ፅጌ ከበቀለ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጠች በኋላ፥ አንደኛውን ከሠር ሜዳ ተመልሶ እንደሆን በማለት ስትጠይቀው በቅርቡ ወደ ሰሜን ጦር ግንባር እንደሚመለስ ስለ ነገራት፥ «ወይ በሞትኩት! ምን ነው?» አለች፡፡

@OLDBOOKSPDF



አይታይባትም ነበር፡፡ የክብር እንግዶቻቸው ስለሆን እባክህን ብላ ለመነችኝ፡፡ ደስ እንዲላት እሺ ብዬ ማታ ሄድን፡፡ አንተቸም ግብዣው ላይ ነበር፡፡

«ራት እየበላን ስለ አብዮቱ ማውራት ጀመርን፡፡ አንተዋ ከአገር ከኮበለለው ስለ ብቃት ሠራዊቶች፣ ኢንጂነሮች፣ መሀንዲሶችና ባለስልጣኖች፣ ስለ ከዱት አምባሳደሮች አንድ በአንድ እየዘረዘረና፣ አገሪቱ ባዶዋን ቀርታለች፡፡ ከተማሩት ሰዎች የቀሩት በኛናም ተስፋ የላቸውም፡፡ ጀምበር ሳትጠልቅ መዘጋጀት ብልህነት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በኢትዮጵያ ኮሚዩኒስታዊ ስርአት ሲመሰረቱ ነው የተነሱት፡፡ ይገባሃል? እና፣ ማን ነው የትጋዳን ነገን ለመኖር የሚመርጠው? እኔ መቼም እንዲህ አይነቱን ነገር አልመርጥም አለኝ፡፡

«የጋበዘን እንግሊዝ በበኩሉ ስለ ኢትዮጵያ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ አንስቶ፣ በምስራቅ፣ በደቡብና በሰሜን ከፍተኛ ሀገር ያለው አደገኛ አገዛዝ ኮተትኮ በሁዋላ፣ አሁን ያለው አመራር ካልተለወጠና ህጋዊ መንግስት ካልተመሰረተ ኢትዮጵያ ምንም አይነት ርዳታና ድጋፍ ከውጭ እንደማታገኝ አመልክቶ፣ የሚጠብቃት እድል ውድቀትና ፍጅት ነው፡፡ ሁኔታው ይህ በመሆኑ የውጭ ነጋዴዎች እየወጡ ናቸው፡፡ ያገራችሁ ኢኮኖሚ እየወደቀ ነው፡፡ በዚህ ላይ በደርጉም ውስጥ ሆነ በሰራዊቱ መካከል ስምምነት የለም፡፡ ሳንድ አገር አንድ ንጉስም ያስቸግራል፡፡ መቶ ሃያ ንጉሶች ግን የማይታሰብ ነው፡፡ ወደ ዘመነ መሳፍንቱ ተመልሳችሁአል፡፡ ይህችን ታላቅ የነበረች አገር በመጨረሻ የሚጠብቃት መራራ ጽዋ የእርስ በርስ ጦርነትና እንደ ዶሮ ብልት መገንጣጠል ነው፡፡ ምስኪን ኢትዮጵያ! ብሎ ወደኔ፣ ወደ ማርታና ወደ አንተዋ ተመለከተና፣ 'እኔ እናንተን ብሆን ከሁኑ ከዚህ ገሃነም የምወጣበትን መንገድ እፈልጋለሁ' አለ፡፡ የማርታ እናት ቀበል አደረገና፣ 'ታዲያስ ሲራክ ምን ታስባለህ?' አለኝ፡፡ 'ስለምን?' አልኩት፡፡ 'ከዚህ ገሃነም ስለ መውጣቱ ጉዳይ' አለኝ፡፡

«ከሁሉ አስቀድሞ ኢትዮጵያ ገሃነም አልሆነችም፡፡ አትሆንምም፡፡ ብትሆንም ለጥቂቶቻችን ነው፡፡ ለብዙሀኑ ግን ገነት ትሆናለች፡፡ ርግጥ የኢትዮጵያ ገዥ መደቦችና ኢምፔሪያሊስቶች የሚፈልጉዋት ኢትዮጵያ የለችም፣ ከእንግዲህም የምትኖር አይመስለኝም፡፡ ብዙሀን የሚፈልጉዋት ኢትዮጵያ ግን እየተወለደች ነው፡፡ እንዲያው ዝም ብለን የአዞ እንባ ነው የምናነባው፡፡ እኔ ከዚች አገር ምን ቢመጣ ምን እግሬን አላነሳም፡፡ የዚህ ህዝብ እድል እድሌ፣ ሞቱ ሞቴ፣ ደስታው ደስታዬ ይሆናል፡፡ የለም ጎበዝ! እትብቴ የተቀበረበትን አገር ትቼ ወዴት? እኔ ዶራሲ መሆን ነው የምፈልገው፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹አሁንም ግዳጅ ላይ ነኝ›› አላት።

‹‹ምን ነው እስከ መቼ?

‹‹በድል አድራጊነት እስከምንወጣ››ብሎ ወደ ሲራክ ዞር በማለት፣ ‹‹ለእሳቸውም ቅድም ይህንኑ ስነግራቸው ነበር። በዚህ ቀውጢ ጊዜ፣ እብዩቱ አገሬ የሚል ሁሉ እንደ ችሎታው ባለበት ዘብ መቆም አለበት። ደራሲም በድርሰቱ›› አላት።

ፅጌ ወደ ባልዋ ቀጥሎም ወደ በቀለ አይኖችዋን ወረወረች።

በቀለ ቀጥሎ፡ ‹‹ቅድም አልነገርኩዎትም እንጂ፣ እኔ እኮ እርስዎን የማውቀው በመፅሀፍዎ ነው›› አለው ሲራክን።

ፅጌ ቀደመችውና፣ ‹‹ኤጭ! መፅ ሀፍ ብሎ ነገር እቴ! ወረቀት ቢለቀልቁት ምን ፋይዳ አለው!›› አለች፣ ትላልቅ አይኖችዋን ወደ ውጭ ጎልጉላ እያወጣች።

‹‹እረ እሜትዬ እንዲህ አይበሉ›› አለ በቀለ። ‹‹ድርሰት ትልቅ ሙያ ነው። ክቡር ተሰጥዎ ነው። ከዚያም አልፎ እቻ የሌለው ሃይል ነው። ባለቤትዎ እስካሁን አረም በሊቶት የቀረውን የጥቁናች ታሪክ ፅፈው ለትውልድ እንዲያስቀሩ ማበረታታት ነው እንጂ እንዴት እንዲህ ይላሉ?››።

‹‹ይሻላል!›› አላት ሲራክ።

በትላልቅ አይኖችዋ እንደ ጦር ወግታው፣ በቀለን፣ ‹‹አንተን አንኩዋን ለቤትህ አበቃህ ወንድሜ›› ብላ፣ ሄዳ እትዬ አልታዬ አጠገብ ቁጭ አለች።

‹‹ባለቤትዎን ድርሰት ምን አስጠላቸው?›› አለው በቀለ።

‹‹ያመጣባት እዳ ነው ያስጠላት›› አለ።

‹‹የማተሚያ ቤት እዳ!›› አለ በቀለ በመገረም።

‹‹እሱ ነው ይሄውልህ›› ብሎት ፈገግ በማለት፣ ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ፣ ወር ከማታደርሰው ደሞዛችን ላይ እየገፈፍኩ ነው›› አለው።

@OLDBOOKSPDF

በቀለ ራሱን ነቅንቆ፣ «የሚገርም ነው፡፡ ደራሲ ሲባል የማተሚያ ቤት እዳ የሌለበት አላየሁም፡፡ የማተሚያ ቤት ሰራተኛ ስለሆንኩ ብዙ ደራሲያን በእዳ ሲከሰሱ አይ ነበር» አለ፡፡

ሲራክ ከወንበሩ ላይ ተመቻቸና፣ «ታሪካችን ባጭሩ ይኸው ነው» ሲል፡-

በቀለ ነገሩን ቀበል አደረገና፣ «ታዲያ ቢሆንም ቢዘህ ተስፋ መቁረጥ የለባችሁም፡፡ ይልቅ መበርታት ያለባችሁ አሁን ነው፡፡ ብሩህ ተስፋ የተፈጠረላችሁ ይመስለኛል፡፡ ድርጅት ሃይል ነው፡፡ ለምን አትደራጁም?» አለው፡፡

«እሱስ እየተደራጀን ነው» ብሎ ነገሩን በመቀጠል፣ «የኛ መሰባሰብ ብቻ ለችግራችን መፍትሄ አይሆንም፡፡ ከመንግስት ርዳታ ያስፈልጋል፡፡ የኛ ችግር የአሳታሚ ድርጅት አለመኖር ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ለጥራትም ይበጅ ነበር» አለና በረጅሙ ወደ ውጭ ከተነፈሰ በሁዋላ፣ «ለጊዜው ግን እንገቢጋቢ ችግር የሆነብኝ የባለቤቴ አመለካከት ነው፡፡ የድርሰት ነገር ሲነሳባት ቀንድዋ ይቆማል፡፡ 'ለመከራ የጣፈው ቢነግድ አይተርፈው' እያለች ትተርትብኛለች፡፡ 'ወረቀት ቢለቀልቁት ምን ፋይዳ አለው? ትርፉ እዳ፡፡ ምናለ ብትተወውና ኑሮአችንን የሚያሻሽል ነገር ብትሰራ' ትለኛለች፡፡ እኔ ደግሞ 'ድርሰት የተልእኮ ጉዳይ ነው እንጂ የትርፍ ማግኛ ዘዴ አይደለም' እላታለሁ፡፡ እንዲሁ ስንነታረክ እንኖራለን» አለው፡፡

«ሀይለኛ ቅራኔ ነው» አለ በቀለ ፈገግ ብሎ፡፡

ሲራክ ላንዳፍታ አይኑን ወደ ሚሰቱ ወርውሮ ወደ በቀለ መለስ በማለት «አዎን» ካለ በሁዋላ፣ «ቅራኔው በእኔና በእሰዋ መካከል ብቻ የተፈጠረ አይደለም፡፡ ሶክራቲስና ባለቤቱ ዛንቲፔ እንደ እኛ በኑሮና በተልእኮ መካከል ባለው ልዩነት ላይ ሲጣሉ ነው የኖሩት፡፡ 'እውቀት ሳያንስህ፣ እንደ ጉዋደኞችህ በተድላ በደስታ ለመኖር ስትችል፣ ቡቱቶ ለብሰህ፣ ባዶ እግርህን በየመንገዱና በየገበያው እየዞርክ ለምን እንደ እብድ ትለፈልፋለህ?' እያለች ነጋ ጠባ ትወተውተው ነበር ይባላል፡፡ ካርል ማርክስም ለአለት ጉርሱ ከድንች አቅም እየቸገረው፣ ልጁ ሳትሞት ከፊን የሚገዛበት አጥቶ በችግር ተቆራምዶ ኖሮ የሞተው ተልእኮውን ከግብ ለማድረስ ሲል ነበር፡ ደግነቱ ባለቤቱ ጄኒ ስለ ኑሮአቸው አንዳንዴ ብትማረርም፣ የባልዋ ተልእኮ ስለሚገባት ምሬትዋን በትእግስት እየለወጠች ታብረታታው ነበር፡፡

@OLDBOOKSPDF


እና፣ ዶራቢ የምሆንበት ጊዜው አሁን ይመስለኛል፡፡ ሶስት ሽህ ዘመን ባለ ኩራት ተከናንባ በተገኘች አገር ታሪክ እየተፈፀመ ነው፡፡ የዚህ ታሪክ አካል ከመሆን ሌላ ምርጫ የለኝም፡፡ አብዮት መቀጣጠል ከጀመረበት አገር ወዴት? በዚች አገር በህይወቴ ካጋጠመኝ ግሩም ነገር አንዱ ይህ አብዮት ነው — ሳዓስበው፣ በድንገት፣ ግብታዊ አብዮት፣ ግብታዊ ልምድ — አስደናቂ ጊዜ ነው፣ ብዬ ስጨርስ፣ ማርታና እናትዋ ተያዩና የተመካከሩ ይመስል ባንድነት 'ከልብህ ነው!?' አሉኝ፡፡ 'ካንጀቴ ነው፡፡ እኔ የትም አልሄድም' ብዬ ልዘጋ ስል፣ ፈረንጁ፣ 'ስለ ልጅህ የወደፊት እድልና ስለ ባለቤትህ ደስታ ምንም አታስብም ማለት ነው?' አለኝ፡፡ 'ማሰቴም ሆንች ልጄ ከኢትዮጵያ ህዝብ የተለየ እድልና ደስታ መሻት የለባቸውም' ብዬ ዝም አልኩ፡፡

‹‹በማግስቱ እናትዋ ቢሮው ድረስ ጠራችኝና ለስራ ጉዳይ ባስቸኳዋይ ወደ አዋሳ እንድሄድ ጠየቀችኝ፡፡ ወዲያውኑ ተነስቼ ሄድኩ፡፡ ከሳምንት በሁዋላ ስመለስ ቤት ማንም አልነበረም፡፡ ማርታ ልጁን ይዛ ወደ እናትዋ ቤት ሄዳ ይሆናል በማለት ደክሞኝ ስለነበረ ዝም ብዬ ተኛሁ፡፡ እኩለ ሌሊት ላይ ስነቃ አሁንም ቤቱ ባዶ ነው፡፡ እዚያው አድራ ይሆናል በማለት ተመልሼ ልተኛ ሞከርኩ፡፡ እንቅልፍ አልወሰደኝም፡፡ ስገላበጥ አደርኩና ጥዋት ተነስቼ ወደ ዕሀፊት ጠረጴዛ ስሄድ አንድ እንቨሎፕ አየሁ፡፡ 'ለሲራክ' የሚል ተፅፎበታ፡፡ የማርታ እጅ ፅሁፍ ነው፡፡ ከፈትኩና አነበብኩ፡፡ እንደ ገና አነበብኩ፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ አነበብኩትና መሳቅ ጀመርኩ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እንባ ነበር የሚወርደኝ፡፡››

ሰብለ፣ ‹‹ምንድን ነው የፃፈችው?›› ብላ ጠየቀች፡፡

ስሕቱን ሰረቅ አድርጎ እየና፣ ‹‹ባጭሩ፣ 'የምወድህ ባሌ ደህና ሁን፡፡ እግዜር ካለ አንድ ቀን በአይኑ ቢጋ እንገናኝ ይሆናል፡፡ ከዚህ አገር አብረን እንድንወጣ በብዙ መንገድ ሞክሬ ነበር፡፡ ነገር ግን፣ አንተ በሌለህበት አንተ ከዚሁ መሞት ስለ መረጥክ፣ እኔ ልጄን ይዤ እንተ በሌለህበት ሄጃለሁ' የሚል ነበር፡፡ ለዘመዶችዋ ልደውል አሰብኩና ምን ያደርጋል ብዬ እንደ እብድ ብቻዬን እየሳኩና እያለቀስኩ ሾንጣዬን ይዤ ወጣሁ›› አላት፡፡

‹‹ቤታችሁስ?››

‹‹ምን ቤት ቀረኝ!››

‹‹እንዴሁ ጥለኸው ወጣህ?››

@OLDBOOKSPDF



‹‹በተልእኮና በኑሮ መካከል ያለው ግጭት አስቸጋሪ ነው፡፡ ተልእኮ ያለው ሰው፣ ለዚያ ተልእኮ ምኞቱን ብቻ ሳይሆን ውድ ህይወቱንም ጭምር አሳልፎ መስጠት አለበት፡፡ ዲሞክራቱስ የተባለው የግሪክ ፈላስፋ ለእውቀት የነበረው ጉጉት እልረካ ስላለው፣ አእምሮው በደበልጥ ብሩህ እንዲሆን አይኑን አወጣ ይባላል፡፡ ተልእኮ እስከዚህ ድረስ ነው፡፡

‹‹ታዲያ ተልእኮ ያላቸው ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚጨነቁትና የሚያገዙት ለራሳቸው ሳይሆን ለሚወድዋቸው ሰዎች ነው፡፡ በኑሮና በተልእኮ መካከል እስረኛ ከመሆን የበለጠ ጭንቀት ያለ አይመስለኝም፡፡ አንድ ደራሲ ወደ ኑሮ ካመዘነ የህይወት ቅጥረኛ ወይም አትራፊ ነጋዴ መሆን ይመጣል፡፡

‹‹ማለቴ የኪነት ሰው ገንዘብ አያስፈልገውም አልልም፡፡ ነገር ግን አንድ ደራሲ በምንም ሁኔታ ለገንዘብ ሲል መፃፍ የለበትም፡፡ ኪነት ሸቀጥ አይደለችም፡፡ ተልእኮ ናት፡፡ ቤራንዤ የተባለው የፈረንሳይ ሊቅ፣ 'የምኖረው ሙዚቃ ለመድረስ ነው፣ ጌታዬ ድጋፉን ከሰቶኝ ካባረረኝ ግን፣ ሙዚቃ የምደርሰው ለመኖር ያህል ብቻ ይሆናል' ያለው እዚህ ላይ ትዝ ይለኛል፡፡ ኪነትን ሸቀጥ አደርጋታለሁ ማለቱ ነበር፡፡ የደራሲ ችግር ቀላል አይደለም›› ሲል፡-

በቀለ በነገሩ ተመስጦ ያዳምጠው ነበርና በእምነታ ራሱን ነቅንቆ፣ ‹‹ማንኛውም ተልእኮ ቆራጥነትንና መስዋእትነትን ይጠይቃል፡፡ ጥቂቶቻችን ካልሞትን፣ ብዙዎቻችን ልንኖር አንችልም፡፡ እንዴ! ባለቤትዎም ይህን መረዳት አለባቸው፡፡ የጋራ ተልእኮ ነው፡፡ የእርስዎ የትግል ታሪክ፣ ከቶም ሆነ ደግ፣ ነገ የእሳቸውም ታሪክ መሆኑ ይቀራል ወይ?›› ከማለቱ፡-

ሲራክ ነገሩን ቀበል አደረገና፣ ‹‹እንዲያው በሞቴ፣ አሁን ያልከውን ለእሰዋም ንገራት›› አለው፡፡

‹‹ደግ፡፡ ትግል በየፈርጁ አይደል፡፡ እሺ ራት ላይ›› አለው፡፡

ራት ቀረበ...

በገበታ ላይም፣ ሆነ ገበታው ከፍ ካለም በሁዋላ በቀለ ስለ ድርሰትና ደራሲያን አንስቶ፣ ለጭቁኖች እርነት የቆሙ ደራሲያን የህብረተሰቡን እስተሳሰብ በማነፅና ታሪክን በማራመድ፣ ብሎም

@OLDBOOKSPDF



«እንዳለ ነው ትቼው የወጣሁት፡፡»

«የት ለመሄድ?»

«የት እንደምሄድ አውቅ ነበር፡፡ የት ይመስልሻል?» አላት ሰብለን፡፡

«የት ነው የሄድከው?»

«በቀጥታ አሁንዋ ሚስቴ ቤት – በራተኛ በፈር፡፡»

«በምን ትገ፤ አለችህ?»

ሰአቱን እንደ ገና ተመለከተና፣ «ያን ምሽት ከተዋወቅን ጊዜ ጀምሮ አልፎ አልፎ ትገ፤ ትለኝ ነበር – ከዚያም በሁዋላ ካንድም ሁለት ጊዜ ተመሳልሼ ጠይቄአታለሁ» ካላት በሁዋላ፣ «ከትም ጋር ተቆራኝቶ የከረመውን እትብቴን ወደ ምድር የመለሰችልኝ ይመስለኝ ነበር – ቤትዋ ስሄድ፣ ደግሞ እንዴት አድርጌ ከዚህ ኑሮ ላውጣት? የሚል አሳብ ነበረኝ፡፡ እና፣ ከቤት ስወጣ የታየችኝ እሰዋ ነበረች» አላት፡፡

ሰብለ ዝም ብላ ስታሰብ ቆየችና፣ «የኛስ እድል ምን የሚሆን ይመስልሃል?» አለችው፡፡

እሱም በተራው ሲሰብ ቆየና፣ «መዋደዳችን አይበቃም ወይ?» አላት፡፡

አይኖችዋ እንባ እንደማቅረር˜ ብለዋል፡፡ ስሜትዋ ሁሉ ተለዋውጦ ታየው፡፡ ሌላ የሚላት ነገር አልነበረውም፡፡ ሊያሳዝናትም አልፈለገም፡፡ በመካከላቸው ያለው ፍቅር እውነተኛ ፍቅር ይሁን አይሁን የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ አዎን፣ እሰዋም ልታየኝ፣ እኔም ላያት እፈልጋለሁ፣ ግን ለምን? ሁለታችንም በማወቅ ወይም ባለማወቅ የምንሸሸው ነገር አለ፡፡ ግን፣ የኛ መገናኘት ለዚህ ሽሽት መልስ ሊሆን ይችላል? ወይስ ዝም ብለን በሌለ መሰረት ላይ የአዬ ፋሲልን ግንብ በመገንባት ላይ ነን ያለነው? ብሎ አሰበ፡፡

አለክንድር «ዕሳል እንዳይሆን» ያለው ትዝ አለው፡፡

«እኮ፣ የመዋደዳችን መጨረሻው ምንድን ነው?» አለችው፡፡

«ማን ያውቃል?» አላት ቀለቀት ባለው ድምፅ፡፡

@OLDBOOKSPDF



የነገውን አዲስ ሰው በመፍጠርና ብሩህ ተስፋን በማብሰር ረገድ ስለሚጫወቱት ታላቅ ሚናና ስለሚጠበቅባቸው ከፍተኛ መስዋእትነት፣ (መስዋእትነታቸውን፣ ለሌላው ብርሃን እየሆነች፣ ለራስዋ ነዳ ከምታልቅ ሻማ ጋር እያነፃፀረ) እንሱም በተራቸው ወደ ፊት ስለሚጠብቃቸው ብሩህ እድልና እነዚህ ብርቅ ተሰጥዎ ያላቸው ብርቅ ሰዎች ስለሚገባቸው እንክብካቤ፣ በዚያ ርቱእ አንደበቱና ንቁ አእምሮው እየተንተነ ከተናገረ በሁዋላ፣ «እኔም ደራሲ ለመሆን እመኝ ነበር። ደራሲ የመሆን ፍላጎትክ በሁሉም ልብ ውስጥ ያለ ነገር ነው። ድርሰት ልዩ ተሰጥዎ ስለ ሆነች ደራሲ የሚሆኑት ጥቂቶች ናቸው» ሲል ሁሉ፣ ዕጌ ዝም ብላ ከማዳመጥ በስተቀር የሰጠችው አስተያየት ስላልነበረ፣ ሲራክ ያደረባትን ስሜት ለማወቅ ቸኩሎ ነበር።

በዚህ የተንሳ እስተሳሰብዋ ይለወጣል የሚል ግምት ባይኖረውም፣ አብዛኛውን ጊዜ በህይወት ውስጥ በሰው ላይ ከፍተኛ ለውጥ የሚያደርሱት ታላላቅ ሁኔታዎች ሳይሆኑ ሳያስቡዋት ድንገት የምትመጣ ትንሽ አጋጣሚ ናት የሚል እምነት ስላለው ምንም ዋጋ የለውም በማለት ዝም ብሎ አልተወውም። ስለ ራሱ እንደሆን፣ ከራት በሁዋላ – ከበቀለ ቤት ሲወጣ – ስለ ራሱም ሆነ ስለ ህይወት የነበረው ግምት ከስሩ ተንዶበት እርቃን ከእስተያሚ ገፅታው ጋር እየታየው ነበር ቤት የደረሰው።

በመጀመሪያ ለራሱ ያቀረበው ጥያቄ ቢኖር፣ «ከምሬጥራቸው ገፀ ባህርያት አጥብቁ የምጠይቀው ምግባራዊ ድፍረት፣ ትህትናና ፍቅር – ታማኝነትና ሀቀኛነት – ቀጥተኛነትና መስዋእትነት – በእኔ ባህርይ ውስጥ የት አለ?» የሚል ነበር። እግዜር ራሱ ይህን ጥያቄ ለራሱ ባቀረበ፣ እለ በልቡ።

የሰው ልጅ ከግፍ ከጭቆናና ከምዝበራ ተላቆ ራሱን ከጭፍን ጥላቻ፣ ከምቀኝነት፣ ከርኩስ ቅናት፣ ከአጉል ትእቢትና ራስ ወዳድነት ነፃ ቢያደርግና በነፃነት፣ በእኩልነትና በፍትህ ላይ የቆመ የጋራ ህይወት መስርቶ በፍቅር ለመኖር ቢችል፣ ይህች እጭር ህይወት ምንኛ ጣፋጭ፣ የደስታና የሰላም ገነት በሆነች ነበር! እያለ ሲያስብ አጋፋሪ እንደሻው ብቅ አለበት።

– አንተ እንደምታስበው ፈሪ አይደለሁም።

– ታዲያስ?

@OLDBOOKSPDF



- ለእድዋ ጦርነት ባልደርስም ማይጨው ላይ ደሜን አፍስሻለሁ፣ እጥንቴን ከስክሻለሁ፡፡ በህይወትና በሞት መካከል ያለውን የመጨረሻ ፈተና ቀምሼአለሁ፡፡ እምስቴን የመከራ ዘመን በጫር በገደሉ ተሰድጄ ቁርና ሀሩር፣ ረሀብና ጥማት፣ ችግርና ቸነፈር እየተፈራረቀብኝ በየእለቱ ከሞት ጋር እየተፋጠጥኩ ታግያለሁ፡፡

- እና?

- እና፣ ይገፎ የወጣሁዋትን ባንዲራ ክብር ሳላስነካና ሳላሳትፍ ይገፎ ስመለስ ባንዳዎችና የድል አጥቢያ አርበኞች ቀድመውኝ አገኘሁ፡፡ የጭተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ ሆነ፡፡ የዚህን ጉድ መጨረሻ ሳያሳየኝ አይግደለኝ አልኩ፡፡

- እሺ፡፡

- ይህ ጉድ እንደሚደርስ ድሮውኑ አውቄው ነበር፡፡ ንጉሱ አገር ጥለው እንዳይሄዱ የተሳፈሩበትን ባቡር አሳደው ለማቆም ከሞከሩት ሰዎች ውስጥ አንዱ ነበርኩ፡፡ በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርምና ሲመለሱ ተሰደድኩ፡፡ በስደት ኑሮ እድሜዬን ገፋሁ – የዚህን ግፍ መጨረሻ ሳታሳየኝ አትግደለኝ እያልኩ፡፡

- እና፣ አሁንስ?

- የዚያን የግፍ ኑሮ መጨረሻ ለማየት በቃሁ፡፡ አይኔ ጉድ አሳየኝ፡፡ ሁሉም ባሳገር ሲሆን አየሁ፡፡ ትቢያ ላይ ወድቆ የኖረው ሁሉ ቀና ብሎ አገሬ ሲል ሰማሁ፡፡ ደካማ ከንድ ተሰባስቦ ጠንካራ ሃይል ሲሆን አየሁ፡፡
የነበረው እንዳልነበረ፣ ያልነበረው ደግሞ ሆኖ አየሁ፡፡ አሁንም ይህ ተአምር ወዴት እንደሚያመራ ሳታሳየኝ አትግደለኝ አልኩ፡፡ እልሞትም፡፡ እኖራለሁ፡፡ ይህ ህዝባዊ ተአምር ግቡን መቶ ሳይ፣ ያኔ ነው ከመቃብር በላይ እኖራለሁ የምለውና ከሞት ጋር ዘለአለማዊ ሰላም የምመሰርተው፡፡ ወዳጄ ልቤ፡፡ የህልም ግንብ በአየር ላይ ለመስራት ግንበኛ መሆን አያስፈልግም፡፡ ብዙ ከመኖር፣ ህይወት አጭር መሆንዋ ተገንዝቤአለሁ፡፡ የእህል ዘር ካፈር ውስጥ ወድቃ ካልሞተች፣ ብዙ ፍሬ ሳትሰጥ እንዲሁ መና ሆነ ትቀራለች፡፡ የሰውም ዘር እንደዚሁ ነው፡፡ የተፈጥሮ ህግ ነውና መኖር እንዳለ ሁሉ መሞትም አለ፡፡ ግን የመጨረሻ ዕጭን ሞት አይደለም፡፡

@OLDBOOKSPDF



– ሰዎች የሞትን ነገር ሲሰሙ ይደነግጣሉ፡፡ ሞት የማይቀር ቢሆንም ሀይወት ታጉዋጉዋ የለ፡፡ እኔ ግን ያለ ምንም ስጋት ነው የምጠብቀው፡፡ በሰው ህልውና ውስጥ ሞት እንደ ሆድ ድርቀት ተራ ነገር ነው፡፡ ሞት ምን ያስፈራል? ቂ...ቂ...ቂ... ሁላችንም አንድ ሀይወት ናት ያለችን፡፡ ችግሩ ሞት አይደለም፡፡ ትልቁ ጥያቄ ባለችን ሀይወት ምን እናድርግ ነው? ምን እንደምናደርግባት ስንቶቻችን እናውቃለን? ቂ...ቂ...ቂ... አሳባችን ማረፍ ያለበት በሀይወት ላይ ነው—በሞት ላይ አይደለም፡፡ ሞት በሀይወት ድል ይሆናል፡፡ ያለፈውም ጊዜ በመጭው ዘመን ድል እየተነሳ ይሄድ የለ?

– ታዲያ ይህን እያወቁ ከመልአክ ሞት ጋር ለመፋለም ጋሻ ለምን አነሱ?

– የሰው ልጅ የመጨረሻዋ ዕዋ ሞት አይደለም ብዬ ነዋ፡፡ ሰው እንዴት ሙቶ ይቀራል፡፡

– ምን ይሆናል ታዲያ?

– በልጁ፥ በዘሩ፥ በትውልዱ፥ ስርቶት ባለፈው ስራ ይኖራል፡፡ ሀይወት ማለትኮ አንዱ ትውልድ ለሌላው እቀጣጥሎ የሚያስተላልፈው የተስፋ ችቦ ነው፡፡ ከመቃብር በላይ እንድንውል የሚያደርገን ይኸው ተስፋ ነው፡፡ ሌላ ምን አለ ብለህ? ዋ ወዳጄ? ከሰው ልጅ ሌላ ምን የሀይወት ዛፍ አለ? የሀይወት ዛፍ ራሱ ሰው ነው...ቂ...ቂ...ቂ...

– አልገባኝም!

– ምኑ? የሀይወት ዛፍ ራሱ ሰው ነው ማለት?

– እምን፡፡

– ልብ አድርግ እንግዲህ፡፡

– እሺ፥ ልብ አላለሁ፡፡

– ልብ ካልክ ጥሩ፡፡ የሀይወት ዛፍ ራሱ የሰው ልጅ ነው ማለት፥ ከአለም ውጭ የሆነ፥ ከሰው ልጅ በላይ የሆነ የሀይወት ዛፍ የለም ማለቴ ነው፡፡ አለም ከርስዋ ውጭ የሆነ ፈጣሪ የላትም፡፡ አለም ራስዋን የቻለች፥ የነበረችና የምትኖር አካል ናት፡፡ የሰው ልጅም የአለም አካል ስለሆነ የተለየ ባህርይ የለውም፡፡ ልብ በል፡፡

@OLDBOOKSPDF



- ልብ ብያለሁ፡፡
- አለም ራሱን የቻለ ተፈጥሮ እሳት ካልገ፥ ሀልውና ምንድን ነው? ትለኝ ይሆናል፡፡ ሀልውና ተቃራኒ የሆኑ መንትያ ነገሮች ነፀብራቅ ናት፡፡ ምድር–ሰማይ፥ ብርሃን–ጨለማ፥ ህይወት–ሞት፥ ባለ–ሚስት፥ ደግ–መጥፎ ሰላም–ጦርነት፥ ላይ–ታች፥ ፍጥነት–ዝግታ፥ ማደግ–ማርጀት፥ ማበብ–መክሰም፥ ግለሰብ–ህብረተሰብ፥ ፍቅር–ጥላቻ፡፡ ተቃራኒ የሌለው ሀልውና የለም፡፡ ልብ ብለሃል ወይ?

- ልብ ብያለሁ፡፡ ግን…

- ግን ምን?

- ሰው እንደ ተፈጥሮ ፈጣሪ የለውም፡፡ ራሱን የቻለ ነው፡፡ እ… ሀልውና የተቃራኒ መንትያ ነገሮች ነፀብራቅ ናት ብለናል፡፡ እኔን የጨነቀኝ የህይወት ትርጉም ነው፡፡

- ወቼ ጉድ! ወደዚያ ልመጣ አይደለም ወይ?

- እሺ፡፡ ትእግስት አጣሁ መሰለኝ!?

- የልጅ ነገር! ሀልውና ዘለአለም እየተለወጠ የሚሄድ ነገር ነው፡፡ ዘለአለም ቋሚ ሆኖ የሚቀር ነገር የለም፡፡ እንግዲህ የሰው ልጅ መከራ፥ ስቃይና ጭንቀት ከዩህ ላይ ነው፡፡ ቋሚ ያልሆነውን ነገር ቋሚ አድርጎ ለማስቀረት ይመኛል፡፡ የሰው ልጅ ሰውነቱን፥ እጹኛውን፥ ክብሩን፥ ፍቅሩን እንዲያዘ ዘለአለም ለመኖር ይፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ ታዲያ የህይወት ትርጉም ምንድን ነው እያለ ይነጫነጫል፥ ይበሳጫል፥ ይሰቃያል፡፡ ትግሉም ማንኛውም ነገር ለዘለአለም ሀያው ሆኖ የሚኖርበትን እለም ከዚህ አለም ውጭ ባላቡ ይፈጥራል – መንግስተ ሰማያት ሁሉ – በሂቸው አለም በሰው ልጅ ልብ ውስጥ እንዳልሆንች የሰው ልጅ የእውቀት ዛፍ፥ የህይወት ዛፍ የምንለው ራሱ የሰው ልጅ እንዳልሆነ ሁሉ፡፡ ልብ ብለሃል ወይ?

- ልብ ብያለሁ፡፡ የሰው ልጅ ስቃይ ምንጭ ምን እንደሆነ ነገሩኝ፡፡ የደስታውስ ምንጭ ምንድን ነው?

- ግለፊያ ጠይቀሃል፡፡ የሰው ልጅ የተፈጥሮን ህግ ሊለውጥ አይችልም፡፡ ለምሳሌ፥ ቀንና ጨለማን፥ ሞትና ህይወትን፥ ማደግና ማርጀትን፥ ማበብና መክሰምን ሊለውጥ አይችልም፡፡ እነዚህን እሜን የማይለውጡ የተፈጥሮ ህግጋት አሉ ማለት ነው፡፡ እሜን ብሎ ብሎ መቀበል እንዱ የደስታ ምንጭ ማለት ነው፡፡

@OLDBOOKSPDF



ተቀብሎ ዝም ማለት ብቻ አይደለም፡፡ የህይወት መጨረሻ ግቡ የሰው ልጅ በዚህች አለም ላይ በሚኖርበት አጭር ዘመን ውስጥ ተፈጥሮውን አሙዋልቶና ተደስቶ ለመኖር ስለሆነ፣ እያንዳንዱ ሰው ተፈጥሮውን እንዳያሙላና እንዳይደሰት የሚያደርጉትን መጥፎ ነገሮች ሁሉ ከራሱ ልብም ውስጥ ሆነ ከአካባቢው ለማስወገድ መጣር አለበት፡፡ ይህን ለማድረግ፣ አየህ ወይ ወዳጄ፣ ልበሙሉ መሆን ያስፈልጋል፡፡ የሰው ልጅ ክብር ዋስትና መስዋእትነት ነው፡፡ መስዋእትነት ደግሞ ያለ ልበ ሙሉነት መቼ ይሆናል፡፡ ለራሳቸው እየነደዱ አልቀው ለሌላው ብርሃን የሚሆኑት ልበ ሙሉዎች ብቻ ናቸው፡፡ መፅሀፉ ምኑ እሹ ታገኛላችሁ፣ አንኳኩ ይከፈትላችሁአል ያው ሌላ ሳይሆን የራሳችንን ልብ ነው፡፡ ራስን ማወቅ የመጨረሻ ጥበብ ነው፡፡

- መልካም፡፡
- ራስን ማወቅ ሌላውንም ማወቅ ይሆናል፡፡ ካወክ ዘንድ ለራስህ የምትሻውን ለሌላውም ትመኛለህ፡፡ ለራስህና ለሰው ልጅ ሁሉ በጎ ፈቃድና ፍቅር ይኖርሃል፡፡ ከዚህ እውቀት ደረጃ ላይ ስትደርስ ለምታደርገው ነገር ሁሉ ምስጋናም ሆነ ጥቅም ከሰው ዘንድ አትሻም፡፡ ልብህ ጥቅም ላይ ካተኮረ የተፈጥሮን በጎ ምግባር ትስታለህ፡፡
- በጄ፡፡
- ወዳጄ ልቤ፣ የሰው አካልና ነፍስ አንድ ስለሆኑ፣ የሚፀድቀውና የሚኮነነው በራሱ ልብ ውስጥ ነው እንጂ በሌላ ቦታ አይደለም፡፡ የማንኛውም ነገር መለኪያና ሚዛን ራሱ ሰው ነው፡፡ ከሰው በላይ ምንም ነገር የለም፡፡ ቂ...ቂ...ቂ...

ሲራክ ያጋፋሪን ሳቅ እያዳመጠ ትክዝ ብሎ ቀረ፡፡ ነፍሱ ከህይወት እንቆቅልሽ ማጥ ውስጥ ባትወጣም፣ ለጊዜው በጊዜያዊ እፎይታ ንፁህ አየር ስትተነፍስ ተሰማው፡፡ መፅሀፉን እንዴትና በምን እንደሚጀምረው ቁልጭ ብሎ ታየው፡፡ ፊንግ ከማለቱ፣ ፅጌ ከጉዋዳ ብቅ ብላ፣ ‹‹አልተኛህም እንዴ? ምን እንቅልፍ ነሳህ? አለችው፡፡

ሁኔታዋ አላማረውም፡፡ ዝም አለ፡፡

‹‹ስንተዋወቅ አንተኛንቅ!›› አለች፡፡

‹‹ምን ማለትሽ ነው?›› አላት፣ ረጋ ብሎ፡፡

@OLDBOOKSPDF


«የሌባ አይኑ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ አሉ እቴ! እንቅልፍ የነሳህን ነገር መቼ አጣኸውና! ፍቅር ነው» ብላው፥ ከት ብላ እንደ እብድ ሳቀችና፥ «ፍቅር ያዘኝ ብለሽ እትብይ ደንበር ጎተር፥ እኛም አንድ ሰሞን እንዲህ አ'ርጎን ነበር አሉ፡፡ ጨርቅህን ጠቅለህ እንደ መጣህ ጨርቅህን ጠቅለህ ሂድላት! ለኔ ብለህ እንደሆን! ፅጌ ከእንግዲህ ደንታ የላትም፡፡ እግዜር የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም፡፡ አንድ ልጅዋን ማሳደግ ያቅታታል ብለህ አትሰጋ፡፡ ቅጠል ለቅማም ቢሆን አሳድገዋለሁ፡፡ ሂድላት፡፡ ዶራሲ ትወዳለች፥ አሉ፡፡ መፃፍክን እያደነቀችልህ ጥሩ ኑሮ ለመኖር ትችላላችሁ፡፡ ከኔ ከማይምዋ ጋር ምን ቦጣህ!» አለችው፡፡

ነገሩ ገባው፡፡ ሰብለ ስለ እትዬ አሊታዬ ያጫወተችው ትዝ አለው፡፡ እውነት የምትወጣበት ሰአት መቃረብዋን ተገነዘበ፡፡ ሊዋሻት አልፈለገም፡፡ እንደ ምንም ብሎ ልቡን አደፋፈረና፥ «ሰብለን ነው የምትዪው?» አላት፡፡

«ስምዋን አትጥራብኝ፤ ስምዋን ቂስ ይጥራውና!» አለች፥ ድምፅዋን ከመጠን በላይ ከፍ አድርጋ፡፡

«የውነቱን ማወቅ ትፈልጊያለሽ?» አላት፥ ሊዘጋ በደረሰ ጉሮሮ፡፡

«ቀባሪን አረዱት አሉ» አለች፡፡

«ሁቱን ማወቅ ትፈልጊያለሽ ወይ? ነው የምልሽ! አላት አይኖቿን አፍጥጦ፡፡

«አውዳታለሁ በለኝ፡፡ ሌላ ምን ሁቅ አለ?» አለችው፥ ኩስትር ብላ፡፡

«አዎን፥ አወዳታለሁ» አላት፡- «ለምን እንደምወዳት ልንገርሽ? ሰላም ስለምትሰጠኝ ነው፡፡ ሁለታችንም በቤታችን ያጣነውን ሰላም ስንፈልግ ነው የተገናኘነው፡፡ ሌላ አይደለም፡፡ ካንቺም ጋር ያገናኘን ይኸው ፍላጎቴ ነበር፡፡ ሌላ አልነበረም፡፡ እንዳልሽውም ጨርቄን ጠቅልዬ የመጣሁት መውደቂያ ወይም መግቢያ አጥቼ ሳይሆን ሰላም አገኛለሁ፤ አብረን ያፍልናል በማለት ነበር፡፡ ለኔ፥ አንቺ የምወዳት ሚስቴ ብቻ ሳትሆኚ፥ ባላቤ ውስጥ ህዝባዊም ትምሳሌት ሆነሽ ነበር የምትታዪኝ፡፡ ግን፥ አሁን ተለውጠሻል፡፡ ደግነት፥ ፍቅርና ታማኝነት አንሶሽ ሳይሆን፥ የምወደውን ሰላም ትነፍጊኛለሽ፡፡ ስራዬን

@OLDBOOKSPDF



በግድ ካልወደድሺልኝ ማለቴ አይደለም፡፡ ስራዬን ባትወጂውም፣ አክብሮት ልትነፍጊው አይገባም፡፡ ግን፣ ከሁሉም ነገር በይበልጥ የምፈልገው ሰላም ነው፡፡ እና፣ ሰላምን ለመሻት የትም እሄዳለሁ፡፡ እንቺም ሆንሽ ማንም ሊያግደኝ የሚችል ነገር የለም፡፡ ሆድዬ፣ ሁቁ ይህ መሰለኝ፡፡...

ሲራክ ሲቃ ይዞት፣ ተበጥሳ ልትወድቅ እንደ ደረሰች እንደ እምና ቅጠል ሰውነቱ እየተርገበገበ፣ ስልቱን በሳተ ድምፅ ከፍተኛ ምርር ብሎ ሲናገር፣ እንደ ሌላው ጊዜ ጣልቃ ገብታ ልታቋርጠው አልሞከረችም፡፡ ዝም ብላ በጥሞና ስታዳምጠው ቆይታ ነበር፣ ሲጨርስ ጠብቃ፣ «እዚህ ቤት ውስጥ የሰላም ጠንቅ የሆነው ማን ነው? እኔ ነኝ? ለቤት ማሰብ፣ ምኑን ከምን ላርገው ብሎ መጨነቅ፣ እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛልና ለመሻሻል እንሞክር ማለት፣ ኑሮ ራሱ ሸክም ሆኖአልና ሌላ እዳ ውስጥ አንግባ ብሎ መምከር፣ ሰላም መንፈግ ነው? ወይ እድሌ፡፡ እመድ አፋሽ አደረገኝ» ስትል፣ እንባዋ ከቃላትዋ እየቀደመ ጣምራ ጣምራ ሆኖ ዱብ ዱብ ይል ነበር፡፡

ማንባሩን እጁ ላይ ደፍቶ ሲያሰላስል ቆየና፣ «እኔም ነኝ የዚህ ቤት ሰላም ጠንቅ የሆንኩት፡፡ ውስጣዊ ሰላም አልነበረኝም፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ውስጣዊ ሰላም ይኖረኛል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» ሲላት፣ ጆሮው ውስጥ ያስተጋባ የነበረው፣ እውሩ ለማኝ፣ «የሰው ብርሃን ሰው ነው» ብለው የተናገሩት ቃል ነበር...

## ምእራፍ ፲፭

የጥዋት ፀሀይ ደግት፣ አየሩ ቀዝቃዛና ሰማዩ የጠራ ነበር፡፡ ሆኖም፣ የሲራክ ስሜት ውብ ከሆነው ከጥዋቱ አየር ጋር ተዋህዶ በትፍስህት የሚቡዋርቅ አልነበረም፡፡

ማልዶ ከቤት የወጣበት ተልእኮ ግልፅ አልሆንለት እያለው ያውከው ነበር፡፡ ቢሆንም፣ ማድረግ አለብኝ በማለት የወጣ ስለሆነ ወደ ሁዋላ ለማለት አላሰቻለውም፡፡

ሰላም የምትጠይቀው ዋጋ አላት፣ የሚሻት ሊያገኛት ከፈለገ የምትጠይቀውን ሁድ ዋጋ መክፈል አለበት፣ እያለ ነበር በሴይቼንተ

@OLDBOOKSPDF



ከተማውን አቋርጦ ዘመን — የሰብለ ባል — ከሚሰራበት መስሪያ ቤት የደረሰው፡፡

የዘመንን ቢሮ ለማግኘት ችግር አልገጠመውም፡፡ ገና ሰሙን ከመጥራቱ ነበር አንድ ረጅም ሸበቶ ተላላኪ እያጋፈረ ወስዶ ቢሮውን ያሳየው፡፡ ሲራክ ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ በሩን በዝግታ ከፍቶ ገባ፡፡ ቢሮው ግዙፍ ነበር፡፡ በጥዋት የተነፋው 'ፍሊት' እፍንጫ ይወጋል፡፡ ከበሩ ጠረጴዛው ድረስ ያለው መንገድ ሩቅ መሰለው ታየው፡፡ እግር ስምጥ፣ ስምጥ በሚያደርገው አረንጓዴ ምንጣፍ ላይ እየተረማመደ ወደ ግዙፍ ጠረጴዛው ሲጠጋ፣ ተልእኮው፣ ደባስ ብሎ፣ ትርጉመ ቢስ ባዳ እየሆነበት ይሄድ ነበር፡፡

ዘመን ከሚያነበው ወፍራም ፋይል ላይ ቀና ብሎ በተለመደው የቢሮክራቶች አነጋገር፣ «ምን ነበር?» አለው፡፡

ይቅርታ፡ ተሳስቼ ነው ብሎ በመጣበት እግሩ ተመልሶ ቶሎ ለመውጣት ልቡ እየፈለገ፣ «ሲራክ እባላለሁ» አለው፡፡

ስሙ ጆሮው ውስጥ ከቶኛ የደወለ ቢሆንም፣ እንደ ገና ለማረጋገጥ ያህል «ማን?» አለው፡፡

«ሲራክ፡፡»

ዘመን ግራ እየገባው በዚያው በተለመደው የቢሮክራቶች ፈሊጥ፣ «ምን ኖሮአል?» አለው፡፡

ተመልሶ ለመውጣት ጊዜው ያለፈበት፣ ተልእኮውም ደብዛው የጠፋበት ቢሆንበትም፣ «ላነጋግርህ ነበር የመጣሁት፡፡ በቀደድከው የመፀሐፈ ረቂቅ ታስታውሰኝ ይሆናል፡፡ ፈቃድህ ከሆነ ብዙ ጊዜ አልወስድብህም፡፡ የመጣሁበት ጉዳይ አጭር ነው» ብሎት ግራና ቀኝ ተመለከተና፣ «እረፍ ለማለት ይፈቀድልኛል?» አለው፡፡

ትክሻው ሰፊ ነው፡፡ እጁ የእንበሳ መዳፍ ይመስላል፡፡ እንገቱ ብቻ አንድ ጅብ ሳያሳድር ይቀራል! እንደ መፀሀፈ እንጀት ጉቦቱን በልቡ፡፡ ቢሚጥቆ በመስኮት አውጥቶ የወረወረኝ እንደሆንስ? አለ በልቡ፡፡ ተነስቶ የመጣበት እንደሆን ብድግ ብሎ ለመሮጥ ያሰበ ይመስል፣ ከወንበሩ ጫፍ ላይ ነበር የተቀመጠው፡፡

@OLDBOOKSPDF



ዘሙን ሲጃራ አውጥቶ አቀጣጠለ፡፡ እጁ ይንቀጠቀጥ ነበር፡፡ ራሱን ለመቆጣጠር ትልቅ ጥረት በማድረግ ላይ እንዳለ ሁኔታው ያስታውቃል፡፡ ሲጃራውን ወደ ውስጥ ምን እቦንንና፡ ‹‹እሺ ጉዳዩ ምንድን ነው? ወይስ ለተቀደደው መፅሀፍህ ካሳ ልትጠይቀኝ ነው የመጣኸው?›› አለው፡፡

‹‹ምንም አይነት ካሳ የለውም፡፡››

‹‹እንዴት ማለት?››

‹‹ኪነታዊ ስራ በዋጋ ሊተመን አይችልም ለማለት ነው›› ብሎት፣ በግድ መጥቶ ፊቱ ላይ የተለጠፈውን ቍፍግግ ያለ ፈገግታ፣ ተሰርቆ በጎን ተመለከተና፣ ‹‹ለማንኛውም ነገር ላነጋግርህ የመጣሁ ስለ መፅሀፉ ሳይሆን፣ እመጣጤ እኔና አንተን በሚመለከት የግል ጉዳይ ነው›› አለው፡፡

በኔና ባንተ መካከል ምን የግል ጉዳይ አለ?›› አለው፣ አጢሶ ያልጨረሰውን ሲጃራ ከትልቅ 'ክሪስታል' መኮስተሪያ ውስጥ እያወደመ፡፡

‹‹ሰብለ›› አለው፡፡

‹‹አንተ ደፋር ነህ ልበል፡ ወይም ሞኝ!›› ብሎት ብድግ ሲል፣ ጉልያድ ራሱ በነፍስ ተመልሶ የመጣ መስሎት ነበር የታየው፡፡ የዳዊት ወንጭፍ ከየት መጥቶ! ልቡ ነበር የተወናጨፈው፡፡

‹‹ሁለቱንም ሳልሆን አልቀርም›› አለ፣ ጀርባውን ተገዝታዛ ላብ እያሰመጠው፡፡

‹‹ምን ልትፈልግ ነው የመጣኸው?››

‹‹ምንም፡፡ ግን...››

‹‹ወይስ ሚስትህን ዳርልኝ ልትለኝ ነው?››

‹‹ብታዳምጠኝኮ...››

‹‹ወይስ ሰይጣናዊ ስራ ልታሰራኝ ነው?››

‹‹አይደለም፡፡ አንድ ጊዜ ብታዳምጠኝ፡፡...

@OLDBOOKSPDF


‹‹ል'ነግልህ እንደምፈልግ ታውቃለህ?›› አለ፥ ጥርሱን እያንቃጨጨ፡፡

‹‹እሱ የራስህ ጉዳይ ነው!›› ብሎ፥ ሲራክ ከተቀመጠበት ተነሳ፡፡

‹‹በሚስቴ ጉዳይ ምን ያገባሀል?›› አለው፥ ጠረጴዛውን ተደግፎ ወደ ፊት እየተንጠራራ፡፡

‹‹ያገባኛል! የሰብለ ብቻ ሳይሆን፥ የማንንም ደስታ የሚመለከት ነገር ሁሉ ያገባኛል!›› አለው፥ ሲራክም ጠረጴዛውን ተደግፎ ወደ ዘመን እየተንጠራራ፡፡

ጠረጴዛው ላይ ተፋጠጡ፡፡

‹‹ምን!›› አለው ዘመን፥ ትላልቅ አይኖቹን ወደ ውጭ ጎልጉሎ፡፡

‹‹ትሰማኛ እንደሆን የሰብለ ደስታ ያገባኛል ነው የምልህ!››

‹‹እብድ ነህ ልበል?››

‹‹እብድም፥ ሞኝም፥ እጉል ደፋርም — የፈለከውን በለኝ! እና፥ አሁን ታዳምጠኛለህ? ወይስ ልሂድልህ?››

ጠረጴዛው ላይ እንደ ተፋጠጡ ቆሙ፡፡ ዘመን የእንበሳ መዳፍ የሚመስለውን እጁን ቡጢ ጨብጦ ጠረጴዛውን እንዲ መታና፥ እንደ ፈረስ አናፋ፡፡ በዚሁ ቁጭት አልወጣለት ስላለው ተንጠራርቶ የጨበጠውን ቡጢ ሲራክ አገጭ ላይ አሳረፈበት፡፡ ሲራክ ተዝለፍልፎ በጀርባው ተዘርሮ ቀረ፡፡ ዞጭ በማለት እረንጉቀዶው ምንጣፍ ላይ በጀርባው ተዘርሮ ቀረ፡፡ ዘመን በንዴት እንደ ጦፈ ጠረጴዛውን ዞሮ መጥቶ ሲራክ እዚያው እግሩን አነሳ፡፡ ግን በጀርባው እንደ ተንጋለለ ሆዱን ሲረግጠው በመንበርከክ ይዞ ቀና አላደረገውም፡፡ እግሩን አሳርፎ፥ ከሲራክ ጎን በመንበርከክ የተሰነጠቀው ከንፈሩ አደረገው፡፡ ትንሽ ቆይቶ ሲራክ ነፍስ ዘራ፡፡ የተሰነጠቀው ከንፈሩ ይደማ ነበር፡፡

ሲራክ አይኑን ሲከፍት አይቶ፥ ‹‹ደህና ነህ?›› አለው፥ ሰተዘጋ ጉሮሮ፡፡

@OLDBOOKSPDF

ሲራክ ራሱን ነቅንቆ ሲያበቃ፣ «ደህና ነኝ፡፡ እቤት የታቀኝ የቀዶ ኮከብ መአት» አለው፡፡

ሲራክ ከእንጨቱ ላይ ደሙን በእጁ ጠርጎና ተመለከተ፡፡ መሀረቡን አውጥቶ ቁስሉን ያዘበትና ራሱን እየነቀነቀ ተነሳ፡፡ ዘመነ የሲራክን አይን ለማየት እያፈረ፣ «አዝናለሁ፡፡ ይቅርታ አድርግልኝ» አለው፡፡

ቁስሉን በመሀረቡ እንደ ያዘ፣ «ምንም አይደል፡፡ ጥፋተኛው እኔ ነኝ፡፡ መጀመሪያውኑ እዚህ መምጣት አልነበረብኝም፡፡ ብቻ፣ ለማንኛውም ነገር ዱላ መፍትሄ አይደለም» ብሎ ሊሄድ ሲል፣ ትከሻውን ያዘ፣ «አትሂድ፡፡ እባክህ እንነጋገር» አለው፡፡

«እኔም የመጣሁት ለዚሁ ነበር፡፡ ካልተደማመጥን ምን ያደርጋል?» ሲለው፡-

«ዝግጁ ነኝ፡፡ አዝናለሁ» ብሎት፣ ሁለቱም ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ፡፡

«እሺ አሁን ምን እንዳደርግ ነው የምትፈልገው?» አለው፡፡

ሲራክ ደሙን እየጠረገ፣ «እኔ ካንተና ከሰብለ ደስታ ሌላ የምፈልገው ነገር የለኝም፡፡ ሰብለ ውብ ልብ ያላት ውብ ሴት ናት፡፡ ሰው ነችና፣ የልብዋ ንፅህናና ውበት እንዲታወቅላት ትፈልጋለች... በተለይም አንተ ይህንን ልትረዳላት ይገባል፡፡ እለበለዚያ አንድ ቀን እንደምታጣት እመነኝ፡፡ ሀብት፣ ጆኒ ምናምን የምትፈልግ ሴት አይደለችም፡፡ ከትዳር ጉዋደኛዋ የምትፈልገው ፍቅርና መግባባት ብቻ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ምን የሚያዳግትህ ነገር አለ? በተለይም፣ ሴቶች እቃ አይደሉም፡፡ ሰዎች ናቸው፡፡ ስሜት አላቸው፡፡ ነፃነትና እኩልነት የሚባለው ነገር ዝም ብሎ ምኞታዊ አይደለም ወንዶች ስንባል ይህን ማወቅ ይገባናል፡፡ ክብርዋን ከማንጠብቅላት ሴት አክብሮት መጠበቅ ከእንግዲህ የሚቻል አይመስለኝም» አለው፣ ረጋ ብሎ፡፡

እጁ እየተንቀጠቀጠ ሌላ ሲጃራ አውጥቶ አቀጣጠለና ባቦነነው ጢስ ውስጥ እያየው፣ «ይህን ያህል ትቀራረባላችሁ ማለት ነው?» ብሎ ጠየቀው፡፡

በሲጃራው ጢስ ውስጥ የደም ስሩ ሲገታተር ይታየው ነበር፡፡

@OLDBOOKSPDF


«ሀቁን ለማወቅ ከፈለክ አዎን» አለው፡፡

ዘመን ሲጃራውን እንደ ያዘ አይኖቹን ጨፍኖ አቀረቀረ፡፡ ሁለቱንም ከባድ ዝምታ ዋጣቸው፡፡ ዘመን አሳብ ውስጥ የሚጉላላውን ነገር ለማወቅ ባለመቻሉ ተጨነቀ፡፡ በመካከላቸው የተፈጠረው የዝምታ አፍታ አመት መስሎ ታየው፡፡ ዘመን ካቀረቀረበት ቀና ብሎ እንደ ቆሰለ ሰው እያቃሰተ፥ «ይህን ሁሉ የምትነግረኝ ለምንድን ነው?» አለው፡፡

በዘመን ሁኔታ በልቡ እያዘነ፣ «የሁለታችሁንም ደስታ ለማየት በመመኘት ነው፡፡ በሌላ አይደለም፡፡ እስገድዶ እዚህ ድረስ ያመጣኝም ይኸው ምኞት ነው፡፡ በጉዳዩ አስብበት» ብሎ፥ ሰአቱን አየና ተነሳ፡፡

ዘመንም ተነሳና የመጣበትን እንባ ለመሸሸግ እየሞከረ፥ «አንተ ለመሆኑ ምን አይነት ሰው ነህ?» አለው፡፡

«አብድ፥ ሞኝ፥ አጉል ደፋር – ሌላ ምን ልጨምርበት?» አለ ሲራክ ፈገግ ብሎ፡፡

«ብርግጥ ጊዜው ተለውጦአል» አለ፥ ከሲራክ ባሻገር፥ በመስኮት ወደ ውጭ እያየ፡፡

«ምግባራዊ ድፍረትን የታደሉ የለውጥ አካል ይሆናሉ» ብሎት፥ ሰላምታ ሰጠውና ወደ በሩ አመራ፡፡

በሩን ሊከፍት ሲል አንድ ነገር ትዝ ብሎት ቆመ፡፡ መለስ ብሎ፥ «ለመሆኑ እንዴት አድርገህ ልትገለኝ ነበር ያሰብከው?» አለው፡፡

ዘመን በግድ ከንፈሮቹን አላቆ ፈገግ በማለት፥ «ሌላ ጊዜ እሜውትሃለሁ» ሲለው፥ ሲራክ ቀበል አድርጎ፥ «ሞኝህን ፈልግ፥ ሁለተኛ አጠገብህ ድርሽ አልልም» ብሎት በሩን ከፍቶ ወጣ...

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፲፮

ሲራክ ያበጠ ከንፈሩንና ያደረበትን ራስ ምታት ይዞ ከዘመን ቢሮ እንደ ወጣ፣ ካንድ ሲይቼንቶ ወደ ሌላ እያለ፣ በቀጥታ የሄደው ወደ ቢሮው ሳይሆን ወደ ቤቱ ነበር። ከደረሰበት ድብደባ ይልቅ ባገኘው ምግባራዊ ድል እየተደሰተ፣ ልቡ ቀለል ብሎት፣ ባሳቡ፣ ከህቅ የበለጠ የሚዋጣ ነገር የለም እያለ ነበር ቤቱ የገባው።

ሚስቱ፣ ከንፈሩ ቆስሎና አብጦ ስታየው በጣም ደንግጣ፣ «ውይ በሞትኩት! ምን ነካህ? ከሰው ጋር ተጣላህ?» ስትለው፣ ነገሩን የባሰውን ውስብስብ ላለማድረግ በማሰብ፡ ዋሽቶ፡ «የሲይቼንቶ በር ገጭቶኝ ነው። ደህና ነኝ» ብሎአት ልብሱን አውልቆ ሊተኛ ሲል፣ ጨው ያለበት ሙቅ ውሀ ውስጥ የተነከረ ጨርቅ፣ ይዛ መጥታ፣ «ይህን ያዝበት። ይህንም አስፕሮ ዋጥ» ብላ ሰጠችው።

ያለችውን ካደረገ በሁዋላ ጥቅልል ብሎ ተኛ። ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደው። የምሳ ሰአት አለፈ። የስራ ሰአት ደረሰ። እሱም አለፈ። ፀሀይ ማሽቆልቆል ጀመረች። ሲራክ እንዷም አልተንቀሳቀሰም። ፅጌ ሲጋችና ሄዳ ቀሰቀሰችው።

እየጋና፣ «ስንት ሰአት ነው?» አላት።

«አስራ አንድ ሊሆን ነው» አለችው።

ደንግጦ፣ «አይደረግም!» አለ።

በዘጠኝ ሰአት ሰብለን ለማነጋገር አቅዶ ነበር።

«እንዳልቀሰቅስህ አሳዘንከኝ» አለችው።

«እፍ... እንደ ዛሬ ጥሩ እንቅልፍ ወስዶኝ አያውቅም» አለ። ከንፈሩን ሲነካካ እየቸውና፣ «አብጠቱ በጣም ጎሎአል። ቁስሉም ይህን ያህል አያስታውቅም» አለችው።

«ግሩም ነርስ ነሽ» አላት።

ድካሙ ጨርሶ አልወጣለትም። ተመልሶ ሊተኛ ሲል፣ አንድ ሥሥ ሙሉ ጥሬ ክትፎ በአይብ ከሁለት ጠርሙስ ቀዝቃዛ ቢራ ጋር አቀረበችለት። አይኑ እያየ እምቢ ብሎ ሊተወው አልቻለም። ሆዱ

@OLDBOOKSPDF



ቋሃን መግደያ እስኪያክል ድረስ ነበር የበላው! በዚያ ላይ ቢራውን አዶሽ አድርጎበት እያገሳ ተመልሶ ተኛ፡፡ ጠዋት ሲነቃ፣ ጎኑን ያገላበጠበት ጊዜ ትዝ አላለውም፡፡ ህልም አልባ የሆነ አጭር የሰላም ሌሊት ነበር ያሳለፈው...

ከእንቅልፉ የነቃው ከሰብለ አሳብ ጋር ስለ ነበረ በጥሩ እረፍትና ሰላም የታደሰ ስሜቱን ፊቱ ላይ እያንፀባረቀ ቢሮዋን ከፍቶ ሲገባ እንዳየችው ከተቀመጠችበት ዘላ ተነሳታ፣ «ትናንት ምን ጉድጉዋድ ዋጠህ አንተ! ስልኩን ስቀጠቅጠው ነው የዋልኩት፡፡ ለሊትም ሲራክን የበላው ጅብ ምን ነው አይራሣህ፣ ስል ነበር» አለች፡፡

ወንበር ስቦ ተቀመጠ፡፡ ያ የሚያውቀው የሽቶ መአዛ መጥቶ አውድ አደረገው፡፡ ግንባርዋ ሰፋ፣ ፊትዋ ረዘም ብሎ ታየው፡፡ ግንባርዋ ላይ ከንበል ደፋ የሚለው ጠጉርዋ ለለውጥ ያህል ወደ ላይ ተበጥርአል፡፡ ነጭና ሰማያዊ መስመር ያለው ባለ እጅጌ ሸሚዝ ከሰማያዊ ጉርድ ቀሚስ ጋር ለብሳለች፡፡

ምንም ጊዜ ሳያጠፋ ባለፈው ቀን ለምን እንደ ጠፋና ባልዋን ለማነጋገር ምን እንዳነሳሳው ረጋ ብሎ አንድ ባንድ ካጫወታት በሁዋላ፣ «አሁን ዘመን እንዴት ነው?» አላት፡፡

ስታየው ፊትዋ ላይ የነበረው ደማቅ ፈገግታ ጃምኖአል፡፡ ባሳብ ጭልጥ ብላ ሄዳ ስለ ነበረ፣ ቅርቡ ሁና ሩቅ ያለች መስላ ታየችው፡፡

የግድዋን፣ «ደህና ነው፡፡ ትናንት ወደ አምስት ሰአት ላይ መጥቶ፣ 'ነይ እንሂድ' ሲለኝ፣ ምን መጣ ብዬ ደንግጬ ነበር፡፡ ይዞኝ ወደ ደብረ ዘይት መንገድ ሄደ፡፡ የት ይዞኝ ሊሄድ ነው? እያልኩ ሳስብ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ጋ ሲደርስ ታጥፎ ወደ መቃብር ቤት ገባ፡፡ መኪናውን አቁሞና ወርዶ ሄዶ አንድ የግራር ዛፍ ጥላ ስር ቆመ፡፡ ተከትዬው ሄድኩና 'የሞተ ሰው አለ እንዴ?' ብዬ ስጠይቀው 'አዎን' አለኝ፡፡ ደንግጬ 'ማን?'... ስለው 'እኔ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ባለፉት አመታት የምታውቂው ዘመን ሞቶአል፡፡ እርሙን ላወጣ ነው የመጣሁት' ብሎኝ ሰውዬው ለየለት እንዴ ብዬ ፍርሃት ሲጀምረኝ፣ ጥቂት ብንቶና በእሱ መሀል ቢሮው ውስጥ የሆነውን አጫወተኝ፡፡ እኔም ምንም ሳልደብቀው ሁሉን ነገርኩት፡፡ 'በርግጥም ጊዜው ተበላሽቶአል፡፡ እኔ ብቻ ነኝ የዱሮው ዘመን መስሎኝ ወደ ሁዋላ የቀረሁት፡፡ ጥፋተኛው እኔ ነኝ፡፡

@OLDBOOKSPDF



ሞቶ ተቀብሮአል፡፡ ግን ወደ ፊት የተሻለ ህይወት ይጠብቀናል' በማለት እያሰቀሰ ይቅርታ ጠየቀኝ፡፡ ከልቡ እንደሆነ ተሰፋ አደርጋለሁ›› አለች በሻከረ ድምፅ፡፡

‹‹የማይለወጥ ነገር የለም›› አላት፡፡

ዝም አለች፡፡ እሱም ዝም አለ፡፡ ዝምታ ዋጣቸው፡፡ ሁለቱም ቀና ሲሉ አይን ለአይን ተጋጩ፡፡ አይኖችዋ እንባ አቅርረው ነበር፡፡

‹‹በቃ የመጨረሻችን ነው?›› አለች እንባ እየተናነቃት፡፡

ሰሜቱን እየታገለ፣ ‹‹የመጨረሻችን አይደለም፡፡ አዲስ ህይወት መጀመራችን ነው፡፡ ይህን ስልሽ፣ ባለው ሁኔታ አብረን ያሳለፍነው ጊዜ ይፀፅተኛል ማለቴ አይደለም፡፡ አብረን ያሳለፍናትን እያንዳንድዋን ደቂቃ ሳስታውሳት እኖራለሁ›› አላት፡፡

እንባዋን እየጠረገች፣ ‹‹የኔና ያንተ ነገር አንድ ቀን እንደሚያበቃ በፊትም ይታወቀኝ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ይሆናል ብዬ አልገመትኩም፡፡ ጥሩ ነው፡፡ አይኔን ከፍተህልኛል፡፡ ፍቅርን ፍቅር የሚያሰኘው አብረው ያሳለፉት ረጂም ጊዜ አይደለም፡፡ ፍቅር የምንላት፣ ያንዲት ሰአት ጉዳይ ብትሆንም፣ ጣእምዋ ለዘለአለም የማትረሳ ከሆነ፣ እስዋን ነው›› አለችው፡፡

‹‹C'est la vie›› ብሎ ሲነሳ፡-

‹‹በቃ ልትሄድ ነው?›› ብላ አቀረቀረች፡፡

‹‹ደህና ሁኝ ማለቴ አይደለም›› አላት፡፡

‹‹ታዲያስ?››

‹‹አንድ ምእራፍ ፅፌ ስጨርስ እመጣለሁ›› ሲላት፡-

እንባዋን ዋጥ አድርጋ፣ ‹‹ታስነብበኛለህ?›› አለችው፡፡

‹‹ሁልጊዜ፡፡፡››

‹‹ታድዬ›› ብላ ጥሉአት መሄዱን በመጥላት፣ ‹‹ምናስቸኩለህ? አጫውተኝ እንጂ›› አለችው፡፡

‹‹ስለ ምን?››

@OLDBOOKSPDF



«ለምሳሌ፥ ስለ ወደፊት እቅድህ» አለች፥ በነገሩ ሳታስብበት። እንባዋ እንደ ገና ግጥም አለ። እሱም ሆዱን ባር ባር አለው።

«እህ... ደራሲ በህይወት ውስጥ ምን እቅድ ይኖረዋል ብለሽ ነው» ብሎ፥ ትንሽ አቅማማና፥ እንደ መተከዝ ካለ በሁዋላ፥ «ስለ ህይወት እቅድ የለኝም – ከመኖር ሌላ። የህይወት ግቡ፥ ራሱ መኖር ነው –ይህችን ውድ የሆነች ትንሽ ቁራሽ ህይወት እንደ አብርሃም ቤት የለኝ፥ እንደ ሙሴ መቃብሬ ሳይታወቅ፤ መኖር፥ መፃፍ–ህይወት በተሰፋ ወደ ፊት እየኖርኩና ወደ ሁዋላም እያስተዋልኩ። ስለ ኑሮ ቀርቶ ስለምፅፈው ልቦለድም ቢሆን እቅድ አላወጣም። ልቦለድም የህይወት ነፀብራቅ አይደል? ሲመጣልኝ ነው የምፅፈው። ቻዎ» ብሎአት እንደ ሎጥ ሚስት የጨው አምድ ሆና እዚያው ቆማ እንዳይቀር ወደ ሁዋላ ሳይገላመጥ እየተቻኮለ ወጥቶ ሲሄድ እንባ ባቀረሩ አይኖችዋ ትከተለው ነበር።

## ምእራፍ ፲፯

ያን ምሽት ደራሲው፥ መፅሀፉ እየጠራው በጊዜ ነበር ቤት የገባው።

ባረጀው ጠረጴዛ ምትክ ገሩም የሆነ አዲስ ጠረጴዛ ተዘርግቶአል። ረጂም መደገፊያ ያለው በአረንጉዋዴ ቆዳ የተለበጠ አንድ ምቾት ያለው ወንበር ቁጭ ብሎ ከሚፅፍበት ቦታ ላይ ቆሞ ይታያል። አዲስ የጠረጴዛ መብራት! ጉድ ነው አለ።

የቤቱ ወለልና ግድግዳ ታጥቦና ተወልውሎ አሽብርቆአል። ቤቱ የተወለወለበት ሰም ሽታ አውድ ያደርጋል። ልጁ በጊዜ ተኝቶአል። ጉድ ነው አለ እንደ ገና በልቡ ፅጌ ተፍ ተፍ ትላለች።

«ይህ ሁሉ እቃ ከየት መጣ እባክሽ?» አለ።

«ተገዝቶ» አለች።

«በምን ገንዘብ?»

@OLDBOOKSPDF



‹‹ለክፉን ከተቀመጠ ገንዘብ›› አለች፡፡

‹‹ሞት ቀረ አሉሽ?›› አላት እየሳቀ፡፡

‹‹በበሽታ ላይ ጠርነት ታውጆ የለ! ለማንም የቁዋጠራትን አይጨርስም፡፡ ሰው ሆኖ ለነገ የማያስብ የለም›› አለች፡፡

ራት በጊዜ ቀረበ፡፡ ውባንቺ በአዲስ ቀይ ሹራብና ጥለቱ ባማረ ያገር ልብስ አጊጣ ነበር፡፡

‹‹ሽክታው ምንድን ነው?›› አላት፡፡

እየተሽኮረመመች፥ ‹‹አትዬ ናቸው የገዙልኝ፣ ፈተናዬን ስላለፍኩ›› ብላ፣ ጉልበቱን ልትስም ጎንበስ ስትል፥ ይዞ ጉንጮዎን ሳመና፥ ‹‹በሙሀ ይለቅ›› አላት፥ በዕጌ መለወጥ በልቡ ጉድ ነው'ኮ እያለ፡፡

‹‹ግሩም ዶሮ ወጥ ነው›› አላት፥ ሚስቱን፡፡

‹‹ማን ያረዳት ይመስልሃል?›› አለችው፡፡

‹‹እኔ ነኝ እንዳትዪኝ!››

‹‹እሳምሬ!›› አለች፡- ‹‹ሶስት ወንዶች ከመንገድ ብጠራ ሶስቱም አንገታቸው ላይ ክር የሚባል ነገር የላቸውም፡፡ ስለዚህ ምናባቱ አልኩና እኔው ቅንጥስ አረኩዋት፡፡››

‹‹ለዚህ ነዋ የጣፈጠኝ›› አላት፥ እየሳቀ፡፡

‹‹ግን እውነቱን ልንገርህና ፈርቼ ነበር›› አለች፡፡

‹‹አይዞሽ፡፡ ሴት ዶሮ ስላረደች የሚወርድ መአት የለም›› አለ፡፡ ‹‹ያጉል እምልኮ ምክንያት መሰረት የሌለው ፍርሃት ነው፡፡ ሰው ራሱን እያወቀና ተፈጥሮን በቁጥጥሩ ስር እያደረገ ሲሄድ የእግዜርን ቦታ ይወስዳል፡፡››

‹‹እዚህስ ላይ በስማም በል›› አለችና አማተበች፡፡

‹‹የሰው ልጅ አካላዊ ደካማነትና ከዚሁ ደካማነት የሚመነጨው ፍርሃት ነው እግዜርን የፈጠረው፡፡ ሌላ አይምሰልሽ›› አላት፡፡

@OLDBOOKSPDF



እንደ ገና እማትባ ዝም አለች፡፡

«እንዲያው በሞቴ ዕጣዬ ማማተቡን ተዉና ስታስቢ አንዱን ጤነኛ፥ ሌላውን በሽተኛ፥ አንዱን ባለፀጋ፥ ሌላውን ሙልጭ ያለ ድሀ የሚያደርግ፥ ከፍጡራት መካከል እየመረጠ፥ ግሚሱን ለመንግስተ ሰማይ የሚያበቃ፥ የተቀረውን ለገሃነም የሚዳርግ ቀልደኛ አምላክ አለ ብለሽ ታምኛለሽ?» አላት፡፡

ለሶስተኛ ጊዜ እማተበችና ተነሳች፡፡

ከራት በሁዋላ፥ ምኝት ካለው አዲሱ ወንበር ላይ ተሰይሞ፥ የጠረጴዛውን መብራት አብርቶ፥ ወረቀቶቹን አዲሱ ጠረጴዛ ላይ በመዘርጋት ብእሩን ሲያወጣ የቆየ ጦረኛ ወደ ጦር ሜዳ ሲመለስ የሚሰማው ስሜት አይነት ነበር የተሰማው፡፡

ርቀውት የከረሙት ስራ፥ በተለይም፥ ፅሁፍ፥ ሲመለሱበት ያስቸግራል የሚል ስጋት ነበረው፡፡ እንደ ፈራው አልሆነም፡፡ ብእሩ አልነከሰም፡፡ ቀለሙ እንደ ጅረት ነበር የሚፈሰው፥ ሃሳቡ ተያይዞ በመቀብ እየሄደ – እየነጎደ – እንደ ጡዋፍ እየነደደ – እየበራ – ጭጋግ ለውጋጋን – ውጋጋን ለብርሃን ቦታውን እየለቀቀ – እጋቱሪ እንደሻው ቲ... ቲ... ቲ... ብለው እየሳቁ – የሰውን ልጅ ሰንደቅ አላማ ከፍ አድረገው ይዘው ከመልአኩ ሞት ጋር ሲፋለሙ፡-

«ሻይ ትፈልጋለህ?»

ፅጌ ነበረች፡፡

«እሺ» ብሎ፥ ስንት ሰአት እንደሆነ ጠየቃት፡፡

«ስድስት አልፎአል» አለችው፡፡

እንደም ቀና ሳይል ለአራት ሰአት ያህል የሰራ ቢሆንም፥ ምንም ድካም አልተሰማውም፡፡ ትኩስ ሻይ ስተታው አጠገቡ ቆሞ ስትል ረስቶት የከረመው ውበትዋ ይበልጥ ውብ ሆኖ ታየው፡፡ ፍቅርና ሰላም ባለበት ስፍራ ሁሉ ውበት ሞልቶአል ለካ፡፡ ህይወት ምንኛ ውብ እና ጣፋጭ ናት ሲል፥ የደስታዋና የስቃይዋ ቃና እቶ ውስጥ የቀለጠ ይመስል እጣጥዋ ምራቁን ዋጠ፡፡

«ተሳካልህ?» አለችው፡፡

@OLDBOOKSPDF



‹‹ምኑ?›› አላት፡፡

‹‹ፅሁፉ?››

‹‹አዎን እየተሳካ ነው›› ብሎ እጅዋን ያዘ፡፡

‹‹ቶሎ የሚያልቅ ይመስልሃል?›› አለች፣ እስዋም እጁን እየያዘች፡፡

‹‹ህይወት አጭር ቢሆን ግን ረጂም ናት ይባላ›› ብሎ፣ ስለመፅሀፉ ያደረባትን ስሜት እያደነቀና ደስ እያለው፣ ‹‹እስካሁን የፃፍኩትን ላንብብልሽ?›› አላት፡፡

‹‹ካልደከመህ›› አለችው፡፡

‹‹የሚወዱት ስራ አያደክምም›› ብሎአት፣ ሻሂውን ቀስ ብሎ ካጣጣመ በሁዋላ፣ ‹‹ግን የማነብልሽ አንድ ነገር እሺ ያልሺኝ እንደሆን ነው›› አላት፡፡

‹‹ምን?›› አለችው፣ ያን ራስዋ ላይ የማይረጋውን ሻሽ እያስተካከለች፡፡

‹‹ፅፌ የጨረስኩትን ትገለብጪልኝ እንደሆን?›› አላት፡፡

‹‹በእጅ?››

‹‹አዎን፡፡ ሁለት ሶስት ኮፒ ያስፈልገኛል...››

‹‹ከዚህ ሁሉ ለምን ያማርኛ ታይፕ አታስተምረኝም?››

‹‹ከልብሽ ነው?››

‹‹የምር›› አለችው፡፡

ትንሽዋ ጣቱን ከእስዋ ትንሽ ጣት ጋር ቆልፎ፣ ከተያያዙ በሁዋላ ለቀቃትና፣ ‹‹ከዛሬ ጀምሮ ሸርክ ነን›› አላትና፣ ትንሽዋን ጣቱን ሳመ፡፡

‹‹ነገ እስጀምርሻለሁ›› ብሎ ሻሂውን ጨለጠና፣ ትኩር ብሎ ይመለከታት ጀመር፡፡

‹‹አንተ ፅፈህ ስትጨርስ እኔ ታይፕ ሳደርግልህ ይታየኛል›› አለች፡፡

‹‹እኔም ይታየኛል›› አላትና እጅዋን በሃይል ያዘ...

ሃጂ ሙስጠፋ ቤት ምርቃቱ ይኸንደንዳል፡፡ ከራማው ገብቶአል፡፡ ጎረቤት የሚኖሩት አሮጊት ደረቅ ሳል ይስላሉ፡፡ ችሎ ማደር ፀጥ ብሎአል፡፡ ሰው ነው ከልቡ አለ — በቀለን አስታውሶ፡፡

‹‹ሰው በላው ጎንደሬ›› ጭጭ ብሎአል፡፡ ብዙ አዲስ ጨርቅ አግኝቶ ይሆን? አለ በልቡ፡፡

ይህች የምድር ጎስቋዋሎች ደቤት — ይህች የመከራና የተስፋ መንደር — ይህች ገሃነም — ይህች ገነት — ተረት ሰፈር — ሲራክ ፈገግ ብሎ የፃፈውን ለሚስቱ ያነብላት ጀመር...

@OLDBOOKSPDF



"ደራሲው" -የበዓሉ ግርማ አራተኛ ልብወለድ መጽሐፍ። ሕይወት፣ ድርሰትና ደራሲ ሲወሳሰቡ በከያኒ ስሜት ውስጥ ጭንቀትና ሐሴት ሽንፈትና ድል ይፈራረቃሉ....

ሲራክ - የመጽሐፉ መሪ ገጸ- ባህርይ-ብዕሩ ነጥፎ ውብት ስትከዳው፣ ባዶው ነጭ ወረቀት ባዶ ሆኖ መልሶ ሲያፈጥበት ይጨነቃል፣ ሰላም ያጣል፣ ከራሱ— ከሰው— ከፈጠራቸው ገፀ— ባህርያትና ከድርሰት ጋር።

ታዲያ ሲራክ ሰላም እንዳጣ ይቀር ይሆን? ወይስ ከእውነታ ጥልቀት ውስጥ ውበት ፈንጥቃ ስትወጣ ሲያይ፣ ከራሱ ዓለም ከሙያው ጋር ይታረቃል?

ኪነት ነው — ድርሰት።

ዋጋው 71.00 ብር

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ
0113691933